# ጃገማ ኬሎ

## የበጋው መብረቅ

(የሕይወት ታሪክ)



ፍቅረ ማርቆስ ደስታ እንደጻፈው

ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ
የመ.ሳ.ቁ. 57
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በጽሑፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የሥነ ጽሑፍና ኪነጥበብ ሥራዎች ባለቤትነትን በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስከ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ እንኳን መልሶ ማሳተም፣ መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።

የመጀመሪያ ኅትመት 2001 ዓ.ም. ሁለተኛ ኅትመት 2002 ዓ.ም

©ሹልዝ አሳታሚ ኃ.የተ.የግ.ማ.

ISBN 978-99944-0-039-3

ማስተር ማተሚያ ቤት
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

# ማውጫ

| ርእስ | ገጽ |
|---|---|
| ምስጋና | ሀ |
| መቅድም | ሐ |
| ፩. ገሮና ጎበና | 1 |
| ፪. አባ ዶዮ | 15 |
| ፫. ጃገማ - አባ ዳማ | 19 |
| ፬. የኢጣሊያ ወረራ | 26 |
| ፭. ጃገማ - የበጋ መብረቆች መሪ በአርበኛነት | 38 |
| ፮. ሰይፍ አይፈሬው ጳጳስ | 62 |
| ፯. ግብታዊ የአርበኛነት ጅማሬ | 70 |
| ፰. ምሽግ ሰበራ | 75 |
| ፱. የፍጻሜው አጥቢያ - ከጂጋ አዲስ አለም | 84 |
| ፲. የእሄ ኃይለ ስላሴ ጉብኝት | 99 |
| ፲፩. የዕለቱን ትቶ የዓመቱን | 109 |
| ፲፪. ከአርበኛነት ወደ ጦር መኮንንነት | 115 |
| ፲፫. ዘመናዊ ጦር ግንባታ | 142 |
| ፲፬. የሞሳዝጊ ልጆች | 148 |
| ፲፭. የጃገማ የትዳር ህይወት | 152 |
| ፲፮. መፈንቅለ መንግስት | 156 |
| ፲፯. የመፈንቅለ መንግስቱ ድራማ | 164 |
| ፲፰. የምህረት አዋጅ | 192 |
| ፲፱. በውጥኑ የቀረ ሌላ የመፈንቅለ መንግስት ሀሳብ | 197 |
| ፳. ሜጫና ቱለማ | 206 |
| ፳፩. የሰውጥ ማዕበል | 211 |
| ዋቢ መጻሕፍት | 223 |
| የጃገማ ታሪክ በፎቶግራፍ | 225 |

# መታሰቢያነቱ

ለታላቁ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር
ለዶ/ር ብርሃኑ አበበ ይሁን።

**This book is dedicated to**
**the memory of another great Ethiopian,**
**the late Dr. Berhanu Abebe.**


# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ፥ ዶ/ር ብርሃኑ አበበ፣ ኮሎኔል ሰምረት መድኃኔ፣ አቶ ተካልኝ ገዳሙ፣ አቶ ገሳን ባገርሽ፣ አቶ አብርሃም ፍስሃ፣ ወ/ሮ ብርሃኔ ደምሴ እና ሌሎችም ሰዎች ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ያደረጉት ልባዊ ጥረት ባይጨመርበ ኖሮ በዚህ መልኩ ተጽፎ ሊታተም ባልቻለ ነበር። በመሆኑም እነዚህ ባለውለታዎቻችን ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት ላደረጉት ከፍተኛ ጥረት ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

በተጨማሪም ይህን መጽሐፍ የማሳተሙ ውጥን ሀሳብ እውን እንዲሆንና ዛሬ አንባቢያን እጅ እንዲገባ ያደረገው የሚስተር ገብርኤል ሹልዝ ያላሰለሰ ጥረት ነው። ስለዚህም ገብርኤል ሹልዝ ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት ላደረገው ጥረት ፒተር ሹልዝ፣ ጄኔራል ጃገማ ኬሎ እና ፍቅረማርቆስ ደስታ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርቡለታል።

# THANKS

This book could not have been written without the generous time and fervent efforts of Dr. Berhanu Abebe, Colonel Semret Medhane, Tekalegn Gedamu, Gassan Bagersh, Abraham Fiseha, Berhane Demissie and others. For your great service to this project we thank you.

Also, it was the tireless efforts of Gabriel Schulze that carried this book from the shadows of an idea to the reality of what you hold in your hands today. Peter Schulze, General Jagema Kello, and Fikremarkos Desta express their deepest gratitude for Gabriel's unwavering commitment to this project.

## ገለታ

በርእበኛነት አገለግል በነበረበት ጊዜ የሚከተሉት ወዳጆቼ ከጎኔ ሆነው እጅግ ይተባበሩኝ የነበሩና ለሀገራቸውም ነጻነት ከልብ የሰሩ በመሆናቸው ስማቸውን ሳልጠቅስ አላልፍም፤

1) ዲባባ ሁርሴ
2) ሙሊሳ ቀርጩ
3) ሙሊሳ ሶሪ
4) የፈይሳ ነገሮ ልጆች
5) ሁሪሳ ሮቢ

**ጃገማ ኬሎ**

**ሐምሌ 2001 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**

# መቅድም

«ሰላም፥ ጀኔራል! እንዴት ነዎት?» ብዬ ጥያቄ አቀረብኩ - ወደተቀመጠበት ቦታ እያመራሁ:: እጅ ለእጅ ተጨባብጠን ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን:: ከእዚህ ቤት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ ከገባሁ አንድ ዓመት ሆኖኛል:: በግድግዳው ላይ ልዩ ልዩ ፎቶዎች ተሰቅለዋል:: ከእነዚህ ውስጥ አንዱ፥ አንድ ወቅት ጃገማ አገልግሏቸው የነበሩት ንጉሰ ነገስት ትልቅ ፎቶ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የህይወቱ አጋር የነበረችው ባለቤቱ ፎቶ ነው:: ያማረ ሱፍ ኮት የለበሱ ሁለት እውቅ ወንድማማቾች ፎቶም እዚያው አቅራቢያ ተሰቅሎ ይታያል:: የወንድማማቾቹ ፀጉር ኀፍሯል:: ኀፈሬው ፀጉራቸውና መልከመልካም ፊታቸው ላይ የሚነበበው ቆራጥነት መኳንንትነታቸውን አደብዝዞታል:: አሁን ወንበር ላይ ተቀምጦ የተቀበለኝ ከእነዚያ ወንድማማቾች አንዱ ነው:: አሁንም የሱፍ ካፖርት ለብሷል:: ምንም እንኳ ሰውነቱን እርጅናና ጉዳት የተጫነው ቢሆንም ያ ግርማ ሞገሱና በራስ የመተማመን መንፈሱ እንዳለ ነበር:: አንድ ጌጠኛ ብእር የያዘ እሽግ በስጦታ መልክ ካበረከትኩለት በኋላ «ጀኔራል! ይህ ትንሽ ስጦታ መጽሐፍህን ለመጻፍ ይረዳህ ዘንድ የተበረከተ ነው» አልኩት:: እሽጉን ከፍቶ ፈገግ አለና አመሰገነኝ::

እም! እድሉን አግኝቼ ከጀኔራል ጃገማ ኬሎ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ከተገናኘሁ አንድ ዓመት አልፎኛል:: የዚያ ጊዜ እንድንገናኝ ያደረጉን ያልታሰቡ ቤተሰባዊ ጉዳዮች ነበሩ:: እርግጥ ከማዕረጉ ተነስቼ የረጅም ጊዜ እኩሪ የውትድርና አገልግሎት የሰጠ መሆኑን ከመገመት በስተቀር ስለእሱ ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ሳገኘው ታሪካዊ ፋይዳ ያለው ገድል ሰርቶ ያለፈ ሰው መሆኑን ፈጽሞ አላውቅም ነበር::

ለመጀመሪያ ጊዜ ስንገናኝ የትውውቅ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለተገናኘንባቸው ጉዳዮች ተወያየን:: ጊዜው እየመሸና ውይይታችንም እየሰፋ በመጣ መጠን ግን ጀኔራሉ ስላሳለፈበት የተከበረ የውትድርና ሞያ ዋና ዋና ጉዳዮችን እያነሳ ያጫውተኝ ጀመር:: በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳደንቀው ያስገደደኝን የዚህን ሰው ታሪክ ለማወቅ በመጓጓት በተመስጦ አዳመጥኩት:: ጥያቄዎችን በመሰንዘር ትረካውን እንዲቀጥልልኝ ስገፋፋው እኪሱ ውስጥ ያስቀመጣቸውን የቆዩ ፎቶግራፎች አውጥቶ በህይወት ዘመኑ ባለፈባቸው ቀውጢ ጊዜያት አብረውት የነበሩ ሰዎችን መልክ አሳየኝ:: እየተወያየንና ደቂቃዎች ወደ ሰዓታት እየተለወጡ ጊዜው በገፋ ቁጥር ጀኔራሉ በኢጣሊያ

ወረራ ጊዜ እንዴት አድርጎ በሙሉ ልብና በቆራጥነት አርበኞችን እየመራ ወራሪዎችን ድል እንዳደረገና የሀገሩን የታሪክ ሂደት እንደቀየረ ለመረዳት ቻልኩ። እያንዳንዱ አስደናቂ የታሪኩ ክፍል ሌላውን እያስከተለ ቀጠለ፤ ባለታሪኩ በህይወት ያለ ህያው ታሪክ በመከታተል ላይ መሆኔንም ልብ አልኩ። ቀኑ እየጨለመ ሲሄድ ከእዚሁ ጋር ተዛማጅነት ያለው ተመሳሳይ ታሪክ ለጄኔራሉ ለማካፈል ወደድኩና አጫወትኩት። አባቴ በአሜሪካ የጦር ኃይል እንዲሁም በነጻው የፈረንሳይ ኃይል ውስጥ ስለሰጠውና ከቻድ በርሃ እስከ መሀል ፓሪስ ስላደረሰው የውትድርና አገልግሎት ሳጫውተው በጉጉት አዳመጠኝ። ጨዋታችንን በማገባደድ ላይ ሳለን ጄኔራሉን ስለእሱ የህይወት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ከሆነ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት። እሱ ራሱ ትንሽ እየጻፈ መሆኑንና ቀስ ብሎም ታሪኩ ተጽፎ እንደሚያልቅ ተስፋ ማድረጉን ነገረኝ። ታሪኩን መጻፉን እንዲቀጥል በእጅጉ ከአበረታታሁት በኋላ ድጋሚ ወደአዲስ አበባ ተመልሼ በምመጣበት ጊዜ መጽሐፉን አጠናቆ እንደሚጠብቀኝ ያለኝን ተስፋ ገለጽኩለት።

አሁን ከአንድ ዓመት በኋላ ከጄኔራሉ ጋር አብረን ቁጭ ብለን ቀደም ሲል የሰጠሁትን አዲስ ብዕር በትካዜ ሲያሽከረክር በመመልከት ላይ ሳለሁ ያን ያጫወተኝን ድንቅ ታሪኩን የመጻፉን ሥራ ብዙም ያልገፋበት መሆኑን ገለጸልኝ። ምንም እንኳን አሁን የሚያስገርም ጥንካሬ ቢታይበትም ሰውነቱ አንድ ቀን መድከሙ አይቀርም። በአርበኛነት የሰራው ገድልም እንዲሁ ተበትኖና ተዘንግቶ ሲቀር መቻሉን፣ ብዙ የሚያኮሩ ታሪኮች ያሏት ሀገርም እንዱን ታሪኳን ልታጣ የምትችል መሆኗን ሳስብ አዘንኩ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በልዩ ልዩ ግንባሮች ተዋግተው እንደነበሩት በርካታ የዓለማችን ሰዎች ሁሉ ጄኔራል ጃገማም ለሀገሩ ስለሰጠው አኩሪ ወታደራዊ አገልግሎትና ስለጀግንነቱ ሰዎች እንዲያውቁለት ለማድረግ ሳይሞክር እንዲሁ ዝም ብሎ በመኖሩ ደስተኛ ነበር። እንዲህ ዓይነት ሰዎች የከፈሉት መስዋዕትነትና የሰሩት ገድል ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆን የራሳቸውን አስተዋጽኦ ወደጎን በመተው አብረዋቸው ሲፋለሙ የተሰዉ ሰማዕታትን ጀግንነት ማስታወስን ይመርጣሉ። ልክ እንደነዚህ ሰዎች ሁሉ ጄኔራል ጃገማም ያሳለፈውን የትግልና የድል ታሪክ መዝግቦ ለትውልድ ማስተላለፍ ያለውን ዋጋ የተረዳው በእርጅና ዘመኑ ነው። ግን ጊዜው እየነጎደ ነው፤ አንድ ቀን ደግሞ ይህ ጀግና ማለፉ አይቀርምና ከሱ ጋር የህይወት ታሪኩ ባከኖ መቅረቱ ነው። ስለሆነም በዚያው እለት የዚህ አስደናቂ ጀግና የህይወት ታሪክ ተጽፎ ለዘመናችን አንባቢያን የሚደርስበትንና ለመጪው ትውልድ የሚተላለፍበትን መንገድ ማመቻቸት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ።



ዛሬ ይኸውና የጄኔራሉ ታሪክ በእጄ ይገኛል፤ ከብክነትም ተርፏል። ይህ የጄኔራሉ ታሪክ በእርግጥም የኢትዮጵያ ሀብት ነው። ስለሆነም የህይወት ታሪኩ የሀገሪቱን ታሪክ የሚመስለውን የዚህን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አርበኛ የጀግንነት ታሪክ ለእናንተ ማካፈል ታላቅ እድል ነው።

ፒተር ቢ. ሹልዝ
ዋሺንግተን ዲ.ሲ.
ሐምሌ 2001 ዓ.ም.

# FORWARD

"Greetings General, how have you been?" I inquired as I walked to the corner where he sat. We warmly shook hands. It had been a year since I had first entered the living room of this home. Various photographs hung on the wall, ranging from a large photo of the Emperor he had once served, to the woman with whom he had shared his life. Another photo showed two distinguished brothers in immaculately tailored wool coats. Their hair was grown out long, and their handsome, resolute faces betrayed an obvious look of nobility. Now, more than seven decades later, one of the brothers sat in an armchair to receive me. He still wore a woolen overcoat, and though his body had paid the price of age and injuries, he still held himself with the same air of dignity and certainty. "General, here is a small gift to help you write your book" I said as I offered a package containing a custom crafted pen. Opening the box, he smiled and thanked me.

Yes, a year had passed since I had first had the privilege of meeting General Jagema Kello. At that time a series of unlikely family circumstances had brought us together. In fact, I had known very little about him, other than assuming his rank denoted a long and significant military career. Certainly at the time I had no idea the man I was about to meet laid claim to a life of dramatic sagas and historical significance.

At that first meeting we exchanged formalities and addressed what had brought us together. But as the afternoon shadows grew long and our conversation deepened, the General began to share highlights of his distinguished career. I listened intently, eager to enjoy the presence of a man whose story quickly commandeered my admiration. As I encouraged him on with questions, the General retrieved some well-worn photos he kept in his pocket and showed me the faces of the men with whom he had shared the critical moments of his life. As the minutes turned to hours I learned that, with courage and determination, he had led the resistance against the Italians and changed the course of history for his nation. Each compelling story led to yet another, and I realized I was in the presence of living history. The day faded, and I took the opportunity to share a few things of common interest.



He listened with great interest as I spoke about my father whose service with the U.S. Army and Free French Forces had taken him from the deserts of Chad to the heart of Paris. As we concluded our discussion, I asked general Jagema if his accounts had ever been recorded in a book. He replied that he was in fact writing a bit and hoped to have a few of his stories recorded eventually. I strongly encouraged him to do so and told him the next time I returned to Addis Ababa I hoped he would have finished these chronicles.

As I sat with the General this one year later, watching him pensively rotate the new pen I had given him in his hands, he confided that he had in fact made only a little progress in recording his remarkable story. Though he exhibited great stamina, his body would one day give out. It saddened me to think his patriotic exploits might also fade away, lost to a nation that had so much to be proud of. Like many men from all parts of the world who had fought in the epic global conflict of World War II, the General had been content to quietly live his life without drawing any special attention to his service and courage. These sorts of men, regardless of their sacrifices and exploits, preferred to remember their fallen comrades as the only heroes, giving little note to themselves. And like many of these men in their later years, the General had come to value the importance of leaving behind a record of what he had experienced. But time was slipping away, and some day with it this hero and his life story. So, on that day, I concluded I would arrange for the story of this fascinating and gallant man to be recorded for readers of our time and future generations to come.

Today, I sit with the General's story in my hands, grateful it has now been preserved, for his story is in fact an Ethiopian treasure. And so it is a great privilege to now share with you the exploits of a true Ethiopian patriot and hero whose story is very much the story of the nation itself.

Peter B. Schulze
Washington D.C.
July, 2009

## ፩

# ገሮና ጎበና

ከተራራው እናት ላይ ካለችው ችምችም ያለች ዛፍ ስር የኦሮሞ ባላባቱ ገሮ እንደ ልማዳቸው ጋደም ብለዋል። ዙሪያቸውን የራባዶሪ፣ ሉባ፣ ዮባ፣ ዮባ ኦዳ፣ ዮባ ሐዮ፣ ዮባ ገዳም ሞጂ የገዳ እርከን አባላትና ልጆቻቸው ተሰባስበው ያወጋሉ።

ትንሽ ራቅ ብሎ ካለው ቁጥቋጦ አጠገብ ደግሞ በገዳ የዘመን አቆጣጠር አራተኛ የገዳ እርከን ውስጥ ያሉት የፎሌ ወጣቶች የኦዳ (ዋርካ) አርማ የሆነውን በኩውን ለአባቦኩው አስረክበው በቅርቡ ኦዳ የሆኑት ጃራ ስለገዳ ሥርዓት ያስተምራሉ።

«...በስምንት ሺህ ዓመተ ዓለም አካባቢ የኩሽ ልጆች ሴታና ኦራ ተጣልተው ታላቁ ሴታ ታናሹን ኦራን ገደለ ... እህታቸው አቴቴ የወንድሟን አስከሬን በሌሊት ተነስታ አባይ ወንዝ ዳር ቀብራ አምላኳ ሰላም እንዲያወርድ ተማፅና የመታሰቢያ ዋርካ ተከለች። የኩሽ አምላክም ዝናብ አዝንቦ ዋርካውን አሳደገው፤ በዚህም ሰላም ሰፈነ...ከአርባ ዓመት በኋላ የአቴቴ ልጆች የነበሩት ቦረና እና ባሬንቱ እንደገና ተጣሉ። ታላቁ ቦረና ታናሽ ወንድሙን ባሬንቱን ገደለው። እናታቸው አቴቴ አምርራ አዘነች። የልጇን አስከሬንም በሌሊት ቀብራ ዋቃ (እግዚአብሔር) ዘላቂ እርቀ-ሰላም እንዲያወርድላት አምላኳን ተማፀነች። ዋቅም ልመናዋን ሰማ፤ ኦዳ እንድትተክልም አዘዛት፤ ልጆቿም የሚዳኙበት አዲስ ሥርዓት ነገራት። ያንንም የሰላም ትንሳኤ ህይወት ገዳ ሥርዓት አለው። ጥንታዊና መሠረታዊ እምነቱ ደግሞ ዋቂፈና ተባለ። ኢሬቻ ይህ ሥርዓት የሚከበርበት በዓል ሆነ ...

«የአፍሪካውያን እናት አቴቴ የአምላኳን ትዕዛዝና በረከት ተቀብላ በወንዙ ዳር ለዳር ኦዳ ተከለች። ወዲያው ዝናብ ዘነበ፤ ኦዳዎቹም አደጉ። ዘላቂ ዕርቀ ሰላምም በልጅ ልጆቿ ሕይወት ላይ ወረደ። ያ የቅድስቷ የኦሮሞ እናት አድባር 'የሰላምና የዕርቅ' ቀን 'ኢሬቻ' ተብሎ ይከበራል። ገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመቱ በቅደም ተከተል ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና መንፈሳዊ ኃላፊነቶችን የሚሸከም የዕድሜ መደብ ያለው የባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ነው። እያንዳንዱ የገዳ መደብ ለስምንት ዓመታት በሥልጣን ላይ

ይቀያል። የሥልጣን ሽግግሩም ፍፁም ሰላማዊና በክብረ-በዓል የታጀበ ነው። ዳ የኦሮሞ ህዝብ የኩራት ውርስ፣ የሥነ ምግባር ዋልታና ማገር፣ የእውነት፣ የእኩልነት፣ የፍቅር ምንጭ ... ከዋቅ የተሰጠ ገፀ በረከት ሆኖ የኦሮሞ ብሔር መተዳደሪያ በመሆን እያገለገለ ነው ...»

* * *

የገሮ ፈረስ፥ ታጭዶ ከፊት ለፊቱ የተቀመጠለትን ሳር በምንጭሩ እየበረቃቀሰ ይሸረማምዳል። ገሮ በቡልኳቸው ተሸፋፍነው እንደተጋደሙ ላው ለፎሌዎች የሚሰጠውን የቃል ትምህርት ያደምጣሉ። ሰማዩ ጥርት የለ ደማቅ ሰማያዊ ሲሆን ንፋሱ ከዮብዶ፣ ጋጅ፣ ግልፍጣ ሰንሰለታማ ተራራ እየታከከ የጥድ፣ የዝግባ፣ የወይራ፣ የአጋም፣ የኮሽም፣ የግራዋ ... ዛፎችን እየወዘወዘና ጎንበስ ቀና እያደረገ ቅጠሎቻቸውን እንሿሽቶ በማወዛወዝ እያንጠባጠበ ይከንፋል ...

ከአምባው ጥጋ ጥግ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ከተቀመጡት ቃፊሮች አንዱ ድንገት ውልብ የሚል ነገር ታየው።

«ውልብ የሚል ነገር አየሁ ወይንስ ዐይኔ ነው?» ቆፍጠን ብሉ ጓደኛ ውን በኦሮምኛ ቋንቋ ጠየቀ - የዐይኑን ሽፋሽፍት ሳይከድን አፍጥጦ ቁልቁል እየተመለከተ።

«ኧረ እኔ አላየሁም» አለ፥ ጓደኛው - እሱ ወደሚያይበት አቅጣጫ ዐይኑን ቀስሮ።

«እኒያውልህ! . . . አየሃቸው? ከተረተሩ ወደ አሉት የዝግባ ዛፎች ሊገቡ ነው»

«አዎ አንተ! ሁለት ፈረሰኞች ናቸው» አለ - ለመለየት ግንባሩን ቋጠር ፈታ፣ አንገቱን ሰገግ መለስ እያደረገ።

«እነማን ይሆኑ?»

«እንጃ! የለበሱት ከእኛ ይለያል ... ፀጉረ ልውጥ ሳይሆኑ አይቀሩም» አለ - እየተጠራጠረ። «እነዚህ ሰዎች ፀጉረ ልውጥ ናቸው» አለ መጀመሪያ ያያቸው።

«ለገሮ እንንገራቸው?»





«ምን ብለን?»

«እንዴት ነው 'ምን ብለን?' ማለት? 'ሁለት ፀጉረ ልውጥ ሰዎች መጡ' ብለን ነዋ!»

«ጦር እንደመጣ ሁሉ ሁለት ሶስት እየሆነ ስለሚመጣው መንገደኛ ሁሉ ብንነግራቸው ያው እንደተለመደው 'ስለምትጠራጠሩ ነው የምትፈሩት' ይሉናላ» አለው። በዚህ መሀል ፈረሰኞቹ በሶምሶማ ወደ አምባው ተጠጉ።

መጀመሪያ ያያቸው ቃፊር «ገሮ! . . . ሁለት ፀጉረ ልውጥ ፈረሰኞች ወደ እኛ እየመጡ ነው» አለ። ገሮ ከተጋደሙበት ሳይነቃነቁ «ሁሉም ነገር ከተራራው ግርጌ ነው። አፋፍ ላይ ስለሆናችሁ ሁሉም ይታያችኋል። መቼም ፈላጊ እንጂ ተፈላጊ አይደክም ... የተከተላቸው ካለ አድፍጣችሁ ቃኙ ...» አሉ።

ገሮ ለማረፍ፥ ከመቀመጥ ይልቅ መጋደም ይበልጣል ባይ ነበሩ። «ከመቆም መቀመጥ፣ ከመቀመጥ ደግሞ መጋደም አያታክትም» ማለትም ያዘወትሩ ነበር። ማንም ይናገር ማን እንደተጋደሙ ያዳምጡታል! ነገሩ ካልጣማቸውና ካልሳባቸው መልስ ሳይሰጡ በዚያው ለሽ ይላሉ። የሚጥማቸው ወይም የሚያሳስብ ጉዳይ ከመጣ ደግሞ ተፈናጥረው ይነሳሉ።

... ፈረሰኞቹ ወደ ዛፏ ስር ቀረብ አሉና ከፈረሶቻቸው እየዘለሉ ወረዱ። ገሮ እንደ ንብ ንግሥት በወገኖቻቸው ተከበዋል።

«እነ ማን ናችሁ? ከወዴትስ መጣችሁ» አለ፥ አንዱ ቃፊር።

«ከራስ ጎበና የተላከ መልዕክት ለገሮ ለማድረስ ነው» አለ፥ ከመልዕክተኞቹ አንዱ።

ገሮ ተከናንበው ወደተጋደሙበት እንዲሄዱ ገለል አሉላቸው።

«ገሮ!» አሉ፥ መልዕክተኞቹ - ገሮ ከተጋደሙበት ፊት ለፊት ቆመው። ገሮ መልስ አልሰጡም፣ ጆሮአቸው ግን እንደ አንቴና ተቀስሯል።

«ራስ ጎበና 'ገብርልኝ' ብሏል» አለ በዕድሜ ጠና ያለው መልዕክተኛ።

«ገብርልኝ?! ገብርልኝ ባዩ ጎበና ማነው?» አሉ ገሮ - ከተጋደሙበት ሳይነሱ እንደዘበት።

«ጎበና የንጉሡ ባለሟልና የጦር መሪ ናቸዋ!» አለ - ከመልዕክተኞቹ አንዱ። የንጉሱ ባለሟልና የጦር መሪ የሚለው ግሳንግስ ለገሮ ስሜት አልፈጠረባቸውም።

«ይሄ ጎበና ያላችሁት ሰው እንደ እኔ ይተኛል?»

«አዎ!»

«እንደ እኔስ ይበላል፣ ይጠጣል?»

«አዎ!»

«እንደ እኔ ይሸናል?»

«እ... አዎ!» ብለው የነገሩ አዝማሚያ አላምር ያላቸው መልዕክተኞች እርስ በርስ ተያዩ።

«እንደ እኔ ዐይነ-ምድርስ ይወጣል?» ሲሉ ገሮ፥ «ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም» አለ አንዱ መልዕክተኛ ወደ ጓደኛው እያንሾካሾከ።

«አዎ ገሮ!» አለ፥ ሽምገል ያለው መልእክተኛ - መዘዙን ፈርቶ። ገሮ ከተጋደሙበት ብድግ አሉና «ጎበና እንደ እኔ ሰው ነዋ?» አሉ - የደመና ክንብንቧን አንስታ ብቅ እንዳለች ጀንበር የቀይ ዳማ ፊታቸው በፌዝ ፈክቶ።

«አዎ! ሰውማ ሰው ናቸው» አሉ ሁለቱም መልዕክተኞች በአንድነት።

«እንግዲያውማ! እኔ የጎዳና ልጅ እንደ እኔ ሰው ለሆነ ሰው እንደማልገብር ንገሩት» አሉ - ዐይናቸው በቁጣ እየተንቀለቀለ። መልዕክተኞቹ ድንገት እንደ እሳተ ገሞራ በፈነዳው የገሮ ቁጣ በድንጋጤ አመዳቸው ቡን አለ።

«ሰማችሁኝ አይደል?» አሉ ገሮ። ሁለቱ መልዕክተኞች እንደ ሃውልት ተገትረው መልስ ለመስጠት ልሳናቸው ተዘጋባቸው። ገሮ ተመቻችተው ተመልሰው ተጋደሙ። የእውነተኛ መሪ ቁጣው አንዴ ነዋ! እንደ ሐምሌ ዝናብ እኝኝ ... የለም። መልዕክተኞቹ የገሮን ወገኖች ቃኟቸው። ሁሉም በገሮ መልስ አንጀታቸው ቅቤ እንደጠጣ ከፈገግታቸው አስተዋሉ።

«ገሮ!» ተጣራ አንዱ መልዕክተኛ። ገሮ መልስ አልሰጡም።

«ገሮ ተኙ» አለ - ወደ ተከታዮቻቸው እያየ።





«ቆዩና ሲነቁ ጠይቋቸው ... መተኛቱን ተኝቶ የነቃ ብቻ ነው የሚያውቀው» አሏቸው - በምፀት። መልዕክተኞቹ ቤተክርስቲያን እንደ ገባ ውሻ በሃፍረት ተሸማቀው ቀልባቸው ተገፎ ወደ መጡበት ተመለሱ።

* * *

ራስ ጎበና መልዕክተኞቹ ያመጡትን የገሮን መልስ ካዳመጡ በኋላ ተቅበጠበጡ። ወዲህ ወዲያ ሄድ መለስ፣ ጎራዴያቸውን ወዝወዝ ... እያደረጉ ተወራጩ። አብረዋቸው የሚመክሩት መኳንንት በየራሳቸው ሃሳብ ጭልጥ ብለው አንዱን እያነሱ ሌላውን እየጣሉ መላ ፍለጋ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ በሃሳብ ባከኑ ...

ራስ ጎበና ድንገት «የገሮን መልስ ሰማችሁት አይደል?» አሉ። ሃሳባቸው ከጥያቄ ይልቅ ማረጋገጫ የመስጠት ቃና ነበረው። የመኳንንቱ ዐይን ራስ ጎበና ላይ ተደገነ።

«ገሮ 'እንደ እኔ ሰው ለሆነ ሰው አልገብርም' አለ። እህ?! ምን ወስን ትሉኛላችሁ ወንድሞቼ?! እውነት አለሁ ገሮ! እንደ እኔ ሰው ነህና መገበር አይገባህም ብዬ የንጉሴን ትዕዛዝ ልጣስ? ... ነው! እኔ እንደ አንተ ሰው አይደለሁም፤ የተቀባ ንጉሥ የመረጠኝ የጦር መሪ ነኝ ብዬ የማይረሳው ቁንጥጫ ልቆንጥጠው እና የንጉሴን ትዕዛዝ ልፈጽም? ... የቱ ነው ምርጫዬ? የቱን መፈፀም ነው ግዴታዬ? በሏ መላ በሉኝ ወንድሞቼ!» አሉ ጎበና - መንታ መንገድ ላይ መቆማቸውን ሳይደብቁ።

አፄ ምኒልክ ሸዋን ለማቅናት ሲወስኑ በበላይ አዛዥነት ያዘመቱት ራስ ጎበናን ነው። ወደ እምባቦ ከመሸገራቸው በፊት ግን የጅባትና ሜጫው ባላባት ገሮ ዘመቻቸውን አጣብቂኝ ውስጥ ከተቱባቸው።

«የገሮ መልስ የንቀት ይመስላል» አለ አንዱ ከወደ ጥግ።

«የት አውቆኝ ይንቀኛል?» አሉ፥ ጎበና።

«ቢያውቅማ ለምን ይንቅዎታል? ባለማወቁ ነው ንቀቱ። ስለዚህ ለእንዲህ ዓይነቱ ተሳስቶ አሳሳች ሰው ክንድን ማሳየት መቼም የግድ ነው» አሉ ወርቀ-ዘቦ ካባ የለበሱት።

«ምንድን ነው ክንድ ማሳየት? እስቲ ገለጥለጥ አርገው» አሉ፥ ጎበና::

«ምን ብዬ ልገላልጠው ጌታዬ? ግልጽ እኮ ነው፤ ትዕቢት ለወጠረው ክንድን ከማሳየት ሌላ ምን አማራጭ አለ?» ብለው የተናገሩትን ሀሳብ ወዲያው ማስላሰል ጀመሩ::

«የሁላችሁም ሀሳብ ይኸው የእሱ ውሳኔ ነው?»

«ነገሩ 'በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል' ሆነብን እኮ ... ተዚህ ሌላ አማራጭ ከየት ይመጣል?» ብለው ሌላው አማካሪ ያለዘቡ መስለው አጥብቀው አሰሩት::

«ገሮ ወደ አልፈለግሁት አቅጣጫ ወስዶ ወንድነቴን ከተፈታተነኝ ጥሩ ነው፤ እንተያያ! ይህ ከሆነ ሀሳባችሁ በሉ እንምከር፤ በሉ ማወላወሉን ትተን ድጋችንን እናጥብቃ!» ብለው ጎበና ብድግ አሉ::

«የለም ጌታዬ!» አሉ፥ ሁሉንም በፅሞና ሲያዳምጡ የቆዩት ሰው::
«እንዴት?»
«እስቲ አንቸኩል፤ የደፈረስ እኮ ከጠበቁት ይጠራል ጌታዬ!»
«እሱ እውነት ነው!» አሉ፥ ራስ ጎበና::
«ይቀመጡ ጌታዬ! እስቲ የኔን ሀሳብ ያድምጡኝ»?

«ያንተ ነገር መቼም ሁልግዜ እንደግመል ሽንት ወደኋላ ነው:: በል እስኪ ሀሳብህን ንገረን፤ ይኸው ቁጭ አልሁ» አሉ ጎበና - እየተቀመጡ::

«ገሮ የሜጫ ኦሮሞው ጀግና የጎዳና ነሞ ልጅ ነው:: አባቱ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሰው ገሎ ኤጀርሳ ለፎ ላይ አንድ እረኛ በወረወረበት እንጪት ተመትቶ በኦሮሞ ባህል ሰው የገደለው ስለማይቀበር የአሞራ ሲሳይ የሆነ ጀግና ነው:: ጎዳና ከሞተ በኋላ ወገኑን የገደለበት አንድ ጠላቱ 'ይሄ ነው ወገኖቼን የጨረሰው' እያለ አጽሙን በጦሩ ሲወጋጋ አንድ አጥንት ቱር ብላ ዐይኑን እጥፍታ ስለገደለችው 'ጎዳና ነሞ ከሞተ በኋላ የግዳዩን ቁጥር አንድ ሺህ አደረሰው' እየተባለ የሚወደስ፣ የሚከበር የሜጫ ኦሮሞ ጎልያድ መሆኑን ያልሰማ በድፍን ሜጫ አይገኝም::





«ይኸው የገሮ አባት ጎዳና ነሞ የአባቱን ግዛት በማስፋት እስከ በርጋ ወንዝ ድረስ ዘጠኝ መቶ ጋሻ መሬት ይዞ በባላባትነት ያስተዳድር ነበር:: ገሮ ጎዳና የጎዳና ነሞ የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ በኦሮሞ ባህል ደግሞ የመጀመሪያ ልጅ ውርስ ተቀባይ በመሆኑ ገሮ በአባቱ እግር የተተካ፤ በአባቱ ታሪክ ሰው የሚያከብረው፤ የአባቱ ወኔ እንደ ፍም እሳት ልቡ ውስጥ የተዳፈነ የኢችልቤ፣ የሰንጎታ፣ የዮብዶ፣ የጎበን፣ የጋጆና የግልፍጣ ባላባት ነው::

«እስኪ በጥሞና መልሱን እናጢነው:: 'እንደ እኔ ለሚበላና ለሚጠጣ ... እንደ እኔ ሰው ለሆነ አልገብርም' ነው እኮ ያለው፥ ገሮ:: ይህ ሰው ከአያት ቅድመ-አያቱ ጀምሮ የባላባት ዘር ነው:: ለአካባቢው እሱም ንጉስ ነው:: ድንገት 'ገብር' ሲባል 'ለምን?' ቢል ምን ነውር አለው:: በዚህ መልሱስ ሊወጋ፣ ደም ሊፈስ ይገባል?» አሉ፥ ሰውየው - የራስ ጎበናን የፊት ገጽታ እያስተዋሉ::

«ምን አልህ?» አሉ ጎበና::

ሰውየው መሬት ተከፍታ የዋጠቻቸው ያክል በድንጋጤ አመዳቸው ቡን አለ:: ቢሆንም አንዴ ነገሩን ጀምረውታልና «ጌታዬ! እምነት ተራራን ያንቀሳቅሳል ይባል የለም፤ እርግጥ ነው ያ እምነት ግን ፅኑ እምነት እንጂ ተልካሻ እምነት አይደለም ... የሚገጥመንን ፈተና ሁሉ በጦርነት፣ ታልሆነ በስምምነት መፍታት ካልቻልን ... ልፋታችን ይበላሻል፤ እስቲ ይሄን አጢኑት ሰዎቼ» አሉ::

«ትንሽ ሀሳብህን እየደጋገምህ አስፋኸው:: ቢሆንም በጎ ነገር ነው ያነሳኸው:: ሁልግዜ አዲስ ችግር ይጋረጥብናል:: ለገጠመን ነገር ጉዳትና ጥቅሙን አመዛዝነን መላ መሻት ግን አለብን:: ሀላፊነት ጦርን በቀኝ፤ ሰላምን በግራ የሚያስጨብጥ አይደል! 'እናንተ ማናችሁ?' አለን ገሮ ብለን እኛም 'አንተ ማነህ?' ብለን ጥያቄውን በጥያቄ ብንመልስ መዘዙ ትርጉም የሌለው ጥፋት ነው፤ እና እስኪ ውስጥ አወቅ ትመስላለህና ብላታ መላ አምጣ» አሉ ራስ ጎበና:: ያን ጊዜ የመኳንንቱ ዝምታ ተገርስሶ፣ የመጀመሪያው ሀሳብ ተረስቶ ሁሉም በአዲሱ ሀሳብ ላይ ተንጠላጠሉ ...

«ምነው ጉሮሮህን ጠረግህ? መላ አገኘህ?» አሉ፥ ጎበና ብላታን::

«እም ጌታዬ! ገሮ ጥሩ ወዳጅ ነው:: በዚያ ላይ የአንድ ወንዝ ልጆች ነን:: እኔ አግባብቼ አስገብረዋለሁ» አሉ::

ሁሉም በአድናቆት እንደገና ትክ ብለው አዩዋቸው፤ ጎበናም «ማስፈያ ነዋ!» አሉና የብላታ ዐይን ላይ አይናቸውን ተከሉ።

«ይመኑኝ ጌታዬ!» አሉ ብላታ - ፈርጠም ብለው።
«ምኒልክ ይሙት አምንሃለሁ! እንዳልከው ከሆነ የብዙ ሰው ህይወት አተረፍክ ማለት ነው። አሁን ተነስ፤ ፈረስ ይጫንልህ፣ ስንቅም ይዘጋጅልህ፤ የሚከተልህ ሰውም ልስጥህ ...» አሉ፥ ራስ ጎበና - የፈገግታ ብርሃን ገፅታቸው ላይ እየወጣ። «የለም ስንቅና ሰው አያሻኝም። በራሴ ፈረስ አሁኑኑ እሄዳለሁ። ከእርስዎ የምፈልገው አንድ ሱሪና አቡከዳዬ ሻሽ ብቻ ነው» አሉ።

«ያልከው ይዘጋጃል! አንተ ብቻ ከዚህ ፈተና ፈጥነህ አውጣን» አሉ፥ ጎበና ...

አቡከዳዬ በዚያ ዘመን የተከበረ ጀግና ራሱ ላይ የሚጠመጥመው ቀይ ሻሽ ነው። ብላታ፥ የፈለጉት ወዲያው ተሰጥቶአቸው ወደ ገሮ ቀዬ ጋለቡ። 'ወይ በለስ' አሉ ሌሎች መኳንንት - በቀና ሀሳቡና በተቀባይነቱ ቅናት እያመሳቸው።

ብላታ ረፋዱ ላይ ፈረሳቸው ላቡ እየተንቆረቆረና አረፋ እየደፈቀ ከገሮ ቀየ ደረሱ። ገሮ ተጋድመው የጠዋቷን ጀንበር ይሞቃሉ። ባለሟሎቹ በሙሉ የየእለት ሥራቸውን ለመከወን ስለሄዱ አጠገባቸው የነበሩት ሶስት ጎረምሶች ብቻ ነበሩ። እንግዳው፥ ገሮ ወደ ተጋደሙበት ተጠጉ ... «ገሮ እንኳን ደስ አለህ! ራስ ጎበና ገብሮልሃል» አሉ። ገሮ ጋቢያቸውን ገለጥ አድርገው ወዳጃቸው ፊት ላይ የሚንቦገቦገውን የደስታ ችቦ ተመለከቱ። ደስታው የእውነት ይመስላል።

«ጎበና ለምን ብሎ ይገብርልኛል?» ገሮ በጥርጣሬ ጠየቁ።

«ገበረልሃ! ... ገበረልህ፥ ገሮ ... ቃሌ እንደዚች ፀሐይ እውነት ነው» አሉ - ሰማዩን እያዩ።

«ጥያቄዬ 'ለምን ብሎ ገበረልኝ?' ነው፥ ወዳጄ?»





«እውነት የተናገረ መቼም በአዋቂ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያገኛል፤ ስለዚህ ለወንድነትህ ሱሪ ይገባሃል፣ ለጀግንነትህ ደግሞ አቡከዳዬ ይገባሃል ብለው ይኸው ጎበና ልከውልሃል ... ተቀበለኝ ገሮ» አሉ ብላታ።

ገሮ ከተጋደሙበት ተነስተው ጎበና የላኩላቸውን ሱሪና የራስ ጥምጥም አገላብጠው አይተው ፈገግ አሉ ... «ልበሰዋ፤ ሞክረው!» አሉ መልዕክተኛው። ገሮ ሱሪውን ለብሰው፣ አቡከዳዬውንም ጠመጠሙት። ወዲያው «ፈረሴን አምጣ አንተ!» አሉ ገሮ። ፈረሱ ቀረበ ... ገሮ ዘለው ጀርባው ላይ ወጥተው አምባው ላይ ሽምጥ ጋለቡ። የአካባቢው ሰው እየተግተለተለ ወደ ዛፉ መጣ። ገሮ ሱሪያቸውን አጥልቀው፣ አቡከዳዬ ጠምጥመው ፈረሳቸውን ደንገላስ እያስረገጡ ሲመጡ ሴቶች እልልታቸውን አቀለጡት፤ ወንዶቹ በራስ ማሰር ጠመንጃቸው እየተኮሱ ፎከሩ ...

«አሁኑኑ ልጆቼን ጥሩ» አሉ ገሮ። ሬባ፣ ዋሚ፣ ሁርሴ፣ ያዴሳ፣ ኬሎ፣ ባቲ የተባሉት ልጆቻቸው እየተጠሩ መጡ። በሉ ሃያ ሃያ ክብት አሁኑኑ አዘጋጁ። ጎበና ስለ ሰውነቴ ገብሮልኛልና እኔም ስለ ሰውነቱ ጀንበር ጠልቃ ሳትቀድመኝ እገብርለታለሁ» ብለው ተሸኝተው አደሩ።

የራስ ጎበና ሠራዊት የከተመበት አዲስ ዓለም የሚገኘው በርጋ አፋፍ በቅጽበት ተሸበረ። ከርቀት አቧራው ሽቅብ ሲነሳ ታዬ። «ገሮ ጦር ላከብን» ብለው መኳንንቱ የፈሩት በመድረሱ በግማሽ ደስታ በግማሽ ፍርሃት ተውጠው ትርምስ ፈጠሩ።

«እርስዎ ነዎት ያነን ቀላማጅ አምነው ጉድ ያደረጉን» እያሉ ጎበናን ገሰጿቸው። ጎበና ግራ ተጋቡ፤ ለጊዜው የተሳሳቱ መሰላቸው። ሳይቀድሙ መቀደማቸው፣ ሳይዘጋጁ አደጋ ላይ መውደቃቸው ስምና ክብራቸውን እንደሚያጎድፈው በማሰባቸው ለእንቢተኛው ገሮ የሰጡት ጊዜ አንገበገባቸው። ብላታንም «ጉድ አደረገኝ» ብለው ደጋግመው ወቀሱ። ነገሩ ሁሉ ስርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ቢሆንም ሁሉም ለመከላከል እንዲዘጋጅ አዘዙ። ራስ ጎበና ወደ አፋፍ ጥግ ሄደው አመች ቦታ ላይ በጦር ሜዳ መነፅራቸው ሲያዩ የታያቸው የከብት ቀንድ ብቻ ሆነ ... መላ ምድሯን ሊወቃ የነበረው ጥቁር ደመና በዚሁ በቅፅበት ተበተነ።

ጎበናና ገሮ ተገናኙ ... ከዚያ ጎበና በአፄ ምኒልክ የአስተዳደር ደንብ መሰረት ገሮን «ገሮ የአባትህን አገር ሰጥቼሃለሁ ... ልጆችህም ከእኔ ጋር ይዝመቱ» አሉ በስማ በለው፤ ገሮ ግራ ገባቸው፤ «ጎበና! በመልዕክት ስንነጋገር ቆይተናል፤ አሁን ግን አጠገብህ ነኝ፤ ቋንቋዬ ቋንቋህ ነው የምን ስማ በለው ነው?» ብለው በሳቅ ፍርስ አሉ ... «ይህ የንጉሰ ነገስቱ

ባለሟሎች ግዴታ ነው ...» አሏቸው ገርን:: ቋንቋ የሚያስለውጠው ግዴታ ገሮን ባይገባቸውም ከጎበና ጋር ግን ተግባቡ:: የገሮ ልጆችም ከራስ ጎበና ጋር እምባቦ ዘመቱ:: ሬባ የተባለው የገሮ የመጀመሪያ ልጅ ከጎበና ጋር ቀረ:: ሬባ የፈረስ ጉግስ ይወድ ስለነበር ሲጫወት ውሎ ሲመለስ አጋፋሪው «ወደ ገበታ መግቢያው ጊዜ አልፏልና አትገባም» አለው:: ሬባ ተቆጣ፤ ንዴቱን መቆጣጠርም ተሳነውና የአጋፋሪውን ራስ ይዞ ወገቡን ሰበረው:: ይህን ሃይለኝነቱንና የመኳንንቱን ደንብ አለመቀበሉን የተገነዘቡት ጎበና ሬባን ወደ ገሮ መለሱት:: ገሮ ደግሞ የሬባ ታናሽ ወንድም የሆነውን ዋሚ ገሮን ቦታውን ተክቶ ከጎበና ጋር እንዲዘምት ላኩት::

* * *

የገሮ አያት ነሞ አንድ ጊዜ በቤተሰቦቻቸውና በልጆቻቸው አምርረው ተቆጡ፤ «በሥራ መጠመድ ብቻ ዋጋ የለውም፤ ጉንዳንም ጠንካራ ሠራተኛ ናት፤ ነገር ግን በኮቴ ተደፍጥጣ ትሞታለች:: በሥራ ተጠምደን መማሰናችን ባልከፋ፤ ቁጥራችን ሲበዛ፣ ቦታችን ሲጠበን ግን ወዴት ነው የምንሸጋሸገው? ጉልበታም ቢመጣ የለፋንበትንና የማሰንበትን እንዳይነጥቀን የእሾህ አጥር ሰርተው፣ እንደ አንበሳ አግስተው የሚያስጥሉን እነማን ናቸው? ይህ ሀሳብ አንዳችሁን እንኳን አስጨንቋችሁ ያውቃል? ነጋ፣ ጠባ ... አየኋችሁ፤ ጠበኳችሁ ... አውራ የላችሁም፤ የምትከተሉት የላችሁም፤ ከባርነት የሚያሸሻችሁ የለም» ብለው አረፍ አሉ::

«የእኔ ዘሮች ጆል ሆናችኋል፤ ለነገ ማሰብ እየተሳናችሁ ነው:: እንደ ከብት አፋችሁ የገባውን ማመንዠክ፤ መስራት፤ እንደገና ማመንዠክ እንጂ ሌላ መሻት፤ ሌላ ለማግኘት መባዘን የተዋችሁ ሆናችኋል» አሉና ከተቀመጡበት ፈንጠር ብለው ሄደው ቆሙ:: ቤተሰቦቻቸው አንገታቸውን ከደፉበት ቀና ብለው አይዋቸው::

«ለወለደ፣ ዘር ላለው ሰው ሞት የጉዞ መጨረሻው አይደለም:: የእኔ የሚለውን ሁሉ ሜዳ ላይ ዝርግፍ አርጎ ውልቅ የሚል ያልወለደ፤ ዘር የሌለው ብቻ ነው:: እስቲ አስቡት! ሞት ዱብ ዕዳ የሚሆንብን ሳናመልጥ ስንሸሽ ስለምንኖር አይደለም? ለዚህ ነው ፈሪ ሞትን የማያሸንፈው፤ ጀግና ግን አይሞትም፤ ለምን ጀግና አይሞትም? ሞትን አይፈራማ! የሚገለው ፍርሃተ ሞት አይደለማ! ጀግና የሚሞተው ፍርሃት በሌለው በሽታ ወይንም ጦር ነው:: ጀግና የሚሞተው የፈለገውን ፈፅሞ ነው::»

ትንሽ ፀጥታ ሰፈነ ...





ከወደኋላ ከተቀመጡት አንዱ «ይሄ የሚቸግር አይመስለኝም ወገኖቼ! አያት ቅድመ-አያቶቻችን የአቆዩልንን ደንብ እየዘነጋነው፤ እየናቅነው እንጂ መላ አለው:: የከብት ዘር አዳቅለን ጠንካራ ዘር እንደምናገኘው ይህም ነገር ቀላል ነው:: የጠንካራ ቤተሰብ ዘር የሆነች ሴት እንፈልግና ባላባታችንን እናጋባ:: ከሁለቱ የሚፈጠረው ልጅ እንደ ዝሆን በግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ ይሆናል፤ እንደ አንበሳ በግሳቱ የሚያርበደብድ ምርጥ የትውልድ አውራ ስናገኝ አለኝታችን፣ ሰብሳቢያችን እናደርገዋለን» አሉ:: ሁሉም በሀሳባቸው ፈነደቁ፤ ሴቶች እልል አሉ፤ ወንዶቹ ፎከሩ::

«ዝናብ በመዝነቡ ብቻ ምርት የለም:: ዝናብ ሲዘንብ መጀመሪያ አፈሩ ይርሳል:: ያን ወቅት ጠብቆ የሚያርስና የሚቆፍር ከሌለ ስለ ዘነበ ብቻ ዘር ቢበተን አረሞች ስለሚውጡት ቡቃያ ሁኖ በሥርዓቱ አያፈራም:: የሚፈለገው ሲገኝና ሆድ ሲጠግብ ደግሞ ጭንቅላት ወዲያው ነገን ማሰብ አለበት ... መጭው ነገ ላይ ወቅትን አጢኖ የሚያርስና አእምሮውን በነገ እውነት የሚያጠግብ ያ ነው - ለእኔ ጀግና:: የዝናብ ውሀ ፈሳሽ ነው፤ አንዳንዱ ሰርጎ ወደ ውስጥ ይገባል፤ ሌላው ከወንዝ ይቀላቀላል፤ ሁሉም ግን ጉዞው ሩቅ ነው:: አንድ ቦታ አይቆምም:: ልባም ጀግናም ሁሌም ወደ ነገ ይፈሳል፣ ርቆ ይጓዛል ...

«ዋቅን የምናመልከው ከመቀበል ይልቅ በመስጠቱ ነው:: በአያቶቻችን ዘመን የነበረ አንድ ሰው አንድ ጊዜ ባለጠጋ ሆነ ... ከብቱ፣ ፍየሉ፣ በጉ፤ አህያው፣ ግመሉ ... እንደ አሸዋ በዛለት:: ከእለታት አንድ ቀን ታዲያ ያ ሰው ዋቅን አንድ ጥያቄ ጠየቀው፤ 'ዋቅ እኔ እንደ አሸዋ የበዛ ከብት፣ ፍየል፣ በግ ... አለኝ:: አሁን እንደ አንተ መመለክ እፈልጋለሁ:: ለዚህ ደግሞ የእኔና የአንተ ሀብት መታየትና መነፃፀር አለበት:: በሀብት ከበለጥከኝ ቀሪ ዘመኔን ሙሉ እሰግድልሃለሁ፤ በሀብት ከበለጥኩህ ደግሞ ለአንተ የሚሰግዱ ሁሉ ለእኔ ይሰግዱልኛል' ብሎ ጠየቀው:: ዋቅም በትዕግስት አዳምጦት 'ጥሩ፤ በሀሳብህ እስማማለሁ' አለውና ሀብታቸውን ለማነፃፀር ቀን ቆርጠው ተለያዩ::

«በቀጠሮው ቀንና ቦታ የባለፀጋው ከብት፣ ፍየል ... ሜዳውን አለበሰውና የዋቅ ንብረት እስኪመጣ መጠባበቅ ጀመረ ... ድንገት ግን አንበሳ፣ ጅብ፣ የመሳሰሉት የምድር አራዊት መጥተው ሁሉንም እንስሳት ፈጇቸው - ጥቂት ፍየሎች ብቻ ሲቀሩ::

«በኋላ ዋቅ መጣ:: 'ምነው?' አለ፥ ባለፀጋው - በምሬት ዋቅን እያየ::

«ከዚያ 'አየህ አንተ መሰብሰብ እንጂ መስጠት አታውቅም፡፡ ለአንተ፥ ዛሬ ወደ ነገ የሚወስድ ጎዳና አይደለም፡፡ ዛሬ ለአንተ ሃብት ማጠራቀሚያ፣ ራስህን ብቻ የምታስብበት ነው፤ ለእኔ ግን ዛሬ ፍጥረታቴን የማስብበትና የምሰጥበት ነው ... እኔ መስጠትን እንጂ መሰብሰብን አልሻም፡፡ እኔ የሰጧቸው ተቆርቁረው ንብረትህን አጠፉብህ፤ አንተ ግን የሰጠሀቸው ስለሌሉ በውድድርህ ቀን የሚረዳህ አጣህ፤ ስለዚህ በስግብግብነትህ፣ በማያስበልጥህ መብለጥ ስለ ሻትህ ተሸነፍህ፤ በመሸነፍህ ደግሞ ያለህ ተወሰደብህል' ... አለው» አሉ፡፡ ምሳሌያቸውን ለማያያዝ ትንሽ አሰብ አደረጉና፤

«ሁላችንም በሰበሰብነው መኖራችንና መመካታችን ዋጋ የለውም፡፡ ለህፃኖቻችን፣ ለወገኖቻችን ስለምንሰጠው በጎ ነገር ማሰብ አለብን» አሉና ፀጥ አሉ፡፡

ከቤተሰቦቻቸው አንዱ «ሀላፊነት ግዴለሽነትንና ስንፍናን እንደሚያጠፋ የመከሩን ከየልቦናችን ምንጊዜም አይጠፋም፡፡ እኔ እንደማስበው ለሀላፊነት የሚሆን ሰው ያስፈልገናል ...» አለ፡፡

* * *

ነሞ ምርጥ የባላባትና የጀግና ዘር የሆነች ሚስት አገቡ፡፡ ወዲያው ወንድ ልጅ ተፀነሰና ተወለደ፤ ስሙም ጎዳና ነሞ ተባለ፡፡ በልዩ ፍቅርና እንክብካቤ ያደገው ሰግላጋውና ጠንካራው ጎዳና እውነትም እንደ ተርብ እየተናደፈና እንደ ቀስት እየተወረወረ የወገኖቹ አለኝታ ሆኖ የወገኑን ግዛት አስፋፋ፡፡ በዚያም የጦርነት ውሎ አፈ-ታሪካዊ ግነት ባለው አቆጣጠር፥ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሰው ገድሎ አንድ እረኛ በወረወረበት እንጨት ተወጋ፡፡ አብረውት የነበሩት ፍርሃትና እልህ እየተናነቃቸው አፋፍሰው አነሱትና እረኛውን ለመፈለግና ለመያዝ ብድግ ሲሉ «ተውት፤ ልጅ ነው» አለ - ጀግናው ጎዳና ...

«ልጅ ቢሆንም፤ የገባበት ገብተን ...»

«ተውት እልኩ፤ ተውት፤ እኔ ስንትና ስንት ሰው ጨርሼ የለም?»
«ቢሆንስ?»
«ስለዚህ ከወደዳችሁኝ የምላችሁን ስሙኝ ... ይልቅስ ጋደም አድርጉኝ» አለ፡፡





ሲያጋድሙት አቃሰተ ... ትኩሳቱ ጨመረ፡፡ ግንባሩ ላይ ላብ ችፍፍ አለ ... በዚያ መጓጓዣ በሌለበት፣ ጉዞው ሁሉ በእግርና በፈረስ በሆነበት ዘመን ቁስለኛውን ጎዳናን መርዳት ተሳናቸው፡፡ ጎዳና እያቃሰተ የሆነ ነገር ለመናገር ሞከረ፡፡ አንገቱን ቢያቃኑት፣ ወደ አፉ ጠጋ ቢሉም የሚለውን መስማት የቻለ አልነበረም፡፡ የሚለውን ለመስማት የፈለገ ወደ ልቡ ዘልቆ ቢያዳምጥ 'ሲያልቅ አያምር' ያለውን አባባል ጥርት አድርጎ በሰማ ነበር ...

ጎዳና ዐይኑን ሰማዩ ላይ ተክሎ ከነገ የዕድሜ ብድር ጠየቀ፡፡ ጥያቄውን ሆነ እልሁን የጊዜ ባንክ አላጤነም፡፡ ስለዚህ፤

«ቢቃ ሳይመሽባችሁ ሂዱ!» አለ ጎዳና ነሞ - የማይቀረውን ሞት ለመቀበል፡፡

«ትተንህ?» አሉ - በመደናገጥ፡፡

ጆፌ አሞራዎች ሁሌም ሰብሰብ ብሎ ሰው ሲጓዝ ከኋላ ከኋላ መከተላቸው የተለመደ ነው፡፡ ግጭት ሲፈጠር የሌላው ስቃይ ለነሱ ሲሳይ ነው፡፡ ያን ጊዜም ጆፌዎችን ቢወረውሩባቸው፤ ቢያባርሯቸው ከዚህ ወደዚያ ከዚያ ወደዚህ እያሉ ይጠባበቃሉ፡፡ የጆፌ አሞራዎቹ አይን ተጋድሞ ወደሚያቃስተው ጎዳና ላይ ነው፤ ጎዳናም በስቃዩ መሃል አጮልቆ የሚያየው አሞራዎችን ነው፡፡ በይና ተበይ ሳያቋርጡ ይተያያሉ... ህይወት ግን መቀጠል አለባት፡፡ ጀግና፥ ህይወት እንድትቀጥል የሚያሸጋግር ድልድይ ነው፤ ጀግና ለወገኑ ጥቅም መስዋዕት ለመሆን የቆረጠ ነው፡፡

ስለዚህ ቀሪውን ሩጫ እንዲሸፍኑ ተከታዮቹን "ሂዱ እልኩኮ!" ብሎ ገሰፀ፡፡ ሰዎቹ ግንባሩን እየሳሙ ከተቀመጡበት ተነሱ፡፡ ጎዳና አንጀቱ እየተላወሰ ዐይኑን ጨፈነ፡፡ ዕንባው ከውስጥ እንደማይንዶሎዶል ሁሉ የዓይን ማዝ ብቻ ነው ዓይኑ ስር የነበረው፡፡ ሰዎቹ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ነብያቸው፣ ጀግናቸው እንዳዘዛቸው ... የሞት እሳትና ዲን ወድቆ ሲመታ ሳያዩ፤ እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ሃውልት ሳይሆኑ የጀግናውን ግንባር ስመው፣ ሰምለም ቅጠል ላዩ ላይ ጥለው ዞረው ሳያዩ ነጎዱ ... ጆፌዎች ክንፋቸውን ዘርግተው፣ አንገታቸውን ቁልቁል አስግገው አንዣበቡ ...

* * *

አፄ ምኒልክ ሸዋን ካቀኑ፣ ገሮም ከገበሩ በኋላ ገሮ በባላባትነት ይዘውት የኖሩት ሁሉ ፀናላቸው... አንድ ቀን ግን የግራዝማች ባይሳ አባት ጭኩ፥ ቱሉጎርምቲን «እባክህ ገሮ፥ ይህ አገር መቼም የእኔ መሆኑን ታውቃለህ፤ ጎዳና ነሞ በጉልበቱ ነው የቀማን ... ስለዚህ ሸጥልኝ!» አሉ ገሮን፡፡

ገሮም «እሺ! በአንድ ጭብጥ ሎኮ ሽጨልሃለሁ» አሏቸው፡፡

«ምኒልክ ይሙት! እኔም ገዝቼሃለሁ» አሉ፥ ጭኮ፡፡

ሎኮ የፈረስ መንተቻ ጠፍር ነው፡፡ አንድ ጭብጥ ሎኮ ማለት ቁጥሩ ሃያ አምስትና ሰላሳ ይደርሳል ... ያ ማለት ደግሞ ገሮ ለጭኮ የሸጡላቸው መሬት ከሃያ እስከ ሰላሳ ፈረስ ያስከፍላል ማለት ነው፡፡ በዚህም የቱለማ ባላባቱ ጭኮ በጎዳና የተወሰደባቸው መሬት ከሜጫ ተወስዶ ለቱለማ በገሮ ተሸጠ፡፡ አንድ ጭብጥ ሎኮው ግን ሳይከፈል ቀረ፡፡



# ፬

## አባ ዶዮ

የገሮ ሁለተኛ ልጅ የነበረው ዋሚ ገሮ ባላባትነቱን ከአባቱ ወረሰ፡፡ ዋሚ ገሮም የባላባትነት ስልጣኑ ሲያበቃ ለመጀመሪያ ልጁ ለአባ ዶዮ አወረሰ፡፡

የኦሮሞ ባላባቶች፥ ማዕከላዊ ግዛት እና አሀዳዊ መንግሥት ባልነበረበት ዘመን የኦሮሞ ህዝብን ያስተዳድሩ የነበሩ ገገርዎች ሲሆኑ በኢትዮጵያ አሀዳዊ መንግሥት ሲመሰረት ይዘውት ከኖሩት መሬት ሲሶውን በመያዝ ከጭቃ ሹም በላይ በመሆን በኦሮሞ ህዝብ ተቀባይነት የነበራቸው መሪዎች ናቸው፡፡

አባ ዶዮ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በተሰጠው አዋጅ መሠረት አያታቸው ይዘውት ከቆዩት «ዘጠኝ መቶ ጋሻ መሬት ውስጥ ሲሶውን ሁለት መቶ ሰባ ጋሻ መሬት ይገባኛል» ብለው እስከ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በትረ-ስልጣን ጊዜ ቢከራከሩም ከስልሳ ጋሻ መሬት በላይ ማግኘት ሳይሳካላቸው ቀረ፡፡ በዚህም ቂም የፓርላማ አባል በነበሩበት ዘመን አባ ዶዮ የንጉሡን ሀሳብ የሚቃረኑ፤ በምክንያታዊ ትችታቸውም ንጉሡን በሀሳብ እንደ ተርብ የሚናደፉ ደፋር እንደነበሩ ይነገርላቸዋል፡፡

አባ ዶዮ ኢጣሊያውያን ፋሽስቶች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ ከኢጣሊያ ያበሩ በመምሰል አርበኞችን በተለይም የአጎታቸውን ልጅ ጃገማ ኬሎን በስውር በማገዝና የኢጣሊያን እቅድ በጃገማ ለሚመሩት አርበኞች በማቀበል ጉልህ አስተዋፅኦ ያደረጉ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር አባ ዶዮ በሥራ አጋጣሚና በግል በተገናኟቸው ሰዎች ሳቢያ በአካባቢያቸው የመጀመሪያው የካቶሊክ እምነት ተከታይ በመሆን 'አገር የጋራ ሃይማኖት ግን የግል' መሆኑን በተግባር ያረጋገጡ ናቸው፡፡

አባ ዶዮ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ በነበረው ፓርላማ አባል ነበሩ፡፡ «የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትነት ስልጣን ከንግስት ሳባና ከንጉስ ሰሰሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳያቋርጥ ተያይዞ ከመጣው ከንጉስ ሳህለ ስላሴ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ትውልድ ሳይወጣ ምንግዜም ይኖራል» በሚለው ሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ጠንካራ ተቃውሞ ያሰሙ፤ በአካባቢያቸው ህዝብም ዘንድ የተከበሩና የተፈሩ ሰው ነበሩ፡፡

ከሁሉም በላይ ግን አባ ዶዮን የሜጫ ኦሮሞ ህዝብ «የሰላም አባት» እንዲላቸው ያደረገው ተግባር ጣሊያኖች በከፋፍለህ ግዛ መርህ የህዝቡን አንድነት ለመበታተንና እርስበርስም ለማፋጀት ያቀዱትን የዘር ልዩነት እሳት ማጥፋታቸው ነው።

ይህም የኢጣሊያ ዕቅድ በአልፈታና ጀልዱ በመጠኑ ተፈጽሟል። በሜጫ ግን እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የአገር ሽማግሌዎች «ከባላባቱ ከአባ ዶዮ ጋር እንምከርበት» ይሉና አባ ዶዮ ቤት ለመገናኘት ይወስናሉ። አባ ዶዮም ስለ እቅዱ የሰሙ ቢሆንም በቀጠሮው ይስማማሉ። ሽማግሌዎች ደግሞ የብልሁንና በህዝቡ የተከበሩትን የአባ ዶዮን ምክርና ድጋፍ  ማግኘት እንዳለባቸው ተማምነዋል።

የቀጠሮው ዕለት ሽማግሌዎች ወደ አባ ዶዮ ቤት ሲገቡ በሩ ላይ ቆመው የሚቀበሏቸው አባ ዶዮ ሽማግሌዎች በስልቻ ከተቀመጠው ሰርገኛ ጤፍ እየዘገኑ እንዲገቡ አደረጉ። እንግዶች በሙሉ መግባታቸውን ሲያረጋግጡ አባ ዶዮም ገቡ። እንደገቡ ሁሉም በእፍኛቸው ሰርገኛ ጤፉን እንደያዙ አዩ ...

«አባ ዶዮ! ምን አርጉት ብለህ ነው ሰርገኛ ጤፍ ያሳፈስከን?» አሉ ሽማግሌዎቹ።

«በሉ ስብሰባችን ከመጀመሩ በፊት ነጭና ጥቁሩን ለዩልኝ» አሉ፥ አባ ዶዮ - ኮስተር ብለው።

«አይ አባ ዶዮ! ትቀልዳለህ? እንዴት ተደርጎ ነው ጥቁርና ነጩ የሚለየው? የማይቻለውን! ምነው ቀለድህብን?» አሉ በአንድነት።

«በሉ ይቅር በሉኝ! ካስቸገራችሁ ተውት» አሉ፥ አባ ዶዮ።

ከዚያ ሚስታቸው ያዘጋጁት ምሳ ቀረበ። አባ ዶዮና ባለቤታቸው በማስተናገድ ተፍ ተፍ ብለው ጨዋታው ደርቶ ተበላ ተጠጣ፤ በመጨረሻም ምሰቡ ተነሳ።

«በሉ ወደ ጉዳያችን እንግባ፤ ስብሰባችን ስለምን ነው?» አሉ፥ አባ ዶዮ።

«አይ! ጣሊያን 'ከአማራ ነፃ የምትወጡበት ጊዜ አሁን ነው' ብሉናል። አልፈታ፣ ጀልዱ አማራን እያባረሩ፣ የሚያንገራግሩትንም እየገደሉ





ነው። እኛ ግን ከእርምጃችን በፊት ለአንተ እንንገርህ፣ ካንተ ጋርም እንምከር ብለን ይኸው እንገናኝ አልንህ» አሏቸው።

«ማለፊያ ሀሳብ ነው!» አሉ፥ አባ ዶዮ።

«ጣሊያን ከባህር ማዶ መጥቶ ከአማራ ነፃ ሊያወጣን ነዋ! ጥሩ ነው፤ በሉ መጣሁ» ብለው ወጡና «ልጆች! አሰፋና ካሣን ባስቸኳይ ጥሩልኝ» ብለው ተመለሱ። አሰፋና ካሣ የአባታቸውን እግር ተከትለው ከተፍ አሉ።

«አማራን እንግደል ብላችሁ አይደል የመጣችሁ!»

«አዎ!» ሽማግሌዎቹ ትንሽ ግራ ተጋብተው ተያዩ።

«በሉ ወደ ውጭ ሳንወጣ በፊት እነዚህን ልጆቼን ቀጥለን ደግሞ እናታቸውን እንግደላቸው» አሉ፥ አባ ዶዮ - ጎራዴያቸውን እየመዘዙ ...

«ምነው ጌታዬ! ለምን የአንተን ልጆች እንገላለን?» ብለው ጠየቁ ሽማግሌዎቹ ተደናግጠው።

«እህ! አሁን ምሣ አብልታችሁ የወጣችው እናታቸው እኮ የመንዝ አማራ ናት። ልጆቹም በአባታቸው ኦሮሞ ቢሆኑም በእናታቸው አማራ ናቸው፤ አማራን መግደል፣ ማባረር ካለብን ከዚህ እንጀምራ» አሉ፥ አባ ዶዮ።

«ይህማ እንዴት ይሆናል? አናደርገውም። አንተስ አማናደርገው ለምን ትጠይቀናለህ?» አሉ - እየተሰቃጠጡ።

«እህ! ምን ላርግ? ቅድም 'ሰርገኛውን ጤፍ ለዩ' ያልኳችሁ እኮ ለዚህ ነው። አማራና ኦሮሞ እንደ ሰርገኛው ጤፍ ተቀላቅሏል ወንድሞቼ... እስከ ከናንተ ውስጥ ከአማራ ያልተጋባ ካለ ይንገረኝ? በተለይ ከሸዋ አማራ ጋ ተቀላቅለናል፤ እኛ ኦሮሞዎች ጣሊያን የማያውቀው፣ የማይገምተው የሚያከራ የ«ጉዲፈቻ» እና የ«ሐርመ ሆዳ» (ጡት መጥባት) ባህል አለን፤ በዚህ ባህላችን ከተለያዩ ጎሳዎች ከመጡት ጋር አንድ ሆነናል። ይህ ባህላች ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአንድነትና የአብሮ መኖር መሰረ ነው። ስለዚህ ጣሊያኖች ተለያዩ ቢሉን እኛ እንዴት መለያየት እንችላለን? አሉ፥ አባ ዶዮ - ግራ ቀኙን በዐይናቸው እየቃኙ። ሽማግሌዎች የአባ ዶ

ሃሳብ ስላሳመናቸው በፋሽስቶች የተቀነባበረው የመተላለቅ ድግስ ተበላሸ፤ የአባ ዶዮ ምሳሌም በህዝቡ ህሊና የማይረሳ የሰላም መላ ተደርጎ እስከአሁን ይታወሳል።

ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን ሕዝቦች በበላይነታቸውና በአይበገሬነ ታቸው ተሰፋ አስቆርጠው በነበረበት በዚያ ዘመን፤ ዓለም አቀፍ ፍትህ ጠፍቶ ጉልበታም ድንበር ጥሶ እየገባ፣ የሕዝቦችን ሀብትና ንብረት እየቀማ በባርነት ቀጥቅጦ በገዛበት በዚያ ዘመን በ«ዐይንህን ጨፍን እናሞኝህ» ብሒል የቀበሮ ባህታውያን ከሚጠቀሙበት መላ ዋነኛው ህዝብን በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ መከፋፈል ነበር።

ያን መሰሪ ዘዴ የተረዳው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የኢጣሊያ ወራሪዎች በአዘጋጁለት ወጥመድ ወገኑን ማጥመድ ሳያስብ በልዩነቱ እየተቻቻለ፣ በዱር ገደሉ እየተሰባሰበ፣ ባልተጠበቀ ሰዓትና ሁኔታ እስከ አፍንጫው ድረስ የታጠቀውን ወራሪ እንደ ተርብ እየተናደፈ እረፍት ሲነሳው ኖረ ...



# ፫

## ጃገማ - አባ ዳማ

የአባ ዶዮ አጎት ኬሉ ገሮ የሜጫ ኦሮሞ ናቸው። በኦሮምኛ ቋንቋ ኬሉ ማለት የመስቀል አበባ ማለት ነው። ሁሉም የሚጠራቸው ታዲያ በፈረሳቸው ስም አባ ጃገማ እያለ ነው። የኬሉ ገሮ እናት የልጃቸው ፈረስ ሲቅበጠበጥ፣ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል አይተው «ይሄ ጃገማ ፈረስ ሃይለኛ ነው» አሉ። ጃገማ በኦሮምኛ ቋንቋ «ትልቅ ዛፍ» ማለት ነው። ስለዚህ ኬሉ ገሮ ከዚያን ጊዜ በኋላ መጠሪያቸው 'አባ ጃገማ ሆነ። 'ስምን መላክ ያወጣዋል' እንዲሉ ድንገት የወጣው ስም ከደንበኛው ስም በለጠና አባ ጃገማ አፍ የሚሞላ፣ ሁሉም የሚወደው ስም ሆነ።

አባ ጃገማ ሶስት ጊዜ ሞራ ለብሰዋል። በኦሮም ባህል አንድ ሰው ሞራ ለመልበስ የአንድ ሺህ ከብቶች ባለቤት መሆን አለበት። አባ ጃገማ ግን ከአንድ አልፈው ሶስት ጊዜ ሞራ ለብሰዋል። አባ ጃገማ በዮብዶ፣ ሰንጎታ፣ ኢችልቤ፣ ጎበን፣ ሜታ አምስት መኖሪያ ቤት ነበራቸው። አባ ጃገማ በወር ውስጥ ዮብዶ ሶስት ቀን፣ ሰንጎታ አስራ አምስት ቀን፣ ኢችልቤ ሶስት ቀን፣ ጎበን ሶስት ቀን፣ ሜታ ሶስት ቀን ያድራሉ፤ በወር ውስጥ ለሶስት ቀን ደግሞ ከቤቶቻቸው ውጭ ያድራሉ። ይህ ስርዓት ከሞላ ጎደል ሁሌም አይዛባም።

አባ ጃገማ ሁሌም ቤታቸውን የሚሰሩት ጫካ አስመንጥረው ነው፤ እፅዋትንና እንስሳትን ይወዳሉ፤ አዲስ መንደር መመስረትም ምርጫቸው ነው። አሮጌ መኖሪያ ቶሎ ይሰለቻቸዋል፤ ስለዚህ አዲስ ነገር ይወዳሉ። ትልቅነት በመከተል ሳይሆን ቀድሞ በመጀመር የሚገኝ ነው ባይ ነበሩ። ስለዚህ ከለማው ይልቅ ወደ አልለማው ይሄዳሉ። አባ ጃገማ ቤታቸውን በሚሰሩበት ቦታ ሁሉ ገበሬዎች አሏቸው። ለምሳሌ ሰንጎታ በተባለው ቦታ አስር ገበሬዎች ከነቤተሰቦቻቸው አብረዋቸው ይኖሩ ነበር። የእሳቸው ቤት ከመካከል ይሆንና ዙሪያውን የአራሾቻቸው ቤቶች ይከቡታል።

የአባ ጃገማ ገበሬዎች ሁለት ቀን ለራሳቸው፣ አንድ ቀን ደግሞ ለአባ ጃገማ ያርሳሉ። «ዝንጀሮና ጦጣ እወዳለሁ፤ ዝንጀሮዎች አባትና እናታቸውን

ይመስላሉ፤ ዲቃላ የላቸውም፤ የዝንጀሮ ልጅ አባቱንና እያቱን ስለሚመስል ደስ ይለኛል» የሚሉት አባ ጃገማ ከመልከኛ ሰው ይልቅ ፋንጋ ሰውን መቅረብና በሰበብ አስባቡ መሸለምም ያዘወትሩ ነበር።

አባ ጃገማ ዝንጀሮና ጦጣን መውደድ ብቻ ሳይሆን ለዝንጀሮና ጦጣ የሚሆን እርሻም ያዘጋጃሉ። እንደ እሳቸውና ገበሬዎቻቸው ዝንጀሮና ጦጣም እሸት ቀምሰው፣ የድርሻቸውን ምርት ተካፍለው ከአባ ጃገማ ጋር ከአንድ ወንዝ ተጎንጭተው መኖር መብታቸው ነው። አባ ጃገማ ማምረት የማይችሉትን መርዳት ፅድቅ ነው ብለው ያምኑ ነበር። ከዝንጀሮና ጦጣ ጋር የሚጣሉት ግን ዝንጀሮና ጦጣ የራሳቸውን ትተው፣ የገበሬውን ቡቃያ አልፈው የሳቸው እርሻ ውስጥ ገብተው ሰብል ከበሉባቸው ብቻ ነው።

«እነዚህ ውለታ ቢስ ባለጌዎች አያችሁልኝ? የራሳቸውን ትተው፣ የገበሬዎችን ማሳ አልፈው የእኔን የሚበሉት እኔን ለማጥቃት አይደል?! እኒህ ልካቸውን የሚያልፉ ጣት ነካሾች አይማረኝ ብምራቸው» ይሉና ጦር ያለው ጦሩን፤ መጥረቢያ ያለው መጥረቢያውን፣ ውሻ ያለው ውሻውን ይዞ ዝንጀሮዎች የሚያድሩባቸውን ዛፎች ከበው ይጨፈጭፏቸዋል።

ይህ ግን ዳግመኛ ለዝንጀሮ እና ለጦጣ ማሳ አላዘጋጅም አያሰኛቸውም። መቼም ዝንጀሮ ሆኖ ማጥፋት አይቀርማ ... እንደገና የዝንጀሮ ማሳ ያዘጋጃሉ፤ እስከአላጠቋቸው ድረስም በሰላም ተከባብረው ይኖራሉ። ካጠፉ ደግሞ ይቀጧቸዋል፤ እንስሳም ቢሆኑ ህልውናቸው መጠበቅ አለበት፤ ዝም ማለት ግን በአባ ጃገማ እምነት ንቀት ነው - ህልውናን የሚያጠፋ ንቀት። ይህ ለኬሎ የማይቀበሉት የሰው ልጅ እብሪት ነው። ዝንጀሮና ጦጣ በልካቸው ያስባሉ፤ ሲያጠፉ ስለሚያውቁ ይሸሻሉ። ሲቀጡ ይገባቸዋል። አብሮ ለመኖር ትንሽ መጋጨት፣ ትንሽ መቀጣጣት፣ ... የኑሮ ማጣፈጫ ቅመም እንደማለት ነው!

አባ ጃገማ እንደ አያታቸው እንደ ጎዳና ነም ያለ ጀግና ልጅ፣ ወገኑን የሚያኮራ አንበሳ መውለድ አቀዱና ስፍር ቁጥር ከሌለው ሀብታቸው የሚበሉትንና የሚጠጡትን ወገኖቻቸውን አማከሩ። በዘሯ ጠንካራ የሆነች፤ በውበቷ ጠምበለል ልጅ የምትተካ፣ እንደ አያቱ ግሥላ የሆነ ልጅ የምትወልድ ሴት በሜጫ፣ ቱለማ፣ አርሲ ... ተፈለገች። ቀን በቀናት፣ ወር በወራት ተተካ። በመጨረሻ ሁሉን የምታሟላ የባላባት ዘር፣ የጀግና ዘር፣ የውበት ምንጭ የሆነች የእነ ኩመላ ፈይሳ፣ ፈይሳ ኢኒካ፣ ኢኒካ ኡለሞ ዘር





ደላንዱ እናቱ ኡለሞ ዱሌ አምቦ አካባቢ ተገኘች። በኦሮምኛ ቋንቋ ደላንዱ ማለት ቁጤማ ማለት ነው።

ቁጤማዋ ደላንዱና የመስቀል አበባው ኬሎ ገሮ ተጋቡ። ደላንዱ ሶስት ልጆችን (ጊዲ፣ ሴንሴ፣ ጤንቁሳ) ወለደች። አባ ጃገማ የሚፈልጉት ልጅ ግን አለመወለዱን መንፈሳቸው እየነገራቸው ጥበቃቸውን ቀጠሉ ... ስለዚህ ኬሎ ደላንዱን በእምስቱም ቤታቸው ሰንጎታ፣ ኢችልቤ፣ ጎበን፣ ሜታ፣ ዮብዶ ለሶስት ዓመታት ይዘዋት ሲዞሩ ቆይተው በመጨረሻ ሌላ ልጅ ፀነሰች። አባ ጃገማ ሚስታቸውን ካጠገቤ አትለይ አሉ።

የልጅ ኢያሱ መንግሥት ወድቆ ንግስት ዘውዲቱ ሲነግሱ፤ ልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን ደግሞ አልጋ ወራሽ ሆኑ። በዚህም ምክንያት ኬሎ ገሮ፣ ሌሎች ባላባቶችና የአገር ሽማግሌዎች እጅ እንዲነሱ ወደ አዲስ አበባ ተጠሩ። ደላንዱ ግን ድርስ ነፍሰጡር ነበረች። ኬሎ አዲስ አበባ ሆነው በሀሳብ ባዘኑ፤ የደላንዱን የምጥ ጭንቀት በቅርብ መከታተል ባለመቻላቸውም ተጨነቁ፤ በመጨረሻም መልዕክት ላኩ።

«ደላንዱ! የዛሬ አስራ አምስት ቀን በማክሰኞና ዕሮብ መካከል ትወልጃለሽ ... የሚወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ የፈረሴን ስም እሰጠዋለሁ - በርች የኔ እናት!» ብለው መልዕክት ላኩ።

ደላንዱ ወደ መንደሯ ዮብዶ ስትመለስ የአባ ጃገማ ወንድም ልጅ መሸሻ ዋሚ ቤት ለቅሶ ሆኖ ደረሰች። ለቅሶው ላይ ከዱጋ የመጡ ዘመዶቿ ለወትሮው ለአስተርእዮ ማርያም ሲሄዱ እንደሚያደርጉት አጅበዋት ሄደው ሲመለሱ ሡንጋ ታርዶ፣ ጠጅ ተጥሎ ይደገስ ነበር። ያን ጊዜ ግን ነፍሰ ጡር በመሆኗ 'በይ ተመልሰን እንመጣለን፤ የተለመደውን አዘጋጅተሽ ጠብቂን» አሉ፥ ድግስ የለመዱት ዘመዶች።

«እሺ ኑ! እረ ኑ ... የለመዳችሁት እንደሁ ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል። እኔን ግን አባ ጃገማ በማክሰኞና ዕሮብ መካከል ትወልጃለሽ ብለውኛል፤ ከወለድሁ ወለድሁ ነው ... ጎንበስ ቀና ብዬ እንደወትሮው ላላስተናግዳችሁም እንጂ ምን ጠፍቶ አባ ጃገማ ቤት» አለቻቸው።

በአስተርእዮ ማርያም ማክሰኞ ማታ በ1913 ዓ.ም በጅባትና ሜጫ አውራጃ፣ በደንዲ ወረዳ ዮብዶ በሚባል ቦታ ግስላው ከነቃጭሉ ተወለደ። አባ ጃገማ ወንድ ልጅ እንደተወለደ ሲሰሙ እንደ እብያ በሬ አገሱ። የሰባ ዓመቱ አዛውንት እንደ እንቦሳ እየዘለሉ ዳንግላስ ረገጡ ...

«ደላንዱ የእኔ ወርቅ! የልቤን አደረስሽው ... ለምንድን ነው እንዲህ የምቦርቀው? ... ለምን ይሆን ስንት ዘመን ርቄው ወደ መጣሁት ልጅነት በእርካታ የተመለስሁት ... ምስጢሩን አላውቅም የእኔ እህት። ጨቅላው ህፃን ግን ከእነ ህፃን መዓዛው ደረቴ ስር ተለጥፏል ... ለካ እሱን ስጠብቅ ነው የኖርሁት! ለካ ከብቶቼ ሳይቀሩ እምቡ...ዋ እያሉ ሲጠሩት የኖሩት እሱን ነው ... ምን ላርግሽ የኔ ወርቅ! ለህፃኑ ሲጠሩኝ የምረካበትን የፈረሴን ስም ሰጥቸዋለሁ ... በዚያ ላይ መቶ ጊደር ሸልሜዋለሁ» አሉ። ከዚያ በኋላ ልባቸው ነጎደ፤ እህል አልዋጥላቸው አለ። ስለዚህ ጥቂት ፈረሰኞችን አስከትለው ከአዲስ አበባ ወደ ዮብዶ ጋለቡ ...

አባ ጃገማ እምቦቀቅላ ህፃኑን አቀፉት፤ ትንሽ ልቡን፤ ትናንሽ እጅና እግሮቹን ... በፍቅር እያዩ ወደ ደረታቸው አስጠግተው ከአቀፉት በኋላ ደግሞ «መቶ ጊደር ጨምሬ ሸልሜዋለሁ» አሉ።

«እረ ሽልማት በዛ!» አሉ፥ አንድ ጓደኛቸው።

«ሰማህ ወይ!» አሉ፥ አባ ጃገማ፤ «ሰባ ዓመት ሙሉ የጠበኩት አንበሳ ይህ ነው ብልህ ይገባህ ይሆን?»

በእነአባ ጃገማ ቤት ደስታ ሰፈነ።

ብዙም ሳይቆይ ግን መንደራቸው በገባ የፈንጣጣ በሽታ ጃገማን ጨምሮ ቤተሰቡ ሁሉ ታመመ። ወላጅ እናቱ ደላንዱ በበሽታው ሳቢያ ከመጣባት መቅሰፍት መትረፍ ሳትችል ቀረችና ጃገማ በተወለደ በአንድ ዓመቱ ጥላው ወደማትመለስበት ሄደች፤ ሞተች። ስለዚህ አባቱ አባ ጃገማ በአክስቱ በወ/ሮ ናቱ እናቱ አማካይነት ሞግዚት ተቀጥሮለት እንዲያድግ አደረጉ። ሞግዚት አስቀጥረው ያሳደጉት አክስቱም ጃገማን ከወንድሙ ከጊዲ ጋር በተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን አስጠምቀው፣ ቄስ ቀጥረው ዳዊት አስተማሩት።

አባ ጃገማ ጃገማ ከተወለደ በኋላ ለአስር ዓመታት ብቻ ቆይተው በ1923 ዓ.ም ከመሞታቸው በፊት የልብ ወዳጃቸውንና የወንድማቸውን ልጅ አባ ዶዮን አስጠርተው «አናዘኝ!» አሉ።

«ይናዘዙ!» አሉ፥ አባ ዶዮ።





«ኑዛዜዬ አጭር ነው፥ አባ ዶዮ! አስራ ዘጠኝ ጋሻ መሬቴንና ንብረቴን ለህፃኑ ጃገማ አውርሻለሁ» አሉ። አባ ዶዮ ትክ ብለው አዩዋቸው።
«ህፃኑን ጃገማን ይወዱታል?»

«አዎ! ነፍሴ ነው። ምነው ጠየከኝ?»

«እህ! ከወደዱት ምነው አስራ አምስት የወንድም ጠላት ይፈጥሩለታል?» አሉ፥ አባ ዶዮ።

«ለምን እንዲህ አልህ?» አሉ፥ አዛውንቱ አባ ጃገማ።

«ሁሉን ንብረትዎን ለእሱ ሲያወርሱ ወንድሞቹ ዝም የሚሉት ይመስልዎታል?» አሉ፥ አባ ዶዮ። አባ ጃገማ ለጊዜው «እኔ ከሰጠሁት ምን ቆርጧቸው ጠላት ይሆኑታል» ብለው ተቆጡ። አባ ዶዮም «ያስቡበት» ብለው ትተዋቸው ሄዱ።

በሶስተኛው ቀን እንደገና ተገናኙ።

«ምክርህ አይከፋም ወንድሜ» አሉ።
«ጥሩ!» አሉ አባ ዶዮ።

«ስድስት ጋሻ መሬት ለጃገማ ሰጥቻለሁ። ሁለት ጋሻ መሬት ደግሞ አንተ ልጄን እንድትጠብቅልኝ ሰጥቻለሁ። ቀሪው ጋሻ መሬት በጃገማ አስተዳዳሪነት ለቀሪ ልጆቼ ይሁን» አሉ። አባ ዶዮም ተስማሙ። አባ ጃገማ በሞቱ በሶስተኛ ቀኑ ለልጆቹ ኑዛዜው ተነገረ። መጀመሪያ የአባታቸውን ኑዛዜ የተቀበሉ ቢመስሉም በኋላ ግን ተቃወሙ።

«አባ ዶዮ ያቀረቡት የኑዛዜ ቃል የአባታችን ሳይሆን ራሳቸውን ለመጥቀም ያዘጋጁት የውሸት ኑዛዜ ነው፤ ስለዚህ የሳቸውም ሆነ የህፃኑ ወንድማችን የኑዛዜ ቃል አይፀናም» ብለው አባ ዶዮን ከሰሷቸው። ጉዳዩ ለዓመታት በፍርድ ቤት ተይዞ ቆይቶ ውርሱም ለጃገማ ወንድሞች ተፈረደላቸው። ጃገማ ይግባኝ አለ፤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አፀናው። በመጨረሻ ለንጉሰ ነገስቱ ችሎት ቀረበ፤ ጃገማም የኑዛዜውን ወረቀት ከእህቱ ከሌንሴ ባል ዘንድ አገኝና በአባቱ ኑዛዜ መሰረት የሚገባውን ሁሉ ተቀበለ።

* * *

ሌላዋ እክስቱ ዘመናዊ ትምህርት እንዲማር የቀድሞው ተፈሪ መኮንን ት/ቤት አስገቡትና ለሶስት ወራት ተማረ፡፡ በኋላ ግን የአባቱ የመሬት ግብር በስሙ ተዛውሮ ስለነበር አርዶፋ ሽኔ የሚባል መተዳደሪያውን ከገባር መሬት የሚያገኝና በፊት የአባቱ አገልጋይ የነበረ ሰው በአውራጃ ገዥው ታዞ ከአዲስ አበባ አስሮ መለሰው፡፡

አርዶፋ ሽኔ ጃገማን ይዞ ሲመለስ ወቅቱ የመስቀል በዓል ስለነበረ ለህፃኑ ጃገማ በግ አርዶ የሚወደውን የፈረስ ጉግስ እንዲጫወት አደረገው፡፡ ይህ ግዴታን እየተወጡ ሰብዓዊ ፍላጎትን ማሟላት፣ ሰዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ ማክበርና ፍላጎታቸውን መጠበቅ የድንቅ ሥነ-ምግባር ምንጭ የሆነው የኦሮሞ ድንግል ባህል ነው፡፡ አርዶፋም ይህን ተግባራዊ ማድረጉ ጃገማ በወጣትነቱም ሆነ በሽምግልናው ወቅት በቀና የሚያስታውሰው ትዝታው ሆነ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላም ጃገማ ግብሩን ከፍሎ ወደ መንደሩ ተመለሰ፡፡ የዘመናዊ ትምህርት ዕድሉም በዚያ ሰበብ ለመጨረሻ ጊዜ በሶስት ወራት ብቻ ተወስኖ ቀረ፡፡

ከዚያም «አባቱ የመረጠው» እየተባለ ዳኝነት መቀመጥ፤ በሌጋ ዕድሜው በገዳ እርከን ፎሌ ደረጃ (ዕድሜያቸው ከሃያ አምስት እስከ ሰላሳ ሁለት) ከደረሱ ወጣቶች ጋር ፈረስ ግልቢያ፣ ጦር ውርወራ፣ ጋሻ አነጋገብና ምከቶሽ፣ ውሃ ዋና፣ ረሃብና ውሃ ጥም መቋቋምን እየተማረ በጥሩ ሥነ-ምግባር መቀረጽ ቀጠለ - ጃገማ ኬሎ ገሮ ጎዳና!

* * *

ጃገማ በልጅነት ዘመኑ ስለቅድመ-አያቱ ስለጎዳና ነሞ ዝና ብዙ ነገር ሰምቷል፡፡ ጎዳና ነሞ ግዛቱን ዳኒሳ ላይ አድርጎ በምዕራብ እስከ አምቦ፣ በምስራቅ እስከ አዲስ ዓለም ፣ በሰሜን እስከ ግንደበረት ፣ በደቡብ እስከ ሶዶ ያለውን በባላባትነት እንዴት ለማስገበር እንደቻለ ፤ መጀመሪያ ላይ ሶስት መቶ ሃምሳ ሰው እንደገደለ ህዝቡ ተሰብስቦ «ሰው ጨረስህ፤ ጦርህን ወርውርልን» እንዴት እንዳለው፤ ጎዳናም ድግስ ደግሶ ህዝቡን ሰብስቦ ከተመረቀ በኋላ ጦሩን ከአጥር ውጭ እንደወረወረ ... የወረወረው ጦር ግን አገር ያስቸገረውንና ከብት ለመዝረፍ የመጣውን ጀላንሴና የሚባለውን ሌባ ወግቶ እንደገደለ፤ ጎዳናም በህዝቡ እንደገና ተመርቆ ጦሩን እንዳነሳና ሌላ ስድስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሰው እንደገደለ፣ በመጨረሻም እረኛ ሹል ዘንግ ወርውሮ ቅድመ እያቱን ጀግናውን ጎዳናን እንደገደለና አንድ የጠላቱ ወገን አፅሙን ሲቀጠቅጥ አንድ አጥንት ተፈናጥራ ዐይኑን አጥፍታ ስለገደለችው





የጎዳና ግዳይ ከሞቱ በኋላ ሺህ እንደሞላ ... ህፃኑ ጃገማ ቢያንስ ለአንድ ሺ ጊዜ ሰምቷል ... ስለዚህ የህፃኑ ጃገማ ህልም ሁሌም እንደ ቅድመ-አያቱ ጎዳና ነሞ ጀግና ሆኖ ብዙ ሰው መግደል ሆነ፡፡

* * *

አንድ ወቅት አንድ ጋዜጠኛ ጃገማን «የልጅነትህ ዘመን ህልምህ ስለምን እንደ ቅድመ-አያትህ ሰው መግደል ሆነ?» አለው፡፡ ጃገማ ከልቡ ስቆ፤ «እየህ በዚያን ጊዜ ከሽማግሌዎችና ከሞግዚቴ የምሰማው የቅድመ-አያቴን ታሪክና የጦርነቱን ውሎ ብቻ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ለህይወቴ ስለተሰጋ ከእረኞች ጋር አልገናኝም፡፡ ቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆነህ አሳ ነባሪ ይታይሃል? አይታይህም፡፡ ስለዚህ እንደ አሁኖቹ ልጆች 'ሐኪም፣ ፓይለት ...' ለመሆን ላስብ አልችልም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ይህ በእኔ ዘመን አልነበረም፡፡ እንደማገኛ ውም ልጅ ህልሜና ምኞቴ ከምሰማው፣ ከማየው የወጣ አይደለም፡፡ ደግመህ 'ለምን' ካልህ ደግሞ ወፍ እንደ አገሯ ትጮኻለች እልሃለሁ» አለው፡፡

# ፬

# የኢጣሊያ ወረራ

በአፄ ምኒልክ አዝማችነት በቅኝ ገዥዎች ላይ በአድዋ የተገኘው የመጀመሪያው የአፍሪካውያን ድል ምንም እንኳን አመታትን ቢያስቆጥርም ሁሌም እንደ አዲስ ቅኝ ገዥዎችን የሚያስቃዥ ሽንፈት መሆኑ አልቀረም። ኢትዮጵያን ዙሪያዋን የከበቧት ቅኝ ገዥ አገሮች የኢትዮጵያውያን የቀድሞ ድል እሳት ላይ እንደወደቀ ቋንጣ ኩምትርትር አድርጓቸዋል። እነ ጄኔራል ስማትን የመሳሰሉ የጦር ሊቆችም «ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ላይ ያገኘችው ድል ለጥቁሮች ታላቅ ድል፣ ለቅኝ ገዢዎች ደግሞ አደጋ ነው። የሚገርመው ደግሞ አንዴ ብልጭ ብሎ የሚያቆም ሳይሆን እንደ ሰደድ እሳት በውሃና በየብስ ላይ እየተፈተለከ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ መስራጨቱና ለማጥፋት አለመቻሉ ነው» በማለት ገልፀውታል። ፈረንሳይ የያዘቻቸው የጅቡቲ ህዝቦች፣ ኢጣሊያና ፈረንሳይ የሚገዟቸው ሶማሌዎች፣ እንግሊዝ የያዘቻቸው ሱዳናውያንና ኬንያውያን ... በአጠቃላይ ቅኝ ገዥዎች የተቀራመቷቸው አፍሪካውያን ቅኝ ተገዥዎች በዜናው፣ በኢትዮጵያ ድል «ይህም አለ» እንዳይሉ የሰጉት የቅኝ ገዥ አገራት ከተጠናወታቸው ራስ ምታት ለመፈወስ የአድዋው ድል በአዲስ ሽንፈት ኮስምኖ የቅኝ ተገዥ አገራት ህዝቦች ቅኝ ገዥዎቻቸውን የማሸነፍ ህልማቸው ከስሩ ተነቅሎ እንዲጠፋ ይፈልጉ ነበር። በካርታ ላይ የነደፉት አፍሪካን የመከፋፈል እቅዳቸውም ምስራቅ አፍሪካ ላይ ተግባራዊ ባለመሆኑ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያ የሃፍረት ካባቸውን እንደለበሱ በጥቅምት ወር 1898 ዓ.ም. ከኢትዮጵያው ንጉሠ ነገስት ከአፄ ምኒልክ ጋር የድንበር ስምምነት ውል ተፈራርመው ነበር። ኢጣሊያ ሽንፈቷን ለመበቀል፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ደግሞ ከሃፍረታቸው ነፃ ለመሆንና ኢጣሊያን አስደንብረው ጀርመን እቅፍ ላለመጣል የሶስትዮሽ ህብረት ፈጥረው የኢትዮጵያን ውስጣዊ የፖለቲካ መዘውር በዘዴ እየጠመዘዙ ወደ ገደል አፋፍ አደረሱት።

የምስራቅ አፍሪካን ሀገራት በቅኝ ግዛት በመያዝ ላይ የነበሩት ሶስቱ ሃያላን አገሮች ቀጣዩ ዘውድ ጫኝ በአፄ ምኒልክ ቤተመንግስት ውስጥ ቤተኛ ከሆኑት ከራስ መኮንን፣ ከአቤቶ ኢያሱና ከተፈሪ መኮንን አይዘልም ብለው ገምተው ነበር። ግምታቸው በከፊል ተሳክቶም አቤቶ ኢያሱ አልጋ ወራሽ





ሆኑ። አፄ ምኒልክ ከሞቱ በኋላ አቤቶ ኢያሱም መንበረ ስልጣኑን ሲረከቡ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ከቱርክና ከጀርመን ጋር አደረጉ።

ይህን ጊዜ ኢጣሊያ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ የጋራ ደህንነታቸው አደጋ ላይ ወደቀ። በኢያሱ ግንኙነት ሳቢያ የሃይል ሚዛኑ የሚዛባበትና ጥቅማቸውን በቱርኮች የሚነጠቁበት ሁኔታ ተፈጠረ። ያን ለማስናከል ቀላሉ ስትራቴጂ በኢያሱ ላይ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ መክፈት እንደሆነ ተስማሙ። ለዚህም ስትራቴጂ ስኬት ዘርን፣ ሃይማኖትን፣ ሰብዕናን፣ ወዘተ. በማጤን ኢያሱን ለማጥቃት የሚበጀውን መረጡና በሃይማኖትና በግል ሰብዕና ላይ ማተኮሩን መረጡ።

በራስ ተፈሪና በልጅ ኢያሱ መካከል ያለውን ቃል ኪዳን ለማፍረስም በሁለቱ ተፎካካሪዎች መካከል አጠራጣሪ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማስረጃዎች ተቀነባበሩ። ለዚህ ዝግጅት አፈፃፀም ደግሞ አርመናዊው ፎቶግራፍ አንሺ ሙሴ ሊዮን፣ እንደበተ ርቱዕውና የመኳንንቱን ምስጢር ለቅሞ የማውጣት ልምድና አቅም የነበረው ሻለቃ ሎምሬንስ ሐረር ገቡ። ልጅ አቤቶ ኢያሱም በተዘጋጀላቸው ወጥመድ እንዲገቡ በሚያምኗቸው ሰዎች ወደ ሐረር በመሄድ ከራስ ተፈሪ ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን እንዲያፈርሱ ተደረገ። ልጅ ኢያሱ ሐረር እንደደረሱ መናገሻ ከተማቸውን ወደ ወሎ እንዲያዞሩ፣ ከእስልምና ተከታዮች መሪዎች ጋር እነ ሻለቃ ሎምሬንስ በተገኙበት እንዲወያዩ ለማድረግ ሤራው ተቀነባበረ ...

በዚህም አካሄድ ልጅ ኢያሱ መስለማቸውን የሚያረጋግጥ ፎቶ በሃያ ሺህ ኮፒ ግብፅ አገር ታተመ። የኢያሱ የአመንዝራነት ባህሪም ማዳበሪያ እየሆነ ለየመኳንንቱ ተሰራጨ። ያን ግዜ «ወጋችን ተበላሸ» ባይ ሹማምንት ውሏቸው ኢያሱን ማማት ሆነ። በሌላ በኩል ደግሞ ራስ ተፈሪ ዝምተኛ፣ የአውሮፓን ቋንቋ የተማሩ፣ ሰው አክባሪና ለልማት ቆርጠው የተነሱ ... የሚል የሰብዕና መግለጫ ተቀነባብሮ መኳንንቱ እንዲሰሙት፣ እንዲያጤኑት፣ በአዕምሮአቸው እንዲመላለስ ተደረገ። የአቤቶ ኢያሱ ስልጣን እንዲህ በተቀነባበረ ዘዴ ተገዝግዞ በኢትዮጵያ ከፍተኛ መኳንንት ስልጣናቸው ተቀማ። የተቀማው ስልጣን ደግሞ ለአፄ ምኒልክ የገቡትን ቃልኪዳን በማክበርና ውግዘቱን በመፍ[illegible] ዘውዱን ለንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ በመስጠት ተፈፀመ። የባለ ሙሉ ስልጣን አልጋ ወራሽነቱን ያገኙት ራስ ተፈሪም ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ከፊት ቀድመው ከኋላ ያስከተሏቸውን ተፈሪን እስከተወሰነ ርቀት የሚያሯሩጡ አጋዥ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ሆነ።

በዚህ ወቅት የራስ ተፈሪ ተቀናቃኝ ኢያሱ በቁጥጥር ስር ዋሉ፤ የንግስቲቱ አለኝታ መኳንንትም እንደ ጉም በየአቅጣጫው ተበተኑ። ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል ሆነች። የራስ ተፈሪንም ሰብዕና ለማጎልበት ለራስ ተፈሪ የአውሮፓ ጉብኝት ተመቻቸ። ራስ ተፈሪ ውስጡን ለቁስ በሆነው የኢጣሊያ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ ... እንግዛ ረኩ።

* * *

ጣሊያኖች ኤርትራ ምድር ላይ ሆነው የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ እንቅስቃሴ በመከታተል በዓድዋ ላይ የደረሰባቸ ውን ሽንፈት ለመበቀል አስፈላጊ ዝግጅቶቻቸውን ጨራርሰው አይጧን ለማጥመድ ጉድጓዱ ዳር አደፈጡ። በተለይም ኢትዮጵያን ዳግም ለመውረርና ቅኝ ግዛት ለማድረግ ብዙ የሃይማኖት መልዕክተኞች፣ የምህንድስናና የህክምና ባለሞያዎች፣ የታሪክና የፖለቲካ ተንታኞች፣ የከርሰ ምድር አጥኝዎችና የወታደራዊ ሳይንስ ጠበብቶች ከኢጣሊያ በመምጣት አገሪቱን አብጠርጥረው ለመመርመር ሰላማዊ ወረራ አደረጉ።

በአፄ ምኒልክ ዘመነመንግስት በአድዋው ጦርነት በኢጣሊያ ላይ በደረሰው ሽንፈት የወቅቱ ሃያላን አገራት ጥልቅ የሆነ የፖለቲካ ቼዝ እየተጫወቱ የፈጠረውንና ወደፊትም የሚፈጥረውን ተፅዕኖ አስልተውታል። ፖለቲካዊ ትርፍ ያለው ሆኖ ስላገኙትም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በድጋሚ እንድትወር ይገፋፉ ነበር።

ይሁን እንጂ «አባብ ያዬ በልጥ አይጫወትም» እንዲሉ ኢትዮጵያውያንን ማንበርከክ ቀላል እንደማይሆን በመረዳት «ኢትዮጵያን አትያዛት፤ ግን በዝብዛት» የሚል መርህ ፈጥረው ስውር የጥፋት ሚሳይላቸውን በመተኮስ፤ በመሃል አገርም በዲፕሎማሲው መስክ ከኋላ ሆነው እየቆነጠጡ በማስበርገግ ኢትዮጵያውያንን እርስ በርሳቸው በማጣላቱ ገፉበት።

በተለይም «ኢትዮጵያን አትያዛት ግን በዝብዛት» የሚለውን መርህ ለማስፈፀምና የአፄ ምኒልክንም እመኔታ ለማግኘት በ1898 ዓ.ም ኢጣሊያ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመቀበል በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው ጦርነት የቅኝ ገዥና ተገዥ ጦርነት ሳይሆን የሁለት ሉዓላዊ አገራት ግጭት መስሎ እንዲቆጠር ፍላጎታቸውን አሳዩ። የታሪክ





ድርና ማግ ሲጠና ግን በወቅቱ የነበሩ ጣሊያኖች ደግመው ደጋግመው ይሹት የነበረው የአድዋን ቂም ለመበቀል በኢትዮጵያ ላይ ድልን መጎናፀፍን ነበር። ስለዚህ በጥቅምት ወር 1898 ዓ.ም የተደረገው ውል ለኢትዮጵያ መልካም ዜና ቢመስልም ለኢጣሊያ ግን ጊዜ መግዣና የጦር እቅድ ውጥን ማረጋገጫ ነበር።

በኢጣሊያ ደግሞ በ1914 ዓ.ም ሙሶሊኒ ስልጣን ላይ ወጣ፤ የፋሽዝምን የፖለቲካ አቅጣጫ መከተልም ጀመረ። በ1915 ዓ.ም በኢጣሊያ ግፊትና ትብብር ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ አባል እንድትሆን ተደረገችና አዲሱን የማደንዘዣ መርፌ ተወጋች። ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ አባል አገር ከመሆኗ በፊትና አባል ከሆነች በኋላም በእነ ሙሶሊኒ «እርቆ አስተዋይ» የተባሉ ኢጣሊያውያን በሽንጎ እየተቀመጡ የወረራውን ጥቅምና ጉዳቱን ተነተኑት። «ትልቅ አሳ ወጥመድህ ውስጥ እንዲገባ የሚወደውን መንጠቆህ ላይ ሰክተህ ሳትንቀሳቀስ ፀጥ በል» በሚለው ዘዴ ኢትዮጵያ ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ በመግባቷ ደስተኛ እንደምትሆንና በአባልነት የታቀፉት አገሮች ሉዓላዊነታቸው ቢጣስ ሌሎች አባል አገሮች ከጎኗ እንደሚቆሙ ስታውቅ ባገኘችው ምቾት ተኝታ እስከትነቃ ዘመናት እንደሚነጉዱ «እርቆ አስተዋዮች» ተነበዩ።

ይህም ለኢጣሊያ እንደሚረዳና ኢትዮጵያ እንቅልፏን ስትለጥጥ አልያም ከእንቅልፏ ነቅታ ስትንደፋደፍ እነ ሙሶሊኒ ቀላሉን የቤት ስራ በጦር ሃይላቸው እንደሚፈጽሙ ተረጋገጠ። በሌላ በኩል ደግሞ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ህግ በማውጣት ይደራጅ እንጂ ያወጣውን ህግ ለማስከበር በቂ ጥንካሬና ወታደራዊ ሃይል ስለሌለው «ጥርስ የሌለው አንበሳ» በመሆኑ አዋጁንና ህጉን ለማስፈፀም ጥርስ ማብቀል እንዳለበት፣ ጎፈሩ አንገቱ ላይ የተደፋ ሽንጣም አንበሳ እስኪሆንም ዘመናት እንደሚቆጠሩ ታምኖበታል።

ከዚህ በተጨማሪ ኢጣሊያን ለውጤት እንደሚያበቃ የታመነበት ነጥብ ደግሞ በ1908 ዓ.ም የአንደኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር እንግሊዝና ፈረንሳይ ኢጣሊያ ከእነሱ ጋር ወግና ፀረ ጀርመን አቋም ይዛ ከታገለች ከድል በኋላ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቷ እንድታደርግ የገቡላት ቃልኪዳን ነው።

ራስ ተፈሪ የአውሮፓን ጉብኝት ከፈፀሙ በኋላ የፈጠሩት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ የጀመሩት ልማት፣ በተለይም በቤልጅየም መንግስት ትብብር የጀመሩት የጦር ሃይል ማሰልጠኛ ተቋምና በካሪቢያን አገሮች የተነሳው የራስ ተፈሪያን እንቅስቃሴ የኢጣሊያ የቤት ስራ በአስቸኳይ

በ1928 ዓ.ም ኢጣሊያ ከተደላደለችበት ከሶማልያ ተነስታ ኦጋዴንንና ጅጅጋን ያዘች:: በሲዳሞም የኢትዮጵያን ግዛት ደፈረች:: በወቅቱ እጅግ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀውን የኢጣሊያ ሰራዊት መቋቋም ለኢትዮጵያውያን ከባድ ሆነ:: እያቅራራና እየፎከረ ጠላትን መግጠም የለመደው የኢትዮጵያ ሰራዊት ጠላቱን ከፊት ለፊት ሲጠብቅ ቦንብ ተሸካሚ አውሮፕላኖች እንደ አሞራ ሰማይ ለሰማይ እየመጡ እጠቁት:: በምስራቁ የኢትዮጵያ አቅጣጫ በተጀመረው የኢጣሊያ ጥቃት የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ ጀግናው ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት ከበባ ተደርጎ ካለ አጋዥ ተገደሉ! የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የትኩረት አቅጣጫ ወደ ምስራቅ ቆራሄም ተያዘች:: የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የትኩረት አቅጣጫ ወደ ምስራቅ ሲሄድ በሰሜን ደግሞ የኢጣሊያ ጦር የሽንፈት ጽዋ የጨለጠበትን አድዋን በመስከረም ወር 1928 ዓ.ም በእጁ አደረገ::

ጦርነቱ ከየአቅጣጫው በጣሊያኖች ሲለኮስና ሰደዱ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ መላ ለመምታት ባለሟሎቻቸውን ሰበሰቡና እስከ አፍንጫው ስለታጠቀው ኢጣሊያ ብቻ ሳይሆን ስለ ከዷቸውም እንግሊዝና ፈረንሳይ ተወያዩ:: በመጨረሻም ንጉሰ ነገስቱ ወደ ማይጨው ለመዝመት ወሰኑ ...

መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም የጦርነት ክተት አዋጅ ታወጀ:: አዋጁ ግን እንደ አፄ ዮሐንስ፣ እንደ አፄ ምኒልክ ዘመን ህዝቡን ከዳር እዳር የሚያንቀሳቅስ አልሆነም:: በየጠቅላይ ግዛቱ ከሚገኙት ባላባቶች ጋር ግንኙነታቸው በመሻከሩም ባልጠበቁት በኩል ለመጣባቸው ጥቃት ወገናቸውን ለማስተባበር አስራ አንደኛው ሰዓት በመድረሱ እንደ ቀደምት ነገስታት ወገናቸውን በአንድ ልብ ከዳር እዳር ለማስተባበር ሳይችሉ ቀሩ:: ቢሆንም ግን ታሪካዊ ግዴታቸውን ለመወጣት በዚያ ቀውጢ ሰዓት ችሎታ ያላቸውን ሳይሆን የሚተማመኑባቸውን ቤተዘመዶቻቸውን ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ላይ በመሾም ለጦርነቱ ተዘጋጁ::

በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም መቀሌ በኢጣሊያ ጦር በተያዘች በሳምንቱ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከመናገሻ ከተማቸው ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ሄዱ:: ደሴ እንደደረሱ ከመሃል አገር የኢትዮጵያ ጦር አዝማች ሆነው የሄዱትን ራስ ሙሉጌታን ሽረው ወደ መንፈሳዊነቱ የሚያደሉትን ራስ ካሳን የጦር ሚኒስትርና አዝማች በማድረግ ራሳቸውን ዋና የጦር አዝማች አደረጉ:: ከሳምንት በኋላ የኢጣሊያ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በንጉሰ ነገስቱና በሰራዊታቸው ላይ የቦምብ ውርጅብኛቸውን እንደ ዝናብ ሲያወርዱት ቀዳማዊ





ኃይለ ስላሴ ራሳቸው 'ኦርሊኮን' (የአየር መጣያ) ተኳሽ ሆነው የኢጣሊያን አውሮፕላኖች ለመጣል ሞከሩ::

ከታህሳስ 15 እስከ ጥር 23 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ የራስ ስዩም መንገሻና የራስ ካሳ ሰራዊት በጥምረት የኢጣሊያን መከላከያ ምሽግ ለመስበር ችልቅ ውጊያ አደረገ:: በሲዳሞ ዶሎ ግንባር የጄኔራል ግራዚያኒ ጦር የቀዳማዊ ኃይለስላሴን አማች ራስ ደስታን አጥቅቶ ተቆጣጠረ::

ኢትዮጵያውያን በተከፈተባቸው የጦርነት ግንባር ሁሉ የጠላትን ሃይል በወኔ ተጋፈጡ:: እንዲያውም ኢትዮጵያውያን ከመከላከሉ ወደ ማጥቃቱ ሲያዘነብሉ የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ተደናገጡ:: ከአርባ ዓመት በፊት የደረሰው ሽንፈትም በሀሳባቸው እየተመላለሰ አርበተበታቸው:: ይህን ከፍተኛ ስጋት ለማስወገድና የኢትዮጵያን ጦር በመግታት ለማሸነፍ የሚቀራቸው አንድ ምርጫ ብቻ እንደሆነ የጦር መሪዎች ተማመኑ:: ያም የመጨረሻ ስምምነት ከአየር የሚጣለውንና በሊግ ኦፍ ኔሽንስ የተከለከለውን የመርዝ ጋዝ ጢስ በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ መርጨት ሆነ:: ኢጣሊያ ሶስት መቶ አውሮፕላኖችን እየተጠቀመች የ«ሙስታርድ» ጋዝ በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ ረጨች:: ያን ጊዜ ነው የደጃዝማች አያሌው ብሩ አዝማሪ፤

«ከሃበሻ ፀሎት ጣሊያኖች በለጡ፣
በአርባ ዘመናቸው ክንፍ አውጥተው መጡ» በማለት የተቀኘው::
የኢትዮጵያ ሰራዊት በማያውቀው የመርዝ ጋዝ ጢስ እንደቅጠል እረገፈ:: የመጣውን መዓት የሰማው የአዲስ አበባ ክርስቲያንና ሙስሊሙ ህዝብ በአንድነት ሆኖ የአንድ ሳምንት ሱባኤ ገባ:: የኢጣሊያ ሰራዊት ግን የራስ ስዩምንና የራስ ካሳን ሰራዊት አጥቅቶ ወደ መሃል ገሰገሰ ...

መጋቢት 1928 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴና ሰራዊታቸው ኮረም ደረሱ:: የኢጣሊያ አውሮፕላኖች የሰራዊቱን ቀለብ አቃጠሉት፤ የመርዝ ጋዝ ጢስ መርጨቱንም ቀጠሉ:: በዚህ ሰቅጣጭ ወቅት ግን የኢትዮጵያ ሰራዊት መጋቢት 13 ቀን 1928 ዓ.ም በወራሪው ላይ የግንባር ለግንባር ውጊያ ሰንዝሮ እስከ ጨበጣ ውጊያ የዘለቀ የሞት ሽረት ፍልሚያ አደረገ:: የኢጣሊያን የከባድ መሳሪያ፣ የቦምብ ውርጅብኝና የመርዝ ጋዝ ጢስ ግን የኢትዮጵያ ሰራዊት መቋቋም ተሳነው:: የአየር ጥቃት ሙሉ ለሙሉ የኢጣሊያን የበላይነት አረጋገጠ:: ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴም ለሰራዊታቸው በማዘን እንዲሸሽ አዘዙ ...

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በወሎ እንዳይመለሱ ህዝቡ በልጅ ኢያሱ መሻርና በንጉስ ሚካኤል ጥቃት የተቆጨ በመሆኑ ፈሩት፡፡ የአፋርና የሰማሌን ባላባቶችም የጋብቻ ዝምድና የፈጠረላቸውን ልጅ ኢያሱን ከስልጣን በማውረዳቸው ምክንያት የነበረውን ቂም ስለሚያውቁ ሰጉ፡፡ በጎንደር ደግሞ የራስ ጉግሳን የግፍ አገዳደልና በደጃዝማች አያሌው ብሩ ላይ የፈፀሙትን ቃልን ያለማክበር ችግር ስለሚያውቁ ፈሯቸው፡፡ የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ግዛት መውረድ የማይዋጥላቸውንም ለመሸሽ ብቸኛውን አማራጭ በመምረጥ በላሊበላ፣ በወረኢሉ በመንዝ በመርሐቤቴ አድርገው ሚያዝያ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ጠዋት አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

አዲስ አበባን በከንቲባነት የሚመሩት ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት የኢጣሊያን ድል፣ የኢትዮጵያን ሰራዊት ሽሽትና መበታተን፣ ንጉስ ነገስቱም ያሉበት አለመታወቁን ሲረዱ የከተማውን ፏሪ ጃንሜዳ ላይ ሰብስበው ወደ አዲስ አበባ የሚገሰግሰውን የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ጣርማ በር ላይ በማገድ ህዝቡ መስዋዕትነት እንዲከፍል ጥሪ አደረጉ፡፡ በዚህ መሃል ግን ንጉሰ ነገስቱ አዲስ አበባ የመኖራቸው ዜና ተሰማ፡፡ ብላታ ታከለ ንጉሰ ነገስቱ ወደ አውሮፓ ለመሄድ ማሰባቸውንም ሰሙ፡፡ ይህን ጊዜ «አይሆንም! ንጉሰ ነገስቱ ወደ አውሮፓ ለመሄድ ቢሞክሩ የእኔ እስረኛ ይሆናሉ» በማለት ቆራጥ ውሳኔያቸውን ተናገሩ፡፡ ምሽት ላይ ንጉሰ ነገስቱ አስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ፡፡ በተሰብሳቢዎች ስለ ንጉሰ ነገስቱ ዕጣ ፋንታ ውይይት ከመደረጉም በላይ ወራሪውን የኢጣሊያ ጦር መቋቋምና ማባረር ስለሚቻልበት ዘዴ ሁለት ስትራቴጂዎች በሃሳብ መልክ ቀረቡ፡፡

እነ አቶ መኮንን ሃብተወልድ «ንጉሱ ወደ አውሮፓ ሄደው ለሊግ አፍ ኔሽንስ ያመልክቱ፤ ዕርዳታም ይጠይቁ ... የኢትዮጵያ መናገሻ ግን ወደ ጎሬ ተዛውሮ በደጃዝማች ወልደ ፃድቅ እንደራሴነትና በራስ እምሩ የጦር ሚኒስትርነት የአርበኝነት ትግል ይጀመር» አሉ፡፡ ይህ ሃሳብ የመነጨው ከመኳንንቱ ይሁን እንጂ የእንግሊዝና ፈረንሳይ ዲፕሎማቶች ሃሳብ ስለመሆኑ ብዙም አያጠራጥርም፡፡ ሁለቱ አገራት ንጉሰ ነገስቱ ወደ መናገሻ ከተማቸው ከመመለሳቸው በፊት እንደ ፍቱን መላ ወስደው ንጉሱ በወጣላቸው መረብ ተጠቅልለው ወደ አውሮፓ እንዲሄዱ መወሰናቸው ለኢጣሊያ መንግስት ሳይቀር ተገልፆ ነበር፡፡ ለዚህም ዋናው ነጥብ የተበታተነው የኢትዮጵያ ሰራዊት ያለ ንጉሰ ነገስቱ፥ ንግስት እንደሌለው የንብ መንጋ ተበትኖ ይቀራል የሚል እምነት ነበር፡፡





ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ የአገር ፍቅር በሚያንሰፈስፋቸውና የጠላትን ድፍረት ለመቀልበስ በሚጓዙት ቆራጥ ኢትዮጵያዊ በብላታ ታከለ የቀረበ ነው፤ «ዋናው የጦር ሰፈር ከአዲስ አበባ ወደ ጎሬ ይዛወር፤ የኢትዮጵያ አርበኞች የሽምቅ ውጊያ እንዲጀምሩ ይደረግ፤ ከእንግሊዝ ጋር በመደራደርም ለጎሬ ቅርብ በሆኑት አገሮች በኩል መሳሪያ ተገዝቶ ይምጣ ... ወራሪን መሸሽ ሳይሆን እንደ አባቶቻችን እየገጠምን ድል ማድረግ አለብን» አሉ፡፡ ሹማምንቱ ወደ ብላታ ታከለ ሃሳብ አዘነበሉ፡፡ ንጉሰ ነገስቱ ግን የሚሆነውን ከማድረግ እንደማይመለሱ እያወቁት ስብሰባው ለቀጣዩ ቀን ተቀጠረ፡፡

በማግስቱ የእነ አቶ መኮንን ሃብተወልድ ሃሳብ ቀርቦ የብላታ ታከለ ሃሳብ ከአጀንዳ ውጭ ሆነ፡፡ በተሰብሳቢዎች መካከል አለመግባባቱ ተካረረ፡፡ በመጨረሻ ግን የንጉሰ ነገስቱ ስደት ተቀባይነት አገኘ፤ ደጃዝማች ወልደ ፃድቅ እንደራሴ፤ ራስ እምሩ ደግሞ የጦር ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡

የነብላታ ታከለን ደጋፊዎች በመፍራት ማታውኑ ንጉሰ ነገስቱ ከልዑላን ቤተሰቦቻቸው፣ ከታማኝ መኳንንቱና አሽከሮቻቸው፣ እንዲሁም በእንግሊዝና በፈረንሳይ ዲፕሎማቶች ከተወከሉ ጥቂት የውጭ ዲፕሎማቶች ጋር በባቡር ወደ ጅቡቲ ለመሄድ አቃቂ ሄደው ተሳፈሩ፡፡ በጉዟቸው ላይ የንጉሱ ስደት ያልተዋጠላቸው ኢጣሊያውያን ንጉሰ ነገስቱ በተሳፈሩበት ባቡር ላይ የቦንብ ጥቃት ለማድረስ እንግሊዝንና ፈረንሳይን ተማፀኑ፡፡ እንግሊዝና ፈረንሳይ ግን የንጉሰ ነገስቱ ስደት የኢጣሊያን ድል ከማጠናከር ውጭ የሚያመጣው ጉዳት እንደሌለ፤ የሊግ አፍ ኔሽንስ አቤቱታም በእንግሊዝና ፈረንሳይ ተወካዮች እንደሚመከን በማስረዳት አግባቧቸው፡፡ ኢጣሊያውያኑ ግን ንጉሰ ነገስቱን ሳይዙ ወይም ሳይገድሉ ቅኝ ገዥነታቸው እንደማይረጋገጥ ቢሰጉም የእንግሊዝንና የፈረንሳይን ወዳጅነት ጥሰው ንጉሰ ነገስቱን በያዘው ባቡር ላይ አደጋ ከማድረስ እንደተቆጠቡ ይገመታል፡፡

ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም. ንጉሳውያን ቤተሰቦች መልህቋን በህንድ ውቅያኖስ የጅቡቲ ወደብ ላይ ጥላ በመጠባበቅ ላይ ካለችው «ኢንተርፕራይዝ» ከተባለችው የጦር መርከብ ደረሱ፡፡ በባቡር ተጭነው የሄዱት መኪኖችና ሻንጣዎች ጦር መርከቧ ላይ ተጫኑ፡፡ አቃቂ ላይ ከንጉሰ ነገስቱ ጋር ለመሰደድ የወሰኑት ጠባቂዎች በፈረንሳይ መንግስት «የጦር መሳሪያ ይዛችሁ አትገቡም» ተብለው እንዳይጓዙ ተከለከሉ፡፡ ስለዚህ በጦር መርከቧ ላይ የተሳፈሩት ንጉሰ ነገስቱ፣ ባለቤታቸው፣ ልዑላን ቤተሰቦችና ታማኝ መኳንንት ብቻ ነበሩ፡፡

ንጉሰ ነገስቱ በስደት በሄዱ በጥቂት ቀናት ውስጥ የጄኔራል ባዶሊዮ ሰራዊት በየካ በኩል ወደ መናገሻ ከተማዋ ገባና አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ወደቀች፡፡ በሶስተኛው ቀን 1928 ዓ.ም ሙሶሊኒ «ሁለተኛዋ የሮም ኤምፓየር ተመሰረተች» ብሎ ደስታውን ለዓለም አበሰረ፡፡ በንግግሩ መጨረሻም «አዲሷን የሮማ ኤምፓዬር የሚያናውጥ ሃይል ምድር ላይ የለም!» ብሎ አብሪቱን ጨመረበት፡፡

የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ውል ሲሻር፣ ኢጣሊያ የተከለከለውን የመርዝ ጋዝ ኢትዮጵያ ላይ በማርከፍከፍ ፍትህ የጎደለው ጦርነት ስትፈፅም «ሃይ ባይ» ጠፋ፡፡ ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ዕድርተኞቿ ከጎኗ ሳይቆሙ ምድሯ በሬሳ ተሞላ፡፡ በ1880 ዓ.ም በአፄ ምኒልክ አማካይነት ይዛው የነበረው የግዛት ክልል በኢጣሊያ በመደፈሩ ንጉሰ ነገስቱ አቤቱታቸውን ለማቅረብ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም ከባዝ ከተማ "ሊግ ኦፍ ኔሽንስ" ወደሚገኝበት ጄኔቭ አቀኑ፡፡ በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ እንደደረሱም የፋሽስት ኢጣሊያን ወረራ ለአባል አገራቱ ለማሳወቅ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ወደ መድረኩ አመሩ፡፡ ኢጣሊያውያን ጋዜጠኞች የንግግራቸው መልዕክት እንዳይሰማ በጩኸትና ፉጨት አወኩ፡፡ ትዕግስተኛው መሪ ግን ማዕበሉ እስኪቆም ጠብቀው፣ ረብሻ ፈጣሪዎች ከአካባቢው ሲወገዱ ነውጥ ፈጣሪ ታሪካዊ ንግግራቸውን ለአባል አገራቱ አሰሙ፣ «... እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ» ብለው የአባል አገራት ተወካዮችን ህሊና የተፈታተነውንና መፈናፈኛ ያሳጣ ንግግራቸውን አድርገው ጨረሱ፡፡ አቤቱታዋን ግን እንግሊዝና ፈረንሳይ ውጠው አስቀሩት፡፡

* * *

ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ ተወርራ ህዝቧ ፍዳውን በሚያይበት በዚያ የጭንቅና የመከራ ወቅት ግን የአገራቸውን ነፃነት ለማስመለስ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ጀግኖች እየተጠራሩ በዱር በገደሉ እየተሹለከለኩ ፀረ-ወረራ ትግሉን አፋፋሙት፡፡

ጃጊ ጃገማን የመሳሰሉት ጀግኖችም ከዚያ ከተፋፋመ ትግል አብራክ ተወልደው ለበርካታ አመታት የተዘጋጀውንና እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የኢጣሊያ ጦር እየነደፉ አበሳውን አስቆጠሩት፡፡

ጀግናው የአርበኞች መሪ ጃገማ ኬሎ በአርበኝነት ጭልም ጫካ ውስጥ እያለ ስለዚህ ሁሉ፣ ስለኢትዮጵያ ታሪክ እና ለሀገራቸው ሀልውና ሲሉ እንገታቸውን ለጠላት ስለሰጡ የሀገሪቷ መሪዎች ብዙ ሰምቷል፡፡





ለምሳሌ ከ1847 - 1860 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት የነበሩት አፄ ቴዎድሮስ በዘር ላይ በተመሰረተው ሰለሞናዊ ስርወ መንግሥት ሽግግር ሳይሆን ይዘውት በተነሱት ህልምና ጀግንነት መሪ ለመሆን የበቁ፣ የአገራቸው መፃኢ ዕድል የሚወሰነው በአንድነትና ስልጣኔ መሆኑን የሚያምኑ መሪ እንደነበሩ ጃገማ የሰማው እዚያው የጭልም ጉድባ ውስጥ ሆኖ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ «ወዳጆች ነን» ባዮቹ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር በቀይ ባህር በኩል መጥተው ሳለ የሱዳን ማህዲስቶች ሰራዊታቸውን ሰብስበው ዳግም ኢትዮጵያን ለማጥቃት በሰሜን ጎንደር በመተማ አቅጣጫ በተንቀሳቀሱ ጊዜ በወቅቱ ንጉስ የነበሩት አጼ ዮሐንስ አራተኛ ለሀገራቸው ደህንነት ሲሉ እንገታቸውን መስጠታቸውንም የተረዳው በዚሁ የአርበኝነት ዘመኑ ነው፡፡ ከዮሐንስ ቀጥሎም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነመንግስት የፋሽስት ኢጣሊያ መንግስት ኢትዮጵያን በግፍ ወርሮ በ1888 ዓ.ም. አድዋ ላይ በተደረገ ጦርነት ኢትዮጵያውያን በጦርና በጎራዴ ተዋግተው ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀውን የኢጣሊያ ጦር ድል ማድረጋቸውንና ይህም በጥቁር ህዝቦች የነጻነት ተጋድሎ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን የሰማው በአርበኛነት ጫካ ውስጥ ሳለ ነው፡፡

## ፫

# ጃገማ - የበጋ መብረቆች መሪ በአርበኛነት

ኢትዮጵያ የብዙ ወንዞችና ጅረቶች ባለቤት ናት፡፡ ከኦሮሞ ምድር የሚነሳው አዋሽም ከእነዚህ በርካታ ወንዞች አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን አዋሽ ወንዝ በብዙ ነገሩ ከሌሎች ወንዞች ለየት ይላል፡፡ አዋሽ ወንዝ ምንጩ ጊንጪ ከተማን አለፍ ብላ ካለች ወርቃ ከረብታ ስር ነው፡፡

አዋሽ ከሌሎች ወንዞች ጋር ሳይቀላቀል እንደ ንስር አሞራ ብቻውን ብዙ ይጓዛል ... ከሌሎች ወንዞች ጋር የሚቀላቀል መስሎም ተመልሶ አቅጣጫ ቀይሮ ዘወር ይላል፡፡ ተሳስቶ ከሌላ ወንዝ ጋር አይቀላቀልም፡፡ ግርም የሚያደርገው ታዲያ ኩሩውን የአዋሽ ወንዝን ብዙ ከሱ የሚበልጡ ወንዞች መጥተው ሲቀላቀሉት ነው፡፡ በመጠን ከሱ የሚበልጡት ወንዞች የአዋሽ ወንዝ ገባር ሆነው እሱን ያደረጁታል፡፡ ከዚያ አብዛኛውን ጊዜ ሜዳ ሜዳውን እየመረጠ ሳይዋከብና ሳይጣደፍ በእርጋታና በግርማ ሞገስ ይጓዛል፡፡ በዚህም ባህሪው አዋሽ ወንዝ የሰው ልጅ ህልውና አጋር፣ ለአራዊትና ለአእዋፍ ጥም ቆራጭ፣ መጠለያ ... ከመሆኑም ባሻገር ከአገሩ ተነስቶ፣ በአገሩ ተገዞ፣ በአገሩ ውስጥ ጉዞውን አጠናቆ በአገሩ አሸዋ ይሰርግና በአገሩ ከርሰ ምድር ወርዶ ለሽ ይላል - የመነጨባትን ምድር ጥሎ፣ ወደ አለው፣ ወደ ደረጀው ውቅያኖስ ሳይፈስ፡፡

አዋሽ ከወንዞች ሁሉ የተለየና የተመረጠ ባህሪ አለው፡፡ ይህ ወንዝ ከጀግናው ጃገማ ህይወት ጋር ቀጥተኛ የሆነ የህይወት እንቅስቃሴና ቁርኝት ያለው ይመስላል፡፡

ጃገማና አዋሽ ወንዝ ከአንድ አካባቢ የመነጩ ናቸው፡፡ ጃገማ ገና በህፃንነቱ የታላቅ ወንድሞቹ አለቃ የሆነ፤ በአፍላ ወጣትነቱ የሶስት ሺህ አምስት መቶ አርበኞች አለቃ የሆነ፤ የራሱን ፅኑ እምነት የሚከተል፤ ዘመናዊ ትምህርት ያላቸው፣ ውቅያኖስ አቋርጠው ሄደው ዘመናዊ የውትድርና እውቀት የቀሰሙና ዘመናዊ ኑሮ የነበራቸው ሰዎች ገባሩ የሆኑለት ጀግና ነው፡፡

ቅድመ አያቱን ጎዳና ነሞን ይተካል እየተባለ ሲተነበይለት ያደገው ጃገማ በአፍላ ወጣትነቱ ባልታሰበበት ቦታ የዝና መሰላል ሲወጣ፣ የጀግንነት





ተግባር ሲፈጽም ታየ፡፡ የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንዲሉ ያ ተግባሩ የወደፊቱን የሚጠቁም ምልክት እንደሆነ ታመነ፡፡ እንደ ቅድመ አያቱ ለመሆን አንድም ቀን ሳይታክት ሲያልም ኑሯልና በአድዋው ጦርነት ተሸንፈው የነበሩት ጣሊያኖች ቂም ይዘው ኖረው ኢትዮጵያውያንን ለመበቀልና ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ለመውረር ያደራጁት ዘመናዊ ጦር ወደ አካባቢያቸው መጥቶ ሽማግሌና ህፃን ሲገድል፤ ሲሾምና ሲሽር፤ የወገኖቹን ሃብትና ቤት ሲዘርፍና ሲያቃጥል፤ ያልተከለውን ዛፍ ሲቆርጥና ያላሳደገውን ፈረስ ሲጋልብ ... አንገቱን የደፋውን፣ የወራሪው ግፍ አስጨንቆት እንባውን የሚያፈሰውን ወገኑን ነፃ ሊያወጣ፤ ሃፍረቱን ሊያስወግድ ... 'እረ ጥራኝ ጫካው፤ እረ ጥራኝ ዱሩ' ብሎ የአርበኝነት ህይወትን ለመጀመር ወሰነ፡፡

ከጉዞው በፊት ጃገማ የአባ ዶዮን ልጅ አሰፋ አባ ዶዮን «እንሸፍት» ብሎ ማግባባት ጀመረ፡፡ አሰፋ በጃገማ ሀሳብ ማለለ፡፡ ወኔው እንደ አልኩል ቢሰራ አካላቱ ተሰራጭቶ አሰከረው፡፡ ጃገማ ወኔውን ይበልጥ ለማጋጋል እሳቱን ይበልጥ አግለበለበው ... የአሰፋ ወኔ ጋለ፡፡ የምሬት፣ የወኔ ላብ በሰራ አካላቱ ችፍ አለ፡፡

«በቃ ወስኛለሁ!» አለ አሰፋ፡፡

«ምን ወሰንህ?» አለ ጃገማ በወኔ፡፡

«እሸፍታለሁ፤ እነዚህን ነጫጭባዎች እፋለማቸዋለሁ!» አለ፥ አሰፋ - ወኔው እየናጠው፡፡

«በል ተከተለኝ» አለ ጃገማ - የደበቀውን መውዜር ጠመንጃ ከደበቀበት መዞ ትከሻው ላይ እያስቀመጠ፡፡ ጃገማ ከአሰፋ ጋር ቀዬውን ለቆ ጫካ ገባ፡፡

ብዙ ሳይጓዙ የአውሮፕላን ድምፅ ሰሙ፡፡ ቆፍጣናው ጃገማ የአጎቱን ልጅ አሰፋን ዞሮ ተመለከተው፡፡ አሰፋ የለበሰው ልብስ ነጣ ያለ ነው፡፡ «ና፤ ሩጥ ተከተለኝ!» ብሎ አሰፋን ወደ ቁጥቋጦው ይዞት ሮጠ፡፡ ጃገማን ጨነቀው፡፡ የአሰፋን ልብስ ቅጠል መቀባት ፈለገ፡፡ አውሮፕላኑ ግን እየቀረበ ስለነበር ይህን ሀሳቡን ትቶ አሰፋን ጫጩቶቿን ከጭልፊት በክንፎቿ እንደምትከልል ዶሮ ከስሩ አድርጎ በመሸፈን አውሮፕላኑን አሳለፈው፡፡ ወጣቱ ጃገማ ምንም እንኳን ድርጊቱ የልጅ ቢመስልም ነጭ ልብስ ለአውሮፕላን አብራሪ እንደሚታይ፤ በዚያም ሳቢያ ሊጠቁ እንደሚችሉ ማንም

ሳያስተምረው በመረዳቱ የጦር ጥበብ አዋቂነት ተሰጥዖ እንዳለው ፍንጭ አሳየ::

ገና በአስራ አምስት ዓመቱ አሰፋ አባ ዶዮን አሳምኖ በማስከተል ጫካ ገባ እና አርበኛ ሆነ፤ ወንድሞቹና እህቱም ተከተሉት፤ ገበሬዎች፣ ወታደሮች፣ ሹፌሮች ... ተቀላቀሉት:: ጃገማ እንደ አዋሽ ወንዝ ትላልቆች ገባሩ እየሆኑለት ጫካ ለጫካ ፈሰሰ ... የኢጣሊያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ጃገማ ጫካ ሲገባ አዋሽ ወንዝ ከትላልቅ ወንዞች ጋር ተቀላቀለ ሲባል በኩራት ዘወር እንደሚለው ሁሉ ገበሬዎች፣ ወታደሮች፣ ምሁራን በእሱ ስር ተሰባሰቡ:: አዋሽ በመጠኑ ከማንም በልጦ አይደለም ገናና ወንዝ የሆነው:: አዋሽ ትሁት ነው - እንደ ጃገማ፤ አዋሽ ታጋሽ ነው፤ አዋሽ ወንዝ ዝም ያለ ነው - እንደ ጃገማ! ትላልቅም ሆኑ ትናንሽ ወንዞች ዘንድ ሲደርስ ግን በኩራት እጥፍ ይላል:: ትላልቆቹም ሆኑ ትናንሾች ወንዞች ትንሽነቱን ሳይንቁ ሄደው ይቀላቀሉታል:: ከዚያ ይዟቸው ይሄዳል:: በአገሩ ውስጥ ተጉዞ፣ ለመጠጥና እርሻ አገልግሎት ሰጥቶ ተመስግኖ አገሩ ምድር ውስጥ ይሰርጋል:: ጃገማም እንደ አዋሽ ወንዝ ነው፤ አባቱ የመረጠው፣ ኩራቱ ያስመረጠው፣ የሚመራውን ለሽንፈት የማይዳርግ፣ በእብሪት አፍንጫውን ዳመና ውስጥ የማይሰነቅር ትሁት ጀግና ...

አሰፋ ዶዮ በጃገማ ቅስቀሳ ሸፍትነት ቢጀምርም አጎቱ ዲባባ ሁርሴ ከተደበቁበት ጫካ ሄደው፤ «አንተ የወንድሜ ልጅ ብትሆንም አባት የለህምና የምትፈልገውን መምረጥ ትችላለህ:: አሰፋ ግን የኔ ወንድም ልጅ ነው:: ልጁ ሸፍቷል ሲባል ወንድሜን ጣሊያን ይገድለዋል:: ቤት ንብረቱንም ያወድማል» ብለው አሰፋና ጃገማን በመነጠል አሰፋ ከኢጣሊያ ወራሪ ጦር አዛዦች ምህረት እንዲያገኝ ተደርጎ ገባ::

ጃገማና አሰፋ የአርበኝነት ኑሮ ሲጀምሩ ሰላሳ የሚደርሱ የወንድም፣ የእያት፣ የቅድመ አያት ልጆች አርበኛ ለመሆን ተቀላቅለዋቸው ነበር:: ቤተሰቦቻቸው ግን በአገልግሎታቸው ስንቃቸውን ቋጥረው አብረው በመዞር ቀስ በቀስ እያግባቡ ከአርበኝነት ህይወታቸው አስኮበለሏቸው:: ወላጅ አልባዎቹ ጃገማና ወንድሞቹ ብቻ በዱር በገደል ቀሩ:: ጃገማ ያን ጊዜ ከፋው፤ የሙት ልጅ በመሆኑ ከልቡ አዘነ:: ነገር ግን ያ ድርጊት ይበልጥ እልህ፣ ይበልጥ ጥንካሬ ጨመረለት:: ጥንካሬውንና ቆራጥነቱን ያዩ ወንድሞቹና ሌሎች ወጣቶችም ቀስ በቀስ ተቀላቀሉት ...





በ1926 ዓ.ም ባል አግብታ ወደ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ሄዳ የነበረችው እህቱ ሌንሴም በእገባች በሁለት አመቷ «ወንድሞችሽ ሸፈቱ» ሲሏት ባሏን ፈትታ እነ ጃገማን ጫካ ውስጥ ተቀላቀለች:: የሌንሴ መምጣት ለጃገማ ሌላ ጥንካሬ ፈጠረለት:: ሀሳባቸው ይወላውል የነበረ የኦሮሞ ወጣቶችም ጃገማን ለመቀላቀል በእየለቱ መጉረፍ ቀጠሉ ...

ጃገማና ተከታዮቹ እስኪጠናከሩ ድረስ የጫካ ውስጥ ወፍ አጥኚዎች ("ኦርኒቶሎጂስት") ሆኑ:: ወፎችን ያያሉ፤ የወፎችን ባህሪ ይከታተላሉ:: በመጨረሻም የወፍ ቋንቋ አጠኑ:: «ወፍ እንግዳ ይመጣል አለች፤ ወፍ ሂዱ አለች፤ ወፍ ደግ አለች ...» እያሉ መተርጎም ጀመሩ:: ወፎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም:: እዚህ ሲሏቸው እዚያ፣ እዚያ ሲሏቸው እዚህ ቢሉም ወፎች የተፈጥሮ ምርጫና ከሌላው የሚያስበልጡት አካባቢ ግን አለ:: ወፎች ፀጥታና ሰላምን ይፈልጋሉ:: ወፎች አያሳብቁም፤ «ኑር፤ ሌላውም እንዲኖር ፍቀድ» የእነሱ የአኗኗር ዘይቤ ነው::

ጃገማ በአርበኝነት ጅማሮው ወቅት የነበረውን ሲያስታውስ «ሰው አይቀበለኝ እንጂ ሁሌ ራሴን እንደ ወፍ ስበር አየዋለሁ:: የወፎች ኑሮና ምርጫም ወፍ ሆኜ ያየሁት ያህል ይገባኛል:: እንደ ወፍ የዛፍ እናት ላይ ቆጭ እላለሁ፤ እንደ ወፍ አዜማለሁ፤ ዛፍ ላይ ቅጠል ሰብሼ እተኛለሁ፤ ወፍ ሲንጫጫ እነቃለሁ፤ ከጓደኞቼ ጋር "ወፍ ምን አለ?" እላለሁ:: ሁሌም የጣሊያኖችንና የባንዳዎችን እንቅስቃሴ ዛፍ ላይ ወጥቼ እቆጣጠራለሁ:: እንደ ወፎችም እዚህ ሲሉኝ እዚያ፤ እዚያ ሲሉኝ እዚህ እያልሁ ... ለጣሊያን አልጨበጥ ብዬዋለሁ:: ጣሊያኖችም የዋዛ አይደሉም:: ዝግባ ዛፍ ላይ መወጣጫ አበጅተው፣ ማማ ሰርተው እንቅስቃሴዬን ይቆጣጠራሉ:: እነሱ ጭልሞ እኔ ሰንጎታ ሆነን ... እባብ ለእባብ ዛፍ ለዛፍ እንተያያለን ...» ይላል::

ጃገማ በአርበኝነት መኖር እንደጀመረ አንድ ቀን ከአንድ ዘመዱ ቤት ቆይቶ አልባሌ ሰው መስሎ መንገድ ሲያቋርጥ ሶስት የኢጣሊያ ባንዳዎች መሳሪያቸውን ደግነው ሲገሉት ሲጠጉ አይቶ ቀደማቸውና አንዱን አቆሰለው:: ጭልሞ የነበሩት የኢጣሊያ ወራሪ ጦር አዛዦች በደረሰባቸው ጥቃት ተቆጡ:: «ይህች ጥሬ ከአደረች አትቆረጠምም» ብለውም ያን ድፍረት በእንጭጭነቱ ለማጥፋት ወሰኑ:: ውሳኔያቸውንም ተግባራዊ ለማድረግ ስለአካባቢው መረጃ ወደሚጠይቋቸው ሰዎች ዘንድ ሄዱ:: ጣሊያኖች ከእነዚህ ሰዎች መካከል የጃገማን የአጎት ልጅ አባ ዶዮን «አንተ ሸፍታ የለም እያልህ ይኸው ታስገድለናለህ!» ብለው አፋጠጧቸው:: አባ ዶዮም «እናንተ ሰው ላይ

ከተከሳችሁ ህዝቡ አይተዋችሁም፤ ይተኩስባችኋል፤ አለበለዚያ ግን ደግሜ ልንገራችሁ፥ ሽፍታ የለም» አሏቸው።

«ሽፍታ የለም! ጥሩ! ነገ አሰሳ እናደርጋለን፤ አንተም እፊት እፊት ትሄዳለህ ...» አሏቸው። አባ ዶዮ «እሺ!» አሉ።

ምሽት ላይ ግን ወደ ጃገማ መልዕክት ላኩ፤ «ጃገማ! ጣሊያኖች ሽፍታ ከተከሰብን አንተን እንገልሃለን ብለውኛል ... ስለዚህ እነሱ ከሚገሉኝ አንተ ብትገለኝ ይሻላልና ፈቃደኛ ከሆንህ አካባቢህን ልቀቅልኝ፤ በጣሊያኖች ትዕዛዝ ነገ ከእነሱ ጋር መጥቼ ቤትህን ለማቃጠልም ተስማምቻለሁ» አሉት። በሚቀጥለው ቀን አባ ዶዮ ጣሊያኖችን እየመሩ ሰንጎታ አምባ ላይ ወጥተው የጃገማን ቤት ሲያቃጥሉ ወጣቱ ጃገማ በጦር ሜዳ መነፅር ተደብቆ እየተመለከታቸው ነበር። ጎሽ ለልጄ ስትል ተወጋች እንዲሉ ግን ለአጎቱ ልጅ ሲል ወጣቱ አርበኛ ትልቅ ትዕግስት ፈፀመና የትንሽ ትልቅነቱን አሳዬ!

* * *

በ1928 የኢጣሊያ ወረራ ዘመን ከጊንጪ ወደ ጋጂ የሚወስድ የመኪና መንገድ አልነበረም። ጋጂና ጭልሞ ግን የእንጨት መሰንጠቂያ ነበረ። እዚያ ውስጥ የደጃ/ች ገብረ ስላሴ አሸከር እንደነበር የሚነገርለት አላባሽ 350 የኢጣሊያ የባንዳ ሠራዊት ይዞ ጋጂ ላይ ሰፍሮ ነበር። የጃገማ አጎት ልጅ አቶ ዲባባ ሁርሴ ኦሮሞውን፣ አማራውን፣ ትግሬውን፣ ነፍጠኛ ውን አስተባብረው ጦርነት ሲገጥሙ ጃገማ ጦር ይዞ የወንድሙ የጊዲ ኬሉ ጥይት ያዥ በመሆን ጦርነት ቦታ ተገኝቶ ነበር። ጦርነቱ ሲጀመር፣ ጥይት ሲያፋጭ ... ጃገማ ድንገት ወደ አንበሳነት ተቀየረ ... ዐይኖቹ እነጣጠሩ! ስሮቹ ተገታተሩ፤ ክንዱ እንደ ብረት ጠነከረ፤ እግሮቹ መሬቱን የሚደልቁ ሆኑ ... ከዚያ የጥይት አሩር እያፏጨበት፣ ሬሳ እዚህም እዚያም ሲወድቅ እየተመለከተ፣ የጦር ሜዳ ልምድ ካላቸው በላይ እንደ ጥንግ እየተወረወረ በጦር አልሞ ወግቶ የጠላቱን ማንቁርት እየያዘ ሁለት መሳሪያ ገፈፈ ...

«የኔ ፍላጎት ሰው እንዲወደኝ ማድረግ ሳይሆን ሰዎችን የምወድ መሆኔን ማረጋገጥ ነው» የሚለው ጃገማ አንድ ነገር ትዝ ይለዋል። አርበኝነት ጀምሮ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሲሆነው አንድ ንቀት ሰማ።

ከአምቦ መንገድ በላይ ያሉት ኗሪዎች ጥራጥሬ እያዋጡ፣ ቆሎ እየቆሉ ... የአገኙትን ሁሉ እየሰጡ ቤቱንና ንብረቱን ትቶ በዱር በገደል ለሚኖረው አርበኛ ይረዳሉ። ከአምቦ መንገድ በታች ያሉት ግን «የጃገማ





አርበኞች ሙጀሌ የወረሳቸው ስለሆኑ ይህን የተሰነጣጠቀውን የደባይ መሬት ስንጥቅ እግራቸው ችሎ ሊራመዱ አይችሉም። ስለዚህ እንኳን እኛን ከኢጣሊያ ሰራዊት ሊጠብቁንና ሊረዱን ለራሳቸውም ስለማይሆኑ በምንም ነገር አንረዳቸውም» ማለታቸውን ሰማ።

አንድ ቀን የጃገማ አርበኞች፥ ወደ ናቋቸው አካባቢዎች ሄደው ወደ ሃያ ሺ የሚደርሱ ከብቶቻቸውን ነዱባቸው። ያን ጊዜ ኗሪዎቹ «ምላሳችንን በቆረጠው» በሚል ተደናገጡ። ጥፋተኛነታቸውንም ለመግለጽ ቀንበራቸውን ትከሻቸው ላይ በመስቀል አርበኞች ከሚኖሩበት አምባ ላይ ወጥተው «እግዚኦ!» አሉ።

ወጣቱ የአርበኞች መሪ አጠገባቸው ሄዶ «እኛ ከእናንተ የወጣን የእናንተ ልጆች ነን፤ ጠላት የሚንቀን አንሶ የእናንተ እኛን ሙጀሊያም ማለት ለምን ነው? እኛ ከብቶቻችሁን የነዳነው አቅማችንን ለማሳየት ነው። ከብቶቻችሁ አንድም ሳይቀር ይመለሱላችኋል። ለወደፊቱ ግን እንዲህ አትበሉ። የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ እኛ ስንናናቅ ጠላት ይጠቀማል» ብሎ ከብቶቻቸውን ሰጣቸው። በፍቅሩም የኗሪውን ፍቅርና ከበሬታ አግኝቶ መረዳዳቱ ተጀመረ።

* * *

ጃገማ ከጊንጪ ጫካ ይበልጥ በጊንጪ ወገኑ ይመካል። ድፍን የዮብዶ፣ የሰንጎታ፣ የኢችልቤ፣ የጎበን፣ የሜታ ሰው የአባቱ ውለታ ያለበት ነው። መቼም በአባቱ እጅ ያልበላ፣ ያልጠጣ፣ ከብት ያልተቀበለ ስለሌለ ሁሉ ደጋፊው ነው። ብዙ ሰዎች እንቁላልና ዶሮ ይዘው ለጣሊያኖች ይሸጡና ከባንዳዎች ጥይት ገዝተው ለጃገማ ይወስዱለታል። ቀስ በቀስ ደግሞ የኢጣሊያን ጦር እንቅስቃሴ በመንገር ብዙዎቹ የውስጥ አርበኛ ሆኑ። በዚህም አርበኞቹ ድንገተኛ ጥቃት እየወሰዱ ጣሊያንን መፈተን ጀመሩ። ጣሊያኖችም ጃገማንና ተከታዮቹን ለመያዝ ሙከራ ጀመሩ፤ ቤት አቃጠሉ። ጃገማንና አርበኞችን ግን መያዝ ቀርቶ መክበብ ተሳናቸው። ይልቁንስ እነ ጃገማ ጣሊያን ሲንቀሳቀስ ጥይት የሚጭንባቸውን ከብቶች በጥይት እየመቱ፣ የፍተሻ ተኩስ እየከፈቱ ጥይታቸውን እያስጨረሱ ጣሊያኖችና ባንዳዎች ሲሸሹ ጥይት ማጠራቀም ቀጠሉ። ቀስ በቀስ የጃገማ ስም ጣሊያኖችን የሚያስበረግግ እየሆነ ሄደ። ጃገማ ሲመጣ የኢጣሊያ ምሽግ በፍርሃት መናጥ ጀመረ ...

የበጋ መብረቆቹና መሪያቸው መጀመሪያ አካባቢ የሚጫሙት ጫማ አልነበራቸውም። በሬ ሲታረድ ቆዳው ተሽጦ ጥይት ይገዛበታል፤ የሚታረዱ

በሬዎች ግንባር ላይ ባለችው ቆዳ ግን ጫማ መስራት ጀመሩ:: ሁሉም አርበኛ ተራውን እየጠበቀ ለጫማ መስሪያ የሚሆን የግንባር ቆዳ ይደርሰዋል:: ያን ጫማ ቀን ቀን በእጁ አንጠልጥሎ ይውላል፤ ማታ ማታ ደግሞ ከእሾህና እንቅፋት ለመዳን ይጫማዋል::

አርበኞች መንደር ገብተው ያገኙትን ከበሉ በኋላ ሰንጎታ ጫካ ገብተው እስከዛሬ «የጃገማ ጥድ» እየተባለ ከሚጠራው ጥድ ስር ዳስ ሰርተው ይተኛሉ:: ጥዱ ዝናብ ቢዘንብ እንኳን የማያስገባ ችምችም ያለ ነው:: ሲተኙ ጠላት ካለበት አፋፍ ጀምሮ እነ ጃገማ እስከሚተኙበት ድረስ በየተራ የሚጠብቁ ዘቦች አሉ:: ዘቦቹ ጠላት ሲንቀሳቀስ ሲያዩ ቀድሞ ያየው አንድ አምስት መቶ ሜትር ሮጦ ከእሱ ቀጥሎ ላለው ይነግራል፤ የሚቀጥለውም ተመሳሳይ ርቀት ተፈትልኮ ለሌላው ይነግራል:: በዚህ ዘዴ መልዕክት ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው እንደ ዱላ ቅብብሎሽ ወደሚፈለገው በአስቸኳይ ይደርሳል:: ከዚህ ውጭ ግን በድምፅ መጠራራት ክልክል ነበር::

ወጣቱ አርበኛ ጃገማ ከልጅነቱ ጀምሮ ውሃ ዋና፣ አደን፣ ፈረስ ጉግስ፣ ሩጫ፣ ተኩስ ይወዳል:: አንድ ጊዜ በመስቀል በዓል ጃገማ ጉ ስ ጉግስ ለመጫወት መጫወት አማረው:: ስለዚህ «የመጣው ይምጣ» ብሎ ጉግስ ለመጫወት ለኢጣሊያ ሰራዊት ይርቃል ባለው ቦታ ሄደና ጉግስ ሲጫወት ዋለ:: በነጋታው የኢጣሊያ ጦር በአካባቢው ትልቅ አሰሳ አደረገ፤ ነውጠኛው ግን ከቦታው ተመልሶ ጥዱ ስር የአዛውንቶችን ተረት ይሰማ ነበር::

ለነፃነት ፍልሚያ ቆርጦ ዱር የገባው አርበኛ በህዝቡ ትብብር በወራሪው የኢጣሊያ ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በመሰንዘሩ ጣሊያኖች ጊንጪ፣ ሐሮታ ላይ ጠንካራ ምሽግ ሰርተው መሣሪያቸውን ጠምደው ተቀመጡ:: ይህ የጠላት ጦር ጀልዱ የጭልሞ እንጨት መሰንጠቂያ ካምፕ ከሚገኘው ጦር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ፈጥሮ ትዕዛዝና መረጃ እየተለዋወጠ ተጠናከረ:: በጃገማ የሚመሩት አርበኞች በሐሮታና በጀልዱ ጦር መካከል ያለውን ግንኙነት ካጤኑ በኋላ በሁለቱ ጦሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመበጠስ ስኬታማ አደጋ በመጣልና መተላለፊያ መንገዱን በመቁረጥ በጠላት ሰፈር ድንገተኛ ሁከት እየፈጠሩ መሳሪያና ትጥቅ አጠናከሩ::

ይህን ጥቃት ከመፈፀማቸው በፊት ግን አርበኞች የሥልጣን ተዋረድ ያለው፣ ጥቃቱን የሚያዝና የሚያስተባብር አመራር አስፈለጋቸው፤ በዚህም አርበኞች ሸንጎ ተቀመጡ:: መሪ መረጣ ተከራከሩ፤ ተወያዩ:: ነገር ግን በአባቱ የተመረጠውንና የተሾመውን፣ አንጊ ግርማ ሞገስና የማስተዋል ችሎታ የታደለውን ጃገማን ልቆ የተገኘ ተቀናቃኝ ጠፉ:: ስለዚህ ጃገማ





የአርበኞች መሪ ሆኖ ተመረጠ:: እርግጥ ነው የኦሮሞ ብሔር በዕድሜ ገደብ ላይ የተመሰረተ እጅግ የተዋጣ የአስተዳደር ስርዓት ያለው ነው:: በዚያ የአርበኝነት ዘመን ጃገማ የአስራ አምስት ዓመት ወጣት ነው:: በገዳ ስርዓት ከዘጠኝ እስከ አስራ ስድስት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የሁለተኛ የገዳ እርከን ውስጥ የገቡ ኢቲመኮ ናቸው:: አንደኛው የገዳ እርከን ዳኤመን ሲሆን አንድ ህፃን ከተወለደበት እስከ ስምንት ዓመት ዕድሜው የሚገኝበት ደረጃ ነው:: ጃገማ የአርበኞች መሪ በሆነበት ዕድሜው በገዳ ስርዓት ደንብ መሠረት ጊደር ተሰጥቶት ፀጉሩን የሚላጭበት፣ የዘር ግንድ ቆጠራ ተምሮ የኦሮሞ የመጨረሻ አባት የሆነውን ዋቃ (እግዚአብሔር) የሚያውቅበት የዕድሜ ክልል ውስጥ ነበር::

ኢቲመኮ የነበረው ጃገማ የአስተዳደር መሪ ለመሆን በደበሌ፣ ፎሌ አልፎ ቢያንስ ራባዶሪ (ከ33 እስከ 40 ዓመት) የዕድሜ እርከን ውስጥ መድረስ ነበረበት:: የኢቲመኮ እርከን ውስጥ የገቡ÷ የኦሮሞ ብሔርን ባህል፣ አንድነት፣ አውቀው ብሔሩንና ግዛቱን ለማስተዳደር የሚያዘጋጃቸውን ባሕላዊ ህግ፣ አስተዳደር፣ ታሪክና ባህል ያጠኑ ሊሆኑ ይገባል:: ኢቲመኮ የእድሜ ዕርከን የደረሱ ለኃላፊነት የሚያበቃቸውን ዕውቀት እየቀሰሙ፣ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ስትራቴጂያዊ ቦታዎችን፣ የብሔሩን ወሰን፣ ወንዞችንና ተራሮችን በማየት፣ የታላላቆቻቸውን ምክር እየሰሙ፣ ትዳር መስርተው ስድስተኛው የገዳ እርከን ሉባ (ከ41-48 ዓመት) የሚደርሱ ናቸው:: ይህ የዕድሜ እርከን ለመሪነትና ለኃላፊነት የሚያበቃ የዕድሜ ደረጃ ነው::

ጃገማ ግን በአስራ አምስት ዓመቱ ከእድሜ እርከኑ ቀድሞ ስለ ኦሮሞ ባህል፣ ስለ አያት ቅድመ አያቱ ያወቀ፣ በፈረስ ግልቢያ፣ ውሃ ዋና፣ ጉግስ ... የላቀ ችሎታ የነበረው፤ ግፍን የማይወድ፣ ብስጭቱ ቶሎ አሸንፎት ስለማይወጣ ሰውን የማያስቀይም ተወዳጅ ስለነበረ በተለይም በሁሉም ዘመዶቹ ተወዳጅ የነበሩት አባቱ የመረጡት ስለሆነ የእድሜውን ሁለትና ሶስት እጥፍ ዕድሜ የነበራቸው አርበኞች ሳይቀሩ ጃገማን መረጡት:: ጃገማን እንዲያግዙት ደግሞ ጊዲ ኬሎ፣ ጤንቁሳ ኬሎ፣ የሸነህ ወርቅነህና አበበ ተሰማ ተመረጡ::

* * *

ከ1929 እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ ጃገማ ጋጂ ይገኝ በነበረው የኢጣሊያ ምሽግ ላይ እንደ በጋ መብረቅ ድንገት እየተወረወረ ጥቃት በመፈፀም ጠላትን መፈታተንና ማተራመስ ቀጠለ:: ወራሪ ሠራዊት ወጣቱን ነውጠኛ በቁጥጥሩ

ስር ለማድረግ መደለያ አዘጋጅቶ ጃገማን ለያዘ ሽልማት እንደሚሰጥ በሚስጥር አሳወቀ:: አታለውና ትዘናግተው የሚይዙትንም አሰማርቶ በፍለጋ ባዘነ:: ባጠቃላይ የጋጂ ምሽግ ሹማምንት አተራማሹን ወጣት የአርበኛ መሪ ለመያዝ ያገኙትን ድንጋይ መፈንቀል ጀመሩ:: ቤቱን አቃጠሉ:: ከእለት ወደ እለት የተከታዮቹ ቁጥር እየጨመረ የሄደውን ጃገማን ለመቆጣጠርና ለማክሰም የኢጣሊያ ሰራዊትም ጊንጪ፣ ሐሮታ ከተባለው ቦታ ጠንካራ ምሽግ ገነባ:: የኢጣሊያ ወታደሮች የምሽግ ግንባታውን በማስፋት በጀልዱና ግንደበረት አዳዲስ ምሽግ ለመጨመር ሲንቀሳቀሱ ግን ወጣቱ የአርበኞች መሪና በእሱ የሚመሩት አርበኞች የኢጣሊያ ሰራዊትን እንኳን ተጨማሪ ምሽግ ሊያሰሩ በገነቡት ምሽግ ውስጥም እንደ ልብ መንቀሳቀሻ አሳጧቸው::

በ1931 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ውስጥ በጃገማ ትዕዛዝ ሐሮታ የመሸገው የአርበኞች ሰራዊት የጠላት ጦር ከጀልዱ ጦር ጋር ያለውን ግንኙነት በኃይል ለመበጠስ አደጋ የመጣል፣ መንገድ የመዝጋት እርምጃ ወሰደ:: አርበኞቹ በወኔና ሞራል እየተዋጉ ሐሮታ የሚገኙትን ጣሊያኖችና ባንዳዎች ማሸበሩን አፋፋሙት:: ከዚያ «ጃገማ የተባለ የኦሮሞ ባላባት ልጅ በጅባትና ሜጫ በረሃ ገብቶ ጣሊያንን እያርበደበደ ነው» የሚለው ከእረኞች ዜማነት እና ከልጃገረዶች ሙገሳ አልፎ አዲስ አበባ ድረስ ተሰማ:: ይህ ደግሞ የአገሩ በጠላት መደፈር ያንገበገበውንና የኢጣሊያ ግፍ ያንገሸገሸውን ኢትዮጵያዊ ለአርበኝነት ትግል ወደ ጅባትና ሜጫ እንዲጎርፍ ምክንያት ሆነው:: ከእነዚያ «እምቢ ለአገሬ» ባዮች ውስጥ በቀሪ ዘመኑ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ከፍተኛ የጦር መኮንኖች አንዱ የሆነው የትግራይ ተወላጅ ወልደ ዮሐንስ ተክሉ (በኋላ ብርጋዴዬር ጀነራል) ይገኝበታል::

ጃገማ ኬሎ ልበ ሙሉነቱንና ጀግንነቱን ካረጋገጠባቸው አጋጣሚ ዎች አንዱ ምሳ ተጋብዞ ወደእሬራ የሄደበት ቀን ነው:: የጭልሞን መንገድ አቋርጦ ወደ እሬራ ሲሄድ ከጊንጪ ገበያ ውለው ወደ ጭልሞ የሚመለሱ ገበሬዎችን ዘራፊዎች መንገድ ላይ እስቁመው ንብረታቸውን ሲነጥቋቸው ጃገማ እየ:: ጃገማ ከአርበኞች ጋር ሳይሆን በርቀት ከሚጠብቁት በጣት የሚቆጠሩ አጃቢዎቹ ጋር ነበረ:: የዝርፊያው ቦታ ከኢጣሊያ ምሽግ ብዙ አይርቅም:: ስለዚህ ጣልቃ ቢገባ አደጋ ላይ ይወድቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ ወገኖቹ በዘራፊዎች ንብረታቸውን እየተዘረፉ በመሆናቸው ዝም ብሎ ለማየት የሚያስችል ጥንካሬ አጣ:: ጃገማ በአካባቢው የነገሰው ጩኸት ሲጨምር ወገኖቹን ከዘራፊዎች ለማስጣል እንደ ጦር ተወርውሮ ሄደ:: ጃገማን ያዩት ዘራፊዎች ጥቂቶቹ እግሬ አውጭኝ ብለው ፈረጠጡ:: ሌሎቹ ደግሞ በፍርሃት እየተርበደበዱ የዘረፉትን መለሱ:: ከዘራፊዎች አንዱ ቁም እያለው





እግሬ አውጭኝ ብሎ ሲፈተለክ ጃገማ ወደ ሰማይ ተኮሰ:: ጃገማ የተበታተነውን አሰብስቦ ለወገኖቹ ሲያከፋፍል የመኪና ድምፅ ተሰማ::

«አባ ዳማ!» አሉት (በፈረስ ስሙ)፤ «አባ ዳማ! አንተ ካለህ የተዘረፍነውን ቀስ ብለህ ታስመልስልናለህ፤ ያስመለስህልንንም እኛ እንከፋፈላለን:: አሁን ግን የጠላት ጦር ሊወጋህ እየመጣ ነው ... እምልጥ! ... ለእኛ ስትል፤ ቶሎ እራስህን አድንልን» እያሉ ሴቶች ተርበተበቱ፤ ወንዶች ሲቃ ታፈኑ::

«ተው አሁን፤ ፀጥ ብላችሁ መንገዳችሁን ቀጥሉ» አለ ጃገማ - ሙውዜር ጠመንጃው ምላጭ ላይ አመልካች ጣቱን አሳርፎ:: ከዚያ ጎፈሬውን ከምበል ደፋ እያደረገ ወደ ጉብታዋ ላይ ወጣና የመኪና ድምፅ ወደሰማበት ጆሮውን ቀስሮ በመራኸር ዐይኑ አፍጥጦ ተጠባበቀ:: ድንገት ግን ከወደኋላው ኮቴ ሰማ:: ዘወር አለ ጃገማ - ከመቅጽበት:: ሶስት የጠላት ወታደሮች ወደ እሱ ሲጠጉ አያቸው:: «ጃጌ - ጃገማ» አለና ተኮሰ:: የተመታው ሲወድቅ ሌሎች ድንብርብራቸው እየወጣ ሮጡ:: ጃገማ እንደ ሚዳቋ እመር ... እመር ሬ ብሎ የተመታው የጠላት ወታደር አጠገብ ሄዶ ተኛ:: ወታደሩ በደም እንደተለወሰ ሽጉጡን ደረቱ ላይ አድርጎ ተኝቷል:: ጃገማ እየተሳበ ጠጋ ብሎ ሽጉጡን ከወታደሩ ደረት ላይ አንስቶ ከጎኑ ሻጠው...

ጃገማ ልብ ያላለው ወታደሩን የመታው እግሩ ላይ መሆኑን ነው:: ወታደሩ ግን ደሙን እፊቱና እሆዱ ላይ መቀባቱን ጃገማ አላስተዋለም:: የወታደሩ ጓደኞች ልብ ገዝተው ተመልሰው እንደገና ጃገማ ላይ ተኩስ ከፈቱበት:: ጃገማ ከተኛበት እየተገለባበጠ አከታትሎ ተኮሰ፤ ሲሮጡ አያቸው:: በዚህ መሀል የሚያጅቡትም ያሳድዷቸው ጀመር:: መጨረሻ ጃገማ ያቆሰሰው ወታደር ተመለሰና ትጥቁን ፈትቶ ሄደ:: ወታደሩ ጃገማ ራቅ ሲልለት ተነስቶ ሄዷል:: ጃገማ መታለሉ ገባው:: በጥሞና ሲያስበው ደግሞ ፈገግ አለ:: ወታደሩ እሱ መሆኑን ሲያውቅ ፍርሀት ስለዋጠው ማሰብ ተስኖት እንጂ በቀላሉ ሊገድለው ይችል ነበር::

ባልታሰበ ሁኔታ ከጠላት ጦር ጋር በተደረገው የተኩስ ልውውጥ አርበኞቹ በአካባቢው መኖራቸው እስከታወቀ ድረስ የኢጣሊያ ጦር ሊወጋቸው እንደሚችል በማመን በነጋታው ጃገማና አርበኞች በተጠንቀቅ አድፍጠው ይጠባበቁ ጀመር:: የኢጣሊያው ጦር አዛዥ (ካራቢኔሪ) ግን ጦር በመላክ ይልቅ ያልታሰበ ደብዳቤ ለጃገማ ፃፈ::

«ይድረስ ለልጅ ጃገማ ኬሎ፡፡

«... በጭልሞ ጎዳና ላይ አድፍጠው ገበያተኞችን የዘረፉትን ወሮበሎች አባረህ፣ የህዝቡን ሀብትና ንብረት በማስመለስህ የጫካ ዘበኞች ወሮበሎች አባረህ፣ የህዝቡን ሀብትና ንብረት በማስመለስህ የጫካ ዘበኞች

በአንተ ላይ ተኩስ መክፈታቸውን ሰምቻለሁ፡፡ ለተተኮሰብህ አፀፋውን በመመለስ ራስህን ስትከላከል አንድ ሰው ማቁሰልህ ሪፖርት ተደርጎልኛል፡፡ በመመለስ ራስህን ስትከላከል አንድ ሰው ማቁሰልህ ሪፖርት ተደርጎልኛል፡፡

ለተከፈተብህ ተኩስ የተዘረፈውን የገበያተኛ ንብረት በማስመለስ ላይ እያለህ ለተከፈተብህ ተኩስ ባደረግከው መከላከል የኢጣሊያ መንግሥት አይጠይቅህም፡፡ ስለዚህ ወደ ኢጣሊያ በፃፍኩልህ ደብዳቤ መሠረት መከታተል ስለማይደረግብህ ወደ ኢጣሊያ መንግሥት እንድትገባ ሙሉ ምህረት ተደርጎልሃል» ይላል የደብዳቤው መልዕክት፡፡

ጃገማ ራሱን ግራና ቀኝ እየወዘወዘ ደብዳቤውን ደግሞ ደጋግሞ አነበበና «እያችሁ ይህን ደብዳቤ?» ብሎ ለጓደኞቹ አሳየ፤ «እሰው አገር መጥቶ፣ የሰው መሬት ወስዶ ... መኖሩን ተመክቶ 'ሙሉ ምህረት ተደርጎልሃልና ግባ' አለኝ፡፡ እኒህን ደፋሮች፣ እኒህን ግፈኞች አገሬን ለቀው እስኪሄዱ ድረስ አይማረኝ ብምራቸው» አለ ጃገማ፡፡ በመጨረሻም፤ «እኔ የማውቀው ምህረት ሰጭ እንድ ፈጣሪን ነው፡፡ ሰው ምህረት የሚሰጥ ከሆነ ግን ምህረት ሰጭው አገር የወረረ ሳይሆን አገሩ የተወረረበት እኔ ነኝ» ብሎ የመልስ ደብዳቤ ላከ፡፡

* * *

ፋሽስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመው ግፍ አገሪቱን ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ በሰላማዊው ሕዝብ ላይ በሚያካሂደው ጦርነትና ግድያ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያን አንድነት ለመበታተንና ህዝቡንም እርስ በርሱ ለማፋጀት ዕለት በዕለት የተለያየ ተንኮል ይሸርባል፡፡ በተለይም የቋንቋና የሃይማኖትን ልዩነት በማስፋት የማይበርድ እሳት እያቀጣጠለ፤ ረመጡንም እያዳፈነ እንደ ቦንብ ከመቅበር አልቦዘነም፡፡

በዚያ የፈተና ወቅት አገራቸውን ከወራሪው መንጋጋ ፈልቅቀው ለማውጣት በዱር በገደል የሚዋደቁት የላስታዎቹ ደጃዝማች ወንድወሰን ካሣና አበራ ካሣ፣ የሲዳሞዎቹ ደጃዝማች በቀለ ወያና ገብረማርያም ጋሪና፣ የመንዙ ኃይለማርያም ማሞ፣ የትግራዩ ደጃዝማች ገብረሕይወት፣ የጎጃሙ በላይ ዘለቀ፣ የዋጉ ደጃዝማች ሃይሉ ከበደ፣ የመርሐቤቴው ራስ አበበ አረጋይ፣ የጎንደሮቹ ራስ ውብነህ ተሰማ፣ ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ፣ ደጃዝማች ዳኘው ተሰማ ... የወሊሶው ደጃዝማች ገረሱ ዱኪና ሌሎች በግልና





በጋራ የኢጣሊያን ጦር ጉያው እየገቡ በማተራመስ እየነደፉ አበሳውን ያሳዩት ነበር፡፡ የረባ ትጥቅና ስንቅ ያልነበራቸው አርበኞች እስከ አፍንጫው በዘመናዊ ጦር የታጠቀውን የኢጣሊያ ጦር ከጉድጓዱ የማይወጣ አውሬ አድርገውት ነበር፡፡ በዚያ የወረራ ዘመን በዱር በገደል የተሰማሩት የአርበኞች መሪዎችና አርበኞች የኢጣሊያን የፖለቲካ ረመጥ እያጠፉ፣ በልዩነታቸው እየተቻቻሉ፣ አንዱ የሌላው ደባቂ እየሆኑ ይረዳዱ ነበር፡፡

ጃገማም ትግሉን እያርገበገበ ምዕራብ ሸዋ የነበረውን የኢጣሊያ ጦር ለቅዞ በመያዝ መውጫ መግቢያ አሳጣው፡፡ ሃይሉን ለማጠናከርም ጀግና ኢትዮጵያውያን እንዲቀላቀሉት በስራውና በጀግንነቱ ይጣራ ጀመር፡፡ በተለይም ዘውዴ ጥላሁንን (በኋላ ደጃዝማች የሆነውን) የእሱ ለማድረግ ብዙ ጥረት አደረገ፡፡

ዘውዴ ጥላሁን የተወለደው ጅባትና ሜጫ ነው፡፡ በኋላም የክብር ዘብ አባል ሆኖ ከንጉሰ ነገስቱ ጋር ማይጨው ዘምቷል፡፡ በወረራው ዘመን ጣሊያኖች አማራና ኦሮሞ በሚል ህዝቡን ከፋፍለው ሲያጫፋጭፉ ዘውዴ የኢጣልያ ተንኮል ቀስ በቀስ ገባው፡፡ በ1932 ዓ.ም ዘውዴ ጥላሁን ጓደኞቹን እሳልፋኝ ብሎ በየካቲት ወር ጀልዱ ምሽግ ገብቶ ሶስት ኢጣሊያውያንን ገድሎ የኢጣሊያን ምሽግ ይዞ ሲዋጋ ከሰነበተ በኋላ ሜታ ውስጥ ካሉት አርበኛ ከደጃዝማች ከበደ ብዙነህ ዘንድ ሄዶ ተቀላቀለ፡፡

የኢጣሊያ ጦር አዛዥ «... አርበኛም፣ ገበሬም ዘውዴ ጥላሁንን እንዳታስጠጉ» የሚል አዋጅ በአውሮፕላን በትኖ ስለነበር በደጃዝማች ከበደ ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በኢጣሊያ ጦር ተደረገ፡፡ በዚህ ጦርነት መሃል ግን ወጣቱ የአርበኛ መሪ ጃገማ ኬሎ ዘውዴ ጥላሁንን የእሱ ለማድረግ በቀኛዝማች ወዳጆ በኩል ጥረት አደረገ፡፡ ዘውዴ ጥላሁን ግን «የጃገማ የአጎቱ ልጅ አባ ዶዮ ለኢጣሊያ ያደሩ ስለሆኑ ይዘው መሸሚያ ያደርጉኛልና አልሄድም» አለ፡፡ በኋላ ግን ደጃዝማች ከበደ ብዙነህ ጥቃቱ ስለበዛባቸው ዘውዴን ወደ ሌሎች አርበኞች እንዲሄድ ጠየቁት፡፡

በዚያ መሠረት ዘውዴ አስራ ሁለት ተከታዮቹን ይዞ ቀኛዝማች ወዳጆ ዘንድ ሄዶ «ወደ አማራ ክልል አሳልፉኝ» አላቸው፡፡ ቀኛዝማች ወዳጆም እሱን እያግባቡ «ጃገማ ያን ጀግና አግኝቶልሃለሁና ነገ ዛሬ ሳትል መጥተህ ውሰደው» ብለው ላኩበት፡፡ ጀግና ወዳዱ ጃገማ ጊዜ ሳያጠፋ ገስግሶ ሄደ፡፡ ዘውዴ ጃገማን ሲያየው ለጊዜው ተከፋ፤ ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጃገማ ግን «አሳልፌ ብሰጥህ ነፍሴ አይማር፤ እኔ ሳልሞት አንተ አትሞትም» ብሎ ዘውዴን ሰንጎታ ይዞት ሄዶ ስሙን አስቀይሮ ገብረማርያም አለው፡፡ ከዚያም

ጃገማ አባ ዳማ የአርበኞች መሪ፣ ዘውዴ ቀኝ መሪ፣ ጠንቋላ ኬሎ ደግሞ ግራ መሪ ሆኑ። እጋፋሪ፣ የእልፍኝ አስከልካይም መረጡ።

እነ ጃገማ የተለየ የውጊያ ስልት ነበራቸው። በኢጣሊያ ሰራዊት ላይ ጥቃት ከሰነዘሩ በኋላ አርበኞች ለሶስትና አራት ወራት ከአካባቢያቸው ይሸሻሉ፤ የሚሸሹት ግን የኢጣሊያን ጥቃት በመፍራት ሳይሆን በቂ የመዋጊያ ጥይት ለማጠራቀም እንዲችሉ ነው። መሳሪያ እንጂ ጥይት አልነበራቸውም። ስለዚህ ምንም እንኳን ከበቂ በላይ የሆነ መሳሪያ ቢያገኙም ጥይት ለማጠራቀም መታገስ ነበረባቸው። አርበኞቹ ጥይት ለማግኘት በዘወትር ዘዴያቸው መጠቀም ጀመሩ። ጥይት ከሚያገኙባቸው መንገዶች አንዱ ከአካባቢው ህዝብ በድብቅ መቀበል ነው። የአካባቢው ህዝብ ዶሮና እንቁላል በመያዝ ወደ ኢጣሊያ ሰራዊት ካምፕ ይሄድና ለኢጣሊያ ገንዘብ (ሊሬ) ይሸጣል። ከሸጠ በኋላ ለተለያዩ ጉዳዮች ገንዘብ ከሚፈልገው የኢጣሊያ ወታደር ላይ በድብቅ ጥይት ይገዛል። ሞኛሞኝ ገበሬ በመምሰልም የኢጣሊያን ወታደራዊ እንቅስቃሴ፣ የአዳዲስ ምሽጎችን አቅጣጫ፣ ማድረግ የተፈለገውን ዕቅድ ... ካገኙ በኋላ ሌሊቱን አርበኞች ወደሚገኙበት ቦታ ይሄዱና ጥይቱንና መረጃውን ለጃገማ አባ ዳማ ያቀብላሉ።

አምስት ዓመት ሙሉ በነበረው የአርበኝነት ዘመን ወጣቱ የአርበኛ መሪ አንድም ቀን በጠላቶቹ ተሸንፎ ወይንም ተማርኮ አያውቅም። ለዚያ ደግሞ ዋናው ምክንያት ግጥግጥ ያለው የጭልሞ ጫካ ብቻ ሳይሆን ዋናው መመኪያው ህዝብ ነበር። ህዝቡ አርበኞችን ይደግፋል፤ የሚፈልጉትንም ያውቃል ... ህዝቡና አርበኞች አሳና ውሃ እንደማለት ናቸው። አሳዎቹ ከውሃ ተሰውረው መኖር አይችሉም። አሳዎቹ በኢጣሊያ መረብ እንዳይያዙ ግን ዘዴኛና ጀግና መሆን አለባቸው። አርበኞችም ሆኑ ህዝቡ የኢጣሊያ መረብ አሳ እንጂ ውሃ እንደማይዝ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ውሃው ደግሞ ህዝቡ ነው - በመረብ የማይያዘው፤ ስለዚህ ለአርበኞቹ ትግል ስኬት ውሃው መኖር አለበት። ውሃው ከሌለ አርበኞች ይሞታሉ። ያለ ውሃው ጀግና መሆን፤ ህልውና፣ ትግልና ህይወት እንዲቀጥል ማድረግ ዘበት ነው። ለዚህ ነው ጃገማ «ለእኛ አርበኝነት፣ ለእኛ ድል፣ ለእኛ ጀግንነት መሰረቱ የአገሬ ጫካ ብቻ ሳይሆን የአገሬ ህዝብ ነው» በማለት ደጋግሞ የሚናገረው።

ምንም እንኳን የኢጣሊያ ፋሽስቶች አርበኞችን ረድተዋል ያሏቸውን ነዋሪዎች ቤቶች ቢያቃጥሉ፣ ዘመዶቻቸውን በሞትና እስራት እየቀጡ ቢያሰቃዩም የአንዱ እግር ሲነቀል መቶ እየተተካ የአርበኝነት ድጋፉ ይቀጥላል። ከዚያ በተጨማሪ የጃገማ አባ ዳማ ስኬት ደግሞ በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች ለወራሪ «እምቢ አልገዛም» ያሉ ወታደሮች፣ ምሁራን ከጃገማና እሱን ከመሰሉ መሪዎች ለመቀላቀል ከያሉበት መጉረፋቸው ነው።





በሁለት ሰው የተጀመረው የአርበኞች ቁጥር ከመቶ ወደ ሺህ፣ ከሺህ ወደ ሶስት ሺህ አምስት መቶ እያደገ ተመነደገ። የአርበኞቹን ትግል ከልብ የሚደግፈው ሁሉ ደግሞ ሙሉ ከለላ ከመስጠቱ አልቦዘነም።

ሁለተኛው የእነ ጃገማ ጥይት የማግኛ ዘዴ ደግሞ እንደ ደራሽ ወንዝ ጠላት ሳያስብ አካባቢውን እንደ ንብ ወረው በኢጣሊያ ምሽግ ላይ መተንኮሻ ጥይት መተኮስ ነው። ያኔ የኢጣሊያ ሰራዊት መትረየሶች አፋቸውን እንደ ጉማሬ ይከፍታሉ፤ የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች ይንጣጣሉ ... አርበኞች ተንኩሰው ሄደው የኢጣሊያ ወራሪ ኃይሎች እንደ ብራቅ እየጮኹ ጥይታቸውን ሲያንጣጡ ... እነ ጃገማ ወደ ቦታቸው ተመልሰው እየሳቁ ገበጣ መጫወት ይጀምራሉ።

ገበጣ በቁጥር ላይ ተመስርቶ የሚጫወቱት ጥበብና ማስተዋል የሚጠይቅ ... አንድ ጠጠር አንስቶ፣ አንድ ጠጠር ጥሎ የተጋጣሚን ጠጠሮች እየወሰዱ ባላጋራን ባዶ አስቀርቶ የማሸነፍ ጥበብ መማሪያ ጨዋታ ነው። አርበኞቹ የጥይት ጠጠር ጥለው በነጋታው ህዝቡ እንቁላልና ዶሮ ይዞ ሄዶ የጥይት ጠጠሮችን ተሸክሞ ይመጣል ... በጥበብ ጨዋታ ... ጥይት ከኢጣሊያ ካምፕ ወደ አርበኞች ኮሮጆ ይጠራቀማል።

አርበኞች ሁልጊዜ የኢጣሊያ ምሽግ ላይ ትንሽ ከተኮሱ ከጠላት ወገን ተኩሱ ይቀልጣል ... የዚህ ፋይዳው ደግሞ ራሽኑ የማይበቃው የኢጣሊያ ሰራዊት ሃያ ጥይት ከተኮሰ ሰላሳ፤ ሰላሳ ጥይት ከተኮሰ ሃምሳ እያለ አባዝቶ ይናገርና ትርፉን ጥይት ለአገሬው መሸጡ ላይ ነው - ለውሃው፤ ውሃው ለአሶች ምግባቸውን ያቀርባል! ስለዚህ ለአርበኞች የመሳሪያና ጥይት ጥገቱ ራሱ የኢጣሊያ ሃይል ነው። ይህን ሃይሉን ተማምኖም ነው ነፃዋን አገር፣ ሉዓላዊነቷን አውቃለሁ ብሎ ላይደፍራት የመተማመኛ ስምምነት የፈረመላትን ኢትዮጵያን የወረረው። ትጥቅና ስንቅ የሌለው የኢትዮጵያ አርበኛ የአገር ፍቅሩንና ወኔውን ይዞ ጫካ ገባ። ከዚያ የኢጣሊያን ጠመንጃ እየቀማ፣ ጥይቱን እየወሰደ ተሸክሞት በሄደው መሳሪያ መልሶ አጠቃው።

ሶስተኛው የእነ ጃገማ ጥይት የማግኛ ዘዴ ደግሞ በቅሎና አህዮችን መግደል ነው። የኢጣሊያ ሰራዊት ለአስሳም ሆነ ለግዳጅ መንገድ ለቆ ጀልዱ፣ ግንደበረት ኢያ... ሲሄድ ገደላማ ቦታ ላይ አርበኞች በደፈጣ ውጊያ ጥይት የሚጫንባቸውን አህያዎችና በቅሎዎች በጥይት ይመቷቸዋል። ያን ጊዜ በቅሎዎችና አህያዎች ተንከባልለው ገደል ይገባሉ። ኢጣሊያውያን ወደገደል ወርደው በበቅሎዎቻቸውና በአህያዎቻቸው ላይ ተጭኖ የነበረውን ጥይታቸውን ከመውሰድ ይልቅ ቀሪውን ለማትረፍ እየተታኮሱ ይሸሻሉ። ጃጌ-

ጃገማ ተጠባባቂ ቃፊር አቁሞ ያስጠበቀውን የጥይት ሳጥን ሌሊቱን ከጭነቱ አራግፎ ያስወስዳል። ያን ጥይት እየቆጠቡ ሌላ ተጨማሪ ጥይት ማግኛ እያደረጉ አርበኞች ከዕለት ወደ ዕለት ተደራጁ።

በጫካ ውስጥ በጃገማ የሚመሩት አርበኞች ውሎአቸው ጦርነትና ገበጣ ጨዋታ ብቻ አልነበረም። የአርበኞች መሪውን ጃገማን ጨምሮ በአርበኞች መካከል አንዱ የሚያውቀውን ለሌላው የማሳወቅ ባህል ነበር። ወጣቱን ጃገማን በለጋ ወጣትነቱ የአርበኞች መሪ ያደረጉት ከእሱ በዕድሜ የሚበልጡ ብዙ የህይወት ልምድ የነበራቸው አርበኞች ናቸው። መሪ አድርገው ጃገማን ለመቀበል ግን መስፈርቱ ዕድሜ፣ አካል፣ ልምድ አልነበረም። የመሪነት መስፈርቱ ኩሩነት ነው። እንደ አዋሽ ወንዝ ኩሩ መሆን። ኩሩነት ደግሞ ከጥሩ ሥነምግባርና ከራስ መተማመን የተገኘ እንጂ የእኩይ ባህሪና እብሪት ውጤት አይደለም። ጃገማ ገና ሲወለድ አባቱን አስፈነደቀ፤ የአባቱን በረከት ተቀበለ። የአባቱን ሃብትና ሰብዕና ወረሰ።

አንድ ጊዜ አንድ ከመሃል አገር መጥቶ ጃገማን የተቀላቀለ አርበኛ የአስራ ዘጠኝ ዓመቱን ወጣት የአርበኞች መሪነት ህሊናው አልቀበልልህ አለው። ይህ ሰው ጃገማን ጫካ ውስጥ ከሚያስተምሩት አንዱ ነው። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሩን፣ የሃይል አሰላለፉ መቀየሩን፣ የንጉሰ ነገስቱን ስደት፣በውጭ አገር ያደርጉታል የሚባለውን እንቅስቃሴ፣ የኢትዮጵያ አርበኞች ትግል መፋፋሙን ... ለጃገማ ከሚነግሩት ሰዎች አንዱ ነው። በኋላ ግን «ይሄ ጎረምሳ እንዴት የአርበኞች መሪ ሆነ?» ብሎ መብሰክሰክ ጀመረ።

አንድ ቀን አንዱን የአርበኞች ጀግና ኦሮሞ ጠጋ ብሎ ቅሬታውን ከገለጸ በኋላ «በዕውቀት የተሻለ ሰው ቢመራንስ?» ብሎ ጠየቀው። «ስለ አዋሽ ወንዝ ታውቃለህ?» አለው፥ አርበኛው። «አላውቅም» አለ። ሰውየው ትንሽ ተክዞ ቆየና እንግዲያው አንድ ተረት ላጫውትህ፤ ከዚያ የጠየቅኸኝን እመልሳለሁ» አለው። ጠያቂው ተጠያቂው ዙሪያ ጥምጥም መሄዱን ባይወድም ለማዳመጥ ፈቃደኛ ሆነ።

«በኦሮሞ አፈ ታሪክ የሚወራ አንድ ገጠመኝ አለ» ብሎ ትኩር ብሎ አየው። «አንድ ጊዜ አንዱ አፋፍ ላይ ቆሞ ከብት ሲጠብቅ እንበሳ፣ ዝሆን ... የገደሉ ጀግኖች እየፎከሩ፣ እየዘፈኑ ሲመጡ ህፃን አዋቂው፣ ሴቱ ወንዱ እየሮጠ ሲከተላቸው አየ። እሱም ከብቶቹን ለአንድ እረኛ አደራ ሰጥቶ ሄደና አዳኞቹን አጅቦ ቤተሰቦቻቸው በኩራት ሲቀበሏቸው፣ ቤታቸው ሲደምቅ፣





እልል ሲባል አይቶ ከተመለሰ በኋላ እልህ እየተናነቀው ለመሄድ፣ ለአደን በርሃ ለመውረድ ለራሱና ለዘመዶቹ ቃል ገባ።

«ከዚያ ምኞቱን ለማሳካት እንዲረዳው ጠመንጃ አነጋገብ፣ አልሞ አተኳኮስ፣ ሩጫ ... ተለማመደ። በዚህ ብቻ ሳያበቃ ግዳይ ወደጣሉት ቀዬ እየሄደ 'ለማደን ምን ማድረግ አለብኝ?' እያለ ጠየቀ። 'አልመህ መተኮስ ከቻልክ ቀሪው ብልጠትና ፈጥኖ የመወሰን ብቃት ነው' አሉት። 'ሌላስ?' ብሎ ብዙ ለማወቅ ለፋ። 'የአውሬ ዱካ ተከተል፣ ከለላ የሚሆንህ ጉድባ ወይ ግንድ ፈልግ ...' ተባለ።

«በቂ ዕውቀት ማግኘቱን ሲያረጋግጥ ከአዳኞች ጋር በርሃ ወረደ። ከዚያ አውሬ እንዴት መታደን እንደሚገባው፣ አንድና ሁለት ክንድ የሚረዝም ቀንድ ስላላቸው አጋዘኖች፣ ጎሽ በቀንዱ ወግቶ በምላሱ ልሶ ስለገደለው ሰው፣ ስለ አንበሳ ባህሪና አንበሳ ስለሚገኝበት አካባቢ፣ ጥሩ ማደኛ አልባንና መውዜር ጠመንጃ መሆኑን ... ምን አለፋህ! ስለ አደን አብረውት የሄዱትን አዳኞች እያወራ አፋቸውን አስከፈታቸው። ልባሞች ስለሆኑም ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ከጨዋታው ብዙ ዕውቀት አገኘ ...

«አንድ ቀን ታዲያ ያ ሰው በቅርብ እርቀት ሜዳውን የሞላ ሸንጣም ጎፈር አንበሳ አየ። አንበሳውን እንዳየ ግን ወዲያው መሬት ላይ የሆነ ነገር ይፈልግ ጀመር» ብለው ጨዋታቸውን አቆሙት።

«ከዚያስ? ከዚያ በኋላ ምን ሆነ?» አላቸው - በጉጉት።

«ከዚያማ የራሳቸውን ግዳይ ጥለው እሱ ቀንቶት አውሬ እስኪገድል ሲጠባበቁት የሰነበቱት አጠገቡ የነበሩ አዳኞች 'ምን ሆነ?' ብለው እርስ በርስ በምልክት ሲነጋገሩ ቆዩና 'አንበሳውን አልመህ አትገድለውም፤ አቀርቅረህ ምን ትፈልጋለህ?' ሲሉት 'ልተኩስ ነው፤ ከዚያ በፊት ግን' ብሎ ዝም አለ። 'ከዚያ በፊት ምን?' አለው አንዱ ከመሃል። 'ከዚያ በፊት ዱካውን ፈልጌ ላግኝ ብዬ ነው' አላቸው። በሳቅ ፍርስ አሉ አዳኞቹ። አንበሳውም ድምፅ ሲሰማ ወደ ጫካ እጥፍ ብሎ ተሰወረ። አዳኞችም ጓዛቸውን እየሸከፉ 'በል እንሂድ! ማደን የአንተ ገድ አይደለም፤ ማውራቱ ነው የሚያምርብህ' ብለው ወደ ቀያቸው ጉዞ ጀመሩ። እሱም ሲዘፍኑ፣ ሲያቅራሩ ፈንጠር ብሎ እየሰማ ወደ ቀየው ተመለሰ፤ ህዝቡም እንደተለመደው ግዳይ የጣሉትን እልል ... እያለ ተቀበላቸው» አለውና ዝም ብሎ አስተዋለው። ጠያቂው ነገሩ ገባው፤ ነጭ ላብ ግንባሩ ላይ ችፍፍ አለ ...

ሰውየው ጠበቀው፣ ጠበቀውና «ጥያቄህን ደግመህ ባለመጠየቅህ ጀግናና አዋቂ ሰው ነህ» ብሎት ሄደ፡፡ ያ ሃሳብ ከወጣቱ የአርበኞች መሪ ከጃገማ ጆሮ አልደረሰም፤ ከዚያች ቀን በኋላ ግን ጃገማን ሲያስብ አዋሽን፤ ጃገማና አዋሽን ሲያስብ እውቀትን ወደ ተግባር ስመለወጥ መወሰን በሚገባበት ሰዓት ወደኋላ የሚያየውን አዳኝ እያሰበ ለጃጌ ጃገማ ያለው አክብሮትና ፍቅር ጨመረ ...

* * *

ጥቅምት 9 ቀን 1933 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ሰላሳ የኢጣሊያ ቸራኖ መኪና እንጨት የሚጭን መስሎ ወደ ጭልሞ አለፈ፡፡ በቸራኖው ውስጥ ግን የኢጣሊያ ወራሪ ወታደሮች በፀጥታ ተገጥግጠዋል፡፡ እነዚያ ወታደሮች አካባቢውን የሚያውቅ መሪ ይዘው እነ ጃገማ ወደነበሩበት ሰንጎታ ተራራ በጥንቃቄ ወጡ፡፡ ሰንጎታ ላይ ጃገማ፣ ዘውዴን ጨምሮ አስራ ሰባት አርበኞች ብቻ ነበሩ አብረውት የነበሩት፡፡ ከሶስት መቶ ሃምሳ የሚበልጡ የኢጣሊያ ወታደሮች ጃገማ ሊኖርበት ይችላል የተባለውን መንደር በጠቋሚ ከበቡ፡፡ ጃገማ አብረውት ከነበሩት ጥቂት አርበኞች ጋር እንደሆነ መከበቡን አረጋገጠ፡፡ ባንዳዎቹ ከብትና ንብረት እየዘረፉ አሰሳ በማድረግ እነ ጃገማ ወደአሉበት ተጠጉ፡፡ ጎፈሪያም አርበኞች ደግሞ ጃገማን ትክ ብለው አዩት፤ ተረጋግቶ አያቸው፡፡ «የጠላት ቁጥር ብዙ ነው፤ እኛ ደግሞ ትንሽ ነን ምን እናድርግ?» ብለው እያንሾካሾኩ ጠየቁት፡፡ ጃገማ በምልክት በግራና በቀኝ የሚያጠቁትን መደበ፤ እሱ ከመሃል ሆነ፡፡ የጠላት ወታደሮች የሚዘርፉትን ከብትና ንብረት ሲያሸሹ እ...ኞች ደግሞ ወደ አርበኞች ይበልጥ ተጠጉ፡፡

አርበኞቹ የጃገማን ትዕዛዝ እየተጠባበቁ ነው፡፡ ድንገት ጃገማ የጀምሩ ምልክት አሳይቶ ከአደፈጠበት ዘሎ ታየና በመትረየሱ የተኩስ እሩምታ ሲከፍት የኢጣሊያ ሰራዊት አንበሳ እንዳየ ሚዳቋ እየዘለለ በየአቅጣጫው ፈረጠጠ፡፡ እነ ጃገማ በለመዱት ጫካ እንደ እውሬ እየተሹለከለኩ ጠላትን እያባረሩ የዘረፈውን ንብረትና ከብት አስጣሉት፡፡ ስድስት የባንዳ ወታደሮች ገደሉ፤ ሰባት አቆሰሉ፡፡ ስድስት ጠመንጃም ማረኩ፡፡ እስከ አፍንጫቸው የታጠቁ ሶስት መቶ ሃምሳ የጠላት ስልጡን ወታደሮች በአስራ ሰባት አርበኞች ጀግንነት ጊንጪ ድረስ ተባረሩ፡፡

ጃገማ በሁለት ቀን ውስጥ ሁለት ጊዜ አይበገሬነቱን አረጋገጠላቸው - አንዴ ገበያተኞችን ከዘራፊዎች ያስጣለ እለት ብቻውን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአርበኞቹ ጋር በመሆን፡፡ የጃገማ ጀግንነት እንደ ተራራ ገዘፈ፡፡ ፍጥነቱንና ቅልጥፍናውን፣ ተኩሶ አለመሳቱን ... ያዩ ሁሉ ወሬውን አዛመቱት፡፡





የአካባቢው ሰው ደግሞ የጃገማን ቅድመ አያት ጀግንነት ሶስት መቶ ሰው ገድሎ ህዝቡን ጨረስህ ጦርህን ጣልልን መባሉን፣ ጦሩን ሲጥል አንድ ሌባ ወግቶ መግደሉንና እንደገና ጦሩን አንስቶ ከፊቱ የሚቆሙትን ጠላቶቹን ሁሉ የፈጀ መሆኑን፤ ጃገማም ልክ እንደ ቅድመ አያቱ ሳተናና አንበሳ መሆኑን እየተናገሩ በጠላት ካምፕ የተነሳውን ፍርሃት አባባሱት፡፡

ጃገማ የጠላትን ጦር እንደ በሰለ ፓስታ አልፈስፍሶና ካምፓቸውን ቀውጢ አድርጎ በጥቅምት ወር አርበኞቹን ይዞ ወደ ስሙ-ጥሩው የአርበኞች መሪ ደጃዝማች ገረሱ ዘንድ የወሊሶ መንገድን ተሻግሮ ሄደ፡፡ ጃገማና ገረሱ ሃይላቸውን አቀናጁ፡፡ ይህን የአላወቀው የኢጣሊያ ሰራዊት የደጃዝማች ገረሱን ሃይል ለማጥቃት ያለ የሌለ ሰራዊቱንና ሃይሉን አሰልፎ ውጊያ ከፈተ፡፡ ውጊያው ተካረረ፤ ምድር ቀውጢ ሆነች፡፡ የማታ ማታ ድል ለአርበኞች ሆነ፡፡

ጀግናው ደጃዝማች ገረሱ «አንተን የመሰለ ጀግና የወለደች እናት ቺባረክ...» ብለው ለጃገማ አይበገሬነት ከጀግና ለጀግና የሚገባውን አድናቆት ገለፁ፡፡ ጃገማም በደጃዝማች ገረሱ ወኔ፣ የአገር ፍቅር፣ የአመራር ብልጠትና እተኳኮስ ተደንቆ ነበር፡፡ የዚያን ጊዜ የጦር መሪዎች እንደ አሁኑ ከኋላ ሆነው የጦር ስልት የሚያወጡና የሚያዋጉ አልነበሩም፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩት የኢትዮጵያ አርበኛ መሪዎች የጦርነት ችቦውን የሚለኩሱት፣ በጠላት ላይ ቀድመው የጨበጣ ውጊያ የሚጀምሩት እነሱው ናቸው፡፡ ተከታዮቻቸው የእነሱን ፈለግ እያዩ ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ ተብለው የሚሞገሱ ተርቦች ናቸው፡፡

* * *

አንድ ጊዜ ወሎንኮሚ ላይ በወጣቱ የአርበኞች መሪ በጃገማ የሚመሩት አርበኞችና የኢጣሊያ ወራሪ ጦር የፊት ለፊት ውጊያ ሲያደርጉ ዋሉ፡፡ በነጋታው የኢጣሊያ ጦር ተመልሶ መምጣቱ እንደማይቀር የተረዳው ጃገማ አርበኞችን በመያዝ ጀምጀም ወንዝን ተከትለው ወደ ወሎንኮሚ ግንባር በመሄድ ውጊያ እንዲያደርጉ የቀኝ መሪውን ዘውዴ ጥላሁንን፣ የግራ መሪውን ጠንቋሳ ኬሎን አዘዘ፡፡ ጃገማ ራሱ ደግሞ ከሐሮታ ምሽግ ትይዩ ካለው ዮብዶ አፋፍ ላይ ሰላሳ አርበኞችን ይዞ ወጥቶ ከሐሮታ ምሽግ ውስጥ የነበረው አንድ ሺ አምስት መቶ የኢጣሊያ ወራሪ ጦርና ስምንት መቶ ፈረሰኛ ከኋላ በዮብዶ በኩል መጥቶ የአርበኞችን ጦር እንዳይቆርጥ በማድፈጥ መጠባበቅ ጀመረ፡፡

ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ አርበኞችና የጠላት ጦር ውጊያ ጀመሩ:: ውጊያው እያየለ፣ እየተጠናከረ ቀየ:: በኋላ ጋጂ ያለው የኢጣሊያ ወራሪ ሃይል ለእርዳታ ወደ ወሎንኮሚ ሲንቀሳቀስ ጃገማ በጦር ሜዳ መነፅሩ ተመለከተ:: አርበኞችን ሊቆርጥ ይችላል ተብሎ የተገመተው የጠላት ጦር ግን መንገዱን ተከትሎ ወደ ጀምጀም ወንዝ ድልድይ አመራ:: ከዚያ አንድ አጋዥ የጠላት ጦር ተጨምሮ የጀምጀምን ተረተር እየተከተሉ የአርበኞችን ጦር ለመቁረጥ ውጊያ ቀጠሉ:: ጃገማ እሱ ከሚመራቸው አርበኞች ጋር የተቀላቀሉትን ቀኛዝማች አብርሃ መሸሻን ከሰባት አርበኞች ጋር እንዲቆዩ አደረገ:: ሌላ አጋዥ የጠላት ጦር ከአምቦ ከመጣ ሰው ልከው እንዲነግሩት አብርሃን አዘዘና ሃያ ሶስት አርበኞችን ከኋላው አስከትሎ ጀምጀም ውስጥ የገባውን የጠላት ጦር ለመምታት ፈረሱን ኮልኩሎ ሸመጠጠ::

የጃገማ ሃሳብ ከዮብዶ አፋፍ እየጋለበ የሄደው የጠላት ጦር የጀምጀም ድልድይን እንደተሻገረ ከኋላ ካለችው ጉብታ ላይ ሆኖ ለመውጋት ነበር:: ጃጌ ጃገማ መትረየሱን ፈረሱ ላይ አጋድሞ ብቅ ሲል ግን ያሰባት ቦታ ቀይ ኮፍያ ያደረጉ የኢጣሊያ ጦር ወታደሮች ተገጥግጠው ደፈጣ አድርገው ተኝተውባታል:: ስለዚህ የአርበኞች መሪ ወጣቱ ጃገማ ብቅ ሲል ተኩሱን ሲያንጣጡት የጃገማ አባ ዳማ ፈረስ በሶስት ጥይት ተመትቶ ዘፍ አለ:: ጃገማም ወደቀ:: ከወደቀበት እንዳለ እጁን፣ እግሩን ... ተመትቻለሁ ብሎ ደባበሰ:: ያ ሁሉ የጥይት ውርጅብኝ ዘንቦ ጃገማ አልተመታም:: አለመመታቱን ሲያውቅ ሳብ ብሎ ከፍ ያለች ቦታ ላይ ሆኖ ቁልቁል ሲያይ በሥነ ልቦና የተሸነፈው የጠላት ጦር እግሬ አውጭኝ እያለ ይሸሻል:: ጃገማ እየተገረመ መትረየሱን ጎትቶ ጠመደና የሚሸሸውን የጠላት ጦር ይተገትገው ጀመር:: ከኋላ በእግር ይከተሉ የነበሩት አርበኞችም ደረሱለት::

ጃጌ ጃገማ የሚሸሸውን የጠላት ጦር እያነጣጠረ ሲለቅም አንዲት ጥይት አፈሩን ጭራ ጭርር ስትል አያት:: ያች ጥይት ለጥቂት መሬቱን ባትመታ ኖሮ ደረቱን ትመታው ነበር:: ትክ ብሎ ሲያይ አጠገቡ ከነበረ ጉቶ ስር ጠመንጃ ውልብ ሲል ታየው:: ለካ በቅርብ ርቀት የነበሩ የጠላት ወታደሮች እያነጣጠሩ ይተኩሱባቸው ኖሯል:: ዝናር ሙሉ ጥይቱን፣ መውዜርና አልቢን ይዘው ከሚከተሉት ጋሻ ጃግሬዎች አንዱን «ስጠኝ፤ ስጠኝ ጠመንጃዬን» ብሎ ተቀብሎ ጃጌ ጃገማ አነጣጥሮ ሲተኩስ ጉቶውን ፈለጠው:: ያን ጊዜ ሶስት የኢጣሊያ ወታደሮች እንደ ሚዳቋ እየዘለሉ ሲሮጡ ሶስቱም እየተመቱ ወደቁ::

ከዚያ ወጣቱ የአርበኞች መሪ ስድስት የውሃ፣ አስራ አምስት ሌጀራ መትረየሶችን ጠምደው የቀኝ መሪውን ዘውዱ ጥላሁንን አቁሰለው አርበኞችን





ሲያስጨንቁ የዋሉትን የጠላት ወታደሮች ለማስለቀቅ ከወሎንኮሚ በላይ ያሉትን የቱሉ ኮራ ኮረብቶችን ለመያዝ ወጣ:: መሬቱን የሚያርሰው መትረየስ አላንቀሳቅስ ቢላቸውም ጃገማና አንድ አርበኛ ብቻ እንደምንም በተአምር ቱሉ ኮራ ላይ ወጡ:: ከዚያ ጃጌ ጃገማ መትረየሱን ጠምዶ ሲያርከፈክፍባቸው መትረየስ ተኳሾቹ በሙሉ ነቅለው ሸሹ:: ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት የጀመረው ውጊያ የሰላሳ አርበኞች ህይወት ተከፍሎ፣ ከጠላት ወገንም እጥፍ ሰው አልቆ በአስራ አንድ ሰዓት ተጠናቀቀና ድል ለአርበኞች ሆነ::

ከድሉ በኋላ ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጃገማና አርበኞቹ አሸንፈናል ብለው ሲመለሱ ጠላት መድፍ ተኮሰባቸው:: መድፉ ከጃገማ ታላቅ እህትና ከተከተሏት ሴቶች አልፎ ወደቀ:: ሌንሴ በወላፈኑ ተገፍትራ ወደቀችና ራሷን ሳተች:: ጃገማ እንደ ግስላ ተቆጣ:: «ወይኔ ጃገማ! እህቴን ተነጠቅሁ ...» ብሎ ላይዋ ላይ ወደቀ:: ነፍሷ እንዳልወጣ ሲያውቅ ወደ ጠላቶቹ አቅጣጫ ሮጠ ... አርበኞች ተከተሉት፤ ምድር ቁና ሆነች:: ጃገማ ሌንሴ ላይ የተኮሱትን እስኪያባርር ነፍሱን አያውቀውም ነበር:: ከዚያ አደብ ገዛ:: የተረጋጋው፣ ትዕግስተኛውና ፈገግተኛው ጃገማ ጠላት ላይ ባገኘው ድል ተጽናንቶ ወደ እፎቱ ተመለሰ:: ሌንሴ ለጃገማ እህት ብቻ ሳትሆን እናቱም ነበረች፤ እህትና እናቱ ብቻም ሳትሆን አጋርና መከታውም ነበረች::

* * *

ከሁለተኛው የወሎንኮሚ ጦርነት በኋላ በቅበላ ሰሞን የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በእነሱ አጠራር 'ሽፍቶች' የሚሏቸውን ጃገማንና በእሱ የሚመሩትን አርበኞችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ አስራ አምስት ሺህ የኢጣሊያ ሰራዊት ከጀምጀም ወንዝ ጀምሮ አንቀሳቀሰ:: የጠላት ጦር ያለ የሌለ መሳሪያውን አንግቦና አቅድ አውጥቶ የማጥፋት ዘመቻውን አርበኞች ይገኙባቸዋል ባላቸው አካባቢዎች ሁሉ አሰሳ በማድረግ ጀመረ:: በዚያ አሰሳ እንደተሰመደው የአካባቢ ሰዎች፣ ህፃናትና ሴቶች በፍርሃት እንዲርዱ ተደረገ:: ቀኑን ሙሉ አሰሳው ቀጠለ ... የአካባቢው ገበሬዎች አርበኞች የሚገኙበትን ቦታ «ጠቁሙ» እየተባሉ በስደፍ ተደለቁ፤ ተገረፉ:: ነዋሪው በእሪታና በለቅሶ በወራሪው ሰራዊት ላይ ምሬቱን ሲገልጽ ዋለ:: አርበኞች ግን የውሃ ሽታ ሆኑ::

ከቀኑ አስር ሰዓት ላይ የኢጣሊያ ሰራዊት ሲያስስና ሲዳክር ውሎ ተዳከመ:: ከዚያ ወደተዘጋጀው የማደሪያ ሰፈር ሄደው ዘብ አቁመው ከተመዳደቡ በኋላ ለዘረፋ ከመውጣታቸው በፊት ድንገት የበጋ መብረቁ

የአርበኞች ጦር በመሪው በጀግናው ጃገማ እየተመራ ከሰማይ ይምጣ ከምድር ሳይታወቅ ዱብ አለና እንደ ውሃ አዙሪት ሲሽከረከር በዋለው የጠላት ጦር ላይ የተኩስ እሩምታ ለቀቀበት:: የኢጣሊያ ወታደር በደመነፍስ ተደነባበረ፤ አዛዦች አመራር መስጠት ተሳናቸው:: ከኢጣሊያ ጦር በኩል ገሚሱ ምሽግ ሲቆፍር ቀሪው ደግሞ አፀፋ ተኩስ እየተኮሰ ተኩሱ ለሰዓታት ቀጠለ:: ፀጥ ያለ ሲመስል ደግሞ አርበኞች እሩምታ ተኩስ ተኮሱ:: የኢጣሊያ ጦር ጥይቱን ሲያንጣጣ ጃገማና አርበኞቹ የወራሪው ጦር ራቱን ሳይበላ ሌሊቱን አይኑን አፍጥጦ እንዲያድር አድርገውት የአንድ ቀን መንገድ ሄደው ቆሎአቸውን ቆረጣጥመው፣ ውሃቸውን ተጎንጭተው ተኙ::

የኢጣሊያ ጦር ቀን ቀን በሚያስገባው እየገባ፣ በማያስገባው እየተኮሰ እያሰሰ፣ በአስር ሰዓት ደግሞ ማደሪያው ቦታ ይሰፍራል:: የበጋ መብረቆችም ድንገት ከች ይላሉ:: ጠላት ምሽግ ይቆፍራል፤ ይታኮሳል:: አርበኞች የጠላትን ጦር እንዲህ እያሸበሩ ሽቅብ ሲስቡ ቆዩና በአስራ አራተኛው ቀን ከጀምጀም የጀመረው አሰሳ ግንደበረት አፋፍ ላይ ጮቢ ደረሰ::

ወጣቱ የአርበኞች መሪ አልመው የተኮሱት መሬት ጠብ የማይለውን የፌይሳ ነገሮን ልጆች፤ ናታቴን፣ ድርብሳንና ታደሰን እንዲሁም ከእነሱ ጋር የነበሩትን አራርሶ ጅማን፣ አያና ኢዳንና ሌሎችንም «እኛ አርበኞች አስራ አራት ቀን ሙሉ እኛን ፍለጋ አሰሳ እያደረገ የሚዳክረውን የጠላት ጦር በዘዴ ስበን፣ ስበን ግንደበረት አፋፍ አድርሰነዋል፤ ከእንግዲህ ያለው ቀሪ ጥቃት የናንተ ነው» ብሎ በማስተባበር መላው አሳምኖ ወደ ላይ ተመለሰ::

ወደ ግንደበረት አፋፍ ጮቢ ለመግባት ኢያ የሚባል መንደር አለ:: ኢያ ጎንጋ አንድ አንድ ከብትና ሰው ብቻ የሚያልፍበት ገደላማና ጠባብ መንገድ ነው:: የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ያን ቦታ ለማለፍ አንድ ቀን ሙሉ ይፈጅበታል:: በጃገማ መልዕክት መሰረት ለአስራ አምስት ቀን አሰሳ ላይ የከረመውን የጠላት ጦር የፌይሳ ነገሮ ልጆች ግራና ቀኝ ካለው ጋራ ላይ ወጥተው ኢያን ለማለፍ እንደተኮለኮለ ተኩስ ከፍተው እንደ ደረቀ ቅጠል አንጠባጠቡት:: አሰሳ ያደርግ የነበረው የጠላት ጦር መግቢያ መሄጃ ሲያጣ ወደኋላ መሸሽ ጀመረ::

አሰሳው ሲጀመር በአንደኛው የዓለም ጦርነት የተካፈለ የኢጣሊያ ጦር አባል ጭልሞ ያለውን መግቢያ መንገድ ከሶስት ጣሊያኖች ጋር ሆኖ ሲያሰራ የጃገማ አርበኞች ደፈጣ አድርገው ሁለቱን ገድለው እሱን ማረኩት:: ሽማግሌው የኢጣሊያ ወታደር ጎፈሪያማ አርበኞቹን ሲያይ ከጥፍር እስከ





ራሱ በፍርሃት ተንቀጠቀጠ:: ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጃገማ ምርኮኛውን ኢጣሊያዊ ሊገድሉት መሳሪያ የደገኑትን አርበኞች «ተዉ» ብሎ ከአርበኞቹ ጋር ወደ ጫካው ተመለሰ:: ማታም አርበኞች ቆሏቸውን እየቆረጠሙ፣ ውሃቸውን ሲጎነጩ ... ጃገማ ለኢጣሊያዊው ምርኮኛ ቂጣ ተጋግሮ እንዲሰጠው አድርጎ ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው የተገደሉባቸውና ቤታቸው በጣሊያኖች የተቃጠለባቸው አርበኞች ሌሊት እንዳይገድሉት ጃገማ አጠገቡ አስተኛው::

የተማረከው የኢጣሊያ ወታደር ለግላጋውን የሃያ ዓመት የአርበኞች መሪ እንደ ልጅ አስር እስሩ ሲሄድ አስተዋለው:: አንድ ቀን ጃገማ አባ ዳማ ምርኮኛውን አስቀምጦ አምስት መቶ የሚደርሱ አርበኞቹን አንዴ በሶስት፣ አንዴ በአራት፣ አንዴ በአምስት እየደጋገመ እያሰለፈ ለአንድ ሰዓት ተኩል 'የአርበኞችን ብዛት' አሳየው:: «አየኸው አይደል! እኔ ጃገማ ይህ ሁሉ ጦር አለኝ፤ በዚህ ሃይሌ ከፈለግሁ የኢጣሊያን ጦር ልደመስሰው እችላለሁ» አለው::

የፌይሳ ነገሮ ልጆች ኢያ ላይ የኢጣሊያን ወራሪ ጦር ሲያራውጡት ወደኋላ የሚሸሹትን የኢጣሊያ ወታደሮች ለኢጣሊያው ምርኮኛ እያሳየው ደግሞ «እያቸው፤ የኢጣሊያ ወታደሮች ቤት ከማቃጠል፣ አሮጊትና ህፃናትን ከመግደል በስተቀር ይኸውልህ የእኛን ጦር እያዩ ዝም ብለው ነው የሚያልፉት» አለው::

ጃገማ ምርኮኛውን ቢለቀው የአየውን ሁሉ ለጣሊያኖች እንደሚነግር ተረድቷል:: ይሁን እንጂ ዝም ብሎ ቢለቀው ምስጢሩ ሊገባው ስለሚችል ወታደሩን «እኔ ልለቅህ እችላለሁ፤ የምለቅህ ግን ለጥይት መግዣ የሚሆነኝ አስር ሺ ሊሬ ከከፈላችሁኝ ነው» ብሎ ከምርኮኝነቱ የተለቀቀበት ምክንያት የገንዘብ ክፍያ ነው ብሎ እንዲያስብ አደረገው:: ይህን ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ ጃገማ የአገሬው ሰው በተለምዶ ፋናንስ ለሚለው ኢጣሊያዊ መልዕክት ላከበት:: ፋናንስ ከኢጣሊያ ወረራ ሶስት አራት ዓመታት ቀደም ብሎ ጅባትና ሜጫ አውራጃ ውስጥ የኖረ ነው:: ጅባትና ሜጫ አውራጃ ውስጥ ጀምጀም፣ ጋጅ፣ ጫንጮ፣ ግርፌጣ፣ ጭልሞና በጅሮ በሚባሉ ቦታዎች ስድስት የእንጨት መሰንጠቂያዎች ነበሩ:: እነዚህ ከጀምጀም እስከ ጅሮ የተቋቋሙት የእንጨት መሰንጠቂያዎች የሚገኙት አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ብቻ በነበረው ደን ውስጥ ነው::

የመጀመሪያውን የእንጨት መሰንጠቂያ ጀምጀም ላይ የከፈቱት ሙሴ ኢሻሌት ናቸው:: ፋናንስ እንደመጣ ስራ የጀመረው ግርፌጣ የእንጨት

መሰንጠቂያ ውስጥ ነው። ጃገማ ፋናንስን የሚያውቀው ገና ልጅ ሳለ ነው። የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ወደ አካባቢው ከመጣና ጃገማም አርበኛና የአርበኞች መሪ ከሆነ በኋላ ፋናንስ ከግርፌጣ ወደ በጅሮ እንጨት መሰንጠቂያ ተዛወረ። ፋናንስ የኦሮምኛ ቋንቋ ተምሮ እየተናገረ የኦሮሞ ሚስትም አግብቶ ነው ከህዝቡ ጋር አብሮ የኖረው። እንዲያውም የአርበኞችን መሪ ሻለቃ ጃገማን ፈቃድ ጠይቆ ስለፈቀደለት ፋናንስ ወደፈለገው አካባቢ ሁሉ ብቻውን ፈረሱን እየጋለበ በነፃነት ይንቀሳቀስ ነበር።

ፋናንስ ለአርበኞች ልብስ፣ ወይን ጠጅ ከአዲስ አበባ እየወሰደ ይጠቅማቸው ነበር። ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጃገማም አርበኞቹን አዲስ አበባ ልኮ ጥይት ያስገዛል። ጥይቱ በፍራሽ ውስጥ ከሳር ጋር ጥቅጥቅ ተደርጎ ተሰፍቶ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ፋናንስ መኪና ላይ ይጫናል። ከዚያ አርበኞቹ ኬላውን በእግር ያልፉና በፋናንስ መኪና ወደ ደኑና ሽንተረራቸው ይመለሳሉ። የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ኢትዮጵያን ለቆ ከወጣ በኋላ ጃገማ የፋናንስን እርዳታና ትብብር በመመስከር የኢትዮጵያ መንግስት ዜግነት እንዲሰጠው አድርጓል።

ጃገማ ወዳጁን ኢጣሊያዊ ፋናንስን አስጠርቶ «የኢጣሊያውን ምርኮኛ ለመመለስ የጋጂው የኢጣሊያ ጦር አስር ሺ ሊሬ እንዲከፍለኝ ጠይቅልኝ» ብሎ ጠየቀው። ፋናንስ የጃገማን ጥያቄ ለጣሊያኖች አቅርቦ ሃያ ሺህ ሊሬ ሰጡት። አስር ሺውን ለጃገማ ሰጥቶ፤ አስር ሺውን ደግሞ ወደ ኪሱ ከቶ ምርኮኛው ከኢጣሊያ ሰራዊት ጋር ተቀላቀለ። ከዚያ ቀን በኋላ ምርኮኛው ለአዛዦቹ «እናንተ ምን ጦር አላችሁ? ጦር ያለው ጃገማ ዘንድ ነው። የእናንተ ጦርም የአርበኞችን ጦር እያየ ነው የሚያልፈው» እያለ ማስረዳት ጀመረ። የምርኮኛውን አስተያየት የጠላት ጦር ቢቀበለውም የጠላት ጦር አዛዦች ግን ሽማግሌውን የጃገማ ምርኮኛ «የአበደ ወሬኛ ነው» ብለው አዛወሩት።

* * *

ጃገማ በአርበኝነት ዘመኑ እጅግ የሚያደንቃቸው ሴቶች ሁለት ናቸው። አንዷ እህቱ ሴንሴ ስትሆን ሁለተኛዋ ወ/ሮ ሽዋረገድ ገድሌ ናቸው። ሴንሴ ጊንጪ ጫካ ውስጥ ከአርበኞች ጋር ከተቀላቀለች ጀምሮ ከሃያ እስከ ሰላሳ የሚጠጉ ጠባቂዎች ወንድሟ ጃገማ መድቦላታል። መውዜር ጠመንጃ ለራሷ መጠበቂያ ትይዛለች። የእሷ ዋናው ተግባሯ ግን የአርበኞች እናት መሆን ነው - በዱር በገደሉ። አንድ አገልግል ነበራት፤ ሰላሳ እንጀራ ጢም አድርጎ ይይዛል። በጦርነት ወቅት አንድ በግ ታሳርድና ፈትፍታ በአገልግሉ





ትከተዋለች። በበቅሎ ይጫናል። ያን ይዛ አርበኞች በሚዋደቁበት አቀበትና ሽንተረር ትከታተላለች። አርበኞች በረሃብና ጥም ጥንዝል ብለው በየዛፉ ስር ጋደም ጋደም ሲሉ እህት ሴንሴ ዳጎስ ያለ አንድ አንድ ጉርሻ እየዞረች ታጎርሳቸዋለች። ከዚያ ነፍሳቸው ተመልሳ ወደ አፎቷ ስትገባ ቡረቃው፣ እንጉርጉሮው፣ ሽለላው፣ ዘፈኑ ... ይጀመራል።

የሴንሴ ሌላው ተግባሯ ደግሞ የቆሰለውን ማስታመም፣ የሞተውን መቅበር፣ የአርበኛውን ጎፈሬ ቅቤ መቀባትና ማበጣጠር ነው። ሴንሴን የሚረዱ ሴቶች እህት ሴንሴ የምታደርገውን እየተከተሉ አርበኛውን ይንከባከባሉ። አንዳንድ ጊዜ ሴንሴ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ ስትሆን ደግሞ ከአርበኞች ጋራ እየተሽሎከሎከች ትታኮሳለች።

ሁለተኛዋ ሴት ወ/ሮ ሽዋረገድ ገድሌ ጃገማ ኢጣሊያን ገልቦ እርቃኑን እንዲያስቀረው የረዱና በውስጥ አርበኝነት ታላቅ ጀብዱ የፈፀሙ ቆፍጣና አርበኛ ናቸው። ከኢጣሊያ ወታደሮች የሚያገኙትን የማጥቃት እቅድ እየተቀበሉ ለአርበኞች የሚያደርሱ፣ በከተማ ውስጥ ያሉ የውስጥ አርበኞችን በምስጢር የሚያስተባብሩ፣ ለአርበኞቹ ጠመንጃና ጥይት የሚያቀርቡና ስንቅ የሚያቀብሉ የተከበሩ ስመ-ጥር አርበኛ ነበሩ። ሽዋረገድ ገድሌ ለህይወታቸው ሳይሳሱ በየዱር ገደሉ የሚዋደቁትን አርበኞች ከመርዳት ቦዝነው አያውቁም።

እኒህ ሴት ጃገማ ከደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጋር የነበረውን ቆይታ አቋርጦ ለምሽግ ሰበራ በአስቸኳይ አዲስ ዓለም እንዲደርስ ያደረጉ ናቸው። ወይዘሮ ሽዋረገድ በኢጣሊያ ሰራዊት ምሽግ ቁልፍ ሚና የነበራቸውን ኢትዮጵያውያን አስተባብረው የጥቃት ኢላማዎችን፣ መግቢያ መውጫውን፣ የጠላትን መገኛና የመሳሪያ ግምጃ ቤቱን ለወጣቱ የአርበኞች መሪና አብረውት ለሚዋደቁት ጀግኖች ያሳዩና ጥቃቱ ከመፈፀሙ ጥቂት ሰዓታት በፊት አዲስ ዓለምንና የሞቀ ህይወታቸውን ጥለው የተሰወሩ ናቸው። እኒህ ወይዘሮ በኢጣሊያ ወራሪ ጦር ላይ ፅንፈኛ አቋም የነበራቸውና ግፍን እጥብቀው የሚጠሉም ነበሩ።

# ፮

## ሰይፍ አይፈሬው ጻጳስ

ንጉሰ ነገስቱ ስለተሰደዱበት ንግስት እንደሌለው የንብ መንጋ ይበተናል የተባለው ህዝብ እንደታሰበው ሳይበታተን ቀረ፤ ይልቁንም ጊዜ በአስነሳቸው አርበኞች ውስጥ ውስጡን እየተደራጀ ወራሪውን ጦር ለመመከት ተዘጋጀ። የኢጣሊያ ሰራዊት አዲስ አበባን ገና ለመያዝ ሲቋምጥ ደብረሲና ላይ፥ ያልጠበቀው ደፈጣ ውጊያ በባሻ ወልዴና ፊታውራሪ ተሰማ ባለሟሎች ተሰነዘረበት። ሚያዚያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም ደግሞ ስሙ-ጥሩ አርበኛ ሃይለማርያም ማሞ ደብረ ብርሃን መንገድ ላይ የኢጣሊያን ሰባት አርበኛ ካሚዮኖች አቃጥሎ ወደ መቶ አርባ የሚደርሱ የኢጣሊያ ወታደሮችን በመግደል የአርበኝነት ትግሉን ለኩሶ አንቦገቦገው።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የኢጣሊያ ንጉስ ወንድ ልጅ ወለደ ተባለ። ይህን «ደስታ» ለሁለተኛዋ የሮም ኤምፓየር ህዝብ ለማብሰር በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ላይኛው ግቢ (ገነተ ልዑል) ቤተ መንግስት ግራዚያኒ ማማው ላይ ቆሞ ዲስኩር ሲያሰማ የወራሪን ዕብሪት ለማስተንፈስ በዱር በገደል እየተዋደቁ የነበሩት አርበኞችና የውስጥ አርበኞች ባቀነባበሩት ስልት መሰረት አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ቦንብ ወረወሩበት። ግራዚያኒ መሬት ፀሐይን የምትዞርባቸውን ቀናት የሚደርስ ቁጥር ያለው የቦንብ ፍንጣሪ አካሉ ላይ ተሰግስጎ ተዘረረ። በዚህ ጊዜ የኢጣሊያ ወታደሮችን ጭካኔ ያረጋገጠው ጭፍጨፋ በጥይት፣ በአካፋና ዶማ ተጀመረ። በዚያ ጭፍጨፋ ቁጥራቸው ወደ 30000 የሚደርስ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ቀኑን ሙሉ በግፍ ተጨፈጨፉ፤ ቤታቸው ተቃጠለ። አዲስ አበባ በወራሪዎች ግፍና እብሪት በደም አበላ ተጥለቀለቀች።

ይህም አልበቃ ብሎ ግራዚያኒን በቦምብ ባቆሰሉት ላይ ክትትሉን አጠናከረ። አብርሃምና ሞገስ ግራዚያኒን አቁስለው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ለጥቃት ባዘጋጁት ታክሲ በመሄድ ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። «ኢትዮጵያን ለማሰልጠን ነው የመጣነው» የሚለው የኢጣሊያ ሰራዊት በአዲስ አበባ የጨፈጨፈው ሰው አንሶት በደብረ ሊባኖስ ገዳም የነበሩትን መነኮሳትን፣ ዲያቆናትንና መዘምራንን ገደለ። «የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን እማኞችን





በሙሉ ለማሰርና ለመፍጀት ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ። ለዚህም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ብቻ 358 የሃይማኖቱ ተከታዮች ተገድለዋል። ይህ ውሳኔዬ ለገናናው ለቢኒቶ ሙሶሊኒ በክቡርነትዎ በኩል ይቅረብልኝ ...» የሚል ቴሌግራም ጀኔራል ግራዚያኒ ወደ ኢጣሊያ በመላክ በእሱ ላይ ለተደረገው የግድያ ሙከራ የሺዎችን ህይወት እንደሚቀጥፍና ለእስር እንደሚዳርግ የሚገልጽ የወታደራዊ ጥቃት ስልት ለአለቃው አስተላለፈ።

በኢጣሊያ ጦር ሰራዊት አዛዥ ላይ በተፈጠረው የቦምብ ጥቃት ጦስ የጥቁር አንበሳ አባሎች በመሆን የኢጣሊያ ሰራዊትን ሲያራውጡ የተማረኩት የኢትዮጵያ ወታደሮች አብዛኞቹ እየታደኑ ተገደሉ። የኢጣሊያ ሰራዊት በተጠቀመው የመርዝ ጢስ ብዙ ወገኖቻቸው በማለቃቸው እጃቸውን ለኢጣሊያ መንግስት እየሰጡ ወደ ዕለት ኑሯቸው የተመለሱ መኳንንት፣ የጦር አዝማቾች፣ ባላባቶችም እጅ ስጡ እየተባሉ በግፍ ተጨፈጨፉ ... የኢጣሊያን የመርዝ ጢስ በመቋቋም የቆየውና ጎሬ የመሸገው ጦርም አዲስ ጥቃት ተሰነዘረበት። የጦሩ መሪ የነበሩት ራስ እምሩም ከጎሬ ሸሽተው ወደ ጅማ ሲጓዙ በጣሊያኖች ተማረኩ። የተረፉትም በግልና በቡድን ወደ ጎረቤት አገር ተሰደዱ።

በተለይም ማይጨው ላይ ፋሽስት ኢጣሊያ ለጊዜው ድል ማድረጉ ከተረጋገጠና ንጉሰ ነገስቱ የኢትዮጵያን ወረራ ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ በማቅረብ እገዛን ለማግኘት ባህር አቋርጠው ከሄዱ በኋላ በሰላሌ፣ ጊንጪ፣ ግንደበረት፣ ደብረ ብርሃን፣ ወዘተ. የኢጣሊያን ወራሪዎች ይፋለሙ የነበሩት አርበኞች ግፍ አንገሽግሿቸው በተቀላቀሏቸው ወገኖቻቸው ሃይላቸውን አጠንክረው በአዲስ አበባ የሚገኘውን የኢጣሊያ ጦር ሰራዊት ሃይል ሰብረው ለመግባት ወሰኑ። ያን ህብረት ለመባረክና የአርበኞችን ሞራል አጠንክሮ ወራሪውን እንዲደመስሱ ለማድረግ አቡነ ጴጥሮስ አዲስ አበባ መጡ።

በወቅቱ የኢትዮጵያ ችግር በነበረው የመገናኛ እጥረት ምክንያት የአርበኞች የጥቃት እቅድ ባለመሳካቱ በአርበኞች እጅ ሊገባ የነበረው ድል እንደ አሳ አሟልጮ ከመሃል እጃቸው ቁር ብሎ አመለጠ። ይህም በየግንባሩ ጥቃት ለመሰንዘር የመጡትን አርበኞች ወደኋላቸው እንዲያፈገፍጉ አደረጋቸው። አንድ መነኩሴ ግን «የመጣሁበትን ሳልፈጽም ወደ ኋላ አልመለስም» በማለት እምነታቸውን በመመከት ህዝቡን ለማስተማር ወሰኑ። ጥናቸውን ማበላሸት የፈለገው ፋሽስት ደግሞ ቤተመንግስት ውስጥ አሰራቸው።

ከዚያም ጳጳሱ የኢጣሊያን ገናናነት አምነው፣ የቪክቶር አማኑኤልንና የሙሶሊኒን ገዥነት ተቀብለው በሃይማኖታዊ ተልዕኮአቸው እንዲሰብኩ ተጠየቁ፡፡ ጥቂት ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከድተው በአድርባይነትና በጥቅም ለግፈኛው ጠላት ድጋፍ እንደሰጡ ሁሉ ጳጳሱም ጣሊያኖች የነገሯቸውን ተግባራዊ ቢያደርጉ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መሪነትን፣ የሰብከት ማስፋፊያ የሚሆን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሊሬ፣ የተንጣለለ መኖሪያ እንደሚሰጣቸው የሚያረጋግጥ የቃል መግባት ዜና ተንቆረቆረላቸው፡፡ ለጥቅም ያደሩ የእምነት አባቶችም ኢጣሊያውያን የሰጧቸውን ዕድል እንዲጠቀሙ ጳጳሱን ተማፀኗቸው፡፡

«የኢጣሊያን ገናናነት እንዳምን፣ የአማኑኤልንና ሙሶሊኒን ገዥነት እንድቀበል ነው የፈለጋችሁት?» ብለው መስቀላቸውን ጠበቅ ላላ እያደረጉ ጠየቁ፡፡

«... በትክክል!» አሉ ጣሊያኖች ስጋ ሲወረውር ለመቅሰብ እንደተዘጋጀ ውሻ እያለከለኩ ...

«እምነቴን ልተዋ ... መነኩሴነቴን ትቼ ቆቤን ላውልቃ፣ መስቀሌን ወርውሬ የእብሪታችሁ ጋሻ ጃግሬ ልሁና!» አሉ፥ ጳጳሱ - ልባቸው ስብር ብሎ፡፡

«ማመን ብቻ በቂ ነው፤ ከዚያ ስልጣኑ፣ ገንዘ...» ሲሉ ጳጳሱ ገሰጿቸው፡፡

«በቃችሁ! - በቃችሁ ... ይህች ክብሯን የደፈራችኋት አገር ለመሆኑ የሙሴ ጽላት መገኛ፣ የክርስቶስ ግማደ መስቀል ያለባት ... 'መኳንንት ከግብፅ ይወጣሉ ... ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች' የተባለላት ቅድስት አገር መሆኗን ታውቃላችሁ?! ይህች የቆማችሁባት ምድር ለእብሪተኞች ረመጥ፣ እንደ እሳት የምታቃጥል መሆኗን ብታውቁ ምን ያህል በሃዘን ጥርሳችሁ እየተፋጨ በተንገጫገጫችሁ ነበር! ግን ግብዝ ሆናችኋል፤ በሃይላችሁ ተማምናችኋል...

«እኔ የምፈራው የሰው ሰይፍ አይደለም ... የእናንተ ጉልበት፣ የእናንተ እብሪት ትንሽ ጉም ነው - ትንሽ ነፋስ የሚበትነው ... እና የፋሽስት ኢጣሊያን የበላይነት ከምቀበል ሞቴን እመርጣለሁ፡፡ ወደ እግዚአብሔር እጆቿን የዘረጋችውን ቅድስት አገሬን እብሪተኛ ሲደቀድቃት እንዲኖር አልፈቅድም፤ እምነቴም ይህን በፍፁም አይፈቅድልኝም...» አሉ፥ ጳጳሱ -





አምርረው፡፡ ይባስ ብለውም «እናንተ የኢጣሊያን ገዥነት የተቀበላችሁ ሁሉ አወግዣችኋለሁ፤ የኢጣሊያን ገዥነት ከተቀበለ እንኳን ሰው ምድሯ የተረገመች ትሁን» አሉ፥ አቡነ ጴጥሮስ - ጣታቸውን ቀስረው ሰማይ ሰማዩን እያዩ፡፡

ጄኔራል ግራዚያኒ በብስጭት እንደ እሳት ተንቀለቀለ፤ የኢጣሊያ መኮንኖች በንዴት ነፈሩ፡፡ «ውሰዱልኝ!» ብሎ ጮኸ ግራዚያኒ፡፡ ወዲያው አቡነ ጴጥሮስን ለጥብስ ለማድረስ አንድ ኢጣሊያዊ የመሃል ዳኛና ሶስት ኢትዮጵያውያን ተሰይመው፥ እንዲጠቀሙና ከሞት እንዲድኑ የቀረበላቸውን ፍስሃ አሽቀንጥረው የጣሉትን ጳጳስ እንደ ቀጠፉ፣ እንደ ሰረቁ፣ ግፍ እንደፈፀሙ፣ እንደ ገደሉ፣ እንደ ሸፈጡ ሁሉ በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ ወሰኑ፡፡

አቡነ ጴጥሮስ ለእውነት ሲሉ ተዋረዱ፤ ተደበደቡ፤ ደማቸው ፈሰሰ፤ ስጋቸው በጥይት ተበሳስቶ ደማቸው እንደ ጎርፍ እንዲፈስ ተወሰነ፡፡ በጳጳሱ የእምነት ፅናት ሁሉም ራሱን ለመፈተሽ ወደ ህሊናው ውስጥ ተንጎዳጎደ፡፡ የአገራቸውን ነፃነት ለማስመለስ በዱር በገደሉ ርሃብና እርዛት እያንጠራወዛቸው የሚታገሉትን የአላማ ፅናታቸው እንዲጠነክር መንፈሳዊው አባት በተግባር አስተማሩ፡፡

ሀብትና ዝናን ፈልገው አገራቸውን የከዱት፣ የፋሽስቶችን የበላይነት የተቀበሉትና «ሊያሰለጥኑን መጥተዋል» ብለው ለጣሊያኖች ያደሩት ሁሉ በአንገታቸው መቁጠሪያ፣ በእጃቸው መስቀል፣ በህሊናቸው የቅዱስ መጽሐፍ ቃል በያዙት አቡን ሞራላቸው እንደ መስታዋት ወድቆ ሲንኮሻኮሽ በዐይናቸው በብረቱ አዩት፡፡ ለራሱ ብሎ ደልሎ፤ በራሱ ቅጥፈት እብሪቱ የተጋለጠበት ፋሽስት ይዋል ይደር እንጂ በማንም ላይ የሚወስደው ግፋዊ እርምጃ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ጤና እንደሚነሳው ፍንትው ብሎ ታዬ፡፡

ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ ፓጂያሎ ስለ አቡኑ አሟሟት ሲገልጽ «ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. ከጥዋቱ አራት ሰዓት ግድያው ከሚፈፀምበት ቦታ ቀድመን ተገኘን፡፡ የሐበሻው ጳጳስ ጦር መሳሪያ በወደሩ የኢጣሊያ ወታደሮች ታጅበው መጡ ... እንደደረሱ ትልቅ ሰዓትና መጽሐፍ ቅዱስ አወጡ፡፡ ከዚያም መጀመሪያ ሰዓቱን ቀጥሎ መጽሐፍ ቅዱሱን አገለባበጡ» ይላል፡፡ ፓጂያሉ ሞትን አይፈሬው የእውነት መልዕክተኛ ያሳዩትን ቆራጥነት ሲገልጽ «'ዓይንዎን በጥቁር ጨርቅ እንዲሸፈኑ ይፈልጋሉ?' ተብለው ተጠየቁ» ይልና «እናንተ እንደፈለጋችሁ አድርጉት፤ እንደ እኔ ምርጫ ግን

የወራሪን፣ የእብሪተኛን ሞት ፊት ለፊት ገጥሜ ድል አድርጌ መሞት ስለምፈልግ ባትሸፍኑኝ ደስ ይለኛል» ብለው መመለሳቸውን ጽፏል።

ጳጳሱ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ እንዳዞሩ ስምንት ወታደሮች የመሳሪያቸውን አፈሙዝ ጳጳሱ ላይ አነጣጠሩ። ኮማንደሩ "ተኩስ" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ በአስራ አንድ ጥይት ተመትተው ከእንገታቸው በታች ሰውነታቸው ተበሳሳ። ይሁን እንጂ ለእምነቱበት ውሳኔ ሕይወታቸውን የሰጡት ጳጳስ ቢወድቁና ሰውነታቸው ቢበጫጨቅም ነፍሳቸው አልወጣችም። ኮማንደሩ ሽጉጡን ከአፎቱ በመምዘዝ በሶስት ጥይት ጭንቅላታቸውን መታቸው - ያኔ ህይወታቸው አለፈች።

ለእውነት የተሰዉት መንፈሳዊ መሪ ሬሳ ጨው ተራ እንደ ብቅል ተሰጥቶ ዋለ። ያን ቀን ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ ጮኸች! የአዲስ አበባ ሰማይ በግፍ ዳመና ተዋጠች! እንቅልፍ ከነዋሪዎቿ ርቃ ሄደች ... ኡኡታ ከጋራ ጋራ አስተጋባ።

አቡነ ጴጥሮስ በፅናትና ጀግንነታቸው የጠላታቸውን ህሊና በረጋግደው እውነቱን እንዲያይ አደረጉት! መቅረዙን ለኮሱት ... እሳቸው ግን በእውነት አደባባይ በተከሉት ሃውልት ለዘለዓለሙ በፅናታቸው ቆሙ። ይህም የኢትዮጵያን ጀግኖች ትግል እንደ ቋያ እሳት ይበልጥ እያንቀለቀለ በየቀየውና ሸለቆው በየአምባውና ተረተሩ እየተስፋፋ እንዲንቦገቦግ አደረገው።

የኢጣሊያን ጭካኔ ያዩት የኢትዮጵያ ጀግኖች ውርደትና ስቃይን ከእንግዲህ አናይም እያሉ «ኧረ ጥራኝ ዱሩ፣ ኧረ ጥራኝ ጫካው ...» በማለት ቤታቸውን እየዘጉ፣ ቀያቸውን እየለቀቁ የዱር አውሬ ሆኑ። ትግልን በአንድ ማዕከል መምራት በማይቻልበት፣ መገናኛ፣ በቂ መሳሪያና ስንቅ ባልነበረበት ፋኖ የሆነው አርበኛ በያለበት የየአቅሙን መስዋዕትነት ሲከፍል ንጉስ መልአከፀሐይ ኢያሱና ደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱ እንደ ነበልባላዊ ሰይፍ በሰሜን ኢትዮጵያና ምስራቅ ሸዋ ላይ ብልጭልጭ ብለው ተመዘዙና «እይዟችሁ! የተገፋ ያሸንፋል፤ የቆረጠ ከግቡ ይደርሳል ...» ብለው የአርበኞችን ትግል መስመር ለማስያዝ ብቅ አሉ።

«በማስተባበር ስም የመጣ ሁሉ የተባረከ ነው» በማለት አርበኞች ራሳቸውን ንጉስ ብለው የመጡትን የባተሌውን የልጅ እቤቶ ኢያሱን ልጆች ተቀበሏቸው። እንደ ፀሐይ እንቁስላሴና ከፈለው ወልደፃድቅ ያሉ ታላላቅ ሰዎች «ከጠቅል ሌላ ጌታና ሿሚ የለንም» ብለው ድንገት ብቅ ያሉትን ንጉስ





እንቀርብም በማለት ከመበርገጋቸው ውጭ ባላምባራስ አበበ አረጋይን ራስ፣ ልጅ ኪዳኔ ወልደኪሮስን ደጃዝማች፣ ጸሐፌ ትዕዛዝ ከበረን ከንቲባ ብለው በስልጣን እንበሸበሿቸው። «አገር ካለንጉስ ፋይዳ የለውም፣ አገር ሲኖር ንጉስ ይኖራል፤ አገር ከሌለ ንጉስ ይሸሻል...» ብለው በንጉስ መልአከፀሐይ መሪነት የኢጣሊያን ፋሽስቶች ያርበደብዷቸው ጀመር። በጎንደርም የአርበኞች ትግል ተፋፋመ፤ እነ ደጃዝማች ታከለ ወልደሃዋርያትም ሱዳን ሆነው የአርበኞችን ትግል ማገዝና ማነቃቃት ቀጠሉ። ከድል በኋላ ኢትዮጵያ በሪፑብሊክ የፖለቲካ ፍልስፍና የምትተዳደር አገር መሆን ይገባታል» እያሉ የአርበኞች ልብ እንዳይከፈልና የደጃዝማች ዮሐንስ አመራር እንዳይቀዘቅዝ እሳቱን ከዳር ሆነው ያራግቡ ጀመር። መልአከፀሐይ ግን አምርረው እያዋጉ የነፃነት ጎህ እንዲቀድ ሲጥሩ ከቁርጠት የምትቆጠር ሆድ ህመም ያዘቻቸውና ሞቱ ተባለ። እሳቸውንም እንደ ቀንዲል መኳንንት ሁሉ የተለመደው ድንገተኛ ሞት ታኮ ሆኖ ከጉዟቸው አቆማቸው። አገራቸውን የሚያስቀድሙት አርበኞች ድንጋይ ስር ተቀምጠው፣ መሳሪያቸውን እንደ እንቦቀቅላ ህፃን ታቅፈው «እህህ!» ብለው አቃስተው አዘኑ። የአርበኝነት ትግሉ ግን እንደ አጀማመሩ በጀግኖቹ የየግል ስልት ፍም እሳቱ ሳይጠፋ እየተቀጣጠለ የኢጣሊያ ወራሪዎችን መለብለብ ቀጠለ ...

በባዶሊዮን እግር ተተክቶ በኢጣሊያ መንግስት የተሾመው ግራዚያኒም የስልጣኑ ፊርማ ሳይደርቅ የሙሶሊኒን ምኞት የሚያረሰርስ የቅኝ ግዛት ካርታ አወጣ። ኤርትራንና የኢጣሊያ ሶማሌ ምድርን ጨምሮ በስድስት ክፍለ ሀገር ከፋፈለ። በየአካባቢውም የመንገድና የድልድይ ስራዎች ተጀመሩ። በተለይም በጂማ፣ ጎንደር፣ አዲስ አበባ አዳዲስ ህንጻዎች በፍጥነት ተገነቡ። በኢጣሊያ ያሉ ኢጣሊያውያን ባለ ሀብቶች ወደ ሁለተኛዋ የሮማ ግዛት በመምጣት ትናንሽና ከፍተኛ ኢንዱስትሪያቸውን እንዲከፍቱ ተቀሰቀሱ። ለዚህም እንዲያመች ሰም ቦታዎች ተዘጋጁ። የባለ ሀብቶችንና የሌሎችን ኢጣሊያውያን ክብር ለማስጠበቅም የአገሬውና የኢጣሊያውያን የገበያ ቦታዎች፣ መኖሪያዎች፣ መዝናኛዎች ወዘተ ተለዩ። «ልናሰለጥን ነው የመጣነው» የሚለው ቃላቸው ሳይደርቅ የቀለም ልዩነታቸውን፣ የዘር መድሎአቸውን አጠናከሩ። የአርበኞችን እንቅስቃሴ ለመደምሰስም የኢጣሊያ ወታደሮች ቁጥር እንዲጨምር ተደረገ።

በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የስልጣን ዘመን ግዛታቸው የተነጠቀባቸው፣ በተለያየ ምክንያትም ለግዞትና ለእስራት የተዳረጉት ኢትዮጵያውያን ለሮማ መንግስት በማደር አገራቸውንና ወገናቸውን መክዳታቸው እንሶ የጣሊያኖችንና የአርበኞችን ፍልሚያ የዝሆንና ቁንጫ ያህል ልዩነት ያለው በማስመሰል አርበኛው ሁሉ እጅ ሰጥቶ እንዲገባ ዘመቻ አካሄዱ። ለዚህም

ውለታቸው በሺ የሚቆጠር የኢጣሊያ ሊሬ በወር ደመወዝነት ይከፈላቸው ጀመር።

በኋላ ደግሞ የኢጣሊያ መንግስት አዲስ ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ። በጣሊያኖች ይቀማጠሉ የነበሩት መኳንንትና ባንዳዎች ገፋ እየተደረጉ አርበኞችን ማሞካሸትና ባሉበት እንደሆኑ ገበርዲንና ገንዘብ መስጠት፤ «እንከባበር እንጂ አንነካችሁም» ማለት፤ አርበኞች በሚወስዱትም እርምጃ «አበጃችሁ፤ የኢጣሊያ መንግስት በዚህ አይጠይቃችሁም» ማለት ጀመሩ። ይህን ጊዜ ሃሞታቸው የፈሰሰው ባንዳዎች ክብር ሲነፈጋቸው፣ ሲናቁ፣ «ጀግኖች የሚሰሩትን ያውቃሉ፤ የኢጣሊያ መንግስት ጀግና ይወዳል» ሲባሉ ምራላቸው ሚስማር እንደ ወጋው ጎማ ተነፈሰ።

በተለይም በግራዚያኒ ላይ በተወረወረው ቦንብ ጦስ የተጨፈ ጨፋት ኢትዮጵያውያን፣ በጳጳሱ ላይ የተደረገው የጥይት ድብደባ፣ በጥቁር አንበሳ ማህበርተኞች ላይ የተደረገው ድብደባና ግድያ ... በአጠቃላይ በህዝቡ ላይ ወራሪዎች ያደርሱት የነበረው ጭፍጨፋ፥ የኢጣሊያ ተረት "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንደሆነ አረጋገጠ። ይህም በጥርጣሬ የተከፈለውን፣ በቂም በቀል ለጠላት ለማገደር የወሰነውን አስደነበረው ... የቦንቡ ውርወራ በአንድ ጊዜ እውነታውን ለውጦ የተረጋጋውን ኢትዮጵያዊ ልብ አሸፈተው።

በአስር አመታቸው ከኤርትራ መጥተው አዲስ አበባ በሚገኙት በተፈሪ መኮንንና በስዊድን ሚሲዮን ት/ቤቶች የተማሩት ሎሬንሶ ትዕዛዝ ፈረንሳይ አገር ተምረው ባገኙት የህግ እውቀት በመታገዝ ስለወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ ሃሳባቸውን ማቅረብ ጀመሩ። እነ እንግሊዝ እውቅና የሰጡትን የኢትዮጵያን የኢጣሊያ ግዛት መሆን እያጣጣሉ «ንጉሰ ነገስቱ ሳይያዙ፣ የአገሪቱ ማህተም በጠላት እጅ ሳይወድቅ፣ ህዝቡ ወረራውን ለመመከት ከዳር ዳር እየተንቀሳቀሰ በመቃወሙ በግፍ እየተጨፈጨፈ ... ኤምፓየርነትን ምን አመጣው?» በማለት የኢጣሊያ ድርጊት ከወረራ ያላለፈና ኢትዮጵያ ነፃነቷን እንደጠበቀች መሆኗን አስረድተው የፈረንሳይን በጀርመን መወረር ምሳሌ እያጣቀሱ ተከራከሩ።

እንግሊዛዊቷ ሲልቪያ ፓንክረስትም «ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያ ኒውስ» በሚል ጋዜጣቸው በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ የነበረውን ግፍ፣ በስደት ላይ የሚገኙትን ንጉሰ ነገስት ሃሳብ፣ ወዘተ. እያቀረቡ የነፃነቱን ትግል ዓለማቀፋዊ ባህሪ እንዲኖረው በማድረግ ትግሉን እያጎለበቱ፣ በኢጣሊያ





ፋሽስቶች ላይ ተፅዕኖ አደረጉ። ዘርዓይ ደረስም የኢጣሊያን ፋሽስቶች ያሳቀቀ ተቃውሞ በኢጣሊያ ምድር፣ በጣሊያኖች ፊት በጀግንነት ፈፀመ።

እነ ዶክተር መላኩ በያን «ቮይስ ኦፍ ኢትዮጵያ» በሚለው ጋዜጣ ባስነሱት ወረራን የመመከት እንቅስቃሴም በሺዎች የሚቆጠሩ ጥቁር አሜሪካውያን ወደ ዘማቾች ከኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፈው ለመዋጋት ተመዘገቡ። የነፃነት ጥማት የነበረው ጥቁር አሜሪካዊ፥ ነጭ ወራሪን አድዋ ላይ ወደ አሸነፈችው ኢትዮጵያ ቀድሞውንም ፊቱን አዙሮ ስለነበር በአፄ ምኒልክና አቤቶ ኢያሱ ጊዜም አፍሪካዊ አሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያ ቢመጡ ለደመወዛቸው ወርቅ ይከፈላቸዋል ተብሎ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥቁር አሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር። ስለዚህ ወረራውን በመቃወም ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የተመዘገቡት ጥቁር አሜሪካውያን ዜና «የጥቁር ህዝቦች ጽዮናዊነት ያመጣል» የሚል ተቃውሞ በቅኝ ገዥ አገራት በማስነሳቱ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት የአፍሪካዊ አሜሪካውያንን ተነሳሽነት በዝምታቸው እንዲያቀዘቅዙት ተደረገ ...

## ፯

# ግብታዊ የአርበኝነት ጅማሬ

ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ግብታዊነት ብሎ ነገር የለም። ሁሉም ክስተት የድርጊያና የምላሽ ድርጊያ (የ"አክሽን"ና "ሪአክሽን") ውጤት ነው። በዚህ ስሌት ሳይሞቅ መፍላት እንደሌለ የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ ግብታዊነት አንፃራዊ አመለካከት የሚያስገኘው ግንዛቤ ነው። በተለይም ለሌላው በማይታይ እኔነት የተዋጠና የወል በሆነ መልኩ በገሃድ የማይታይ ውጤት ነው ግብታዊ የሚባለው። ስለዚህ ግብታዊነት በውጫዊ ውጤት ላይ የማይመሰረት፣ በውጫዊ ምክንያትም የማይወሰን የራስ ስሜት፣ የራስ ኩራት፣ በውስጣዊ ለውጥ፣ በእምቢ ባይነት ላይ የተመሰረተ የግለሰባዊ እልህ ድምር ውጤት ነው።

የኢትዮጵያውያንን የአርበኝነት እንቅስቃሴ በሶስት መደቦች መክፈል ይቻላል። አንደኛው ክፍል ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው፣ ስልጣን እንደሚገባቸው የሚያምኑ ከፍተኛ መኳንንት ያሉበት ነው። ከእነዚያም አርበኞች መካከል በምሳሌነት ራስ እምሩንና መልአከፀሐይ ኢያሱን መጥቀስ ይቻላል።

በሁለተኛው ምድብ የነበሩ አርበኞች ደግሞ በመንግስት መዋቅር መካከለኛ ስልጣንና ሃላፊነት የነበራቸው፣ ወላጆቻቸው የከፍተኛ መኳንንት ባለሚሉች የነበሩ፣ በእቋጥሪኝ ዝምድና የባላባት ዘር የሆኑና በጥንካሬና ማስተዋላቸው ንጉሰ ነገስቱን መማረክ የጀመሩ «ትናንሽ» መኳንንት ናቸው። ከእነሱም ውስጥ ለአብነት ራስ መስፍን ስለሽን፣ ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁ ስላሴንና ባላምባራስ አበበ አረጋይን መጥቀስ ይቻላል።

ሶስተኛው የአርበኞች መደብ ገበሬውን፣ የጥቁር አንበሳ ሰራዊትንና ዝቅተኛውን የህብረተሰብ ክፍል ያቀፈው የአርበኞች ስብስብ ነው። በዚህ በሶስተኛው መደብ የሚገኙት አርበኞች ከእለት ህይወታቸው በዘለለ ከመንግስት ጥቅም ያላገኙ ናቸው። በስም ካልሆነ ንጉሰ ነገስቱን አያውቋቸውም፤ ለመመስገን፣ ከድል በኋላ ሹመት ለማግኘት፣ ወዘተ. ያለመ ህልምም አልነበራቸውም። እነዚህ በሶስተኛው መደብ ወደ አርበኝነት የገቡት በሺዎች የሚቆጠሩት አርበኞች ብሔራዊ የአርበኝነት እንቅስቃሴውን የተቀላቀሉት በግብታዊነት ነው።





ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ያገኙትን ነፃነት ላለማጣት፣ ግፍና በደልን ቁጭ ብሎ እጅን አጣጥፎ ላለመመልከት፣ እንደ በግ ላይነዱ፣ ክብራቸው ሳይገፈፍ ግፈኛን እንደ አንበሳ አድነው ለመሞት «ጥራኝ ዱሩ» ብለው ደረታቸውን ለጥይት፣ አካላቸውን ለስቃይ አሳልፈው የሰጡ እና መስዋዕት ሆነው ሀገራቸውን ለማስከበር የቆረጡ ስም አልባ ጀግና ሰማዕታት ናቸው። በዚህ የአርበኝነት መደብ ስር የሚገኙት እነዚህ አርበኞች የአርበኝነት ትግሉ ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ገጽታ እንዲኖረው ያደረጉ፣ «ነፃነቴን እንጂ፤ ሺህ ቢታሰብ ያው በገሌ» ያሉ ቆራጦች ናቸው።

ከእነዚህ ውስጥ እነ በላይ ዘለቀን፣ ሃይለማርያም ማሞን ... በመቶ ሺዎቹ የሚቆጠሩ ተከታዮቻቸውን ማውሳት ይቻላል። የአገር አቀፍ አርበኝነቱ የትግል ቋያ በውስጥ አርበኞች ማገዶነት እየተንቀሰቀሰ መላ የኢትዮጵያን ምድር ረመጥ በማድረግ ኢጣሊያውያን ፋሽስቶችን አምስት ዓመት ሙሉ መርገጫ አሳጥቶ ቁም ስቅላቸውን ያሳየ ነው። ለዚህም ግንባር ቀደም ተጠቃሾች በሶስተኛው የአርበኞች መደብ ስር የሚገኙ አርበኞች ናቸው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ ግን የአርበኝነት ትግሉ የኢጣሊያን ፋሽስቶች በአዲስ አበባ፣ በጅማ፣ በደብረ ማርቆስና በጎንደር ከተሞች ብቻ ገድቦ እንደ ጉንዳን ጉያቸው ስር እየገባ ያዘልላቸው የነበረው ትግል የሁሉም አርበኞች የጋራ ክንድ ጥንካሬ ውጤት ነበር። ከዚህ ባሻገርም የአርበኝነት ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ያገዙት ኤርትራውያን ወንድምና እህቶች ናቸው። ኢጣሊያውያን ኤርትራን ባላት ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ከኢትዮጵያ ነጥለው ቅኝ ግዛት ባደረጓት ጊዜ የኤርትራ ህዝቦች የክፉ ቀን መደበቂያ ነፃዋ አገር ኢትዮጵያ ነበረች። በዚህም ምክንያት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ኤርትራውያን መሸሸጊያቸውና መመኪያቸው የሆነችው አገር በመደፈሯ እምርረው አዘኑ። ሐዘናቸውንም በፀረ ፋሽስት ትግሉ ከኢትዮጵያ ጎን በመሰለፍ አረጋገጡ።

ከእነዚህም ትብብሮች ሁለቱ እጅግ የሚያስደንቁ ናቸው። የኢጣሊያ ፋሽስቶች ከሶማሊያ፣ ከኤርትራ፣ ከሊቢያ ቅኝ ግዛቶቻቸው የመለመሏቸውን ወታደሮች በኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉ ጦርነቶች አሰልፈዋል። በተለይም ከኤርትራ ያመጧቸውን የሰራዊት አባላት የሚያሰልፉት ከፊት ነበር። ምንአልባት ለዚያ ምክንያቱ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች አንድ ህዝብ ስለነበሩ የአንዱን የጦር ስልት ሌላው ያውቀዋል በሚል ግምት ይሆናል፤ አልያም ደግሞ «እሾህን በሾህ» ብለውም ይሆናል።

አንጀሎ ደልቦካ በጽሑፉ እንደመሰከረው ግን በውጊያ ጥበብ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን ከኢጣሊያውያን ልቀው ተገኝተዋል:: የኢትዮጵያ አርበኞች የኤርትራ ተዋጊዎች ከኢጣሊያ ሰራዊት ፊት እንደሚሰለፉ ያውቃሉ:: ስለዚህ በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ያለው ፍጅት በምርጥ ዘዴ መገታት ነበረበት:: ለዚህ ደግሞ ኤርትራውያኑና ኢትዮጵያውያኑ በስውር በመገናኘት ውሉ በቀላሉ የማይገኝ መላ ፈጠሩ::

ያም መላ ይህ ነበር፤ ኤርትራውያን ባሩድ ያለውን ጥይታቸውን ለአርበኞች ይሰጡና ባሩድ የሌለውን ጥይት እየተኮሱ ያንጣጣሉ:: የኢትዮጵያ አርበኞች ደግሞ ከፊት ለፊት እንደ እንቦሳ እየዘለሉ የሚዋጉትን ኤርትራውያን ትተው የኢጣሊያ ፋሽስቶችን እያለሙ ይመታሉ:: የኢጣሊያ ወራሪ ጦር መሪዎች በውጊያ ወቅት ብዙ የኢጣሊያ ወታደሮች የማለቃቸውን ምስጢር ለማወቅ መሞከራቸው አልቀረም:: ለዚያም 'ተገኘ' የተባለው ምክንያት የኢጣሊያ ወታደሮችና ባንዳዎች የሚለብሱት ዩኒፎርም መለያየት ነው ብለው በማመን የሁለቱም አንድ አይነት ዩኒፎርም እንዲሆን ተደረገ:: ያ መላ በተወሰነ መልኩ ቢሰራም ዘላቂ መፍትሄ መሆን ግን አልቻለም::

ሁለተኛው ትብብር ደግሞ ከዚህ የላቀ ነው:: ኤርትራውያን የኢጣሊያ ፋሽስቶችን ዘዴና ተንኮል ከኢትዮጵያውያኑ በበለጠ ያውቁታል:: ለዚያ እውቀታቸው ደግሞ ዋናው ምክንያት ኤርትራውያኑ የኢጣሊያ ፋሽስቶች ቅኝ ተገዢዎች ሆነው መቆየታቸው ነው:: ኢጣሊያ የኢትዮጵያ አርበኞች ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ በመቸለስ እሳቱ እንዲጠፋ ከእነ ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ጋር ሽንጎ እየተቀመጠች በምክር ላይ ታች ትላለች::

ይህን የተረዱት ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ደግሞ የአርበኞች ትግል ፋሽስቶች በሚቸልሱት ውሃ እንዳይጠፋና ይበልጥ እንዲቀጣጠል በበኩላቸው ሸንጎ እየተቀመጡ ይመክራሉ:: የውስጥ አርበኞች በሚያደርሷቸው የጣሊያኖች ስትራቴጅም ይወያያሉ:: በየካቲት ወር 1929 ዓ.ም. ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን ዘንድ አንድ መልዕክት መጣ:: መልዕክቱ አዲስ አበባ ውስጥ በፋሽስቶች የተቀነባበረ በዓል እንደሚኖርና ግራዝያኒ ንግግር እንደሚያደርግ ተደረሰበት:: ኤርትራውያኑና ኢትዮጵያውያን አርበኞች በጉዳዩ በጥልቀት መከሩ:: ቦምብ እንዲወረወር ወሰኑ:: ቀደም ብሎ በሌላ ምእራፍ እንደተገለጸው ቦምቡ ተወረወረ:: የበርካታ ንፁሐን ደምም ፈሰሰ:: ያ አጋጣሚም የኢጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ቀን በቀን እስኪታክተው እየተጋተ ወራሪውን «ልጥ ነው÷ እባብ?» እያለ ግራ





ለተጋባው ህዝብ እውነቱን የሚያረጋግጥ ሆነና የፀረ ፋሽስት ትግሉ እንደ እቶን እሳት ተንቀለቀለ::

መቶ አለቃ ሙላት ገብሩ «ብዙው ኢትዮጵያዊ ከኢጣሊያ ፋሽስት ወረራ በፊት 'ነፃነት ማለት ምን ማለት ነው?' ቢባል ነፃነቱን አጥቶ ስለማያውቅ እጥጋቢ መልስ አልነበረውም:: ነፃነት በቃላት የሚተረጎም አይመስለኝም:: ያልተራበ ረሃብን አያውቅም፤ እንደዚሁም ደግሞ ስለ ነፃነቱ ያልተሰደደ፣ ያልተገፈፈ፣ ያልተሰቀለ፣ ስለ ነፃነቱ ያልሞተ፣ በዱር በገደል አጥንቱን ያልከሰከሰ ስለ ነፃነት ቢያወሩለት የሚገባው አይመስለኝም:: ሰው ነፃነቱን ለማወቅ መፈተን አለበት፤የተወለድክበት መሬት፣ ያደግህበት መንደር፣ የረገጥከው አፈር የአንተ አይደለም ብለው ሊያስተባብሉህ ሲሞክሩ... ሙከራቸው ተሳክቶላቸው ስታይ፤

ሰው ባገሩ፣ ሰው በወንዙ፤
ቢበላ ሳር፣ ቢበላ መቅመቆ!
` ይከበር የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ::

ብለህ ለነፃነትህ ትነሳለህ ...» በማለት የነፃነትን ትርጉምና ጣዕም በመግለጽ ጽፈዋል::

እርግጥ ነው በወራሪዎች የተደፈረች አገር ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም:: የወራሪዎች ጎረቤቶችም ወራሪዎቻቸው ነፃነታቸውን ነጥቀዋቸዋል:: እነ ፈረንሳይም ነፃነታቸው በጀርመን ወረራ ተደፍሯል፤ የፈረንሳይን መወረር ለመቀልበስ ጄኔራል ደጎል የወሰደው እርምጃ ብሔራዊ የአርበኝነት ትግልን በአዋጅ መጀመር ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የአርበኝነት ትግሉ የተጀመረው ፈረንሳይ አገር እንደተደረገው በአዋጅ ሳይሆን በሥነልቦናዊ ውሳኔና የመንፈስ ኩራትን ለማረጋገጥ በፈለጉ ኢትዮጵያውያን በጎፈቃድ ነው:: ይሁን እንጂ የአርበኝነት ትግሉ ዓለማቀፋዊ ባህሪ የነበረውና ከፈረንሳይ በአራት አመታት፣ ከዩጎዝላቪያ ደግሞ በአምስት ዓመታት ቀድሞ የተጀመረ ነው::

* * *

«... ሰው መሆንህን ስታጣ፣ የረገጥኸው አፈር 'የአንተ አይደለም...' ሲሉህ፡ ያኔ ነው ነፃነት ምን ማለት እንደሆነ የሚገባህ!» የሚለው አባባል እውነት ሆኖ የኢትዮጵያ አርበኞች ብሔራዊ ትግል በግብታዊነት ተጀመረ:: ብርድና ቁሩን፣ ፀሐይና ንዳዱን፣ ርሃብና ጥሙን፣ በሽታና ብቸኝነቱን ...

በጥንካሬ ተቋቁመው «ራስህን አጥፋ እንጂ እጅ አትስጥ» በሚል ውሳኔ የተዋደቁት ኢትዮጵያውያን ተግባር ምስጢሩ ሲፈተሽ «ማንነትንና ኢትዮጵያዊነትን» ብቻ ላለማጣት የተደረገ መስዋዕትነት ነው።

ስለዚህ ለኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነት ውስጣዊ ማንነት እንጂ ከማንም ያገኙትና የኮረጁት እውቀት አልነበረም። የጥንካሬያቸው መሰረት ያ ተፈጥሮአዊ፣ ግብታዊና ግልጽ የሆነው ነፃ ማንነት ነው። እንደ ጃገማ ያሉ አርበኞችን ለከፍተኛ ክብር ያበቃቸውም ይኸው ይዘውት የተገኙት ውስጣዊ ጥንካሬና «ኢትዮጵያዊ እኮ ነኝ!» በሚለው አነጋገር የሚገለጸው የእኔነትና የእኛነት ድምር ውጤት መሆኑ የማያጠራጥር እውነታ ነው። በዚች በእኛዋ ምድር ላይ ይህ የነፃነት ቋንቋ የሚገባቸውና ከኢትዮጵያ ጎን መቆም የሚችሉ ጥንታዊ አገሮች ደግሞ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።



# ፲

# ምሽግ ሰበራ

ጃገማ ከፈጸማቸው አኩሪ ገድሎች ውስጥ የማዕዘን ድንጋይ የሆነውና የአመራር ብቃቱን ያሳየበት፣ የማስተባበር ችሎታውን ያረጋገጠበት፣ የተዋጣለት አዋጊ መሆኑንም ያስመሰከረበት የኢጣሊያ ጦር ይመካበት የነበረውን የአዲስ ዓለም ምሽግ ደርምሶ ለመግባት የተጠቀመበት ስልት ነው።

ጃገማ ደጃዝማች ገረሱን በመርዳት ሊያጠቃቸው የ ጣውን የኢጣሊያ ወራሪ ድል ካደረገ በኋላ አስቸኳይ መልዕክት ከአዲስ ዓለም መጣለት። «ጃገማ! ያን የተመካከርንበትን ጉዳይ ጨርሻለሁና ነገ ዛሬ ሳትል ሰራዊትህን ይዘህ በረህ ድረስ ...» ይላል፤ የውስጥ አርበኛዋ የወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ መልዕክት። ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ የአዲስ ዓለም ምሽግ ተሰብሮ በወገን ጦር እንዲዘረፍ በቅድሚያ የመከሩት የኢጣሊያ ጦር የመኖሪያ ካምፕ አለቃ ከነበሩት ከቀኛዝማች አብርሃም፣ በኋላ የመቶ አለቃ ከሆኑት ከአቶ ሃይሉ፣ ከአድምቄ በሻህ፣ ከመንግሥቱ ወ/አማኑኤል እና ከስዩም ወ/አማኑኤል ጋር ነው። ጃገማና ደጃዝማች ገረሱ የሸዋረገድን መልዕክት ሲሰሙ መለያየታቸው ስለሆነ አዘኑ። ልበ-ሙሉው አንበሳ ጃገማ ከገረሱ ጋር መቆየት ቢፈልግም ትግሉን ለማጠንከር የሚፈልገውን መሳሪያ መዝረፍ፣ የኢጣሊያን አከርካሪም በመስበር ጋጂ ላይ ባለው የኢጣሊያ ምሽግ ላይ የበላይ መሆን አለበት። በዚያ ላይ ስንት ስመ-ጥር አርበኞች ባሉባት አገር አዛውንቷ የውስጥ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ያን የመሰለ ጠንካራ ዘመቻ ለእሱ ስለሰጡት በደስታ ልቡ ዘለለች። ስለዚህ ጃገማ፥ ዘውዴ ጥላሁንን፣ ሻለቃ ጠንቁሳን፣ ሻምበል ጊዲንና በእነርሱ አመራር ስር ያሉትን ሰብስቦ በአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ላይ በጥልቀት እንዲወያዩ አደረገ። በመጨረሻም ምሽግ ሰበራውን ለመፈፀም ወሰኑና ጃገማ አባ ዳማ አርበኞቹን እየመራ ወደ አዲስ ዓለም በፍጥነት ገሰገሰ።

ለዚህም ምሽግ ሰበራ ጃገማ ኬሎ የጦር አዝማች ሆነ። ኮሎኔል በለው ወ/ጻዲቅ፣ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ግዛው፣ ልጅ ኃ/ማርያም ወ/ጻዲቅ፣ ልጅ አሰፋ ዘርጋው፣ ሻምበል ሹምዬ ደቦጭ፣ ልጅ ተገኝ እሸቴ፣ ልጅ ድጌ ሚጣ፣ ሻለቃ ኃ/ጊዮርጊስ ጥላሁን፣ ዓለሙ መኮንን፣ አድማሱ መኮንን፣ ሻለቃ ከበደ

ተሰማ፣ ልጅ አበጋዝ ለማ ከነጓደኞቹ በጃገማ የቀኝ እንደራሴ በዘውዴ ጥላሁን ትዕዛዝ እንዲንቀሳቀሱ ሆነ።

በግራ እንደራሴው በሻለቃ ጠንቂሳ ኬሉ በኩል ደግሞ ሻምበል ጊዲ ኬሉ፣ ሻምበል ተጆ ወላኔ፣ ሌ/ኮሎኔል ሙሊሳ ሰሪ፣ ቀኝ አዝማች ተሰማ ካሳ፣ አቶ ሙሊሳ ቀርጨ፣ አቶ መንግሥቱ ወ/አማኑኤል፣ ሻለቃ የሻነህ ወርቅነህ፣ ልጅ አበበ ተሰማ፣ አቶ ብሪ መርጋ፣ አቶ ሚደቅሳ ክልል፣ አቶ በከልቻ ኢጉ፣ አቶ ጉተማ ገመቹ፣ አቶ ታደሰ ጋሻው ከነወንድሞቹ፣ አቶ ከበደ ይመር፣ አቶ ወርቅነህ መሸሻ፣ አቶ ያዳ ደራ በምሽግ ሰበራው ላይ እንዲካፈሉና ከላይ ስማቸው ከተዘረዘረው አርበኞች ሌላ ሶስት መቶ ጀሌ (መሳሪያ የሌለው) እንዲዘጋጅ፣ ምሽጉ ከተሰበረ በኋላም መሳሪያ የሚዘርፍ የሰው ኃይል በተጨማሪ እንዲዘጋጅ ተወሰነ።

የአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ከመፈፀሙ በፊትም ዘውዱ ጥላሁን፣ ኮሎኔል በለው ወ/ፃድቅ፣ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ግዛው፣ ልጅ ኃይለማርያም ወ/ፃዲቅ፣ ሻምበል ስዩም ደቦጭና ልጅ ተገኝ እሸቴ ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር አዲስ ዓለም ሄደው ልጅ ዓለማየሁ ከተባለው ሰው ቤት ለሶስት ቀን በመቀመጥ ጥንቃቂ ባለው ስልት ስለላ እንዲያደርጉ፣ መውጫ መግቢያውን እንዲያጠኑና እንዲያስጠኑ፣ የኢጣሊያን የጥበቃ ማማ እንዲለዩና ምሽጉንና ወደ ምሽጉ የሚያደርሱ መንገዶችን እንዲያጣሩ ህዳር 23 ቀን 1933 ዓ.ም ተልከው በርጋ ወንዝ ላይ መንግሥቱና ስዩም ከተባሉ የውስጥ አርበኞች ጋር ተገናኙ ... ከመካከላቸውም አንድ አርበኛ ጎፈሬውን ተላጭቶ፣ የቀን ሰራተኛ በመምሰል በታላቅ ጥንቃቂ ወደ ኢጣሊያ ምሽግ እንዲገባ ተደረገ።

በማግስቱ ጠዋት አርበኞች ካደሩበት ወጥተው ጫካ ውስጥ እንዲደበቁ ታዘዙ። ባጋጣሚ ግን አንድ የአካባቢው ፏሪ ሳያዩት መሐላቸው ገባ። አርበኞቹ ዐይናቸው ፈጠጠ። እሱም ዐይኑ ፈጠጠ። የውስጥ አርበኞች መንግሥቱና ስዩም አዲስ ዓለም ተወልደው ያደጉ ስለነበሩ አርበኞች የሚወስኑት በጠፋባቸው ወቅት ቀረብ ብለው፤ «እኛ ነን ዝም በል» አሉት። አፋፍ ላይ የነበረው የጣሊያኖች ጠባቂ የሰዎች ድምፅ የሰማ ስለመሰለው ጓደኛውን «አንተ! ምንድነው? ከማን ጋር ነው የምታወራው?» ብሎ ጠየቀው። ሰውየው ምን ይል ይሆን ተብሎ ተፈርቶ ሁሉም ዐይን ዐይኑን ሲያየውና እንደ ገመሬ ዝንጀሮ ላዩ ላይ ሊከመሩበት አርበኞች ሲዘጋጁ «አይ፤ ዝንጀሮ ነው፤ አታስብ» አለ - በአልታሰበ መላ። ያን ጊዜ ሁሉም በጭንቀት የተወጠረ አካሉን እያላላ ትንፋሹን በእፎይታ አምቦለቦለው። አርበኞቹን ቤቱ ያሳደረው ዓለማየሁ በጫካ ተሰግስገው ለአደፈጡት አርበኞች ከሶስት ኩንታል ያላነሰ ቆሎ በማዘጋጀት ቀኑን ሙሉ ሲያስቆላና እያመላለሰ አርበኞቹን ሲመግብ ዋለ።





ጨለምለም ሲል የጠላት ካምፕ አለቃ ሆነው የሚሰሩት ቀኝ አዝማች አብርሃ ከእነ ዘውዴ ጥላሁን ጋር ተገናኝተው የኢጣሊያን ካምፕ የጥበቃ አይነት፣ የዘቦችን አቋቋም፣ የመሳሪያ ግምጃ ቤቱን፣ የመሳሪያና ጥይቱን ግምጃ ቤት አቀማመጥ ... በማብራራት አርበኞች እንዲረዱት ገለፃ አደረጉ፤ የጥቃት ፕላንም ተዘጋጀ። ቀደም ሲል ለስለላ አዲስ ዓለም የተላኩት አርበኞች በበኩላቸው ደግሞ አዲስ ዓለም የሚኖሩትን ጣሊያኖች በዝርዝር አቀረቡ። ፅዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚኖሩ ሃያ ባለስልጣኖችና ሃምሳ ወታደሮች እንዳሉ፤ በመኖሪያው ካምፕ ሶስት የኢጣሊያ አዛዦች እንደሚገኙ፤ ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ በሚወስደው አውራ መንገድ ኬላው አጠገብ ባለው ምሽግ ቁጥራቸው ያልታወቀ ወታደሮች ከእነ አዛዦቻቸው እንደሚኖሩ አሳወቁ።

ጃገማና አማካሪዎቹ የጠላትን ይዞታ፣ የጥበቃውን ዓይነት፣ የሰው ኃይሉንና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በአስተማማኝ ከሰበሰቡ በኋላ የመጨረሻ የማጥቃት ስልት ለማውጣት የራሳቸውን ጦር ብዛት፣ በእጃቸው ያለውን መሳሪያም ቆጠሩት። በአርበኞች እጅ ሁለት ድግን መትረየስ፣ ሰማንያ ሶስት ጠመንጃ፣ ሃያ የእጅ ቦንብ መኖሩን አረጋገጡ። መሳሪያ የሚዘርፉ ከሶስት መቶ በላይ ጀሌዎችም ተዘጋጁ። የሚያስደንቀው ታዲያ እኒያ ስልጡን ነን ባይ የኢጣሊያ መኮንኖች ይህ ሁሉ ዝግጅትና ምክር አፍንጫቸው ስር ሲደረግ አንድም የደረሱበት ፍንጭ አልነበረም።

ከዚህ በኋላ ጃገማ የጥቃቱን አሰላለፍ የሚያሳየውን ዝርዝር መመሪያ ለተከታዮቹ ማስረዳት ጀመረ። መንግሥቱ ወ/አማኑኤል፣ ስዩም ወ/አማኑኤልና ሙሊሳ ቁርጩ ከአስራ አምስት ጠመንጃ ጋር ወደ ፅዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ በመዝጋት ከአዲስ አበባ መጥቶ ከኬላው ወደ አምቦ በሚወስደው መንገድ የሰፈረው የጠላት ጦር ከምሽግ ወጥቶ ወደ ጦር ግምጃ ቤቱ እንዳይገባ በተኩስ እንዲያቆሙት ተመደቡ። ምሽግ ውስጥ የነበረው የጠላት ተዋጊ ሃይል ምንም እንኳን ቁጥሩ ባይታወቅም እንደ ልቡ ተንደርድሮ የመሳሪያ ግምጃ ቤቱ ሲዘረፍ ለእገዛ መድረስ ከቻለ አርበኞች ፈተና እንደሚገጥማቸው አውቀዋል። ጃገማና ረዳቶቹም ይህን በመረዳታቸው የመጀመሪያው የተጠናከረ ምደባ በምሽጉ መውጫ መግቢያ ላይ ተደረገ።

ቀጥሎ በሌ/ኮሎኔል ሙሊሳ ሰሪ የሚመሩ አምስት ባለ ጠመንጃዎች ከጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት በስተምስራቅ ከባድ መሳሪያ ወደ አለበት አቅጣጫ ተመደቡ። ከመኖሪያው በላይ በኩል ያለውንና ወደ ፅዮን

ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚያስገባውን መንገድ እንዲጠባበቁና እንዲዘጉ ደግሞ ሻምበል ተጆ አሳኒና ዓለሙ መኮንን አስር ባለጠመንጃዎችን በመያዝ ከኮሎኔል ሙሊሳ ጎን ለጎን ሆነው እንዲጠባበቁ ተመደቡ። ሻለቃ ኃ/ጊዮርጊስ ጥላሁን አስራ አምስት ባለ ጠመንጃዎችን ይዞ ኃ/ጊዮርጊስ የሚባለውን የኢጣሊያ ጦር ሹምባሽ ቤቱ ድረስ ሄዶ እንዲከብና ከጦር ግምጃ ቤቱ ውስጥ ተኩስ ሲከፈት «ጃገማ ወደ እኛ ና ብሎሃል» ብሎ እንዲጠራው፤ አልመጣም ብሎ ከተቃወመ ግን ባለበት እንዲደመስሰው ተመደበ። የመቶ አለቃ ሃይሉ ደግሞ ተኩሱ ሲጀመር በመኖሪያ ካምፑ ውስጥ የሚገኙትን ሶስቱን አለቆች በቀጥታ ገብቶ እንዲገድል፤ ቀጥሎም እስረኞችን እንዲለቅ፤ እስረኛ የነበሩት ከአርበኞች ጋር በመሆን መሳሪያ በመዝረፍ እንዲተባበሩና የአርበኛውን ሃይል እንዲያጠናክሩ ታዘዘ።

ከሶስት መቶ ሃምሳ በላይ የሆኑት ጆሌዎችም ሶስት ጠመንጃ ተመድቦላቸው ከግንቡ ስር በተጠንቀቅ እንዲቆዩና ጡሩንባ ሲነፋ በቀጥታ ወደ መሳሪያ ግምጃ ቤቱ በመሄድ መሳሪያ እንዲዘርፉ ታዘዘ።

የጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን እየፈረሰ ሽቦ በሚደረግበት በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ባለው ጠንካራ ምሽግ በኩል ደግሞ በጃገማና በዘውዴ የሚመሩ ሰላሳ አምስት ባለ ጠመንጃዎችና ሁለት ድግን መትረየስ የያዙ ከፊት ለፊት ባለው በር በመግባት የጠላት ጦር ጠባቂዎችን እንዲደመስሱ ተመደቡ። በኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ምንጊዜም ከባዱን ግንባርና ጠንካራውን ውጊያ የሚጋፈጡ መሪዎች በመሆናቸው ጀግናው ጃገማና አጋሩ ዘውዴ ከባዱን ተልዕኮ ለራሳቸው ወሰዱ።

አሰላለፉ ከላይ በተዘረዘረው መልክ ከተሰናዳ በኋላ ግንኙነቱ በተላላኪና በይለፍ ቃል እንዲሆን ተወሰነ። ጃገማና ዘውዴ የሚያዙትን ምድብ የሚመራው ፀጉሩን ተላጭቶና የጉልበት ሰራተኛ በመምሰል ከቀኝ አዝማች አብርሃም መሸሻ ጋር ገብቶ መውጫ መግቢያውን፣ የጣሊያኖችን መኖሪያ ሰልሎ የተመለሰው አድምቄ በሻህ ነበር። ሁሉ ነገር ሲጠናቀቅ አርበኞቹ በየምድብ አለቃቸው መሪነት ወደየምድብ ቦታቸው እንዲንቀሳቀሱ ጀግናው ጃገማ አዘዘ። ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ከሩብ ላይ አርበኞች ከበርጋ ወንዝ ተንቃነቁ። ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሲደርሱ ለጃገማ የእሱን የአመራር ችሎታና ቆራጥነት የሚፈታተን መልዕክት ተነገረው።

«ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ በሚሄደው መንገድ ስድስት መቶ ወታደሮች ያሉት የኢጣሊያ ጦር መጥቶ ካርቢኔሪ ካምፕ አጠገብ ሰፍሯል። በነበረው ጦር ላይ የዚህ ጦር መጨመር የምሽግ ሰበራውንና የመሳሪያ





ዘረፋውን እቅድ አደጋ ላይ ስለሚጥለው ጦሩ አካባቢውን ለቆ እስኪሄድ ለመጠበቅ የዛሬውን ዘመቻ እቅድ ለሌላ ቀን ብናስተላልፈው ምን ይመስልሃል?» የሚል አዲስ አስተያየት ቀረበለት።

«እዚህ ደርሰን፣ የውስጥ አርበኞችን እንመጣለን ብለን፣ ሁሉም በቆራጥነት ለመፋለም ተዘጋጅቶ ወደ ኋላ መመለስ ብሎ ነገር ጭራሽ የማይታሰብ ነው። ይህን ለእኔ የነገራችሁኝን ነገር ደግሞ ለማንም እንዳትነግሩ፤ እኔ ሰምቻለሁ፤ ወሬውም እኔ ዘንድ ደርሶ ቆሟል» አለ፥ ጃገማ-ኮስተር ብሎ። ተላላኪው እንደገባው ለመግለጽ እጅ ነሳ። «እኔ እንደሰማሁት ለሌላ ትንፍሽ እንዳትሉ» ብሎ በድጋሚ አዘዘ፥ ጃገማ አባ ዳማ።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ወደ ምሽጉ ቀረቡ።

የዕለቷ ጀምበር ጠልቃለች፤ አካባቢው በጨለማ ተውጧል። ውጭ ማደር የለመደው አርበኛ ግን ሰማዩ ላይ ሆጨጭ ብለው የሚብለጨለጩትን ከዋክብት እንደ ልቡ ያያል። በእቅዱ መሠረት እነ ጃገማ ቀስ ብለው እየተሳቡ እጥር ስር ተጠጉ። አድምቄና መሸሻ እየመሩ ዘብ ወደቆመው ፈረንጅ አጠገብ ሲደርሱ እነ ጃገማ በሶምሶማ ተጠጓቸው። ዘቡ ሁለት ጊዜ «ማነህ?» አለ በራሱ ቋንቋ። ማንነታቸውን ያላወቃቸው ሰዎች ዱካ እየቀረበ እየቀረበ ሄዶ አጠገቡ መድረሱን በኮቴያቸው ሲያውቅ እየተርበደበደ መትረየሱን ትቶ ሲፈረጥጥ የምትንፈራገጥ ነፍሱን ሳያተርፍ ወርቅነህ መሸሻ ከኋላው የመጀመሪያዋን ጥይት ተኩሶ መትቶ ጣለው።

ተኩስ ሲከፈት የበጋው መብረቆች በየተመደቡበት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ይራወጡ ጀመር። እነ ጃገማ በቀጥታ መብራት አብርተው ራት ወደሚበሉት ጣሊያኖች ሄደው በተኩስ አጣድፈው ገደሏቸው። በምግብ አዳራሹ ውስጥ ወደ መጋዘኑ ሲሮጡ ከነበሩት ሃያ የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች መትረፍ የቻሉት ሶስት ወይንም አራት ነበሩ። እነዚህም ወደ ፎቅ ወጥተው ቦምብ ቢወረውሩም ጃገማና ዘውዴ እንደ ጉሬዛ ተንጨዋለው ወጥተው አፋቸውን አዘጓቸው።

እነዚህን ከደመሰሱ በኋላ ጃጌ ጃገማና ጓደኞቹ ሃምሳ ጣሊያኖች አሉበት ወደተባለው ከመሄዳቸው በፊት በስህተት ጡሩንባ ተነፋ። የጥሩንባው ድምፅ 'የድል መግለጫ ነው' ተብሎ የተነገረውና ግንቡ ስር ተኮልኩሎ ይጠባበቅ የነበረው ጆሌ የጡሩንባውን ድምፅ ሲሰማ «ሆ!» ብሎ እየዘለለ ወደ መጋዘኑ ሲሮጥ በዚያ አጋጣሚ ሃምሳ ጣሊያኖች መሳሪያቸውን ለመውሰድ ወደ መሳሪያ ግምጃ ቤቱ እየሮጡ ሲመጡ መሳሪያ ለመዝረፍ ከተጠጉት

ጀሌዎች ጋር በመቀላቀላቸው አብዛኛዎቹ ጣሊያኖች የተገደሉት በዱላ ነው:: በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ፈረንጅና አበሻው የሚለየው በቋንቋና በአለባበስ ብቻ ሆነ::

... ሁሉም ከፊት ለፊቱ የሚጋረጠውን የጠላት ጦር ሃይል እየበታተነ ግቡ ወደ ነበረው መጋዘን ተንደረደረ፤ በእቅዱ መሰረትም መጋዘኑ ተከፍቶ ዝርፊያ ተጀመረ:: በግምት እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል እንደቆዩ መውጣት እንዲጀመር ጃገማ ትዕዛዝ አስተላለፈ:: በእቅዱ መሠረት እግረ መንገዳቸውን ምሽጉ አጠገብ የሠፈሩት አስራ አምስቱ አርበኞች በፈፀሙት ያላባራ የማያናገሪያ ተኩስ ምክንያት በኬላው ያሉት አዛዦች ከምሽጋቸው እንዳይንቃነቁና ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆነው እንዲቆዩ በማድረግ በወኔና ብልጠት የታገዙት አርበኞች ትልቁን ዳቦ ሲጥ አድርገው ድላቸውን ካለ ችግር አጣጣሙ::

እስረኞችን ለማስፈታት በመሪነት የተመደበው መቶ አለቃ ሃይሉ በበኩሉ ከጃገማ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተኩሱ እንደተከፈተ ኢጣሊያውያን አዛዦችን ገድሎ፣ መሳሪያቸውን ካስገፈፈ በኋላ በተለያየ ሰበብ በወራሪዎቹ የኢጣሊያ አዛዦች ወደ እስር የተወረወሩት ሰማንያ እስረኞች ያሉበትን በር አስከፈተው:: ወደ እስረኞቹ በመቅረብም መቶ አለቃ ሃይሉ «በጃገማ ኬሎ የሚመራው የአርበኞች ጦር የኢጣሊያን የጥበቃ አከርካሪ እንካከቶ፣ የመሣሪያ ክምችቱን መጋዘን ሰባብሮ የዘመናዊ ትጥቅ ባለቤት ሆኗል:: በዚህች ወሳኝ ወቅትም እናንተ የጠላት ግፍ ገፈታ ቀማሾች የሆናችሁ ሁሉ አርበኞችን ተቀላቅላችሁ የተዘረፈውን መሳሪያ እንደ አቅማችሁ በመሸከም ለእናት አገራችን በጋራ እንድንዋደቅ ጥሪ ተደርጎላችኋል» አላቸው:: እስረኞቹ ሰሚ እስኪጠፋ ድረስ ተንጫጩ:: በዚህ መሃል መቶ አለቃ ሃይሉ አርበኞች ከአዲስ ዓለም ለመውጣት እንዲንቀሳቀሱ ትዕዛዝ መስጠቱና እሱም በፍጥነት እስር ቤቱን ለቆ እንዲንቀሳቀስ መታዘዙ ተነገረው::

«... እንዴ እንደማመጥ? እንደማየው አንድ ውሳኔ ላይ የደረሳችሁ አይመስለኝም፤ እባካችሁ ሃሳባችሁን ግለፁልኝ፤ ጊዜ የለም» አለ፥ መቶ አለቃ ሃይሉ::

«እንደ በግ ታጉሮ በጠላት መጠበቅና ክቡር ህይወትን ማጣት ዘግንኖን ወደ እግዚአብሔር አልቅሰናል፤ ይኸው አሁን ያ ፀሎታችን በአርበኞቻችን ጀግንነት መልስ አግኝቷል:: ስለዚህ ከእንግዲህ እንደ በግ





ታጉረን ሳይሆን እንደ አንበሳ እያገሳን ጠላታችንን እየተዋጋን ከወንድሞ ቻችን ጋር መስዋዕት ለመሆን ወስነናል» አሉ፥ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ እስረኛ::

« 'ወንድሞቻችን' ያሉትን ግልፅ ያርጉት» አለ፥ አንድ ሌላ እስረኛ::

«አርበኞችን ማለቴ ነዋ! ወንድም፣ ወገን በጭንቅ ሰዓት የሚደርስ አይደል!»

«በሉ! የእሱ ውሳኔ ውሳኔያችሁ የሆነ ተለዩ» ሲል መቶ አለቃ ሃይሉ፥ አርባ ሰዎች ብድግ ብለው ተለዩ::

«እናንተስ?» አለ ሃይሉ::

«አገሪቱን የያዘው ጣሊያን ነው:: አሁን ብናመልጥም መልሰን መያዛችን አይቀርም:: ስለዚህ እሱ አርነት ይስጠን እንጂ ከዚህ ወጥተን ዳግመኛ አንንገላታም» አሉ::

«ይህ የናንተ ውሳኔ ነው:: ጣሊያን የምትመኙትን አርነት የሚሰጣችሁ ከሆነ ጥሩ» አለና ሃይሉ ፈቃደኞችን አስከትሎ ከግቢው ወጣ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጃገማ አባ ዳማና አርበኞቹ ጥርግርግ ብለው ለቀው ሲወጡ አዲስ ዓለምን ከሰለቀጣት ጨለማ በተጨማሪ እንደ ሞት የከበደ ፀጥታ ዋጣት::

* * *

በነጋታው ከአርበኞች ጥይት ያመለጡ ጥቂት እድለኛ አዛዦችና ከኬላው አጠገብ የሰፈረው የኢጣሊያ ወራሪ ጦር አዛዦች በፅዮን ማርያም ግቢ የተገኘውን የሶስት መቶ ጀሌዎች ዱላ አሰብስበው ከመሩት:: ዱላ ይዘው ሄደው እያንዳንዳቸው ከአምስት እስከ ሰባት ጠመንጃዎችን ዘርፈው የሄዱትን ጀሌዎች በንዴት እያሰቡ «እንዴት በዱላ ምሽጋችን ይሰበራል?» በሚል ዘቦቻቸውን በንቀት ሲያበሻቅጡ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ከደሙ ንፁህ የሆኑትን ካህናትና ዲያቆናት እየመረጡ ሲያስገድሉ ዋሉ ... የግፍ እርምጃውን በመቀጠልም የአዲስ ዓለም ምሽግ ሲሰበር አዲስ አበባ ሄዶ የነበረውንና እራሳቸው የሾሙትን የወንበር ዳኞች መሪ ገደሉ:: ከዚህም ባሻገር «አገሩ የጣሊያን ነው፤ የት እንደርሳለን?» ብለው እስር ቤት የቀሩትን አርባ እስረኞች፤ «ጀግኖቹ ሲያመልጡ እናንተ ምን ልታደርጉ እዚህ ቀራችሁ» ብለው በመትረየስ ረሸኗቸው::

በአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ዘመቻ ከአርበኞቹ ወገን ልጅ ኃይለ ማርያም ወ/ፃድቅ እስከ ኤጀርሳ ሰፎ ድረስ እነ ጃገማን ከሸኘ በኋላ የኢጣሊያ ምሽግ ሸቦ ይዞ ያስቀረውን ጓደኛውን ለማስለቀቅ እንደተመለሰ ጣሊያኖች አግኝተውት እሱና ጓደኛው ከመገደላቸው ውጭ ከአርበኞች ውስጥ ሌላ የሞተ የለም፡፡

ከጠላት ወገን ግን ሰባ ሁለት የአዲስ ዓለም ምሽግ አዛዥ ኢጣሊያውያንና ጠባቂዎቻቸው፣ በእንግድነት ምሽጉ ውስጥ የነበሩ አንድ ኮሎኔልና ስድስት ጠባቂዎቹ ... በምሽግ ሰበራው የተገደሉ ሲሆን ቆስለው በኋላ የሞቱትና ሬሳቸው ያልተገኘው ቁጥራቸው አልታወቀም፡፡ እንደ አካባቢ ሰዎች የዐይን ምስክርነት ግን በአዲስ ዓለም ምሽግ ውስጥ ይርመሰመሱ ከነበሩት ጣሊያኖች ውስጥ መትረፍና ማምለጥ የቻሉት ሰባት ብቻ ናቸው፡፡

ይህ ጥበብ የተላበሰ፣ የአመራር ብቃት የታየበት፣ በተፈለገበት ሰዓት ተጀምሮ በታሰበው ወቅት የተጠናቀቀ ምሽግ ሰበራ አብቅቶ አርበኞች በድል ወደመጡበት ተመለሱ፡፡ በጉዞ ወቅት አምስትና ከዚያም በላይ ጠመንጃ ተሸክመው ሲጓዙ ቁስለኞችን መሸከም ግድ በመሆኑ የአርበኞቹ መሪ ጀግናው ጃገማ ሳይቀር የሚሸከሙትን አርበኞች ጠመንጃ ተቀብሎ ከራሱ ጠመንጃዎች ጋር በመሸከም ይረዳ ነበር፡፡

በውድቅት ሌሊት ከአዲስ ዓለም በመነሳት ሜጫ ወደሚገኘው ጀምጀም ለመድረስ ሲኳትን ያደረው አርበኛ ሲነጋጋ ሲል ያሰበው ቦታ ደረሰ፡፡ የተዘረፈውም መሳሪያ ዋርካ ዛፍ ስር ተከመረና ትንሽ ረፍት ሆነ፡፡ ከዚያ እያንዳንዱ ጀሌ ከዘረፋቸው ጠመንጃዎች ውስጥ ሶስቱን ጠመንጃዎች ለራሱ እንዲወስድና አንዱን ጠመንጃ ሸጦ ጥይት እንዲገዛ፤ ወደፊት ለግዳጅ ሲጠራ ደግሞ አንድ ሌላ ሰው በመጨመር ሁለት ራስ ሆኖ እንዲመጣ በመስማማት የኋላ ደጀን አዘጋጀ፡፡ ጀግናው ጃገማ የእለቱን ብቻ ሳይሆን የእመቱን ጥቅሙን ያስጠበቀ ውሳኔ አስተላልፎ በማዘጋጀት ልምድና ችሎታ የነበራቸውንና ከእስር የተፈቱትን ከአርበኞቹ ጋር በመቀላቀል ወደ ጉድባው ተመለሰ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ አርበኛ አስራ ሁለት አጭር መውዜር ጠመንጃ ከአዲስ ዓለም ተሸክሞ ጀምጀም ድረስ መጥቶ ለጃገማ አስረከበ፡፡ ያ አርበኛ ለአንድ ወር ደም እያስቀመጠው ታመመ፡፡ ጃገማም አንድም ጠመንጃ ሳይቀንስ ተሸክሞ ያመጣውን መሳሪያ መረቀለት፡፡ ያ አርበኛ በሰጠው ምስክርነት ታዲያ አርበኞች በመጡበት መንገድ ሲመጣ አልፎ አልፎ የወዳደቀ ጠመንጃ ማየቱንና የኢጣሊያ ጦር በዚያ እየተመራ ጃገማን





እንዳይከታተል እየሰወረ እንደመጣ አስረዳ፡፡ ይህን ሁሉ ለምን እንዳደረገ ጃገማ ሲጠይቀው - «በአርበኞች ድርጊት ረካሁ፤ በወንድሞቼ ኮራሁባችሁ ... እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም ረካ! ኮራ! የእኔ ልዩነት እገዛ ማድረግ መፈለጌ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ መሳሪያዎቹን እየተሸከምኩ ቀን ተደብቄ እየዋልሁ፤ ማታ ማታ ስጓዝ ደግሞ ስለ ጃገማና አርበኞች እያሰብሁ ስለምጓዝ በክብደት ብዛት የሚንቀጠቀጠውን ወገቤን ህመም አልሰማውም ነበር» አለው፡፡

ከአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ በኋላ የአርበኞች የጠመንጃ ብዛት ሶስት ሺህ ደረሰ፡፡ የውስጥ አርበኛዋ የሸዋረገድ ገድሌ ዕቅድ ሰምሮ፣ ቤትና ቀያቸውን ለቀው ድንጋይ ትራስ አድርገው በዱር በገደሉ ከጠላት ጋር የሚዋደቁት አርበኞች በዚያ እገዛ ሞራላቸው ጠንክሮ፣ ክንዳቸው ፈርጥሞ የጠላትን ንቀት አሽቀንጥረው ጥለው ወደ አሸናፊነት የሚወስዳቸውን እቀበት ለመውጣት ጉዞ ጀመሩ ... ለጠላት ጦርም የማይጨበጡ ረመጥ እሳት ሆኑበት፡፡

## ፱

# የፍጻሜው አጥቢያ - ከጋጂ አዲስ አለም

ፈረንሳይና እንግሊዝ ኢጣሊያ ከጀርመን ጎን እንዳትሰለፍ በመከላከል ብዙ ቢደክሙም የኋላ ኋላ ግን የተፈራው ደርሶ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር ኢጣሊያ ከጀርመን ጎን ተሰለፈች። በአንደኛው የዓለም ጦርነት የነበረውም የሃይል አሰላለፍ ተቀየረ። በዚህ የኢጣሊያ ውሳኔ ከእንግሊዝ ጋር የአበሩት አገሮች የጀርመንንና የኢጣሊያን ጉልበት ለማድከምና ለመመከት ከባድ ፈተና ላይ ወደቁ። በኋላም የእንግሊዝ ጦር በምስራቅ አፍሪካ የሚገኘ ውን የኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ የማስወጣት ሀላፊነት ወሰደች።

የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት የሃይል አሰላለፍ የቀየረው ሌላው ጉዳይ ደግሞ አሜሪካ የአቶሚክ ቦምብ ባለቤት መሆኗ ነው። እውቁ ሳይንቲስት አንስታይን በአንደኛው የዓለም ጦርነት በፕሮፌሰርነት በርሊን ነበር። ጀርመን የጀመረችውንም ጦርነት እየተቃወመ በፀረ ጦርነት ሰልፎች ተካፍሏል። አንስታይን የአይሁድ ዘር ነው። በጽዮናዊነት ባያምንም ፀረ ጽዮናውያን የያዙትን ፅንፈኛ አቋም ግን ይቃወም ነበር። በዚህ ምክንያት የአንስታይን ፅንሰ ሃሳቦች ትልቅ ጥቃት ተከፈተባቸው፤ የፀረ አንስታይን ተቋምም ተመሰረተ።

ሂትለር በ1925 ዓ.ም ስልጣን ላይ ሲወጣ አሜሪካ የነበረው አንስታይን አልመለስም ብሎ ወሰነ። የናዚ ሚሊሻዎች ቤቱን በረበሩት፤ «አንስታይን ከእንግዲህ ተመልሶ ጀርመንን አይረግጥም» በሚል በበርሊን ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ሆኖ ወጣ። አንስታይን የጀርመን ሳይንቲስቶች ውስው ቢያድሩም የአቶሚክ ቦምብ መስራት መቻላቸውንና በናዚዎች እጅ ከገባ የሚደርሰውን ጥፋት በማሰብ አሜሪካ ቀድማ የኒኩሌየር ቦምብ እንድትሰራ ለሩዝቬልት ሃሳብ አቀረበ ... አሜሪካ ቀድማ የአቶሚክ ቦምብ ባለቤት ሆነች።

ጃፓን ፐርል ሃርበር ላይ የጫረችውን የጦርነት እሳት አሜሪካ መላ ሃብቷንና ዕውቀቷን በመጠቀም እንድትመክት ሩዝቬልት ቀሰቀሱ። አሜሪካ በጃፓን ላይ ጥቃት ሰነዘረች። የአክሲስ ጦር አጋሮቿ ለጃፓን በመወገን አሜሪካ ላይ ጦርነት አወጁ፤ሁለቱ የጃፓን ከተሞች በአቶሚክ ቦምብ ተመቱ።

* * *





በ1931 ዓ.ም የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተፋፍሞ እንደ መሬት ርደት ማዕበሉ ምድርን አንቀጠቀጣት። በዚያ የጦርነት ማዕበል ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ እንዳሉት ታሪክና ፈጣሪ ምስክር መሆን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ሰጭ ሆነው፥ የነበረው እንዳልነበረ ሆነ፤ የሃይል አሰላለፍ ምንቅርቅሩ ወጣ። በጥቅም አፍ ለአፍ ገጥመው እውነትን በመካድና «ጉልበት ሃይል ነው» በማለት አከከኝ ልከክህ ሲባባሉ የነበሩት እንግሊዝና ፈረንሳይ ከወዳጃቸው ኢጣሊያ ጋር የነበራቸው የእፍ እፍ ፍቅር አብቅቶ በፍፁም ጠላትነት ካብ ለካብ የሚተያዩ፣ አንዱ ሌላውን ለመንደፍ የሚጠባበቁ እባቦች ሆኑ።

በሰኔ ወር 1932 ዓ.ም ፈረንሳይ በሰፈረችው ቁና ተሰፍራ ተወረረች። ወረራ የፈፀመችባትን ናዚ ጀርመንን ትታገል ዘንድ ጄኔራል ደጎል ለፈረንሳይ ህዝብ ብሔራዊ የመከላከል ጦርነት እንዲጀመር አዋጅ አወጀ። በ1933 ዓ.ም ደግሞ ጀርመን፣ ኢጣሊያና አልባንያ ዩጎዝላቪያን ወርረው አገሪቷን እንደ ጣቃ ለሁለት ሰነጠቋትና የእነሱን ፍልስፍና አራማጅ የሆነ አሻንጉሊት የክሮዌሽያ መንግስት መሰረቱ።

የኢጣሊያ ወራሪ አብሮ የኖረውን ኢትዮጵያዊ በዘር ከፋፍሎ በማጋጨት ለማጨፋጨፍ በተጠቀመው ቀመርና ስሌት በክሮዌሽያ ሰፍረው በነበሩት ሁለት ሚሊዮን በሚጠጉ ሰርቢያውያንም ላይ ሴራ ተሸርቦ እንዲጨፈጨፉና ወደ ማጎሪያ ካምፖች እንዲወረወሩ የወቅቱ የአልባንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሙስጠፋ ኩሩጃ ለኮሶቦ የኢጣሊያ ወራሪ ሃይሎች ሃሳብ አቀረቡ። የቤት ስራቸው የተሰራላቸው የኢጣሊያ ወራሪዎችም ግጭቱን የሚያስጀምረውን ሽጉጥ ተኮሱ ... ወዲያው የዘር ማጥፋቱ ጭፍጨፋ ተከናወነ። በዚያ ጭፍጨፋም ከአስር ሺህ በላይ ሰርቢያውያን ሞቱ፤ ከሰማንያ እስከ መቶ ሺህ የሚደርሱት ደግሞ ወደ ማጎሪያ ካምፖች ተወረወሩ ...

ይህ ጭፍጨፋ ሰርቢያውያንን ወረራና ጭፍጨፋውን አምርረው እንዲቃወሙና በጆሴፕ ብሮዝ ቲቶ ወደሚመራው የአርበኞች እንቅስቃሴ እንዲቀላቀሉ አደረጋቸው። በቲቶ የሚመሩት አርበኞች ኮሶቮን ነፃ ለማውጣት ከ1933 ዓ.ም እስከ 1936 ዓ.ም ድረስ ፅኑ ትግል አድርገው ኮሶቮ ነፃነቷን ተቀዳጀች።

* * *

ታሪክና ፈጣሪ እንደሚመሰክሩት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረው በ1931 ዓ.ም በተደረገው የቼኮዝሎቫኪያና ፖላንድ ግጭት ይሁን እንጂ በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ስምምነቷን ጥሳ፣ የሊግ ኦፍ ኔሽንስን ህግ ረግጣ ኢትዮጵያ ላይ ባደረገችው ወረራ ጦርነቱ ተጸንሷል ማለት ይቻላል።

እንግሊዝ ውስጥ ባዝ ከተማ ቤት ገዝተው መኖር የጀመሩት የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ እንግሊዝ ለኢጣሊያ ቅኝ ገዥነት እውቅና በመስጠቷ እንደ ተራ ስደተኛ ተቆጠሩ እንጂ በኦፊሴል ከእንግሊዝ ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት አልፈፀሙም። ቀድሞውኑም አቀባበል አልተደረገላቸውም። ለደህንነታቸው በሚል ሽፋንም ንጉሰ ነገስቱ በእንግሊዝም ሆነ ከእንግሊዝ ውጭ የዲፕሎማሲ ተግባር አልፈፀሙም። የእሳቸው እንግሊዝ አገር በስደት መቀመጥና የአገራቸውን ማህተም መያዝ ግን «ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ሁለተኛዋ ኤምፓየር ሆናለች» የሚለውን የኢጣሊያ ፋሽስቶች ልፈፋ ተአማኒ እንዳይሆን እንቅፋት ጋረጠ። ይህም ለእነ ሎሬንስ፣ ሲልቪያ ፓንክረስት፣ ሃኪም ወርቅነህ (ዶክተር ማርቲን)፣ መላኩ በያን፣ ወዘተ. አጋዥ ሃይል በመፍጠር የአውሮፓና የአሜሪካ ህዝብ የኢጣሊያን ልፈፋ ከጉራ ያልዘለለ ባዶ ጩኸት አደረገው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የአርበኝነት ትግል እየተጠናከረ የኢጣሊያን ፋሽስት ሰራዊት ከመንገድ የማይወጣ እና በጥቂት ከተሞች ብቻ ምሽግ ውስጥ አድፍጦ የሚውል ሰራዊት ማድረጉ የውጭውን ዲፕሎማሲያዊ ትግል አፋፋመው። እንደተፈራውም ወረራው አፍሪካዊ አሜሪካውያንን፣ የካረቢያን አገሮችንና በተለይም አፍሪካውያንን ማስቆጣቱ አገራዊና አለማቀፋዊ የተቃውሞ ትግል ላይ ትልቅ ስበትን ፈጠረ። ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴም ከሚያምኗቸው የአርበኞች መሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ እንግሊዝ አገር ሆነውም ሹመት በማፅደቅ የድል ጎህ ሊቀድ እንደተቃረበ ወጋገን ማየት ጀመሩ ... ኢትዮጵያን የሚረዱ፣ ለኢትዮጵያ የሚከራከሩ፣ የሚታገሉ ሁሉ በተስፋ ተጠናከሩ።

በተለይ ደግሞ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሃይል አሰላለፍ ሲለወጥ ፈረንሳይ ሉዓላዊነቷ በጀርመን ተደፍሮ በኢትዮጵያ ቁስል ላይ የከተተችው እንጨት የፈጠረውን ህመምና ስቃይ በራሷ ደርሶ አየችው። እ.አ.አ. በ1940 የፈረንሳይ ህዝብ ጥቃትን ለመከላከል በየአለበትና በሚችለው አቅም የአርበኝነት ትግል በአዋጅ ጀመረ። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያና በመሪዋ ላይ ፊት ያዞሩና በራቸውን ጠርቅመው «የኢትዮጵያን ጉዳይ በሩቁ» ያሉት





እንግሊዞች ፖሊሲያቸውን ለወጡ። አፄ ኃይለ ስላሴ እንዳሉትም እግዚአብሔርና ታሪክ የየራሳቸውን ፍርድ ለመስጠት ሳይዘገዩ የሃይል አሰላለፉ እየተቀየረ፣ የተቧደነው እየተጣላ፣ አቅመቢሱ በተዓምር እየተጠናከረ ጣሊያኖች «አዲሱን ኤምፓየራችንን የሚያናውጥ ሃይል በምድር ላይ ሊኖር ከቶ አይችልም» ያሉት ትዕቢት በጥቂት ዓመታት እንደ ጤዛ ረገፈ። የአርባ ዓመት ዝግጅት ውጤት የሆነው የሶስት መቶ በምብ ጣይ አውሮፕላን፣ የከባድ መሳሪያና የመርዝ ጢስ፣ አምስት መቶ ሺ የሚገመት በዘመናዊ ስልት የሰለጠነ ሰራዊት መሰናዶ... እንደ እንቧይ ካብ ተንዶ በእግዚአብሔርና በታሪክ ፍርድ የነበረው እንዳልነበረ መሆን ጀመረ ...

የተባበሩት ሃያላን አባል የሆነችው እንግሊዝ ከጓደኝነትና አጋርነት በቅጽበት ወደ ጠላትነት የተቀየረችው ኢጣሊያ በርካታ ሰራዊት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳላት ታውቃለች። ያን ሃይል መምታት የኢጣሊያን ጉልበት በእጅጉ ይጎዳዋል ... ያ ሃይል ኢጣሊያ አርባ ዓመት ሙሉ የገነባችው ነው። ያን ሃይል በአፍሪካ አሸዋ፣ በአፍሪካ ደንና ሸንተረር፣ በኢትዮጵያ አርበኞች እርዳታና ከቅኝ ግዛቶቻቸው በሚላክ ሰራዊታቸው መደምሰስና መበተን ታላቅ ወታደራዊ ስልት መሆኑን የእንግሊዝ የወታደራዊ ሳይንስ ጠበብቶች አመኑበት።

በዚህ ስልት እንግሊዛውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኢጣሊያ ሰራዊት መደምሰስ ከቻሉ ድላቸው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ የመምታት ያህል ፋይዳ እንዳለው አስተዋሉት። የኢጣሊያን ሰራዊት በእንግሊዝ ወታደሮች፣ በቅኝ ተገዢ ወታደሮቻቸውና በኢትዮጵያውያን አርበኞች ትብብር ብዙ እንግሊዛውያን ሳይሰዉ መደምሰስ ከቻሉ «ኢትዮጵያ ከጠላት ተዋግተን ያገኘናት አገር ናት» በማለት ከኢጣሊያ ወረራ ነፃ የወጣች እንጂ «ነፃ ሉዓላዊ አገር ያልሆነች» አገር አድርጎ ለመፈረጅ ይመቻቸዋል። በዚህም ለዘመናት በምስጢር ጓዳቸው ውስጥ አስቀምጠውት የነበረው ኢትዮጵያን ካለ ጦርነት ቅኝ ተገዥ የማድረጊያ ህልማቸው እውን እንደሚሆን ተስፋ አደረጉ። ይህ ደግሞ ከህንድ፣ ከሱዳን፣ ከናይጀሪያና ከደቡብ አፍሪካ የሚያሰልፏቸው ተዋጊዎች «ኢትዮጵያውያን ነፃ እንደወጡት እኛም ...» ብለው ሊያስቡት የሚችሉትን ተስፋ ጨለማ እንዲውጠው የሚያደርግ እንደሚሆን ተማመኑ።

ስለዚህ በህዳር ወር 1933 ዓ.ም. ግዳጃቸውን ለመወጣት ዝግጁ የነበሩት እንግሊዞች ይህን ጥቃት ለመፈፀም በሁለት ነገር ላይ ትኩረት አደረጉ። የመጀመሪያው የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጉዳይ ነበር። የእንግሊዙ ዊንስተን ቸርችል ንጉሰ ነገስቱን አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ከእንግሊዝ ሰራዊት ጋር በመሆን ህዝባቸውን አስተባብረው ትግል በማድረግ የጋራ

ጠላታቸው የሆነችውን የፋሽስት ኢጣሊያን ሰራዊት እንዲደመስሱ ወደ ሱዳን ላኳቸው፡፡ ሱዳን ከደረሱ በኋላ ግን ጉዞው ቆመ፤ ግንኙነቱም ላላ፡፡ ንጉሰ ነገስቱ ማብራሪያ ቢጠይቁ፣ ቴሌግራም ቢልኩ ... መንፈስ የሚያረጋጋ መልስ አጡ፡፡ ከዚያ ቀስ በቀስ ምስጢሩ ግልፅ መሆን ጀመረ፡፡ ነገር ግን እንዴ ተስፋቸው በእንግሊዞች የሚወሰን ሆኗልና ንጉሰ ነገስቱ «ቻለው ሆዴ» ብለው ለስድስት ወራት ውሳኔ በሌለው ግዞት ካርቱም ውስጥ ቆዩ፡፡

እንግሊዞችም በበኩላቸው ኢትዮጵያውያንን ሊያግባባ የሚችል መላ እመፈለጉ ላይ አተኮሩ፡፡ በዚህም መሰረት ንጉሰ ነገስቱ በህዝባቸው መወደድ አለመወደዳቸውን ማወቅ፣ የደጋፊና ተቃዋሚያቸውን ቁጥር መረዳት ላይ ቢሰለፉም በጥንቃቄ የያዙት እቅድ እንዳይበላሽባቸው ስለፈሩ ትክክለኛው ጊዜ እስኪመጣ በርቀት ያገኙት የነበረውን መረጃ ወደ ጎን ገፋ አደረጉት፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ህዝቦች ሊቀበሉት ይችላሉ ያሉትን መላ ነደፉና ሁለት እንግሊዛውያን ከሱዳን ወደ ግብጽ ሄደው ከጄኔራል ዌብል ጋር ሸንጎ ተቀመጡ፡፡

«ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ አገር በመሆኗ ወደ ሶስት መንግስታት ትከፈልና ነፃ ትውጣ፡፡ ያ ደግሞ ኢትዮጵያን ከጠላት ተዋግታ ያገኘቻትን እንግሊዝን ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም፥ አንደኛ የኢትዮጵያ ጠንካራ ሃይል እንግሊዝን አይፈታተናትም፤ ሁለተኛ፥ አዲስ የሚፈጠሩት ሶስት መንግስታት የእንግሊዝን ፍቅርና ትብብር ለማግኘት ስለሚንበረከኩ እንግሊዝ ጥቅሟን እያስከበረች በመካከላቸው ግጭት ሲፈጠር አስታራቂ ትሆናለች፤ ሶስተኛ፥ ከሶስቱ መንግስታት አንዱ ችግር ቢፈጥር እንኳን በሁለቱ እያስመታን ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ በቅኝ ግዛት መዳፋችን እናስገባለን» ብለው መከሩ፡፡ ጄኔራል ዌብል በኤርስክንና ብሮክልኸርስት ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ተስማማ፡፡

ይህ ፖለቲካዊ ዘመቻ ከመፈፀሙ በፊት ግን እንግሊዛዊው ኮሎኔል ዊንጌት ከቀዳማዊ ሃይለስላሴ ጋር ባደረገው ውይይትና በሰጣቸው ምክር ንጉሰ ነገስቱ «ወደ አገሬ ወደ ኢትዮጵያ በቀጥታና በአስቸኳይ እንድገባ ይፈቀድልኝ» የሚል ማመልከቻ ፃፉ፡፡ ቸርችልም «እኔ እንደማስበው ንጉሰ ነገስቱን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚያስችሉ ጥረቶች ሁሉ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በእርግጥ በዚህ ውሳኔ ከኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔረሰቦች አካባቢ የሚነሱ ተቃውሞዎች ይኖሩ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የንጉሰ ነገስቱ ወደ አገራቸው መግባት በኢጣሊያኖች ላይ ያለውን ተቃውሞና አመፅ በማፋፋም ህዝቡን ለድል ያበቃዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሊቢያ ላይ ከምናገኘው ድል ጋር ይቀናጃል፡፡ ስለዚህ በእኔ እምነት ንጉሰ ነገስቱ ወደ አገራቸው መግባት





አለባቸው፡፡ በመሆኑም ለንጉሰ ነገስቱ ደብዳቤ የሚስማማ መልስ ለመላክ የሚያስችለኝ ጽሑፍ ቢዘጋጅልኝ እደሰታለሁ» በማለት የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበረው አንቶኒ ኤድንና ለፊልድ ማርሻል ኢዝመይ ማስታወሻ ፃፉ፡፡

ሚስተር ኤድን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ማስታወሻ እንዳዩ ለጉዳዩ ቅርብ ያሏቸውን ሁሉ አማከሩ፡፡ በመጨረሻም ሃላፊነታቸውን ለመወጣት የኢትዮጵያውን ንጉሰ ነገስት እንዲህ በችኮላ ወደ አገራቸው መመለስ ለህይወታቸው ያሰጋል የሚል አንድምታ ያለው ማሳሰቢያ እንዲያቀርቡ አደረጋቸው፡፡

«ንጉሰ ነገስቱ ወደ አገራቸው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለ ራሳቸው ህይወትም ከማንም የተሻለ ራሳቸው እንደሚያውቁ ሁላችንም ልንገምት ይገባናል» አሉና ቸርችል ዜማው ያማረ፣ ውስጡ ግን ክረት የነበረው ጥበበኛ ውሳኔ አስተላለፉ፡፡ በዚህም ቸርችል መኮንኖቻቸው ኢትዮጵያን ለሶስት ሰንጥቀው የመያዝ እቅዳቸው እቅጣጫው እንዲቀየር አደረጉት፡፡ ይህ ውሳኔ ግን ለጄኔራል ዌብልን፣ ለፊልፕ ሚችል፣ ለሞሪስ ኤስ ላሽና ለመሳሰሉት አልተዋጠላቸውም፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት በህዝቡ ያላቸው ተቀባይነት እናላ፣ ተቃዋሚዎቻቸውም ብዙ ናቸው ብለው ያስቡ ስለነበር በእንግሊዝና በኢትዮጵያ አርበኞች የጦርነት ስልት የእላቸው አስተዋጽኦ እናላ ሊሆንና የሚነዛባቸው ተቃውሞ በእንግሊዝ ጦር ላይ ያልታሰበ እክል ሊፈጥር ይችላል የሚል ስጋት ነበር፡፡ ሁለተኛም የእንግሊዝ መንግስት በኦፊሴል ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ተቀብላለች፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የኢጣሊያ ጦር በእንግሊዝ ጦር ቢሸነፍም ኢትዮጵያ በኢጣሊያ አስተዳደር ስር መሆኗ የሚያከትመው ሁለቱ አገሮች በሚያደርጉት የሰላም ስምምነት ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእንግሊዝ ጦር የጠላቱን የኢጣሊያን ጦር እስኪያሸንፍ ድረስ ኢትዮጵያን «ነፃ» ያደርጋል እንጂ ነፃ አገር ስለማያደርጋት በእንግሊዝ ስር ያለች የጠላት አገር በመሆን በእንግሊዝ ወታደራዊና ፖለቲካዊ አስተዳደር ስር ሆና ትቆያለች የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

ለዚያ እምነታቸው መነሻ ምክንያቱ ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አገሮች ከኬንያ፣ ከዩጋንዳና ከሱዳን ጋር አንድ ላይ አቀላቅለው ለማስተዳደር የነበራቸው ህልም ነበር፡፡ ሚችል የኡጋንዳ፣ ላሽ ደግሞ የሱዳን አስተዳዳሪዎች በመሆናቸው ለኢትዮጵያ አስተዳደር ተመሳሳይ የሆነ እቅድ ነበራቸው፡፡ ይህንም ህልማቸውን እውን ለማድረግ የኢትዮጵያ ጦር ሃይል

በእንግሊዛውያን እንዲመራና እንግሊዝኛንም መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን ለማድረግ ተዘጋጁ።

ንጉስ ነገስቱም እግረ-መንገዳቸውን ሱዳን የነበሩ ስደተኞችን አሰባስበው ወታደራዊ ስልጠና እንዲያገኙ አደረጉ። በሌላ በኩል ደግሞ ደጃዝማች ከበደ ተሰማን ከእስራኤል አስመጥተው ለአርበኞች እና ለህዝቡ «ጃንሆይ መንገድ ላይ ናቸው» እንዲሉ ወደ ኢትዮጵያ ላኳቸው ...

* * *

መጋቢት 21 ቀን 1933 ዓ.ም ዋቅጅራ ሰርዳ ፈረሱን አረፋ እያስደፈቀ ከጭልሞ ምሽግ ተነስቶ ወደ ዮብዶ ጋለበ። ሰማዩ አልፎ አልፎ ቁጥር ቁጥር ካሉት ስስ ዳመናዎች በስተቀር ጥርት ያለ ሰማያዊ ነው። ከርቀት የገበሬዎች፣ የአዕዋፍና የወንዝ ድምፅ ይሰማል።

«ጃገማ - አባ ዳማ!» አለ፥ ዋቅጅራ - ከፈረሱ እየወረደ።

«ዋቅጅራ ... ምነው?» ጃገማ ጠየቀ።

«ጣሊያኖች ... ኡሁ ... ጣሊያኖች ... ኡሁ ... የእቃ ቦርሳቸውን እያሳሰሩ ነው» አለ - ቁና ቁና እየተነፈሰ።

«ለምን?» አለ ጃገማ በፅሞና።

«እንጃ! ሁሉም ግን እቃቸውን ይጠፍራሉ» አለ ዋቅጅራ።

«እሽ እመጣለሁ ዋቅጅራ፤ እስክመጣ ለውጥ ካለ ላክብኝ፤ አሁን ግን ቶሎ ሂድ ...» አለ ጃገማ። ዋቅጅራ ፈረሱ ላይ ዘሎ ወጥቶ ተፈተለከ...

* * *

መጋቢት 22 ቀን 1933 ዓ.ም የበጋው መብረቅ ጭልሞን ከቦ ተኩስ ከፈተ።

«ማነህ?» ብሎ አስጠየቀ የጦር አዛዡ - በመልዕክተኛ።

«ጃገማ ነኝ» ብሎ መለሰ፥ ጃገማ አባ ዳማ።

«ለምን ተኩስ ከፈትህብን?» እንደገና ጠየቀ የጦር አዛዡ።

«... እጃችሁን ስጡኝ፤ አለበለዚያ አንላቀቅም» ብሎ መለሰ ጃገማ።

«ተኩሱን አስቁምና አባ ዶዮን አስጠራቸው፤ ከዚያ እሳቸው ባሉበት ተደራድረን እጅ እንሰጣለን» አለ የጦር አዛዡ።

* * *





መጋቢት 23 ቀን 1933 ዓ.ም አባ ዶዮና ጃገማ ጭልሞ ከሚገኘው የኢጣሊያ ካምፕ ገብተው ከኢጣሊያው ወራሪ ጦር መሪዎች ጋር ተደራደሩ። ከድርድሩ በኋላ እነ ጃገማ አገር ሰላም ብለው ከተማ ገብተው፤

«አለ ነገር! አለ ነገር
ዘንድሮ አለ ነገር ...
መቸም ሙተን፣ ሙተን
አንገት ደፍተን አንቀር ... ጎራው፣ ጃሎ» እያሉ መሳሪያቸውን እየነቀነቁ፣ ትከሻቸውን እየወዘወዙ፣ እያቅራሩና እየፎከሩ ሲዝናኑ ከሌሊቱ አስር ሰዓት የጭልሞ ምሽግ አዛዦችና ወታደሮች በአውቶብላንዲ ታንክ እቃቸውን ጭነው ሊያመልጡ ሲሉ የታንኩን ድምፅ ሰሙ። ወኔያቸው ጢም ያለው አርበኞች ከየነበሩበት ተጠራርተው ተከተሏቸው። ጥቂት የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ አምቦ ሸሽተው ሲያመልጡ ቀሪዎቹ ደግሞ ጊንጪ ከነበረው የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ጋር ተቀላቅለው የአርበኞችን ጥቃት በመከላከል ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት ድረስ ተዋጉ። በመጨረሻ የአርበኞች ጥቃት እየከረረ፣ የወራሪዎች ሃይል ደግሞ እየተፍረከረከ ሄደና አስራ ሶስት የኢጣሊያ ወታደሮችና አንድ ሺ አምስት መቶ ባንዳዎች እጃቸውን ወደ ላይ እያነሱ በወጣቱ የአርበኞች መሪ ጦር መጋቢት 24 ቀን 1933 ዓ.ም ተማረኩ። ከዚያም ጊንጪ በአርበኞች እጅ ገባች።

ጃገማ አባ ዳማ ጊንጪን ከተቆጣጠረ በኋላ አርበኞቹ ጊዜ ሳያባክኑና ጣሊያኖች መረጃ ሳይለዋወጡ አንድ ሺ አምስት መቶ እግረኛና ስምንት መቶ ፈረሰኞች ወደሚገኙበት የኢጣሊያ ወራሪ ጦር የሐሮታ ምሽግ እንዲገሰግሱ አዘዘ። የሐሮታ ምሽግ በአካባቢው ከነበሩት ምሽጎች ውስጥ የኢጣሊያ ወራሪ ጦር የሚተማመንበትና ጊንጪን፣ ጋጂን፣ ጀልዱን፣ ግንደ በረትን ለመቆጣጠር የተደራጀ ነበር።

አርበኞች ምሽቱን ሐሮታ በመድረስ የኢጣሊያን ምሽግ በእሩምታ ተኩስ እያስደነበሩ ወራሪዎችን ሲያሽብሯቸው አደሩ። መጋቢት 25 ቀን 1933 ዓ.ም ቀኑን ሙሉ ውጊያው ቀጥሎ ዋለ። የኢጣሊያ ጦር መሪዎች አቅማቸው እየደከመ መሆኑን ቢረዱም ያለ የሌለ ሃይላቸውን በመጠቀም ተከላከሉ። መጋቢት 26 ቀን 1933 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር የሚተማመንበት የሐሮታ ምሽግ ከአርበኞች በተሰነዘረ አዲስ ጥቃት እንደ ጌሾ ተወቅጦ ዱቄት ሆነ። ምሽጉ ሲናድ የኢጣሊያ ጦር ሰራዊት አንዱ በአንዱ ላይ እየተረማመደ እግሬ አውጭኝ ብሎ ነቅሎ ሸሸ። ድል የጠማቸው አርበኞች የሚሸሸውን የኢጣሊያ ጦር እያባረሩ ተከተሉት ...

ከሐሮታ የነቀለው የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ሽሽቱን በመቀጠል ወሎንኮሚን ሊያልፍ ሲል ቀድመው የአደፈጡት አርበኞች ውጊያ በመክፈት አቆሙት። አማራጭ ያጣውና ከፊትና ከኋላ በአርበኞች ጦር የተወጠረው የኢጣሊያ ጦር በፈረስና በበቅሎ የጫነውን መሳሪያ እያወረደ ውጊያ ጀመረ። የኢጣሊያ መትረየሶች አፋቸውን ከፍተው ጥይት መትፋት ቀጠሉ። በዚህ ወቅት ጀግናው የአርበኞች መሪ ጃገማ አባ ዳማ ሽምጥ እየጋለበ፣ ከኋላው አንድ ባለ በቅሎ እየተከተለው ቱሉ በቾ ከተባለው ኮረብታ ላይ ወጣ።

የኢጣሊያና የአርበኞች ጦር በቅርብ እርቀት ገበያ ውስጥ እንደሚገበያይ ገበያተኛ ተቀላቅሏል። ጃገማ ባለ በቅሎውን ከኋላ ጠብቀኝ ብሎ ሁለት ጊዜ ተኮሰ። የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ወታደሮች ደግሞ ከፊት ለፊት ገትረው ያቆሟቸውን አርበኞች አስነቅለው ለመሸሽ መሳሪያቸውን ሲጭኑ ጃገማ በከፈተው ተኩስ አርበኛውና የጠላት ጦር ተለየ። ጃገማ የኢጣሊያን ወታደሮችና መሳሪያ የጫኗቸውን ከብቶች ሲረፈርፋቸው የጠላት ጦር የያዘውን እየጣለ ሸሸ። አርበኞችም ማባረራቸውን ቀጠሉ።

የጠላት ጦር ቀላ የተባለውን ወንዝ እንደተሻገረ አደብ ገዛ። ኮረብታ ላይ በመውጣትም በመትረየስና በቦምብ አርበኞችን አጠቃ። አርበኞች ጥቃቱን ለጊዜው መቋቋም ተስኗቸው ወደኋላ ሲያፈገፍጉ ጃገማ አባ ዳማ ትይዩ ወደነበረው ኮረብታ ላይ ወጥቶ በጦር ሜዳ መነፅሩ ሲያይ የእሱ ጦር እየሸሸ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተቀላቅሎ አየው። በመትረየሱ ሁለት ጊዜ አሳልፎ ሲተኩስ ቀይ ኮፍያ ያደረገው የጠላት ጦር ተለየ። ጃገማ መትረየሱን እያንጣጣ ሲተኩስ የጠላት የውሃና ሌጅራ መትረየሶች አፋቸው ተዘጋ። የውሃና ሌጅራ መትረየስ ጠምደው ሲጨፈጭፉ የነበሩትም ነቅለው ሽሽት ጀመሩ፤ የኢጣሊያ ጦር ሃይል አከርካሪም ተሰበረ። በጠላት ጦር ላይ በደረሰው ጥቃት ምክንያት ፋታ ያገኙት አርበኞች መሸሻቸውን በመተው እንደገና በተከፈተላቸው መስመር እያለፉ የጠላትን ጦር ማራወጣቸውን ቀጠሉ።

በዚያ ፈታኝ ጦርነት የጃገማ አባ ዳማ ጦር ከሐሮታ አምልጦ ወደ አዲስ ዓለም የሸሸውን የኢጣሊያ ጦር በማባረር ስላጠቃው የወሊሶን መንገድ አቋርጠው ወደ ጅማ በመሄድ ካመለጡት ሰላሳ የኢጣሊያ ወታደሮች በስተቀር ሌላው የጠላት ጦር እንደ አሸን ረገፈ፤ ቀሪውም ተማረከና የአርበኞች ጦር የወራሪ ጠላትን ጦር የሽንፈት ፅዋ ግቶ በአዲስ ድል ብዙም ፈተና ሳይገጥመው አዲስ ዓለም ገባ። ጃገማ አባ ዳማንና በእሱ የሚመሩትን አርበኞች ገድል በአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ወቅት የሚያውቀው የአዲስ



ዓለም ህዝብ አዲስ ድል እየተጎነጨ ወደ አዲስ ዓለም የገባውን ባለ ጎፈሬ አርበኛ እልልታውን እያቀለጠ፣ ጉሮ ወሸባየን እየዘፈነ ተቀበለው።

መጋቢት 27 ቀን 1933 ዓ.ም የአርበኞች ጦር ኃይል ወደ ሆለታ ተልኮ ሆለታ በአርበኞች ቁጥጥር ስር ሆነች። ጃገማ ከጊንጪ እስከ ሆለታ ያለውን ሰፊ ቦታ በቁጥጥሩ ስር እንዳዋለ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ጉዞውን ለመቀጠል ሲሰናዳ አዲስ አበባ በእንግሊዞች ጦር መያዟን ሰማ። ወዲያው ጀልዱ ላይ ምሽጉን አጠናክሮ፣ የውሃ ጉድጓድ ቆፍሮ አውጥቶ፣ ስንቁን አዘጋጅቶ ምሽጉን አላስደፍርም በማለቱ ዙሪያውን በአገሬው ህዝብና በአርበኞች ለስምንት ቀናት ተከቦ ሲዋጋ የሰነበተው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የሆነው መኮንን «ጃገማ ኬሎ ካልመጣ እዚሁ እናልቃለን እንጂ እጅ አንሰጥም» ብሏል ብለው ለጃገማ አባ ዳማ ነገሩት።

ጃገማ 'አንተ ካልመጣህ እጅ አንሰጥም' የሚለውን ሲሰማ አዲስ ዓለምና ሆለታ የሚገኙትን አርበኞች እንዲመራና እንዲያስተባብር ለጀግናው ጓደኛውና ቀኝ መሪው ለነበረው ለዘውዴ ጥላሁን ትዕዛዝ ሰጥቶ የበጋው መብረቅ መሪ ወደ ጀልዱ ተመለሰ። የኢጣሊያ ወራሪ ሰራዊት አዛዥ ለጃገማ ካልሆነ ለሌላ እጅ አንሰጥም ማለቱ አንድም ጀግና ወዳድ በመሆኑ እጅ መስጠቱ ካልቀረ ድንገት እየመጣ የኢጣሊያን ምሽግ ሲያንቀጠቅጥ ለነበረውና እንደ አሳ ያዝነው ሲሉ ተሙለጭልጮ ለሚያመልጣቸው ጃገማ እጅ በመስጠት አክብሮቱን ለመግለጽ፤ ሁለተኛ ደግሞ ጃገማ ከዚህ ቀደም ራሱ የማረከውን የኢጣሊያ ወታደር ጥሩ ምግብ እያበላ፣ ከጎኑ እያስተኛ የዓለም አቀፍ የምርኮኛ አያያዝ የሚጠይቀውን መልካም እንክብካቤ አድርጎ የለቀቀው መሆኑ ስለተሰማ እሱም ሆነ በስሩ የነበሩት የኢጣሊያ ወታደሮች የምርኮኝነት ክብራቸው እንዲጠበቅ በማሰብ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጃገማ፥ እንኳን ወዳጅ ጠላት የሚመርጠው ጀግና ነው። የጃገማ ስም በየሸጡ፣ በየሸንተረሩ፣ በየአምባውና በየተረተሩ እረኞችና ሴቶች እያሞካሹ የሚዘፍኑለት ሆነ። «ከሰውም ሰው አለ - እናቱ የወለደችው እለት ጀምሮ በሽልማት የሚንበሸበሽ፣ ጓደኞቹ ወደ እረኝነት ሲወጡ ወንበር ይዞ የሚፈርድ ... በጉርምስናው አርበኛ ሆኖ አምስት ዓመት ሙሉ የኢጣሊያን ወራሪ ሃይል እንደ እርጥብ ቆዳ ወጥሮ፣ እንደ ሳማ ለብልቦ፣ እንደ ጉንዳን ጉያ ገብቶ ቆንጥጦ ... ፍቅር የሚያገኝ፣ መልሶ የሚከበር የሰው ቀብራራ...» እየተባለ ከቅድመ አያቱ ከጎዳና ነሞ በላይ በጀግንነት እየተጠራ ስሙ ከጫፍ እጫፍ እንደ ብርጉድ ጢስ ናኘ።

ጃገማ አባ ዳማ ጀልዱ ሲደርስ አስራ ሶስት የኢጣሊያ ወታደሮችን፣ አምስት መቶ ከተለያየ አካባቢ የመጡ ባንዳዎችን በምርኮኝነት ይዞ ወደ ጊንጪ ተመለሰ። ብዙም ሳይቆይ አርበኞችና የአገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው መከሩና ጃጌ ጃገማን «አምስት ዓመታት ሙሉ መርተህ፣ ተዋግተህ ለድል አብቅተኸናልና እንድንሾምህ ፍቀድልን» አሉት። «የለም አልፈልግም፤ የምፈልገው ሆኗል፤ ስራዬ በስሜ ከተጠራ ይበቃኛል!» ብሎ አሻፈረኝ አለ። ህዝቡ ግን ስንኝ እየደረደረ ከዚህ ቀጥሎ እንደቀረበው ጀግናውን ማወደሱን ቀጠለ።

በሰማይ ቢበር ከታች ነው ወህኒ፣
መሪ እንዳይመስልህ አትመነው፣
　　ያን መሰሎኒ።
ጃገማ ይተኛል ከደኑ ገብቶ፣
ወፍ መስሎህ ድንጋይ አትወርውር ከቶ፤
　　ጃገማ ኬሎ፣
　　ይገባል ገሎ።
ተመፃዳቂ ባንዳ ጋ ወርዶ፣
ጠመንጃ ነጥቆ፣
　　ሸኘው በባዶ።
ጦር በጁ ይዞ ጃገማ ዘምቶ፣
ይኸው ጠመንጃ፣
　　መጣ ቀምቶ፣
ከሃዲ ባንዳን
　　አንገቱን ቀልቶ።
ጃገማ እንዴት ነህ
　　የጅባት መኻል ጀግናው አንበሣ፣
ንጉሥ ኦሮሞ
　　የበጋ መብረቅ ስምህ ሲነሣ።
ጃገማ ጀግናው
　　የድሀው ሰፈር ከለላ ጥላ፣
ልብሱ ያንበሳ ለምድ
　　በሰፈሩ ላይ ተንጎማለላ።
በትልቅ ምኞት ጃጌ ተገዶ፤
ገድሎ ሲመለስ በገደል ወርዶ፣
የኬሎ ነብር ለም እንደሰርዶ፣
ውብ አስተዳደግ ከውብ ተወልዶ።
ጫወታ ወዳድ ጉግስ ጋላቢ
ለወዳጅ ታዛዥ ለጠላት እምቢ።
አገር ቢወረር ምኞቱን ትቶ፣





ጠላት ሊጨርስ
　　ምሽግ መሽገ ጫካ ተኝቶ።
አደን ተወና
　　ባንዳውን ፈጀ ደም አደባይቶ፣
የመጣን ጣሊያን አስቀረው አሽቶ።
　　ሽንት ለቀቁ ባንዳዎች ፈሩ፣
ጅባት አሞሮች ጠግበው አደሩ።
　　ከየት ተገኘህ ከሰማይ ከምድር፣
ባንተ እንኩራ አንተ የጀግና ዘር፣
ያንተ እናት ትውለድ ዛሬም ትጨምር።
　　ተነስ ተሠራ ፀጉር ይነስነስ፣
ጃጌ ሹርባህ ወገብህ ይድረስ።
　　የጃጌ ፀጉር አቤት ርዝመቱ፣
እንደሱ ጀግና ጨምሪ እናቱ።
አባሮ ገዳይ የኬሎ ጀግና፣
አንተ የኔ ቆንጆ ሁሌም በድል ና፣
ብላ መረቀች የጃገማ እናት፣
ባለ ዳማ ፈረስ ልጇ እየታያት።
መሬት ተቃጥሏል የቀትር እሳት፣
　　ለየት ያለ ነው የጃገማ ምት።
መትረየስ እንዲሁ እንደ ቧንቧ ውሃ፣
　　እሳቱን ዘንቦ እሳት ሲተፋ፣
በሱ ቀረርቶ በሱ ፉከራ፣
　　ጣልያን አለቀ ድራሹ ጠፋ።
የሱ ጀግንነት የሱማ ወኔ፣
　　የለውም ወደር፣
ድራሹ ጠፋ ጣሊያን ከምድር።

* * *

ጃገማን ደጋለ ጪሳ ስንብራ ሴቴ ህንደርበተኒ
ሞሶሎኒን ሰሚ እረ ዱማ ሞቲ ሴቴ ህንአብደቲኒ
ጃገማ ኬሎ አጄሴ ገላ
አፍጀጁ ባንደ ቀዌን እሼ ላማ
ጃገማን ዱላ ኦፍከሌቴ ገሌ
ኤቦደን ቀዌ ብጅኤ ገሌ
ባንዳ እሼ ገንቱ ኮኬ እሼ ቀሌ
ጃገማ አካም ጀርተሬ ሌንጫ ጅባት ወለካ

ሰቦንቲቻ ኦሮሞ የእስ ሌሊ በከካ
ያጀገማ ጋዲሳ ጎደ ህዬሣ
ሜናገርማሚ ሁፌዱ ከሎ ሌንጫ
ሃዊን ጃገማ አዳሞ ቱሬ
አጀሴ ገሉፍ በቆፋ ቡኤ
ተጰ ፈርዳፍ ጀላታ ቱሬ
ቁረንሳ ኬሎ ጉድሰ ቶሌ
ብይ ዌረረምናን ሐዊእሳ ዲሴ
ፈረንጂ ፍጡፍ በሶና ጪሴ
ብኔንሳ ዲሴ በንዳ ጬጬብሴ
ጣሊያኒ ዱፍቴ አስእቲ ሀምብሴ
አላቲ ጅባት ኒቡልቼ ቁብሴ
ባንዳን ሶዳቴ ፍንጬን እሼ ቡስቴ
ሀምባን ረሰሳ ኤሳ እከ ቡቴ
ኢሾ ሌንጬኮ በገ ደሰቴ
ሀቲ ሲዱሴ ኦሶ ደበልቴ
አስበኢ ደሰንዱ ሹሩባ ሙዲ
ጉዱሩን ጀጌ ያገኡ ሙዲ
ርፌንስ ጃጌ ያዱሪናሳ
ሀገርሜ ደበሲ ኮርሜ አከሳ
ቀጠሌ ኬሎ ያአጀሳኮ
ምርጋን ነጋሲ ያበሬዳኮ
ጂቴ ኤብስቴ ሀቲ ጃገማ
ጉሉፋ ፈርዳ አባፈርዳ ደማ
ያ ሌንጫ ጅባት ግድርሳ ድራ
ህጅባችሳ ፍንንሳ ዲና
አባን ጃገማ ጬረ ቀቤሳ
ደቤስ ህንጅሩ ደሰ እሳ ኬሳ
ንዱ ቀበቴ ዱማ ቀዌሳ
ከንሳ ማል ህሙ ድረ ደላሣ
ከንሌንሴ ኬሎ፣ ከን ጠንቁሳ
ሰፊቱ ጉበተ ኢብዳ ሣፋ
ኬሳ ጃገማን ያሩኩቻ እሳ
መተረየሲን አባ ብሻኒ
እብዳ ሮባ ከራ አፋኒ
ጣሊያኒ ፊጤ ያጌረርሣ እሳ
ሀርያ ህንቀቡ ጀብኒ ኦኔሳ

* * *



በደቡብ የነበረው የእንግሊዝ ጦር በጦር አዛዡ በጄኔራል ካኒንግሃም እየተመራ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም አዲስ አበባን ከኢጣሊያ ነፃ በማውጣት ከተማዋን ተቆጣጠረ። የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ግን አሜድላ ላይ ባንዲራቸውን አውለብልበው ደብረ ማርቆስ ቢገቡም ከደረሱበት ከተማ እንዳይንቀሳቀሱ በእንግሊዝ የጦር አዛዦች ታዘዙ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ግን እንግሊዞች አዲስ አበባ የነበሩትን መኳንንትና ተደማጭነት አላቸው የተባሉትን ታዋቂ ሰዎች በራሳቸው በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ቤተመንግስት ሰበሰቧቸው። የእንግሊዝ ጦር አዛዥ ለተሰብሳቢዎቹ ቢያሻቸው አዲስ መሪ እንዲሾሙ፤ ካለበለዚያም የቀድሞውን መሪ እንዲያጸኑ ጠይቀው ምርጫው የተሰብሳቢዎች መሆኑን በማስረዳት የእሱ ድርሻ ተሰብሳቢዎቹ የወሰኑትን ውሳኔ በቀጥታ ለእንግሊዝ መንግስት ማስታወቅ መሆኑን አስገነዘበ።

ከዚያ ውይይቱ ተጀመረ፤ በንጉሰ ነገስቱ ያኮረፉና ከእውነት በመነሳትም የተቆረቆሩት «ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ መሪነታቸውን አልተወጡም፣ በርሃብና ጥም የተሰቃየው፣ የተሰቀለው፣ የተገረፈው፣ ቤቱ የተቃጠለው፣ ድህነት ያቆራመደው፣ በገዛ አገሩ አንገቱን የደፋው ... ህዝቡ ነው። ስለዚህ የቀድሞው ንጉሰ ነገስት ዳግመኛ በመሪነት ሊቀመጡ አይገባም» የሚል መከራከሪያ አቀረቡ።

ብዙሃኑ የስብሰባ ተሳታፊዎች ግን፤ «ቂም ሌላ፣ አገር ሌላ ... እኛ ከለመድናቸው ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሌላ አንፈልግም፤ ይልቁንስ በዚህ ቀውጢ ወቅት በፋክክር ስንታመስ አገራችን ተመልሳ የቀበሮ ሲሳይ እንዳትሆን» በማለት በጩኸት አዳራሹን አደበላለቁት። ጄኔራል ካኒንግሃምም በቃሉ መሰረት የብዙሃኑን ውሳኔ «ህዝቡ የንጉሰ ነገስቱን ወደ ስልጣን መመለስ ደግፏል» በማለት ለእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተላለፈ።

* * *

ንጉሰ ነገስቱ አዲስ አበባ ለመመለስና ዘንባባ ይዞ የሚጠብቃቸውን ህዝብ ለማስደሰት ስለሚሄዱበት መጓጓዥ አስተያየት ተኸርጎደጎደ። ለአገራቸው የተዋደቁት አርበኞች «... ንጉሰ ነገስቱ በድል አድራጊነት እንደተመለሱ የሚያረጋግጠው ወታደራዊ ልብሳቸውን እንደለበሱ፣ በፈረስ ተቀምጠው፣ በፈረሰኞች ታጅበው ... መናገሻ ከተማቸው ቢገቡ ነው፤ ይህም አቀባበል አድራጊውን የአዲስ አበባ ህዝብ ያስደስተዋል...» አሉ።

ሌሎች ደግሞ «ከሱዳን ተነስተው እስከ ደብረማርቆስ በእግርና በፈረስ ተጉዘዋል:: አሁን ደግሞ እንደ ጦር ጀኔራል በፈረስ አስቀምጦ፣ በፈረሰኞች አጅቦ ማስገባት ክብር መቀነስ ነው:: ስለዚህ በአልፋ ሮሚዮ መኪና ውስጥ ሆነው በናፍቆት ወደሚጠባበቀው ህዝባቸው መሄድ አለባቸው» አሉ:: ጃንሆይም መኪናውን መረጡና የራስ ሃይሉ ንብረት በሆነችው የአልፋ ሮሚዮ መኪና ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ ግራ ቀኝ ተሰልፎ ይጠባበቅ የነበረው የአዲስ አበባ ህዝብ በዕልልታና ጭብጨባ ታላቅ አቀባበል አደረገላቸው::

ይሁን እንጂ ውሎ ሳያድር በአንድ በኩል እንግሊዞች ኤርትራንና ኦጋዴንን በመያዝ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የነበረውን የኢትዮጵያን ግዛት እየሸራረፉ ወደ ኬንያና ሱዳን በማስገባት ተንኮላቸው ተሰማሩ። በሌላ በኩል ደግሞ ከስደት በተመለሱት አርበኞችና በባንዳዎች መካከል በነበረው የስልጣን ሽኩቻ አገሪቱ ትታመስ ጀመር:: አርበኛው ስደተኛውንና ባንዳውን «ከሃዲና ፈርጣጭ» እያለ ሲኮንን፤ ስደተኛውና ባንዳው ደግሞ አርበኛውን «ደንቆሮ፣ ያልተማረ» በማለት ያንቋሽሹ ጀመር:: ንጉሰ ነገስቱም ከ1927 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም ለቆዩት አርበኞች እንደ አርበኝነታቸው ዓመት ቁጥር አንዳንድ ዘምባባ እየጨመሩ የአርበኞች ሜዳይ ሲሸልሙ ለውስጥና ለስደት አርበኞችም ሜዳሊያ ሸለሙ:: ከፍተኛው ክብርና ሽልማትም ወደ እነሱ አደላ፤ ያን ጊዜ «ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ» የሚለው የዮፍታሄ ግጥም በህዝብ ትካዜና ብስጭት የተቀነባበረ ዜማ ሆነ::



# I

## የአፄ ኃይለ ስላሴ ጉብኝት

ንጉሱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም በደጃዝማች ገረሱ ዱኪና በእንግሊዞች የሚመራ ጦር የጊቤን ድልድይ ሰብሮ በምዕራብ ኢትዮጵያ የምትገኘውን ጅማንና አካባቢዋን የተቆጣጠረውን የኢጣሊያ ጦር እንዲወጋና እንዲያስለቅቅ ተፈለገ:: በአርበኝነት ትግሉ ወቅት ስሙ-ጥር አርበኛ የነበሩትና ከጃገማ ኬሎ ጋር ከኢጣሊያ ወራሪ ጦር ጋር ውጊያ ገጥመው በማሸነፍ የወጣቱ የአርበኞች መሪ የጃገማ ኬሎና የረዳቱ የዘውዴ ጥላሁን ጀግንነትና የጦር ስልት ከአዕምሮአቸው ያልወጣው ደጃዝማች ገረሱ በጅማ የሚገኘውን ጠንካራ የኢጣሊያ ምሽግ ሰብሮ ለማጥቃት «ጃገማ ኬሎና ዘውዴ ጥላሁን ይጨመሩልኝ» ብለው ንጉሰ ነገስቱን ጠየቁ::

ንጉሰ ነገስቱ ስለ ጃገማ ኬሎ ከዚያ በፊት የሰሙት ብዙ ነገር አልነበረም። ንጉሡ ስንት ታዋቂ መኳንንትና አርበኞች እያሉ ማንነቱን የማያውቁትን አርበኛ ማዘዝ ከፍተኛ ክብርን እንደመስጠት ቆጥረውት ደጃዝማች ገረሱን «ምነው ገረሱ? ለማዘዝ የሚገባንን አጥተኸው ነው ለማናውቀው አርበኛ ይህን ግዳጅ እንድንሰጥ የፈለግኸው?» ብለው ጠየቁ::

«ጌታዬ! በጅማ ተሰባስቦና ሃይሉን አጠናክሮ ያለውን የኢጣሊያ ሰራዊት አይደል ምሽጉን ሰብረን እንድናጠቃ የፈለጉት?» አሉና ጠየቁ ገረሱ::

«ነው እንጂ - እንዳልኸው ነው» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ::

«ግርማዊ ጃንሆይ! ያ ሃይል እንዲሰበር ከፈለጉ ወጣቱን ጃገማ ኬሎንና ዘውዴ ጥላሁንን ይስጡኝና የኢጣሊያን ሰራዊት በሊሙ በኩል ገብቼ ልወጋውና ምሽጉን ሰብሬ ልደመስሰው እችላለሁ:: አለበለዚያ ግን ...» ብለው ደጃዝማች ገረሱ ንጉሰ ነገስቱን ትክ ብለው አዩዋቸው::

«ካለበለዚያ ምን? ጨርሰዋ ሃሳብህን» አሉ::

«ካለበለዚያ» ብለው ገረሱ ራሳቸውን ግራ ቀኝ አወዛወዙ::

ንጉሰ ነገስቱ በስደት ዘመን የተፈጠሩ አርበኞችን በአይኑ-ሀሊናቸው እንኳን ለማሰብ ተሳናቸው። ነገር ግን የውጊያ ዘመቻው በአስቸኳይ መጀመር ነበረበት። የኢጣሊያ ሰራዊት ከመናገሻ ከተማቸው ሶስት መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ተቀምጦ እፎይታ አይኖራቸውም። ስለዚህ ክብር እንደመስጠት የቆጠሩትን ደብዳቤ ለጃገማ እንዲፃፍ አዘዙ።

«የጅማን ጦርነት ደጃዝማች ገረሱ እንዲያዘምት አዝዣለሁና አንተ ከነሰራዊትህ በደጃዝማች ገረሱ ስር ሆነህ እንድትዘምት» በሚል የተዘጋጀው የንጉሰ ነገስቱ ደብዳቤ በደጃዝማች እንቁስላሴ ወልደዮሐንስ በኩል ለጃገማ ተላከ።

ጃገማ ደብዳቤው ሲደርሰው ከፋው።

«የት ያውቁኝና ያዙኛል? እኔ ወታደራቸው አይደለሁ፤ ከፈለጉ በአዲስ ዓለም፣ ወሉንኮሚ፣ ጭልሞ፣ ጊንጪ፣ ሐሮታና ሆለታ የማረኩሁትን መሳሪያና ተሽከርካሪ ይውሰዱ እንጂ በሳቸው ትዕዛዝ የትም አልሄድም» አለ በቆራጥነት።

ጃገማ ለአምስት ዓመታት ሙሉ በየጦርነቱ አውድማ የኢጣሊያን ጦር በገዛ ጥይቱና ጠመንጃው አንቆራጦታል። አባቱ ኬሎ ገሮ የመከሩትና የኦሮሞ ሽማግሌዎች እያደነቁ በማውራት እሱን የመሰለ ጀግና እንዲሆን የተመኙለት እንደ ቅድመ አያቱ ጎዳና ነሞ የመሆን ምኞት በሃያ አመቱ ተሳክቶለታል። ድፍን የጊንጪ፣ የአዲስ ዓለም፣ የጭልሞ፣ የአምቦ፣ የሐሮታ፣ የሆለታ ... ህዝብ ገድሉን እንደ ቃለ-ተውኔት አጥንቶ የድል ነጋሪቱ እየተጎሰመ በደመቀበት በዚያ የደስታው ማጣጣሚያ ወቅት ሃሳባቸውን ማስፈፀም እንጂ የሌላውን ሃሳብ ከግምት ያላስገቡት መሪ በቀጭን የትዕዛዝ ቃጭል ሩቅ ሆነው ጠሩት።

ወጣትነትን በዋዛ ፈዛዛ ያላሳለፈው ጃገማ አባ ዳማ ግን የበላይ፣ ንጉሰ ነገስት፣ የመጥሪያ ቃጭል፣ ቅፅበታዊ ትዕዛዝ ... ብሎ ነገር አልገባውም። ለእሱ የነበረው ትልቁ ርዕይ የአባቱ ህልም ነበር። ገና በህፃንነቱ ትናንሽ እግርና እጆቹን እየጨባበጡ «ጀግናው ልጅ አሁን ገና መጣ» ብለው ሁለት መቶ ጊደር የሸለሙትን፣ በአስር አመቱ የብዙ ጋሻ መሬት ውርስና የቤተሰቡ አስተዳዳሪ አድርገው የሾሙትን አባቱን ህልም ጀግና ሆኖ እንደ አባታቸው እንደ ጎዳና ነሞ ገድል በመስራት አሳክቷል።



ጃገማ ህልማቸውን ህልሙ አድርጎ፣ ክብሩንና ማንነቱን አጠንክሮ ለድል በቅቷል። በተረፈ ግን መንግስት የቀጠረው ጦረኛ አይደለም፤ ለግፈኛ ግን አንገት ደፍቶ ክብሩን በምንም መንገድ አሳልፎ ሳለመስጠት ታግሎ አሸንፏል። እንደ አዋሽ ወንዝ የአርበኝነት ትግሉን ለብቻው የጀመረው ጀግና ቀኑ ለጨለመባቸው ኩራቱን እየለኮሰ፣ ተስፋ ለቆረጡት ህይወት እየዘራ ... ትልቁን ዛፍ አምስት ዓመት ሙሉ ገዝግዞ ዘፍ አድርጎ ጥሎታል። ጃገማ አባ ዳማ ከዚያ ድል በላይ የሆነ ሌላ ህልም አልነበረውም። ከድል በኋላ የሚችለውን እየሰራ፣ በቅዱስ ዮሐንስ አስገድዶ የሚስማትን ቆንጆ አግብቶ እንደ ልጅነቱ የኦሮሞ ተረቶችን እያደመጠ መኖር ነበር ፍላጎቱ። ለምሳሌ በአርበኝነቱ ዘመን ከረዱት የኦሮሞ ተረቶች ውስጥ አንዱ አባቱ ኬሎ ገሮ በልጅነቱ የነገሩት ነው።

«አንድ ጊዜ ሁለት የሚተማመኑ ጓደኛሞች ነበሩ። ሁለቱም ምንም መተዳደሪያ አልነበራቸውም። የሚተዳደሩበትን ለማግኘት በጫካ ውስጥ መንቀሳቀስ ጀመሩ። በጫካ ውስጥ እየሄዱ እያሉ አንዱ፤ 'ከብት ተመልከት' አሉ፡ ጓደኛውም 'አየሁት አንተ!' አለው ... ከብት አገኙ። አሁንም ሲጓዙ አንዱ 'ግመል ተመልከት!' አለ፤ ጓደኛውም 'አየሁት አንተ!' አለ ... ግመል አገኙ። 'በይሁን አሉ-ሆነ' መላ አንዱ የፈለገውን ሲል ሌላው ሲስማማ ከብት፣ ማር፣ ፍየል፣ የዝሆን ጥርስ ... እያገኙ ሲጓዙ አንድ ሰው አያቸው። 'እኔ ከብት፣ ገንዘብ፣ ፍየል ... የለኝም። እባካችሁ አብሬያችሁ ልጓዝ' ብሎ ጠየቃቸው። ሁለቱ ጓደኛሞች እምቢ አሉት። 'ለምን አብሬያችሁ እንዳልጓዝ ከለከላችሁኝ?' አለ ሰውየው።

« 'እኛ እርስ በርሳችን የማንጠራጠር ጓደኛሞች ነን። አንዳችን እንፈልጋለን፤ ሌላችን ሆነ እንላለን፤ ይሆናል ...' አሉት። 'እሺ እኔም አልጠራጠራችሁም፤ አምናችኋለሁ፤ ስለዚህ እባካችሁ ወንድሞቼ አብሬያችሁ ልሂድ፤ ፍቀዱልኝ' አላቸው። 'ከተስማማህ ጥሩ፤ ነገ አብረን እንሄዳለን፤ ነገር ግን በጭራሽ እንዳትጠራጠር፣ እንዳትቃወም' አሉት።

«በነጋታው አብረው ጉዞ ጀመሩ... ከዚያ አንዱ፤ 'ከብት ተመልከት' አለ። 'የታል?' አለ ሰውየው...ከብቱ አልነበረም። 'ግመል ተመልከት!' አለ ሁለተኛው ... 'የታል?' አለ ሰውየው ... ግመል የለም። 'ማር ተመልከት!' አለ፣ የመጀመሪያው ጠያቂ፤ 'የታል?' አለ፥ ሰውየው - ተሸቀዳድሞ።

«በዚያ ቀን ሶስቱም ወደ ቤታቸው ባዶ እጃቸውን ተመለሱ። እቤታቸው እንደደረሱ ደሃውን ሰው 'አንተ ተጠራጣሪ ስለሆንህና ጓደኞችህን

ስላላመንኸን ከአሁን በኋላ አትከተለን' አሉት:: በነጋታው ሁለቱ ብቻ 'ተመልከት' ... 'እየሁት' እየተባባሉ ካለጥርጣሬ የፈለጉትን ሁሉ ይዘው ተመለሱ:: መጠራጠር የሚፈልጉትን የሚያሳጣ እኩይ ባህሪ ነው...ጓደኛሞች መጠራጠር የለባቸውም» የሚለውን የኦሮሞ ተረት ጃገማ አብረውት በአርበኝነት የቆዩትን እንዳይጠራጠር ስላደረገው ያሰበው እየተሳካለት፣ በተሰለፈበት የጦር ግንባርም አሸናፊ እየሆነ ለድል በቃ:: ስለዚህ የጃገማ ፍላጎት የኦሮሞን ባህል እየተከተለ፣ ተረቱን እየሰማ፣ ትውፊቱን እያጣጣመ መኖር እንጂ የንጉሰ ነገስት ትዕዛዝ እየፈፀመ ለመኖር ምንም አይነት ህልም አልነበረውም::

* * *

ከሌሎች አርበኞች ጋር ግንኙነት እያላቸው፣ እነ ደጃዝማች ከበደ ብዙነህን የመሳሰሉት የአርበኛ መሪዎች በቅርብ ርቀት እያሉ አፄ ኃይለ ስላሴ ጃገማን ከጊንጪ ማዶ ያስጠሩበት ምክንያት እንቆቅልሽ ቢሆንም «ትዕዛዜን አልተቀበለም» ብለው ምክንያት ለማግኘት በሚፈልጉበት ወቅት ወ/ሮ ሸዋረገድ ገድሌ ንጉሰ ነገስቱ ዙፋን ፊት ቀርበው ለጃገማ የመሰከሩና ከንጉሰ ነገስቱ ቁጣ ያዳኑት ባለውለታው ናቸው::

ወይዘሮ ሸዋረገድ ከንጉሰ ነገስቱ ጋር ቅርበት ስለነበራቸው ከስደት ሲመለሱ «እንኳን ወደ ሀገርዎ ምድር በሰላም ተመለሱ» ሊሉና እጅ ሊነሱ ወደ አዲስ አበባ ሄዱና ደጅ ጠንተው ንጉሰ ነገስቱን እጅ ለመንሳት ተፈቀደላቸው:: ወይዘሮ ሸዋረገድና ንጉሰ ነገስቱ ስለ አምስት ዓመቱ ክፉ ዘመን ትንሽ እንዳወጉ ንጉሰ ነገስቱ ቅር ያላቸውን ጥያቄ አስከተሉ፤

«ምነው ጃገማ ከደጃዝማች ገረሱ ጋር እንዲዘምት ብናዘው ትዕዛዛችንን አልቀበልም አለ?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - የቀኝ እጅ ጣቶቻቸውን ከግራ እጅ ጣቶቻቸው ጋር በማገናኘት ሃይላቸው ከክብዮሽ ኡደቱ እንዳይወጣ እያደረጉ::

«ጃንሆይ!» አሉ፥ ወይዘሮ ሸዋረገድ - አዕምሮአቸውን ከመቅጽበት መመለስ እንዲችሉ እያዘጋጁ:: ወይዘሮ ሸዋረገድ ንጉሰ ነገስቱን ያውቋቸዋል:: አንድን ሰው ከተቀየሙ በዋዛ እንደማይለቁት ያውቃሉ:: እንኳን ትዕዛዛቸውን አልቀበልም ላለ የማያሞካሽና እጅ የማይነሳ በጥሩ ዐይን አይታይም:: ሸዋረገድ ያ ክፉ እጣ ወጣቱ ጃገማ ላይ እንዲደርስበት አልፈለጉም:: ስለዚህ፤ «ጃንሆይ ቢያዩት እኮ የሚያምር አንድ ፍሬ ልጅ ነው:: ኧረ እንዴት ያለ ጨዋ፣ ሰው አክባሪ መሰልዎት:: የእሱ ሃሳብ የንጉሰ ነገስቴን እግር ሳልስም፤





ከሞት ወደ ሞት እንዴት እሄዳለሁ ብሎ እንጂ ትዕዛዝዎን ላለመቀበል አይደለም» ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ «እንዲያ ከሆነ ደግ ነው፤ እኛም ተረድተናል» አሉ ንጉሰ ነገስቱ:: ሸዋረገድ ከላያቸው ላይ የሆነ ከባድ ነገር ተነስቶ ሲወድቅ ተሰማቸው:: ሁለቱም በየራሳቸው አቅጣጫ በሃሳብ ፈረስ ጋለቡ:: ከጥቂት ዝምታ በኋላ ንጉሰ ነገስቱ «ጃገማ የማን ልጅ ነው?» አሉ::

«የኬሎ ገሮ ልጅ ነው፤ የኦሮሞ ባላባት ዘር ነው:: ቅድመ አያቱ ጎዳና ነሞ ይባላል፤ አገር ያወቀው ጀግና ነበር:: ጃገማም በእሱ ነው የወጣው ነው የሚባለው:: አባ ዶዮም አጎቱ ናቸው» አሉ፥ ወይዘሮ ሸዋረገድ:: የአባ ዶዮ ስም ሲነሳ ንጉሰ ነገስቱ ፊታቸውን ለአመል ያህል አዞሩ:: አባ ዶዮን ያስታውሷቸዋል፤ በተለይም «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» እና «የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትነት ስልጣን ከንግስት ሳባና ከንጉስ ሰለሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳያቋርጥ ተያይዞ ከመጣው ከንጉስ ሳህለስላሴ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ትውልድ ሳይወጣ ምንግዜም ይኖራል» የሚለው ከህገመንግስት ካልተሰረዘ በማለት ከኢጣሊያ ወረራ በፊት በነበረው ሸንጎ ተቃውሞ ያሰሙ ነበር::

እንደገና ፀጥታ ሰፈነ:: ወይዘሮ ሸዋረገድ የንጉሰ ነገስቱን ፊት እንደ ህፃን እያዩ ነው የሚያወሩት:: ፊታቸውን ዘወር ሲያደርጉ ሸዋረገድ ነገር እንዳይበላሽባቸው «እምዬ ማርያም የዛሬን ብቻ አውጭኝ» በማለት እየፀለዩ ፀጥ አሉ::

ከቆይታ በኋላ ንጉሰ ነገስቱ ወደ ወ/ሮ ሸዋረገድ ፊታቸውን መለሱና «ወላጆቹ በሕይወት አሉ?» አሉ - እንዳች ሃይል ከቁጣቸው እንደመለሳቸው ሁሉ የፊት ገፅታቸውን እንደ በፊቱ ዘና አድርገው::

«የሉም ጃንሆይ! እናቱ እሱን በወለደች በአመቷ በፈንጣጣ በሽታ ተለክፋ ሞተችበት» አሉ:: ንጉሰ ነገስቱ የጃገማን እናት ሞት ሲሰሙ የእሳቸውንም እናት ወይዘሮ ሸዋረገድን አስታወሱ:: እናታቸውን እያውቋቸውም፤ ከእናታቸው ጉያ የተወሰዱት ገና ወደዚህች ዓለም ሲመጡ ነው:: ስለዚህ የጃገማ ታሪክ ትንሽ ሳባቸው:: «አባቱስ?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ:: ወ/ሮ ሸዋረገድ ፊት ፊታቸውን እያስተዋሉ «ጃንሆይ! አባቱ በአስር ዓመቱ ሞተውበታል:: በእርግጥ አባቱ አስራ ስድስት ልጆች ነበሯቸው:: እሱ አስራ ስድስተኛውና የመጨረሻው ልጅ ነው:: ከፊል ሃብታቸውን ያወረሱትና የቤተሰቡ አስተዳዳሪ ያደረጉት እሱን ነው፤ በኋላ ግን ወንድሞቹ ውርሱን አንቀበልም አሉ ...» አሉ::

ንጉስ ነገስቱ፥ አባታቸው ራስ መኮንን የእሳቸው ታላቅ እያስ እሳቸውን ገና በአስራ ሶስት ዓመታቸው ነው የጋራ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው የሾሟቸው። በዚያ ወቅት የሰውነታቸውን ኮስማናነት እያዩ ናቅ የሚያደርጓቸውን «ይህን ልጅ ተው አትናቁት፤ ትልቅ ሰው የሚሆን ነው...» ይሉላቸው ነበር፥ አባታቸው ራስ መኮንን። ከ«መመነናቸው» በፊትም ለፊታውራሪ ኃይለ ስላሴ «ልጄን አደራ ሰጥቼሃለሁ!» ብለው ቃል እንዳስገቧቸው የሰሙትን አስታወሱ።

«ዕድሜው ስንት ነው አልሸኝ?» በሚያስገመግመው ድምፃቸው ድንገት ጠየቁ - ንጉሰ ነገስቱ።

«ጃንሆይ! ወደ አርበኝነት ሲገባ አስራ አምስት አመቱ ነበር፤ አሁን ሃያኛ ዓመቱን ይዟል» አሉ ወይዘሮ ሸዋረገድ።

«በዚህ ዕድሜው አርበኞች ስለምን መሪያቸው አደረጉት?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - ወደ ሴትዮዋ ሙሉ በሙሉ ፊታቸውን መልሰው ትላልቅ ጆሮዎቻቸውን በመቀሰር።

«ጃንሆይ! አይ እኮ ቢያዩት፤ ያምራል ... በዚያ ላይ አባቱ ሶስት ጊዜ ሞራ የለበሰ ሃብታም፣ ሃብታም ብቻ ሳይሆን ለጋስ፣ ሰጥቶ የማይጠግብ ነበር። ስለዚህ ሰው ሁሉ ይወደው፣ ያከብረው ነበር። ፍቅራቸውን ለመግለጽ አባቱ የመረጠውንና የሾመውን መሪ አደረጉት። በኋላ ግን ቡተሰለፈበት ሁሉ ሽንፈት የማያውቅ፣ ደፋር፣ ማስተባበር የሚችል፣ ትሁት፣ ለሰው አዛኝ ሆነ - ጃገማ። ግርማ ሞገሱም ወደ ...» ብለው ሸዋረገድ ሃሳባቸውን ሳይጨርሱ።

«ይበቃል ሸዋረገድ! . . . መጥተን እናየዋለን፤ ይጠብቀን» አሉ። ሸዋረገድ ለጥ ብለው እጅ ነሱ። አንድ ሜትር ከስልሳ ቁመት የነበራቸው ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከዙፋናቸው ተነሱ። ከዚያም መልከ ቀናው ፊታቸውን ፈካ አድርገው፣ ፍንጭት ጥርሳቸውን ብልጭ በማድረግ አሳይተዋቸው ወደ ሰፊው መስኮት ሄደው ውጭ ውጭውን መመልከት ጀመሩ ...

* * *

በሰኔ ወር 1933 ዓ.ም ንጉስ ነገስቱ ወደ ጊንጪ አመሩ። ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጊንጪ መግቢያ ላይ ንጉስ ነገስቱ የሚቆሙበት ሰገነት አሰርቶ ጠበቃቸው። በእሱ መሪነት ለአምስት ዓመታት በዱር በገደል





የታገሉት ሶስት ሺ አምስት መቶ አርበኞች በባዶ እግራቸው፣ ባት ተሁለታቸውንና ባቷያቸውን ለብሰው፣ ከላይ ከኢጣሊያ ጦር የማረኩትን ገበርዲን ኮትና ኮፍያ ራሳቸው ባወጡት ቅርጽ በመርፌ አበጃጅተው፣ መሳሪያቸውን በመወልወል ተጠባበቁ። ንጉሰ ነገስቱ ሰገነቱ ላይ ቆመው ለነፃነታቸው የታገሉትን አርበኞች በጽሞና ሲያዩ ቆዩ።

ጃገማ ንጉሰ ነገስቱ ፊት ፎከር ተባለ፤ በቅቤ የራሰውን ጎፈሬውን ከምበል ደፋ እያደረገ ሳተናውና ባለግርማ ሞገሱ ጃገማ አባ ዳማ፤

«ገዳይ በልጅነቱ ዶቃ ሳይወጣ ካንገቱ
ጃጌ ጃገማቸው እንደገጠመ የሚፈጃቸው
በናቱ ኦሮሞ ባባቱ ኦሮሞ፣
በጀግንነቱ ፈጃቸው ደግሞ፣
ሁሌ ያደንቃል ሀገር ተገርሞ።
እህቱም ባይ ናት ልሙት ሳገሬ፣
የኢትዮጵያ ጀግኖች አይበገሬ።
አገሬን ከቶ አይደፍርም ጠላት፣
ዘርፎት አይወጣም ያገሬንም ሀብት።
እስቲ ይለፍልህ ያገሬ አሞራ፣
የጠላት ሬሣ ወድቆ ይዘራ» ብሎ ከፎከረ በኋላ፤

«ጃንሆይ! እኔ ፉከራ አላውቅም» አለ።
«ምን ቀረህና!» አሉት ንጉሰ ነገስቱ - ፈርጠም ብለው።

ከዚያ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጃገማ ወደ እሳቸው እንዲመጣ ጠቀሱት። ንጉሰ ነገስቱ ጃገማን እጁን ይዘው መንገድ ዳር ወደ ቆመው መኪናቸው እየሄዱ፤ «እኛን ታውቀን ነበር?» አሉት።

«አዎ! ልጅ ሆኜ ጅባትና ሜጫ አውራጃን ለመጎብኘት የመጡ ጊዜ እትቴ አባ ዶዮ ዋሚ ህዝቡን አሰልፈው አዋሽ ወንዝ ሲቀበሉዎትና መኪናዎ ላይ ወጥተው አካባቢውን ሲያሳይዎት እኔም እርስዎን ለመሸኘት ፈረሴን እየጋለብኩ ተከትየዎት ነበር። ደጋ ወጪ አካባቢ እንደደረስን ግርማዊነትዎ ህዝቡን ሲያነጋግሩ ልጅዎ ልዑል መኮንን ቤሳዎችን እየዘገኑ መንገዱ ግራና ቀኝ ለቆምነው ሰዎች በተኑ። አንዷ ቤሳ ኩልል ... ብላ እፈረሴ እግር ስር ገባች። ከፈረሴ ወርጄ ቤሳዋን አንስቼ አይቼ ያዝኳት። ያችን ቤሳ ለብዙ ጊዜ ለማስታወሻ ትሆነኝ ዘንድ አስቀምጫት ነበር። ጣሊያኖች የአባቴን ቤት

ሲያቃጥሉት ማስታወሻዬም አብራ ተቃጠለች» አሏቸው፡፡ ንጉሰ ነገስቱ ፈገግ ብለው አይተው እንደገና እጁን ያዝ አድርገው መራመድ ጀመሩ፡፡

ጃገማ ንጉሰ ነገስቱ እጁን ሲይዙት ምንም አልተሰማውም፤ የእሱ እጅ እንደ አካፋ ሰፊና ሻካራ፣ የእሳቸው ደግሞ ለስላሳ ከመሆኑ በስተቀር፡፡ ለአጀቧቸው መኳንንት ግን ተአምርና የማይታመን ሆነባቸው፡፡

«ጃገማ! የአርበኞችህን ስም ዝርዝር አምቦ ደርሰን እስክንመለስ ጽፈህ ቆየን» አሉት፡፡ «እሺ» አለ - ለመጀመሪያ ጊዜ የበላይ ትዕዛዝ ተቀብሎ፡፡

ከሰዓታት በኋላ ንጉሰ ነገስቱ በቃላቸው መሰረት ተመልሰው መጡ፡፡ ጃገማ የስም ዝርዝሩን አውጥቶ ለማንበብ ወረቀቱን ዘርጋ ዘርጋ በማድረግ ላይ እያለ አንዱ ከእጁ ወስዶ ሊያነብ ሲል «ጃገማ፥ ካነበብህማ አንተው አንብብልን?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ፡፡ ጃገማ ስም ዝርዝሩን አነበበ፡፡ «ኦሮምኛውስ የእናት የአባቱ ነው፤ ይህን ጥርት ያለ አማርኛ እንዴት ለመደው?» ብለው አሰቡ፥ ንጉሰ ነገስቱ፡፡ ብዙ ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ይወዳሉ፡፡ እሳቸው ራሳቸውም አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ አደርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛና ትንሽ ጀርመንኛ ይችላሉ፡፡

በመጨረሻ ብዙ ነገሩን የወደዱለትን ጃገማን አብሯቸው እንዲሄድ «በል አሁን ከእኛ ጋር አዲስ አበባ ትሄዳለህ ... ግባ መኪና ውስጥ» አሉት፡፡ ጃገማ አባ ዳማ በንጉሰ ነገስቱ መኪና ለመሄድ ከአፋሩ ተወላጅና ከግዙፉ ግራዝማች ዑመር ዲንን ጎን ሹሩባውን ፈትቶ ከእነ ቅቤው ገብቶ ተቀመጠ፡፡ ንጉሰ ነገስቱና እልጋ ወራሹ ጎን ለጎን፤ ሻለቃ አቢይ አበበ ደግሞ እሁለቱ እግር ስር ካለች ትንሽ ኩርሲ ላይ ቁጭ አሉ፡፡

ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆለታ ሲደርሱ የንጉሰ ነገስቱ መኪና ሰዎች ወደ ተሰባሰቡበት ተጠግታ ቆመች፡፡ ሰዎቹ ንጉሰ ነገስቱን ሲያዩ መሳሪያቸውን እየወዘወዙ፣ ወዲያና ወዲህ እየሸለሉ «ጃሎ በል ... ጎራው በል ... የጠቅል አሽከር» እያሉ ቀረርቶና ፉከራውን አቀለጡት፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በተለመደው ያለመርሳት ችሎታቸው በመጠቀም ከሚያቅራሩትና ከሚፎክሩት ውስጥ አንዱን ትኩር ብለው ሲያዩ ቆዩና፤ የመኪናቸውን መስተዋት ወረድ አድርገው፤





«አንተ ስሜ ተክለማርያም አይደለህም?» አሉት፡፡ ስሜ ተክለማርያም ንጉሰ ነገስቱን እንዳየ አቅራራ፣ ፎከረና «አዎ፤ ስሜ ነኝ፥ ጃንሆይ!» አለ፡፡ ስሜ የንግስት ዘውዲቱ አሽከር ነበር፡፡

«በህይወት አለህ ስሜ?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ፡፡

«አዎ ጃንሆይ ... ይኸው በህይወት አለሁ፡፡ ዛሬ ጊንጪ ሄደው ያዩት ህፃን የአዲስ ዓለምን ምሽግ ሲሰብር እኛንም ከእስር ቤት የነበርነውን እስረኞች አስለቀቀን፡፡ አርባዎቻችን ከአርበኞቹ ጋር መሳሪያ ዘርፈን ተከተልናቸው፡፡ አርባዎቹ ደግሞ እዚያው በፈቃዳቸው ቀሩ፤ ጣሊያንም ወንዶች ሲያመልጡ እናንተን ምን ጎለታችሁ ብሎ ፈጃቸው - አንድም ሳይቀር» አሏቸው፡፡ ጃገማ ይህን አልሰማም፡፡ በኋላ ግን ንጉሰ ነገስቱ «አይዞህ ምስክር አግኝተሃል» አሉት፡፡

ሌላው ጀግና ዘውዴ ጥላሁን አባቴ ሃና ካሉባት መኪና ውስጥ ሆኖ ከጃገማ ጋር ወደ አዲስ አበባ ተወሰደ፡፡ ማታ ግብር ሲቀርብ ንጉሰ ነገስቱ ከአባቴ ሃናና ከአልጋ ወራሽ ጋር ጠረጴዛ ላይ፣ ጃገማና ዘውዴ ደግሞ በምስብ ማዕድ ቀርቦላቸው ሲበሉ ንጉሰ ነገስቱ በመደመም ወጣት ጀግኖቹን ለረጅም ሰዓት ሲያስተውሏቸው ቆይተው «ከፉ ነገር መቼም በጎ ነገር እያጣም!» አሉ፡፡ አባቴ ሃና ተገርመው፤ «ምነው ጃንሆይ!» አሉ - በትህትና፡፡ «ይገርማል! የጠበቅናቸው ቀርተው ያልጠበቅናቸው ታሪክ ሰርተው አገኘናቸዋ!» አሉ፡፡ አባቴ ሃና፤ «እውነት ነው ጃንሆይ!» አሉና ንጉሰ ነገስቱ በተናገሩት መንፈሳቸው መነካቱን ለመግለጽ ራሳቸውን ሽቅብ ቁልቁል ወዘወዙ፡፡ አልጋ ወራሹ ግን ዐይናቸውን ሁለቱ አርበኞች ላይ ተክለው በተመስጦ ያይዋቸው ነበር፡፡

በማግስቱ ንጉሰ ነገስቱ ለጃገማ የገበርዲን ሙሉ ልብስ፣ የወርቅ ሰዓትና አስራ ስድስት ሺህ ብር ሸለሙት፡፡ ጃገማ የነፍስ ዋጋ የሚጠ ይቀው፣ ለአካለ ጎደሎነት የሚዳርገው የአርበኝነት ተጋድሎ ትርፍ እንዳለውና ከንጉሰ ነገስት ጋር አስተዋውቆ እንደሚያስሽልም አስተዋለ፡፡

«ጃገማ!» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ ከሽልማቱ በኋላ፡፡

«አቤት» አለ፥ ጃጌ ጃገማ - ፈጠን ብሎ፡፡

«መቼም የጅማን ጦር አዛዥነት ለገረሱ ሰጥተናል፤ እሱ ዘንድ ስትሄዱ አንተና ዘውዴ ለየብቻ ብትሰለፉ ችግር አለው?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ፡፡

«ንጉስ ካዘዘ ችግር የለም!» አላቸው፡ ጃገማ - ፈርጠም ብሎ። «በዚህች ዓለም ቁም ነገሩ ማሰብ ሳይሆን ማድረግ መሆኑን እንዴት ቀድመህ ተረዳህ - ጃገማ!» አሉ ንጉስ ነገስቱ፤ ጃገማ ግን ያሉትን አልሰማቸውም። ከዚያ «ጃገማ! ሚስት አግብተሃል?» አሉት - ትክ ብለው ሲያዩት ቆይተው።

«ኧረ አላገባሁም» አለ፥ በብቸኝነት የቆየው ጃገማ።

«እኛ ነን የምንድርህ፤ እንዳታገባ!» ሲሉት የቤተመንግስቱ በር ሲጢጥ ብሎ ተከፈተ ...



# ፲፩

## የዕለቱን ትቶ የዓመቱን

ጃገማ ንጉሱን ከተሰናበተ በኋላ ከአርበኞች እና ከሜታና ሜጫ ባላባቶች አምስት ሺህ ጦር ይዞ ቅዳሜ ከአምቦ ተነሳ። ከሁለት ቀን በኋላ ከደጃዝማች ገረሱ ጋር ተገናኘ። ጃገማ አባ ዳማ አንድ እንግሊዛዊ የጦር አማካሪ አብሮት እንዲሆን በደጃዝማች ገረሱ ተመደበለትና ጉዞውን ቀጠለ።

አልጋ ኮሶ ላይ የዘውዴ ጦር ቀድሞ ደርሶ ኖሮ በኢጣሊያ ወራሪ ጦር ግራና ቀኝ ተከቦ ደረሰ። ጊዜ ሳይወስድ የተዳከመውን የዘውዴን ጦር ለማጠንከር ውጊያ አስጀመረ፤ ውጊያው ተካረረ። የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የነበረውን ኮሎኔል ጨምሮ በርካታ ኢጣሊያውያን ተገደሉ። በመጨረሻም አስራ ሶስት ጣሊያኖች ለጃገማ እጃቸውን ሰጡ። በማግስቱ እነ ጃገማ ሰቃ የነበረውን የኢጣሊያ ጦር አስለቅቀው አካባቢውን ተቆጣጠሩ። በሶስተኛው ቀን ጃገማ አባ ዳማና በወንድሙ ጠንቋሳ ኬሎ የሚመራው ጦር ጅማ ደረሱና ወደ አጋሮ የሚወስደው መንገድ ላይ የነበሩትን ጣሊያኖች ገድለው ሶስቱን ማረኩ።

ከዚያም ጃገማ ከተማረኩት ኢጣሊያውያን አንዱንና መንግስቱ ቦጋለ የተባለውን የተማረ ኢትዮጵያዊ «ተከበሃል ... ከእንግዲህ መሄጃ የለህም እጅ ስጥ» የሚል መልዕክት አስይዞ ለኢጣሊያው ጦር አዛዥ ለጄኔራል ጋዚራ ላከበት። መንግስቱ መውጫ መግቢያውን እንዳያይ በጥቁር ጨርቅ ተሸፍኖ ወደ ኢጣሊያ ምሽግ ተወሰደ ...

«በቃ ጦርነቱን አቁሙ! እኛም እጃችንን እንሰጣለን» የሚል መልዕክት ይዘው አባ ጆቢር አባ ጅፋር አንድ የሻለቃ ማዕረግ ያለው የኢጣሊያ መኮንን አስከትለው ከመንግስቱ ቦጋለ ጋር ወዲያው መጡ። አባ ጆቢር ከሻለቃው ጋር አባ ጅፋር ግቢ ገቡ፤ ጦርነቱም ቆመ!

በማግስቱ ደጃዝማች ገረሱ በተላከባቸው መልዕክት መሰረት ወደ አዲስ አበባ በሚወስደው መንገድ ላይ ከጅማ ከተማ አስራ አምስት ኪሎ

ሜትር በሚርቅ ቦታ ከግልገል ጊቤ ከመጡት እንግሊዞችና ከእነ ጃገማ ጋር ተገናኙ። ከጊቤ የመጡት እንግሊዛውያንም «ገረሱ! እንግዲህ እርስዎ ጅማን ይዘዋል። እኛ በዓለም ደንብ መሰረት ስለሆነ ኢጣሊያውያንን የምንማርከ የጠላትን ጦር መሳሪያ እናንተ ትወስዳላችሁ፤ እስረኞችን እኛ እናስራለን። ስለዚህ እርስዎና ጦርዎ እዚህ መቆየት አለባችሁ» ብሎ የእንግሊዝ ጦር ጅማ ከተማ ገብቶ የኢጣሊያን ምሽግ ያዘ። ደጃዝማች ገረሱም ጃገማን ወደ አጋሮ፤ ዘውዱ ጥላሁንን ወደ በሰጠ ጫካ ሄደው የኢጣሊያን ጦር እንዲወጉ አዘዟቸው።

የበጋ መብረቁ የጃገማ ጦር አጋሮ ከነበረው የኢጣሊያ ጦር ጋር ሶስት ቀናት የፈጀ ጦርነት አድርጎ አንድ ሺ አምስት መቶ ባንዳ፣ አምስት መቶ የኢጣሊያ ሰራዊት ከእነ አዛዥ ጄኔራሉ ማረከ። ወጣቱ የአርበኞች መሪ አጋሮን፣ ጌራን፣ በደሌን ከጠላት መንጋጋ አላቆ የህዝቡን ነፃነት መለሰ። የኢጣሊያ ጦር ከተደመሰሰ በኋላ ንጉስ ነገስቱ ጅማ ገቡ። ጃገማም ወደ ጅማ ተጠራ። የሚነዳት መኪና መንገድ ላይ ስለተበላሸችበት ንጉሰ ነገስቱ ዘንድ ደርሶ ባያገኛቸውም ደብዳቤ ጽፈውለት መሄዳቸው ተነገረው።

«ጃገማ የሰራኸውን ሁሉ ጀግንነት ገረሱ ነግሮናል ... በጣም ጥሩ ነው። አገሩን በሰላም እየጠበክ፣ ባላገሩም እንዳይጎዳ እየተንከባከብክ፤ ከተማውም እንዳይዘረፍ በማድረግ ጠላትን ብቻ እየተዋጋህ መቆየትህ የሚያስደስት ነው። ማረፍ ኢጣሊያ አገራችንን ሲለቅ ነውና አሁንም የኢጣሊያን ጦር ተከታትለህ ወደ ጎሬ ዝመት ...» ይላል የንጉሰ ነገስቱ ደብዳቤ።

ወጣቱ የአርበኞች መሪ የንጉሰ ነገስቱን ትዕዛዝ ተቀብሎ ወደ ጎሬ ዘመተ። በሐምሌ ወር የደዴሳንና የሶርን ወንዞች ሰው በሐረግ ላይ እየተንጨዋለለ፣ ከብቱ በመጫኛ ታስሮ በመጎተት እየተሻገረ የበጋ መብረቆች ጦር ጎሬ ገባ። ጎሬ ሲገቡ ግን በራስ መስፍን ስለሺ የሚመራው የአርበኞች ሰራዊት ቀድሞ ደርሶ አገኘው። የኢጣሊያ ጦርም ተደመሰሰ። ሰላም ከሰፈነ በኋላ ራስ መስፍን ስለሺ ጃጌ ጃገማን ቡሬን አስጎብኝተውት ወደ ጎሬ ተመለሱ።

ከዚያ በአውሮፕላን ለአርበኞች ወረቀት ተበተነ። ወረቀቱ ላይ የነበረው ፍሬ ሃሳብ «ተለዋጭ ትዕዛዝ እስኪነገራችሁ ድረስ ከኢጣሊያ ሰራዊት ያስለቀቃችኋቸውን አካባቢዎች ፀጥታ በማስከበርና በማስተዳደር እንድትቆዩ» የሚል ነው። በዚያ ትዕዛዝ መሰረት ጃገማ ይዞት የቆየውን ጌራን፣ ጉማይን፣ በደሌንና አጋሮን ማስተዳደር ጀመረ። ደጃዝማች ገረሱም





የከፋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሲሆኑ ጌራና አጋሮ ከጃገማ ተወስደው ለሌሎች ተደለደሉና ጃገማ የጉማይ አውራጃ ገዥ ብቻ ሆኖ ጦሩን ጉማይ ላይ አሰባሰበ።

በመስከረም 1934 ዓ.ም ጃገማ ታሞ ከጅማ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ቀበና አካባቢ ከሚገኘውና ጀርመን ለጋሲዮን ከሚሰራው አጎቱ ቤት ገብቶ ተኛ ። በነጋታው ለህክምና ምኒልክ ሆስፒታል ሄደ። ሐኪሞቹም «ፀጉርህን ተላጭና ተኛ» አሉት። ጃገማ አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ እንደ ጦጣ ሲዘል እያዘናፈለ ይዞት የኖረውን ፀጉሩን ፎቶ ሳልነሳ አልላጭም ብሎ «እምቢኝ .. አሻፈረኝ» በማለት ወደ አደረበት የአጎቱ ቤት ተመለሰ።

ጃገማ ታሞ መምጣቱንና አልላጭም በማለት መመለሱን የሰሙት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ታሞ ከተኛበት ደሳሳ ቤት ድረስ ሄደው ጠየቁት፤ አልላጭም ያለበትን ምስጢርም ነገራቸው። ንጉሱም ፍንጭታቸውን እያሳዩ ደጋግመው ከሳቁ በኋላ የሚፈልገውን አድርጎ እሳቸው ከሚልኩት ሰው ጋር ሆኖ ፀጉሩን ተላጭቶ እንዲተኛ ትዕዛዝ ሰጡት።

ከቀናት በኋላ የጃገማ ሰራዊትና ደጃዝማች ገረሱ መጋጨታቸውን በማገገም ላይ የነበረው የአርበኞች መሪ አዲስ አበባ እንደሆነ ሰማ። ወደ ንጉሰ ነገስቱ በመሄድም «ሰራዊቴና ደጃዝማች ገረሱ ተጋጭተዋል፤ ቢሆንም የአርበኞቼ ጥፋት በዳኝነት መታየት ያለበት በአካባቢያቸው መሆን ስለሚገባው እንዲመለሱ ይፈቀድልኝ» ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ንጉሰ ነገስቱን ፈቃድ ጠየቀ። ንጉሰ ነገስቱም አቤቱታውን ተቀበሉ።

በዚያ መሰረትም ሰራዊቱ ጅማን በሌሊት እንዲያልፍ አስደርጎ ወደ አካባቢያቸው በሰላም ተመለሱ። አቤቱታው ተቀባይነት የአገኘችበት ቀን ግን ህይወቱን ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋገረች ቀን ሆነች።

* * *

እያንዳንዱ ቀን አዲስ ጦርነት ይዞ ይመጣል። ያ ጦርነት ግን አንዳንዴ እንደሚከሰተው ውጫዊ ጦርነት ሳይሆን ሁሌም ማሸነፍ የሚገባን ሌላ ጦርነት ነው - ውስጣዊ ጦርነት። ጃገማ ፊት ለፊት ከሚደረግ የጦርነት እሳት ይራቅ እንጂ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ በውስጣዊ ጦርነት መፈተኑ አልቀረለትም። መሸከም በማይችለው ናስማሰር ገና በአስር ዓመቱ በታላላቅ ወንድሞቹ እገዛ ተኩስ እንዳልተማረ ሁሉ የቤተ-መንግስትን የስልጣን ሽኩቻ አይቶ መቀበል አልተቻለውም። በተለይም ንጉሰ ነገስቱ የአርበኝነት ኒሻን

ሲሸልሙ ባንዶችና ስደተኞች በአርበኞች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመቋቋም ጃገማ ሀሊናውን ማጠንከር ነበረበት።

ንጉሰ ነገስቱ ራሳቸው በተዛዋዋሪ መንገድ የአርበኞች ታሪክ ጎልቶ እንዳይወጣ፣ እንዳይፃፍና የእሳቸውንና የታላላቅ መኳንንትን ስምና ተግባር እንዳያቀል ብርቱ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚያደርጉ ያወቀው ጃገማ ከዚያ ሽኩቻ ክብደት ይልቅ በአስር ዓመቱ ሊሸከመው ያልቻለው ናስማሰር ጠመንጃ የሚቀል ሆኖ ተሰማው። ለምሳሌ የኒሻን ሽልማት ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው መመረጥ የነበረባቸው በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ትግል በዱር በገደል ለሃገራቸው ከተዋደቁት አርበኞች ውስጥ መሆን ሲገባው የሽልማት ኮሚቴው ሰብሳቢ የነበሩት ግን በስደት የቆዩ ነበሩ። ይህ ደግሞ የጃገማን የአዲስ አበባ ቆይታ መጠራጠርና አለመተማመን የበዛበት አደረገው። ሁሉ ነገር ወርቅ የተቀባ እንጂ ወርቅ እንዳልሆነ እየተረዳ መምጣቱ ህይወቱን አታካች አደረገበት።

ጃገማ ሲበሳጭ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። አስቸጋሪ የሚሆነው ተበሳጭቶ ስላበሳጨው ነገር ቶሎ ስለማይናገር ነው። ሲቆይ ደግሞ ብስጭቱ ይበርድና ውስጡ የተነሳው እሳት ወደ ውጭ ከመውጣቱ በፊት እዚያው ጠፍቶ እዚያው ተዳፍኖ ይከስማል። ስለዚህ እንደ አባት የሚቀርባቸው ንጉሰ ነገስት እሳቸውም እንደ ልጅ ይመለከቱት እንጂ የቤተ-መንግስቱ ህግ፣ የሹማምንቱ ንቀትና ጥላቻ እንደ ተራራ ገፋ የማያደርጉት እንደሆነ ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀበትም።

* * *

በ1935 ዓ.ም ለታህሳስ ገብርኤል ጃገማ ንጉሰ ነገስቱን ለማጀብ የታቦት ንግሱ ከሚደረግበት ቤተክርስቲያን ሄደ። ያን ቀን የሚያምር ካኪ ቁምጣና እጀ ጉርድ ሸሚዝ ለብሶ ነበር። ንጉሰ ነገስቱ ስርዓቱ አልቆ ታቦቱ ከገባ በኋላ አስጠሩት።

«ምነው መልክህ በዛ? ፈሪ ነህ መሰል?» አሉት፥ ንጉሰ ነገስቱ - ፈርጠም ብለው።

«ፈሪ ነው የሚል ካለ ይናገር ...» አለ፥ ጃገማ - እሱም ሳቅ እያለ። ንጉሰ ነገስቱ ለትንሽ ሰከንድ በዝምታ ተውጠው ቆዩና «ጃገማ?» አሉት።

«አቤት! - ጃንሆይ» አለ፥ ጃገማ - ፊታቸው ቅጭም ሲል እሱም ኮስተር ብሎ።





«'እንዳታገባ! እኛ ነን የምንድርህ' ያልንህን አልረሳህም አይደል?»

«አልረሳሁም ጃንሆይ!» አለ ጃገማ። ንጉሰ ነገስቱ ትልቅና ወደ ቀኝ ጎን ገደድ የሚለውን ቀኝ እግራቸውን አስቀድመው መሄድ ሲጀምሩ አጃቢዎቻቸው ከፊት፣ ከኋላ፣ ከጎንና ጎን ሆነው አስፍተው ይዘው ንጉሰ ነገስቱ መሃል፤ ከፍተኛ መኳንንቱ ከኋላ ሆነው ወጡ።

ጃገማ «እንዳታገባ! እኛ ነን የምንድርህ ... እንዳታገባ እኛ ነን የምንድርህ፣ እንዳታገባ እኛ ነን የምንድርህ ...» የሚለው የንጉሰ ነገስቱ ቃል ህሊናው ውስጥ እየደጋገመ እየተሰማ ረፍት ነሳው። ጃገማ ንጉሰ ነገስቱ የገቡለትን ቃል ለወራት ሲያወጣና ሲያወርድ ቆየ። በተለይም የጄኔራል አቢይን ሁኔታ ካስተዋለ በኋላ «እንዳታገባ እኛ ነን የምንድርህ» ያሉት ምን እልባት አምቻ ለማድረግ አስበው እንደሆነ ገምቷል። ጃገማ ግን በሶስት ምክንያቶች አምቻነቱን አልፈለገውም።

አንደኛ፤ የንጉሰ ነገስቱን ልጅ ያገባው ጄኔራል አቢይ ቤተመንግስት ውስጥ ሲቀመጥ ከሚስቱ በታች ነው። አንዳንድ ጊዜም እሷ ቤተመንግስት ተጠርታ እሱ ላይጋበዝ ይችላል። ጃገማ ያን ልዩነትና ከፍ ዝቅ መደረግ አልወደደውም። ሁለተኛ፤ አምቻ ከሆነ ምንም ቢያደርግ በስራው ሳይሆን በአምቻነቱ አገኘው ስለሚባል የሰው ሃሜት የሚፈጥርበትን የሥነልቦና ዝባዝንኬ አልፈለገውም። ሶስተኛ፤ ከአንዲት ጉብል ጋር አይነቱ ያልሰየ የዐይን ፍቅር ይዞታል። ለንጉሰ ነገስቱ በገባው ቃል መሠረት «ና እንዳርህ» ብለው እስኪጠሩት ከጠበቀ ህይወቱ ባላሰበው አቅጣጫ ነጉዶ ስንክሳር የበዛበት ማጥ ውስጥ ዐይኑ እያየ መግባቱ ነው።

ለዚህ አጣብቂኝ መፍትሔ የሚሆን አስቸኳይ መላ ቀንና ሌሊት ማሰላሰል ጀመረ። አንድ ቀን ታዲያ ለንጉሰ ነገስቱ ምን ማለት እንዳለበት ወሰነ። ችግሩ ግን ያሰበውን እንዴት እንደሚነግራቸው ነው። በእሱ አንደበት መንገሩ የማይሞከር ሆኖ አገኘው። ስለዚህ ዘዴ ማውጠንጠን ቀጠለ። አንዱን አንስቶ አንዱን ጣለ። በመጨረሻ ሊቀ ጳጳሱን አሰበ። ከጠላት ወረራ በፊት የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ንስሃ አባት አቡነ ጴጥሮስ ነበሩ። አቡነ ጴጥሮስን ግን ፋሽስቶች በጥይት ደብድበው ገድለዋቸዋል። ንጉሰ ነገስቱ ከስደት ሲመለሱ በእሳቸው ምትክ ንስሃ አባታቸው የሆኑት እጨጌ ወልደጊዮርጊስ (በኋላ አቡነ ባስሊዎስ የተባሉት) ነበሩ።

ጃገማ እጨጌው ዘንድ ሄዶ «... አባቴ ጃንሆይ ለእኔ በማሰብ አለማግባቴን ስነግራቸው እኛ ነን የምንድርህ ብለውኝ ነበር። አሁን ከአንዲት ልጅ ላይ ዐይኔ አርፎባታል፤ እሷን ካላገኘሁ ራሴን ስለማጠፋ ለእኔም ለንጉሰ ነገስቴም የምበጅ አልሆንምና እባክዎ ያማልዱኝ?» አሳቸው። እጨጌውም የተናገረውን በፅሞና አዳመጡና፤

«ጥሩ ነው ልጄ፤ እንዳልኸው ቀልብህ ያረፈባት አግኝተህ ከሆነ ጥሩ ነው ... ሆነም አልሆነም ግን አንድ ምሳሌ ልንገርህ፥ የኔ ልጅ። አንድ ጊዜ አንዲት መጓዝ የምትወድ ጥበበኛ ሴት ነበረች። እንደተለመደው እየተጓዘች ተራራ ስትወጣ በጣም የከበሩ ውድ አልማዞች ወንዝ ውስጥ አገኘችና ኮረጆዋ ውስጥ ከተተቻቸው። በነጋታው ስትጓዝ የተራበ መንገደኛ አገኘች። ጥበበኛዋም ኮረጆዋን ከፍታ ከስንቋ አካፈለችው። የተራበው መንገደኛም የዕለት ስንቋን መብላት መጠጣቱ አንሶ ኮረጆዋ ውስጥ ያየውን የከበረ አልማዝ ስጭኝ አላት። አብልቼዋለሁ፤ አጠጥቼዋለሁ ብላ ሳትኩራራ የጠየቃትን አልማዞች መዠልጣ ሰጠችው። መንገደኛው በሚገርም ዕድሉ እየተደሰተ ሄደ። የወሰደው አልማዝ ቢሸጥ የዕድሜ ልክ ወጪውን ሸፍኖ እንደሚያኖረው ሲረዳ ጊዜ አልወሰደበትም።

«በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ግን ለጥበበኛዋ ሴት አልማዙን ለመመለስ ተመለሰ። 'ብዙ ጊዜ አሰብሁ' አላት 'የሰጠሽኝ አልማዝ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነም አረጋግጫለሁ፤ ይሁን እንጅ ከዚህ የበለጠ የከበረ ነገር እንደምትሰጭኝ በመተማመን የወሰድሁትን አልማዝ ልመልስልሽ ነው' አላት። በመቀጠልም እባክሽን ካለምንም ማቅማማት የከበረ ድንጋዩን እንድትሰጭኝ ያደረገሽን የብስለት ምስጢር ንገሪኝ' አላት ይባላል።

«ንጉሰ ነገስቱን ያህል ሰው 'ሳጋባህ' ሲል፣ አምቻነትህን ሲፈልግ ከዚያ ከፍ ያለ ክቡር ነገር የለም። ነገር ግን ከጋብቻው ይልቅ የስራህን ፍሬ እያዩ ከፍ ከፍ ቢያደርጉህ ላንተ የበለጠ ይሆናል። ያን እስተውለህና በራስ መተማመንን መርጠህ ጋብቻው ይቅርብኝ፤ ጌትነትዎ እና ግንኙነታችን ይበቃኛል ማለትህ የዕለቱን ትቶ የዓመቱን የማሰብ ትልቅ ጥበብ ነው» ብለው ልመናውን ለንጉሰ ነገስቱ ለማቅረብ ፈቃደኛ እንደሆኑ ነገሩት። ወጣቱ የአርበኞች መሪ ጃገማ አባ ዳማ እጨጌውን አመስግኖ ሄደ።

ከቀናት በኋላ ሊቀ ጳጳሱ አስጠሩትና «ጃገማ! ለንጉሰ ነገስቱ የሰጠኸኝን መልዕክት አድርሼ ፈቃድ አድርገውልሃልና ሄደህ ጫማቸውን ሳም» አሉት። ጃገማ የዝቋላ ተራራ ከጫንቃው ላይ የተነሳለት ያህል «እምቡር» እያለ ሄዶ የተባለውን አደረገ።



# ፲፪

# ከአርበኛነት ወደ ጦር መኮንንነት

በ1934 ዓ.ም ጃገማ ለንጉሰ ነገስቱ ዕድሜው ሃያ ዓመት እንደሆነና በጦር ሰራዊትነት ከማገልገል ይልቅ ቀደም ሲል ለሶስት ወራት ጀምሮ ያቋረጠውን የቀለም ትምህርት መቀጠል እንደሚፈልግ ገልጾ «ገና ልጅ ስለሆንሁ ያቋረጥሁትን ትምህርት እንድቀጥል ይፍቀዱልኝ» በማለት ይጠይቃቸው ነበር። ንጉሰ ነገስቱ ግን «ወንድሞችህ ሀይለኞች እንደሆኑ ሰምተናል፤ ለአንተም ሆነ ለወንድሞችህ የሚበጀውን እስክናደርግ ጠብቀን» አሉት። ይህን ያሉበት ምክንያት አለ። ሊጋባ ጣሰው የተባሉ አውራጃ ገዥ የጅባትና ሜጫ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው አምቦ ነበሩ። ሊጋባ ጣሰው ጊንጪ ከተማ መጥተው የችሎት ዳኝነት ሲያዩ አሳላፊ ታዬ የተባሉ ሰው ጊንጪ ከተማ የሚኖረውን የጃገማን ወንድም ጊዲ ኬሎን (በኋላ ሻምበል) ከሰው ሊጋባ ጣሰው ፊት ያቀርቡታል። ችሎት ላይ እንደቆሙ አሳላፊ ታዬ ጊዲ ኬሎን ከህግ ውጭ መዝለፍ ጀመሩ። ጊዲ ኬሎ «ጌታዬ እኔ ዳኝነት ያያሉ ብዬ ነበር አክብሬዎት የመጣሁት፤ አሁን ግን ዳኝነት ሳይሆን ስድብ ብቻ ነው የተረፈኝ። ስለዚህ የእርስዎን ዳኝነት አልፈልግም» ብሎ ችሎቱን ረግጦ ሄደ።

ይህን ጊዜ አንዱ ወደ ሊጋባ ጣሰው ጠጋ ብሎ «ጌታዬ የጃገማ ኬሎ ወንድሞች ሃይለኞች ናቸው። ስለዚህ ጊዲና ጠንቋሳ ኬሎ መትረየስ አምጥተው አደጋ ሳያደርሱብዎት ቶሎ ያምልጡ» አሏቸው። ሊጋባ ጣሰው ቶሎ ብለው መኪናቸው ውስጥ ገብተው ወደ አምቦ ተመለሱ። በማግስቱ ወደ አዲስ አበባ የሚያስኬድ ቀጠሮ ስለነበረባቸው ለቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ደውለው «ጃንሆይ! እኔ ለመምጣት አልቻልኩም፤ የጃገማ ወንድሞች መንገድ ዘግተውብኛል» አሏቸው። ንጉሰ ነገስቱም ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸውንና ራስ መስፍን ስለሺን አዘው ጃገማን አስጠሩት።

«ጃገማ! ለአንተም ሆነ ከጅማ ለተመለሰው ሰራዊትህ መተዳደሪያ ለማድረግ እየተዘጋጀ ነው። ለምን ወንድሞችህ እንዲህ የሚጥሩትን ሊጋባ ጣሰውን መንገድ ዘግተው እንዲገድሉ ታደርጋለህ?» ብለው ንጉሰ ነገስቱ አስጠየቁት። «እኔ በፍፁም አልሰማሁም፤ ስለተፈጠረው ነገርም አላውቅም። እኔ ከመስከረም እስከ ግንቦት 1934 ዓ.ም ድረስ ለህክምና ከመጣሁ በኋላ ወደ

ጊንጪ አልተመለስሁም ...» ብሎ ወጥቶ ስልክ ደወለ፡፡ ወንድሙ ጊዲ የሆነውን ሁሉ በሚገባ ነገረው፡፡ ጃገማ ተመልሶ ሄዶ ለቢትወደድ መኮንንና ለራስ መስፍን ጉዳዩን አስረዳ፡፡ እነሱም ምክንያቱን ለንጉሰ ነገስቱ አቀረቡ፡፡

ከዚያ በኋላ ጃገማ ገና ሃያ ዓመቴ ስለሆነ ያስተምሩኝ እያለ ንጉሰ ነገስቱን እየደጋገመ ቢጠይቅም «ቆይ! የአንተ ወንድሞች ሃይለኞች ስለሆኑ እንዴት እንደምትማር እያሰብንበት ነው» ይሉታል፡፡

* * *

ጃገማ እንደሚያስታውሰው ጭልሞ፣ ከአምቦ እስከ ጉደር ድረስ የነበረው ሰንሰለታማ ተራራ በደን የተሸፈነ ነበር፡፡ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት «መሬቱ የአንተ፣ ደኑ የኔ ነው» ብለዋል ምኒልክ እየተባለ አዋጅ እንኳን ሳይኖር በተለምዶ ደኑ የመንግስት መጠቀሚያ መሆኑ በዘውዲቱና በኃይለ ስላሴ ዘመንም ቀጥሎ ነበር፡፡ በተለይም በአርሲ፣ በጅማ፣ በባሌ ደኖች ሳልተከለ እየተሰጡ ከመጨፍጨፋቸውና መሬቱ ከመራቆቱ ሌላ ቅሬታው መንግስትንና ህዝቡን ሆድና ጀርባ እያደረጋቸው ነበር፡፡ መንግስት ደኑን እያከናተረ ሲሸጥ ህዝቡ ግን ዛፍ የመቁረጥ መብት እንኳን አልነበረውም፡፡

ለምሳሌ ጆምጆም ላይ የነበረው ደን ለሙሴ ባሴት ተከናትሮ ሙሴ ባሴት የእንጨት ፋብሪካ ከፍቶ ይመደምደው ነበር፡፡ ጋጅ ላይ የሙሴ ኒኮላስ፣ ጫንጮ ላይ የወስሴ አስላንጼስ፣ ጭልሞ ላይ የግርማዊት እቴጌ፤ እንዲሁም ዮብዶ፣ ግልፍጣና በጅሮ ላይ በአጭር ርቀት በደን በተሸፈነው ቦታ በአጠቃላይ ስድስት የእንጨት መሰንጠቂያ ፋብሪካ ተከፍቶ ደኑ በግሪኮችና በሌሎች የውጭ ሰዎች ሲመደመድ ለስሙ አንድ ዛፍ የቆረጠ በምትኩ ስድስት ዛፍ ይተክላል ቢባልም ያን ሃላፊነት የሚወጣና የሚያስፈጽም አልነበረም፡፡

እነዚያ የእንጨት መሰንጠቂያ ፋብሪካዎች ከባለርስቶች ይዞታ ላይ ተወስደው የተከናተሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ የመሬት ይዞታው ውስጥ ደን ያለው መሬቱን እንዳይነጠቅ ላዩ ላይ ያለውን ደን መንግስት እንዳይቀጣው በስውር ማጥፋት ነበረበት፤ ከተደረሰበት ግን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሚሰው ብሂል ዕጣ ፋንታው ይሆን ነበር፡፡





በ1935 ዓ.ም ከነፃነት ማግስት ጭልሞ የነበረው የግርማዊት እቴጌ የእንጨት መሰንጠቂያ አስተዳዳሪ በመሆን ሃይለማርያም ገዝሙ ተሾሙ፡፡ ሃይለማርያም የሰላሌ ሰው ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ጃገማን አስጠሩት፡፡

«ጃገማ ከእቴጌ ደን ጎን ነው የአንተ የደን ይዞታ ያለው፡፡ በደንቡ መሠረት በአንተ ይዞታ ስር ያለው ደን ከእቴጌይቱ ደን ጋር መዳበል አለበት፡፡ እኔ ግን ከአንተ ተወስዶ ለእሳቸው እንዲሰጥ አልፈልግም፡፡ እንደምሰማው በእርሻ ሚኒስቴር በኩል ደንን በተመለከተ የወጣ ደንብ የለም፡፡ 'ደኑ የኔ ነው' በሚል በምኒልክ ጊዜ ተባለ በሚል የማንም መሬት እየተወሰደ ነው፡፡ እኔ ግን አንተ በአርበኝነት የከፈልከውን መስዋዕትነት እያወቅሁ ደንህን ወደ እቴጌ ደን አልጠቀልልብህም፡፡ ስለዚህ ለአገርህ ማገልገልህን ጠቅሰህ ብታመለክት አይከለክሉህምና ጠይቅ፤ ከዚያ ለእኔ ትሸጥልኛለህ» አሉት፡፡

ጃገማ በሀሳባቸው ተስማማና በወቅቱ «እርሻ ሚኒስቴር» ለሚባለው መስሪያ ቤት ማመልከቻ ጻፈ፡፡ ማመልከቻው እንዲህ የሚል ነበር፤

«ለጅባትና ሜጫ አውራጃ
በኮንሴሲዮን ውስጥ ያልተካለለ፣ ኮንሴሲዮን ለማቋቋምም አቅም የሌለው፣ በምገብርበት መሬት ላይ ያለውን ዛፍ ቆርጬ እንደ ባለኮንትራቶች አዳዲስ ዛፍ ለመትከል ግዴታ በመግባት ዛፎችን ከፍዬ እንድሸጥ ይፈቀድልኝ፡፡»

እርሻ ሚኒስቴር በራሱ መንገድ ሰው ልኮ አጣርቶ «ደኑ የኔ፣ መሬቱ ያንተ ነው» የሚለውን የ«አሉ» ደንብ ላለመተላለፍ «አይፈቀድልህም» በሚል አቤቱታውን ዘጋው፡፡

ከዚያም ጃገማ ሲከፋው ወደሚሄድበት አመራ፡፡

«ጃንሆይ! የምገብርበት ርስቴ ነው፤ አልፎ አልፎ ለሳንቃ የሚሆን እንጨት አለው፡፡ ለኮንሴስዮንም አልተከለለም፡፡ ኮንሲስዮንም ለማቋቋም አያስችልም፡፡ ስለዚህ እዚህ ይዞታዬ ላይ ያለውን ዛፍ ባለ ኮንትራቶች ቆርጠው በሜትር ኪዩብ እንደሚከፍሉት፣ ለመትከልም ግዴታ እንደሚገቡት ገብቼ ቆርጬ እንድሸጥ ይፍቀዱልኝ» ብሎ ጃገማ አመለከተ፡፡ ንጉሰ ነገስቱም «መኮንን ባለበት ንገረኝ» አሉት፡፡ አቶ መኮንን ሃብተወልድ የወቅቱ የእርሻ ሚኒስትር ነበሩ፡፡

ጃገማ ከዚያ ቀደም ብሎ ከጣሊያኖች የማረከውን አንድ «አርዲታ ኮሎኒያሌ» መኪና ገንዘብ ሚኒስቴር «የወታደር መኪና ነው» ብሎ ስለወሰደበት ያን መኪና ለማስመለስ ለንጉሰ ነገስቱ «ጃንሆይ! በሌላው አገር አምሳ አለቆች እንኳን በመኪና ነው የሚሄዱት፤ እኛ ገና ስላልተቋቋምን ነው... እኔ የሻለቃ ማዕረግ ነው ያለኝ:: ስለዚህ እንዴት ከጠላት ማርኬ ይዤው የቆየሁት የወታደር መኪና ተብሎ ይወሰድብኛል?» ብሉ አመልክቶ ነበር::

«አቶ ይልማ ባለበት ንገረኝ» አሉ ንጉሰ ነገስቱ:: ጃገማ፤ «እሺ» አለ::

ንጉሰ ነገስቱ በመስኮት በኩል ይቆማሉ:: ልዑላን፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ከፍተኛ መኳንንት፣ የጦር አዛዦች ከኋላቸው ይቆማሉ:: ህዝቡ ደግሞ ድንኳን ተተክሎለት ይቆማል:: ጃገማም የሚቆመው ከህዝቡ ጋር ነው:: ችሎቱ እንደተጀመረ አቶ ይልማ ወደ ንጉሰ ነገስቱ ቀረብ ብለው በጆሮአቸው የሆነ ነገር ሹክ ብለዋቸው ተመለሱ:: ጃገማ ሊያገኛቸው በጭራሽ አልቻለም:: ከችሎት በኋላ ጃገማ «ጃንሆይ! አቶ ይልማ እኮ መጥተው ነበር» አለ::

«ሲመጣ ንገረን አላልንም?» አሉ ንጉሰ ነገስቱ::

«ጃንሆይ! እንዴት አድርጌ መጥቼ እነግርዎታለሁ፤ እኔ ያለሁት ድንኳን ውስጥ ...» አለ ጃገማ::

እሳቸውም «ፈዛዛ! ማን ከጀርባ አትቁም ብሎ ከለከለህ?... ከአሁን በኋላም በችሎት ጊዜ ከኋላ ከሚቆሙት ጋር ቁም» ብለውት ስለነበር ወጣቱ ጃገማ ንጉሰ ነገስቱ ለችሎት ሲቆሙ ከኋላቸው ከሚቆሙት ልዑላን ቤተሰቦችና ከፍተኛ መኳንንት አንዱ ሆነ:: ጉዳዩም ተፈጸመለት::

ስለዚህ ጃገማ አንድ ቀን ከንጉሰ ነገስቱ ጀርባ እንደቆመ አቶ መኮንንን አያቸው:: ወዲያው ወደ ንጉሰ ነገስቱ ጠጋ ብሎ «ጃንሆይ! አቶ መኮንን እኒያውና፤ ያን ነገር ይንገሩልኝ» አላቸው:: ንጉሰ ነገስቱ አቶ መኮንንን አስጠርተው ካነጋገሩ በኋላ ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግስታቸው ሲገቡ «ጃገማ! ሂድና መኮንንን አነጋግረው» አሉት:: ጃገማ አቶ መኮንን ሃብተወልድን ለማነጋገር ሄደ::

«ሰማህ ልጄ!» አሉ፥ አቶ መኮንን - የጃገማ ትከሻ ላይ ቀኝ እጃቸውን ጣል አድርገው::





«ከአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ 'ደኑ የኔ ነው፣ መሬቱ ያንተ ነው' የሚል ልማድ ስለነበር ይኸው በማንም ሰው መሬት ላይ ያለውን ደን እየነጠቅን በመሸጥ መንግስትን ስንጠቅም፣ ህዝቡን ስንጎዳ ኖረናል:: በዚህ መንገድ እንድንሰራ ግን በእርሻ ሚኒስቴር የወጣ ደንብ የለም!

«አሁን ማንም እየተነሳ ደንብ የለምና አሰራራችሁን ለውጡ ቢለን የተለመደውን ነገር አንቀይርም:: አንተ ግን በወጣትነትህ አርበኛ ሆነህ ለአገርህ ነፃነት ከፍተኛ ተጋድሎ የፈፀምህ፣ የንጉሰ ነገስቱም ምስጋና የተቸረህ አርበኛ ብቻ ሳትሆን የአርበኞችም መሪ ነህ:: ስለዚህ በዚህ አንፃር ብቻ ዛፎችን ቆርጠህ በመሸጥ እንድትጠቀም ፈቅደናል:: በማመልከት ግን የሚሆን አልነበረም ...» አሉት::

* * *

በ1934 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ከጅማ ዘመቻ በድል የተመለሱት በወጣቱ ጃገማ አመራር ይተዳደሩ የነበሩት ሶስት ሺ አርበኞች በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ መተዳደሪያ እየተሰጣቸው ወደ ግብርና ሞያቸው ተመለሱ:: ከግንቦት 9 ጀምሮ አምስት መቶ አርበኞችን ይዘው በሻለቃነት ማዕረግ ሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ የገቡት ጃገማና ሌላው አርበኛ እሉላ በቀለ ከዘብ ጥበቃ በስተቀር የውትድርና ስልጠናውን ለስድስት ወራት ተከታትለው ተመረቁ::

ጃገማ ወጣት የአርበኛ መሪ ሆኖ አፍላ የጉርምስና እድሜው ሳይገድበው በጋጅ፣ አዲስ ዓለም፣ ሐሮታ ... ከጠላት ጋር ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል:: ጄኔራል ጋዚራ የጊቤን ድልድይ ሰብሮ በጅማ፣ በአጋሮ ወታደሮቹን አሰባስቦ፣ ምሽጉን አጠናክሮ ለመድፈር በሚያስፈራራበት ጊዜ የኢጣሊያን ጦር ምሽግ ሰብሮ አምስት መቶ ነጮችን ማርኮ ለእንግሊዞች በደረሰኝ አስረክቧል:: ንጉሰ ነገስቱም ዕድሜውን ሳይሆን ስራውን በማየት ወታደራዊ ስልጣንና ስልጠና እንዲያገኝ አድርገውታል::

ይሁን እንጂ ጃገማ ከባህር እንደወጣ አሳ ከአርበኝነት ዘመኑ በኋላ በራስ መተማመኑና የህሊና እርካታው የንጉሰ ነገስቱ ባለሟሎች በሚያሳዩት መጠራጠር ቀስ በቀስ ይቀንስ ጀመር:: በዘርና በትምህርታቸው የሚመኩትም ከንጉሰ ነገስቱ እንዲርቅ የተንኮል መንጠቆቻቸውን ጥለው ሊያጠምዱት ሞከሩ:: ጃገማ ሆለታ የሚሰጠውን ስልጠና እንዳጠናቀቀ መጀመሪያ አምቦ ተመደበ:: አምቦ ተመድቦ በማገልገል ላይ እንዳለ የአውራጃ ገዥው ሊጋባ

ጣሰው አስጠሩትና «ተከሰሃልና ዋስ ጥራ» አሉት:: አጠገባቸው ከነበሩት ውስጥ «እንዋሳለን» ሲሉ «እኔ ሳልጠይቅ» በማለት ገስፆ የሚያስከስስ ነገር እንዳልሰራና ዋስም መጥራት እንደማይፈልግ ገለፀ - ሻለቃ ጃገማ::

ሊጋባ ጣሰው በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ሌባን በአውጫጭኝ የሚያስወጡ የኢጣሊያ «ኮማንዳቶሪም» ሆነው አምቦ ተሹመው ነበር:: ያን ጊዜ የጊንጪ ባላባት ፊት ነሷቸው:: እንዲያውም አባ ዶዮ በሊጋባ ጣሰው ላይ ሲያፌጡ ጃገማ ኬሎ የሚባል ሽፍታ ዘመድ አላቸው ስለተባሉ ሊጋባ ጣሰው የሚከተለውን በመፍራት ወዲያው ሸሽተው ወደ አምቦ ሄዱ::

በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ደግሞ ሊጋባ ጣሰው እንደገና የአምቦ እንደራሴ ሆኑ:: በሊጋባው የሁለት መንግስታት ተሳትፎ ደስተኛ ያልነበረው አርበኛው ሻለቃ ጃገማ የአገሩን ወራሪ በዱር በገደል እየተንከራተተ ነፃ ያወጣው ቆጭ ብሎ፥ የጠላት የሌባ አውጫጭኝ የነበሩት ሊጋባ ጣሰው ባቀረቡለት የዋስ ጥራ ጥያቄ ባለመደሰቱ «ዋስ አልጠራም፤ እስኪ የሚያመጡትን አያለሁ» አለ::

እምቢ ባይነቱ ደግሞ ሊጋባ ጣሰውን ስጋት ላይ ስለጣላቸው «... ጃገማ በአስተዳደሬ ውስጥ እያለ ስራዬን በሚገባ መፈፀም አልችልም» ብለው አቤቱታ አቀረቡ:: በዚያ አቤቱታ መሰረትም እሳቸው ያገለገሉት የኢጣሊያ ወራሪ ጦር ሲያሳድደው የነበረው ሻለቃ ጃገማ ወደ ቢሾፍቱ ተዛወረ:: ቢሾፍቱም ብዙ መቆየት አልቻለም:: በወቅቱ እጅግ አስፈሪ የነበረውን የትግራይ አመፅ ለማክሸፍ ሄዶ እንዲፋለምና እንደ አበባ የፈካው ጀግና በዚያው ረግፎ እንዲቀር ወደሚንቀለቀለው የጦርነት እሳት ሳንቃ ላኩና አጋፈጡት::

* * *

ጄኔራል ጃገማ ጦረኛ እንጂ ነውጠኛ አልነበረም:: በህይወቱ ከሰው ጋር የተጣላው አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: ጃገማ ከአርበኝነት እንደመጣ አገር ፍቅር አካባቢ ከተሰጠው ቤቱ ተነስቶ ብስክሌት እየጋለበ ራስ መኮንን ድልድይ ሲደርስ ወደ ቤተመንግስት ለመሄድ ሲዞር ከሚውል በሰባ ደረጃ ብስክሌቱን እየገፋ መውጣትን መረጠ:: አንድ ወታደር ሲቪል ለብሶ፣ ሽጉጥ ታጥቆ ከላይ ወደ ታች ይወርዳል:: ጃገማ ደግሞ ከታች ወደ ላይ ሲወጣ ሰውየው ዘሎ አነቀው:: ጃገማም ብስክሌቱን ጥሎ አነቀው ... ሰውየው የጃገማን ሽጉጥ ሲይዝ ጃገማም የሰውየውን ሽጉጥ ያዘበት:: ሰውየው ጥንካሬውን ለመቋቋም ስለተቸገረ የወታደር ፊሽካ ከደረት ኪሱ አውጥቶ





ነፋ፤ ወታደሮች እየሮጡ መጡ:: «አንተ የጣቢያ አዛዥ ናቸው እኮ ...» አሉት ወታደሮቹ::

«ታዲያ ቢሆንስ! 'ፈቃድ አለህ ወይ' አላለኝ፤ ዘሎ ብቻ አነቀኝ:: ፈቃድ ቢጠይቀኝ አሳየው ነበር» አላቸው:: እንደተካረሩ ሲያውቁ ጽሕፈት ሚኒስቴር ጎን ወደ ነበረው ጣቢያ ይዘዋቸው ሄዱ:: ውስጥ ሲገቡ የጦር ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ የነበሩት ነጋ ሃይለስላሴ ቁጭ ብለዋል:: ጃገማን ሲያዩት
«ምንድን ነው? ይህ እኮ ሻለቃ አዛዥ ነው እናንተ፤ አታውቁትም?» አሏቸው::

«ዝም ብሎ ሽጉጤን ያዘብኝ ...» አላቸው፥ የጣቢያ አዛዡ - ለነጋ ኃይለስላሴ::

«እኔ ከታች ወደ ላይ እወጣለሁ፤ እሱ ከላይ ወደታች ይመጣል:: ሳያናግረኝ፣ 'ፈቃድ አለህ?' ብሎ ሳይጠይቀኝ፥ ብቻ ዘሎ አነቀኝ፤ እኔም አነቅሁት ...» አላቸው፥ ጃጋማ::

«እናንተ! ልጅ ስለሆነ ነው እኮ በብስክሌት ሲሄድ ያገኛችሁት ... የታወቀ የአርበኛ መሪ የሻለቃ ማዕረግ ያለውና በአጀብ መሄድ የሚገባው ሰው ነው ... አሁን በሉ ተስማሙ!» አሉ ...

በሌላ ቀን ከ«ተክሉ ደስታ ወርቅ ቤት» አለፍ ብሎ ካለ ቡና ቤት ጃገማና ጓደኞቹ ሲገቡ የጣቢያ አዛዡ ተነስቶ ወደ ውስጥ ሲገባ ጃገማ አየው:: ጃገማ ዝም አለ፤ ቁጭቱን ዋጥ አድርጎ ቆየ:: ሲያየው ብግን ብሏል፤ ምንም ምልክት ግን አላሳየም:: በመጨረሻ ጓደኞቹ ሁሉ ሲሄዱ እሱ ብቻውን ቀረ:: ከዚያ እጁን ሽጉጡ ላይ አድርጎ ጓዳ ሲገባ ሰውየው በመስኮት ዘሎ ሄዶ ኖሮ የለም:: ባለመኖሩ ደስ አለው፤ ቢኖር ኖሮ ገድሎት የእድሜ ልክ ፀፀት ውስጥ ይገባ እንደነበረ ሲያስብ አዘነ:: ከዚያ ቀን በኋላ በመዝናኛ ቦታ ምንም እንኳን ፈቃድ ቢኖረውም ሽጉጥ ይዞ መሄድ አቆመ:: ጃገማ የደስታም ሆነ የፈተና ምንጭ፥ ፈጣሪ ነው ብሎ ያምናል:: የሚሳሳትን ሰው መቻል ... ቢቻል ደግሞ ይቅር ማለት አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል:: ይቅር ባይነት ደግሞ የጠቢብ ጣፋጭ ብቀላ ነው:: ካለበለዚያ ለራሱ ለሚጠነቀቅና ለሚታበይ ሰው፥ እንኳን ሰው ፈጣሪም አያስብለትም፤ ለምን ቢሉ ትምህክቱ፣ ሽጉጡ፣ ስልጣኑ ... አሉለታ!

* * *

በትግራይ የተፈጠረው የህዝብ አመፅ በእነ ብላታ ኃይለማርያም ረዳ እና በሌሎቹም አስተባባሪነት የተቀሰቀሰ ህዝባዊ ነውጥ ነው። የአመፁ ዋልታና ማገር ደግሞ ጭቆና ያንገፈገፈው ህዝብ ነው።

በእንደርታ የተጀመረው የወያኔ እንቅስቃሴ ዓላማ በሽሃና እንዳየሱስ የነበረውን የመንግስት ጦር ደምስሶ መቀሌን በቁጥጥር ስር ማድረግ ነበር። ለዚያ ንቅናቄ መጀመር መነሻ ናቸው ተብለው ከሚነሱት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ባለስልጣኖች ትክክለኛ ፍትህ መስጠት አለመቻላቸው፤ የህዝቡ ኑሮ በሰበብ አስባቡ መመሰቃቀሉ፤ ማይጨው ላይ በተደረገው የ1928 ዓ.ም ውጊያ የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት እንዳልከፈለ፣ የኢጣሊያ ፋሽስቶች ይዘውት በመጡት ዘመናዊ መሳሪያና የመርዝ ጋዝ ጢስም እንዳልተጨፈጨፈ፣ ህዝቡ በዱር በገደል የፈፀመው የአርበኝነት ተጋድሎ ተዘንግቶ ለጠላት እንዳደረ መቆጠሩ፣ ህይወትና ንብረቱን ለአገሩና ለነፃነቱ እንዳልከፈለ በሃሜትና ሽሙጥ፣ በበቀልና ቅጣት መሰቃየቱ ጥቂቶቹ ናቸው።

ይህም የህዝብ ቁጣ በአመፁ አስተባባሪዎች እየተመራ «ለንጉሰ ነገስቱ አንገዛም» አሰኝቶ የፊት ለፊት ውጊያ አስነሳ። ሰኔ 26 ቀን 1935 ዓ.ም ሻለቃ ጃገማ ከእነ ሻለቃ አሉላ በቀለ፣ ደጃዝማች ተሰማ ቡርጂ ጋር የሻለቃ አዛዥ ሆኖ ማይጨው ተላከ። ማይጨው ከደረሱ በኋላ ከሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ ሰልጥነው የወጡት ጃገማ፣ ጠንቋሳና አለሙ ቂጤሳ እያንዳንዳቸው ሃያ ወታደሮችን መረጡና ለሃያ ቀን የጓዶች አመራር፣ የሰልፍ፣ የወታደራዊ ሥነምግባር ትምህርት... በማስተማር አሰለጠኗቸው። የሰለጠኑት ስልሳ ወታደሮች ደግሞ እያንዳንዳቸው ሃያ ሃያ ሰው አሰለጠኑ። በዚህ መንገድ የሰለጠኑት ደግሞ እያንዳንዳቸው ሃያ ወታደሮች እያሰለጠኑ በሁለት ወራት ውስጥ ሻለቃ ጦሩን በሙሉ አሰለጠኑት። ከአርበኝነት የመጣው ሻለቃ ጦር በስልጠናው ዘመናዊ ጦር ሆነ።

ከዚያ ስልጠና ባሻገርም ሻለቃ ጃገማ በእንግሊዞች ከሰለጠነውና 8ኛ ሻለቃ ተብሎ ይጠራ ከነበረው መደበኛ ጦር ጋር የኢላማ ተኩስ እንዲወዳደሩ በማድረግ ከሰኔ እስከ መስከረም በነበረው ጊዜ ሻለቃ ጦሩን ለውጊያ ብቁ የሆነ ጦር አደረገው።

በመቀጠል ደግሞ ጃገማ ወንዝ አስገድቦ መዋኛ በማዘጋጀት በሻለቃው ውስጥ የሚገኙ ወታደሮችን በውሃ ዋና፣ በኢላማ ተኩስ፣ በሩጫ... እያወዳደረና እሱም አብሮ እየተወዳደረ የወታደሮቹን ሞራል እያፍታታ አነቃቃው። በሶስት ወራት ውስጥ በሻለቃ ጃገማ የሚመራው ሻለቃ ጦር





ወታደራዊ ቅልጥፍና ያለው፣ በሞራል የተጠናከረ፣ በአዛዡና ወታደሩ መካከል ጥሩ ግንኙነት የነበረውና ለውጊያ የተዘጋጀ የሻለቃ ጦር ሆነ። ያ ደግሞ ወታደርነት ለጃገማ የዕለት እንጀራ ማግኛው ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ዝንባሌውና ውጤት የሚያስመዘግብበት ተሰጥኦ እንደሆነ አመላካች ሆነ።

እነ ሻለቃ ጃገማ ማይጨው እያሉ የወሎ፣ የትግራይና የጎንደር እንደራሴ የነበሩት ልዑል አልጋ ወራሽ ከጎንደር ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን ማይጨው አድረው አብሯቸው ጎንደር ዘምቶ የነበረውን ሁለት ሻለቃ ጦር ማይጨው ትተውት ሄዱ። አልጋ ወራሹ ደሴ እንደደረሱ የሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ አዛዥ የነበረው እንግሊዛዊ በማይጨው፣ አምባላጌ ... አልፎ አስመራ ሄደና አዲስ አበባ ተመለሰ። እሱ ካለፈ በኋላ ግን በትግራይ አማፅያን መንገዱ ሁሉ ተዘጋ፤ ጦርነትም ታወጀ ...

ሜጀር ጄኔራል አበበ ዳምጠው የትግራይ ጦር አዛዥ ሆነው ተሾሙና ከኮረም ወደ ማይጨው ተንቀሳቀሱ። ማይጨው ከመድረሳቸው በፊት የጃን እንዳለፋ ወረባዩ ላይ ሲደርሱ ውጊያ ተከፈተባቸው። ያንን ውጊያ እየተከላከሉ ማይጨው ወረባዩ ገቡ። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው እንግሊዛዊው ብርጋዴር ጄኔራል ኮቶምም በትዕዛዝ ማይጨው ገባ።

ሜጀር ጄኔራል አበበ ዳምጠውና ጄኔራል ኮቶም ማይጨው አድረው በነጋታው ልዑል አልጋ ወራሹ ትተውት የሄዱትን ሁለት ሻለቃ (የሻለቃ አሉላንና የደጃዝማች ተሰማ ቡርጂን) ጦር ይዘው ወደ አምባላጌ ጉዞ ጀመሩ። አምባላጌን አልፈው «ምቅማጥወር» ሲደርሱ ግን በትግራይ አማፅያን ጦር ተከበቡ። የነበረውን ከበባ ጥሶ ወደፊት መጓዝ ጭራሽ የማይቻል ስለነበር ወደኋላ በመመለስ አምባላጌ አፋፍ ላይ ሰፍረው አጋዥ ኃይል እንዲላክላቸው የጦር ሚኒስትር የነበሩትን ራስ አበበ አረጋይን ጠየቁ።

ኮረም የነበሩት የጦር ሚኒስትር፥ ደጃዝማች (በኋላ ቢትወደድ) ታፈረን ስድስት መቶ ወታደሮች ይዘው ወደ ማይጨው እንዲጓዙ አዘዙ። ደጃዝማች ታፈረ ማይጨው ገብተው ወታደሮቹ ከተሳፈሩበት መኪና እንደወረዱ ሻለቃ ጃገማ የእሱንና የደጃዝማች ከፈለውን ሻለቃ ጦሮች አሳፈረና ለጦር ሚኒስትሩ ስልክ ለመደወል ገባ። ሻለቃ ጃገማ የእሱ ብርጌድ አዛዥ የነበሩት ደጃዝማች በቀለ ወያ የሐረር አውራጃ እንደራሴ ሆነው ስለተዛወሩ ማይጨው ሲገባ የብርጌድ አዛዥ አልነበረውም። ማይጨው እንደደረሰ ግን የሶስተኛው ብርጌድ አዛዥ ደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህ አዛዡ ሆኑ። በዚያ አጋጣሚ ግን ሻለቃ ጃገማ ከብርጌድ አዛዡ ጋር ሳይሆን ከጦር

ሚኒስትሩ ጋር ቀጥታ ግኑኝነት ለማድረግ ስልኩን ደውሎ መልስ ተጠባበቀ:: ራስ አበበ ቀረቡ::

«ጌታዬ! እኔ ከሰኔ ወር ጀምሮ እዚህ ነበርሁኝ:: ጓደኞቼ አምባላጌ ሄደው ጦርነት ላይ ናቸው:: እኔ ግን እዚህ በመቅረቴ በጣም አዝኛለሁ:: ስለዚህ እባክዎ ከደጃዝማች ታፈረ መኪና ወስጄ እንድዘምት ይፍቀዱልኝ» አላቸው::

«ማይጨው እኮ ትልቅ ኃላፊነት የሚፈልግ ስለሆነ ነው አንተ እንድትጠብቅ የተደረገው» አሉ ራስ አበበ::

«ጌታዬ! እርስዎ እኔን ጥሩ ልሁን መጥፎ የት ያውቁኛል? እኔ ከእርስዎ ጋር በአርበኝነት ዘመን አብሬ አልነበርሁ:: ከእርስዎ ጋር የነበሩት ደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህ ናቸው:: እሳቸው ማይጨውን ይጠብቁ፤ እኔ ግን ወደ አምባላጌ ልዝመት:: ካልፈቀዱልኝ ግን ጠፍቼ እሄዳለሁ:: ከዚያ ያለ ትዕዛዝ ጦርነት ሄደ ተብዬ ፍርድ እገባለሁ» አሉ፥ ወጣቱ የጦር መኮንን ሻለቃ ጃገማ::

«ደግ ነው! መኪናውን ከደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህ ወስደህ ወታደሮችን አሳፍር» አሉና ፈቀዱለት፥ ራስ አበበ - ምሬቱንና ልጅነቱን እያሰቡ::

ሻለቃ ጃገማ ደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህን በመልእክተኛ አስጠሩቸው:: ደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህ የተሳፈሩትን ወታደሮች ሲያዩ ተቆጥተው ማንም እንዳይንቀሳቀስ ዘብ አቁመው ለጦር ሚኒስትሩ ሲደውሉ ገቡ::

«ጌታዬ ነህ! ደሞ ብለህ ብለህ ውስጥ እየገባህ ታዝ ጀመር?» አሉ ደጃዝማች ደስታ ሽዋርካብህ::

«እዎ! 'ጓደኞቼ ሄደው እኔ በመቅረቴ አዝኛለሁ' ስላለ ፈቅጀለታለሁ» አሉ፥ ራስ አበበ::

ከዚህ በኋላ ሰኞ መስከረም 2 ቀን 1936 ዓ.ም. ሻለቃ ጃገማ የደጃዝማች ከፈለውን ጦር ጨምሮ ወደ አምባላጌ ሄዶ ለሜጀር ጄኔራል አበበ ሪፖርት አደረገ:: ከቀርስ በኋላ ወጣቱ መኮንን ሻለቃ ጃገማ በጃናሞራ





አቅጣጫ ተመደበ:: ውጊያው ጠንካራና አስቸጋሪ ነበር:: በዚያ በየአቅጣጫው በተከፈተው ጠንካራ ውጊያ ምክንያት ጄኔራል ኢሳያስም ተማርከዋል::

አምባላጌ ላይ ደግሞ እነ ሻለቃ ጃገማ ለአስራ ዘጠኝ ቀናት ተከበቡ:: በለመደው ተራራና ሸንተረር ውጊያውን ያፋፍም የነበረው የወያኔ ጦር የመንግስትን ጦር ሃይል ባስጨነቀበት በዚያ ወቅት የገበሬን የውጊያ ስልት ከልምድ የሚያውቀው ሻለቃ ጃገማ የሚመራውን ጦር ይዞ የአምባላጌን ተራራ እየቧጠጠ ወጥቶ፣ የከበባውን መስመር ከጎን ቆርጦ፣ በገበሬዎቹ መንደር አቅጣጫ ከኋላ ውጊያውን ሲያጠናክር የመንግስት ጦር ከኋላው እንደመጣበት ያየው የወያኔ ጦር መበተን ጀመረ:: በሃያ ቀናቸው ከአማፅያኑ መሪዎች አንዱ ብላታ ሃይለማርያም የራስ ጉግሳን ልጅ ይዘው ከመንግስት ጦር ጋር አምባላጌ ላይ ተዋግተው ተሸነፉ:: እነሱ ድል ከሆኑ በኋላ የአምባላጌው ጦርነትና ከበባም አበቃ::

ሻለቃ ጃገማ፣ ደጃዝማች ከፈለው፣ ሻለቃ አሉላ በጄኔራል አበበ ዳምጠው ትዕዛዝ አምባላጌን ለቀው አካባቢውን በጥንቃቄ እያሰሱ ጉዞ ጀመሩ:: በጉዞው ወቅት ግን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የገበሬው ቤት ሲቃጠልና ሲዘረፍ ሻለቃ ጃገማ፣ ደጃዝማች ከፈለው ... ተቆጡ፤ አዘኑ::

ጃገማ ገጠር ተወልዶ፣ ገጠር ያደገ ነው:: ለስድስት ወር በዘመናዊ ውትድርና ሰልጥኖ «ግዳጅህን ተወጣ» የሚለውን ወታደራዊ ግዳጅ ተግባራዊ ያድርግ እንጂ የገበሬዎች አመፅ መነሻው ምን እንደሆነ፣ ከመንግስትስ ጋር ለምን እንደሚዋጉ አያውቅም:: እሱ አርበኛ ሳለ ጣሊያኖች «ሽፍታ» እንደሚሉት መንግስትም የትግራይ አማፅያንን ሽፍታ ነው የሚላቸው:: የትግራይ አማፅያን ጦር ከሸሸ በኋላ ግን ቤታቸው መቃጠሉ፣ ንብረታቸው መዘረፉ የሚሰጠው ፋይዳ በጭራሽ ሊገባው አልቻለም:: ያ ቅሬታና ተቃውሞ የሻለቃ ጃገማ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሻለቃ አዛዦችም ስለነበር ስብሰባ አድርገው አምባላጌ ለሚገኙት የጦር ሚኒስትሩ «የአገሬው ህዝብ ከብት እየተዘረፈ፣ ቤቱም እየተቃጠለ ነው:: ይህ ደግሞ ህዝቡን እንደገና በርሃ እንዲገባ ከማድረግ ውጭ ሌላ ፋይዳ የሌለው ነውና ድርጊቱ እንዲቆም ለጄኔራል አበበ ጥብቅ ትዕዛዝ ይስጡልን» የሚል ደብዳቤ ለራስ አበበ አረጋይ ጽፈው በሙቶ አለቃ ማሩ ጋተው እጅ ላኩት::

ራስ አበበ የእነ ሻለቃ ጃገማ መልዕክት በሙቶ አለቃ ማሩ ጋተው እጅ ሲደርሳቸው «የገበሬው ንብረት እንዳይዘረፍ፤ ከብቱ እንዳይነዳ፤ ቤት ቃጠሎውም በአስቸኳይ እንዲቆም፤ እስከአሁን የተዘረፈው ንብረትና የተነዳው

ክብትም ለህዝቡ እንዲመለስ አዝዣለሁ» በማለት መልዕክታቸውን ረዳታቸው በነበሩት ፊታውራሪ ሳህሉ እጅ ላኩ።

ጀኔራል አበበም የጦር ሚኒስትሩ ትዕዛዝ ጠንካራና ምንም የማያወላዳ መሆኑን ከደብዳቤው ተጨማሪ በረዳታቸው መምጣት በማረጋገጣቸው ትዕዛዙ ተፈፃሚ ሆኖ የተወሰደው ንብረት፣ የተነዳው ከብትም ተመለሰ። ተጨማሪ ዝርፊያም ቆመ። ግፍና ጭቆና የማይወደው ጃገማና ሌሎች የሻለቃ አዛዦች ባደረጉት ተቃውሞ የተፈፀመው ስህተት ተስተካከለ። ከዚያ በኋላ የመንግስት ጦር ምንም ውጊያ ሳያጋጥመው መቀሌ ገባ።

መቀሌ እንደደረሱ «ከወሎ የመጡትን ነጭ ለባሾችና አንድ ብርጌድ ጦር ይዘው ወደ ራያና አዘቦ በመሄድ እንዲያቀኑ» የሚል አዲስና አስቸኳይ ትዕዛዝ የጦር አዛዥ ለነበሩት ለሜጀር ጀኔራል አበበ ዳምጠው ደረሳቸው። ሜጀር ጀኔራል አበበ በአምባላጌው ጦርነት ማን ጠንክሮ እንደተዋጋ፣ ማን ከጉድ አውጥቶ ለድል እንዳበቃቸው፣ ማን በረቂቅ ወታደራዊ ስልት የወያኔን ጦር መስመር እንደሰበረና ማን ደግሞ በዚያች በጭንቅ ወቅት የሚይዘው የሚጨብጠው እንደጠፋው፣ የእነ ማን ሻለቃ ሽሽት እንደጀመረና የትኛው አዛዥ ተስፋ ቆርጦ ለሽሽት ሲነሳ እንደነበር ስለሚያውቁ አንድ ጥያቄ ለጦር ሚኒስትሩ አቀረቡ።

«ወደ ራያና አዘቦ ሄጄ እንዳቀና ከፈለጋችሁ ሻለቃ ጃገማ አብሮኝ እንዲሄድ ፍቀዱልኝ» አሉ፥ ጀኔራል አበበ።

«የታዘዝኸው የነጭ ለባሽ ጦርና አንድ ብርጌድ ጦር ይዘህ እንድትሄድ ነው። የብርጌድ አዛዦች ደግሞ ጀኔራል ኢሳያስ፣ ጀኔራል ተድላና ደጃዝማች ደስታ ናቸው። ሻለቃ ጃገማ የሻለቃ አዛዥ እንጂ የብርጌድ አዛዥ አይደለም። ስለዚህ በታዘዝከው መሰረት ከእነሱ ውስጥ ይዘህ ወደ ግዳጅህ ተሰማራ» አሉ፥ የጦር ሚኒስትሩ ራስ አበበ።

«ግዳጄን የምፈጽመው ተልዕኮዬን በድል ለመወጣት አይደለም? ሁሉንም በአምባላጌ ጦርነት አይቻቸዋለሁ። ለእኔ ግዳጅ ታዛዥ የሚሆነኝና ውጤታማ የሚያደርገኝ አንድ ሰው ነው - ሻለቃ ጃገማ። እሱን ይዤ ግዳጄን እንድፈጽም ይፈቀድልኝ» አሉ፥ ጀኔራል አበበ በድጋሚ።

«ሻለቃ ጃገማ የሻለቃ አዛዥ እንጂ የብርጌድ አዛዥ እኮ አይደለም፥ ጀነራል አበበ!» አሉ፥ ራስ አበበ።





«ይሹሙታ!» አሉ፥ ጀኔራል አበበ።

ትግራይንና ጎንደርን የሚያስተዳድሩትና የጦር ሚኒስትር የነበሩት ራስ አበበ አረጋይ ትንሽ አሰቡና «እንደምታውቀው የብርጌድ አዛዥ የሚሾሙት ግርማዊነታቸው ናቸው። ለስራው አስፈላጊ ከሆነ ግን ጥብቅ የብርጌድ አዛዥነት እንሹመዋ» አሉ፥ ራስ አበበ - ምክርም መጠየቅም በሚመስል አባባል።

«ይሹሙት!» አሉ፥ ጀኔራሉ።

ሻለቃ ጃገማ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ «ጂማ ያለውን የኢጣሊያ ጦር ለመደምሰስ ጃገማ ይሰጠኝ» ተብሎ እንደተመረጠው ሁሉ መቀሌ ላይ በጀኔራል አበበ ዳምጠው ተደግሞ ተመረጠና የሁለተኛ ብርጌድ ጥብቅ አዛዥ ተብሎ በመሾም በነበረው አንድ የሻለቃ ጦር ላይ ሁለት ሻለቃ ጦር ተጨምሮለት ወደ ራያና አዘቦ ግዳጁን ለመወጣት ከጀኔራል አበበ ጋር ዘመተ።

የራያና አዘቦ ችግር በሶስት ወር ውስጥ ወደነበረበት ተመልሶ ፀጥታው ተከበረ። እውቁ ሳይንቲስት አንስታይን «ትልቁ ቁም ነገር እውቀት ሳይሆን ምናብና ተሰጥኦ ነው» እንዳለው እውቀቱን ብቻ ሳይሆን ምናብና ተሰጥኦውን የሚጠቀመው ጃገማ ወደ ጦር ሳንቃ ተወርውሮ «አስቀለት» ሲባል የተሰማራበትን ግዳጅ በድል እየፈፀመ፣ እንደ እናንያና አዛሪያ ወደ እሳቱ ሲወረወር እሳቱ ሳይነካው ለፈጣን ሹመትና ለተጨማሪ ሃላፊነት በቃ።

የመንግስት ጦር አዛዡ ሜጀር ጀኔራል አበበ ማይጨው ላይ ለነጭ ለባሽ ጦር አለቆች፣ ለብርጌድ አዛዡና ለረዳቶቹ የምሳ ግብዣ አድርገው ነበር። በዚያ ጊዜ ለወሎ ነጭ ለባሽ አለቃ ለእነ ደጃዝማች መንገሻ አቦዬ «... እኔ» አሉ፥ ጀኔራል አበበ፤ «እኔ ለስማንያ ሁለት ጊዜ በኡጋዴን ጦር ግንባርና በሌሎችም ጦር ሜዳዎች ተዋግቻለሁ፤ ከሌሎች አዋጊዎችም ጎን ተሰልፌ አይቻለሁ። ነገር ግን እንደ ሻለቃ ጃገማ በተሰለፈበት የጦር ቀጠና የማሸነፍ ዕድል ያለው አዋጊ አጋጥሞኝ አያውቅም»። በራያና አዘቦ ዘመቻ ወቅት በነበረው ሰላማዊ ጥረትና ስነ-ስርዓት የተደሰቱት ወላጆች ለፍቅርና አክብሮታቸው ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ለወለዷቸው ሰባና ሰማንያ የሚደርሱ ህፃናት ጃገማና አበበ እያሉ ስም አወጡላቸው።

በራያና አዘቦ ዘመቻ አክብሮትን ያገኘውና በአለቃው የተወደሰው ጀግናው ጃገማ የራያና አዘቦው ግዳጅ ካበቃ በኋላ ግን ተከሰሰ። ከራስ አበበ አረጋይ ጋር በአርበኝነት የቆዩትና በጦር ሃይሉም ስልጣን የነበራቸው ደጃዝማች ተሰማ ቡርጂ «ካለህ አገልግሎት አንፃር የብርጌድ አዛዥነት አይገባህም። የብርጌድ አዛዥነት ሹመት መስጠት ያለባቸውም ንጉሰ ነገስቱ ናቸው፤ ስለዚህ መልስህን አቅርብ» ብለው የጦር ሚኒስትሩ ራስ አበበ ፊት አቀረቡት።

«ጥብቅ የብርጌድ አዛዥ አድርገው የሾሙኝ ጦር ሜዳ ውስጥ ራሳቸው የጦር ሚኒስትሩ ራስ አበበ ናቸው፤ ይጠቅማል፣ ይሰራል ብለው። ስለዚህ ለመሾሜ መልስ መስጠት ያለበት የሾመኝ እንጂ እኔ ተሿሚው አይደለሁም» አሉ፥ ሻለቃ ጃገማ - በተከሰሰበት ጉዳይ አዝኖ። ደጃዝማች ተሰማ ቡርጂ በጃገማ መልስ ተናደው የራስ አበበን ዐይን ተመለከቱ። ራስ አበበም «እህ! እውነቱን እኮ ነው፤ የሾመው ሌላ፤ ለምን ይጠየቃል? መጠየቅ አልነበረበትም። ከተከሰሰም፣ ከተወቀሰም ተከሣሹና ተወቃሹ ሹመት የሰጠሁት እኔ ነኝ። ስለዚህ ሻለቃ ጃገማ መከሰሱም፣ 'መልስ አቅርብ' መባሉም ስህተት ነው» አሉ፥ በጀግንነት፣ ትክክለኛ ፍትህ በመስጠት የሚወደዱትና በሚሰጡትም ውሳኔ እጅግ የሚፈሩት ራስ አበበ።

ከኢጣሊያ ወረራ በፊት አበበ አረጋይ አራዳን በሻለቅነት የሚያስተዳድሩ ፖሊስ ነበሩ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጋር ማይጨው ዘመቱ። መስፍን ስለሺ፣ መርዕድ መንገሻና አቢይ አበበ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ሁለት ዓመት በአርበኝነት ከተዋጉ በኋላ ስደት ሊሄዱ ሲሉ ራስ አበበንም አብረዋቸው እንዲሰደዱ ጠየቋቸው። ራስ አበበ ግን «አገሬንና ህዝቤን ትቼ የትም አልሄድም ...» ብለው ቀሩ።

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን የእንግሊዝ ጦር ደብረ ማርቆስ ባገተበት ወቅት «ጃንሆይ! ሃይላችንን ለማጠንከር ወደ አርበኝነት ከገባው ጋር ሁሉ ተባብሬ ስዋጋ የልጅ ኢያሱ ልጅ የራስነት ማዕረግ ሰጥቶኛል፤ እርስዎም እንግሊዝ አገር እያሉ ራስነቴን ተቀብለው ጽፈውልኛል። ይህን ማዕረግ መቀበሌ ግርማዊነትዎን ከመቃወም ሊቆጠርብኝ አይገባም። ስለዚህ ይህን ሹመቴን በጽሑፍ ያፀኑልኝ ዘንድ በደጃዝማች ደበበ በኩል መልዕክቴን ልኬያለሁ ...» የሚል ደብዳቤ ፃፉ። ለራስ አበበ ንጉሰ ነገስቱ ስልጣናቸውን አፀደቁላቸው። በኋላም ኢትዮጵያ ባቋቋመችው ህዝባዊ ጦር የሚኒስትርነት ማዕረግ ተሰጣቸው። ለሃገራቸውና ለመንግስታቸው ታላቅ ተግባር ፈፅመው በሃምሳ ሶስቱ የመንግስት ግልበጣ ወቅት ተረሸኑ።

* * *





በ1935 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ተጀምሮ በ1936 ዓ.ም ለከሸፈው የትግራይ አመፅ መፍትሄው ህዝቡን መውጋት ሆነ። መሪ የነበሩትን ከማሰርና ከማፈናቀል፣ ወታደራዊ አገዛዝ እንዲሰፍን ከማድረግ ውጭ የችግሩን መነሻ ነቅሶ አውጥቶ መፍትሄ መስጠት ስላልተቻለ እሳቱ ከመጥፋት ይልቅ ተዳፍኖ ሲስፋፋ ኖረ ...

ሻለቃ ጃገማ የትግራይ ችግር ጋብ ሲል በፈቃድ ወደ አዲስ አበባ መጣ። የሁለተኛ ብርጌድ አዛዥ የነበሩት ደጃዝማች በቀለ ወያ የድሬዳዋ አውራጃ ገዥ ሆነው ተሹመው ሄዱ። በምትካቸው የሁለተኛ ብርጌድ ጥብቅ አዛዡ ሻለቃ ጃገማ መሆን ሲገባው ቦታው ለሻለቃ ወርቁ አየለ ተሰጠ። ሻለቃ ጃገማ «እኔ በጦር ሜዳ ጥብቅ የብርጌድ አዛዥ ሆኜ ግዳጄን ተወጥቻለሁ። የሁለተኛ ብርጌድ አዛዥ መሆን ይገባኝ የነበረው ጥብቅ የብርጌድ አዛዡ እኔ ነኝ። አሁን ግን የሁለተኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ የተሾመው ሌላ ሰው ነው፤ ለምን እንዲህ ተደረገ?» ብሎ ጄኔራል አቢይን ጠየቀ።

ጄኔራል አቢይም «አንተ የያዝከው የብርጌድ ጥብቅ አዛዥነት ከጦር ሚኒስትሩ እንጂ ከንጉሰ ነገስቱ የተሰጠህ ሹመት አይደለምና ደንቡ አይደግፍህም። ስለዚህ ስልጣንህን ለቀህ በሻለቃ ወርቁ ስር ሆነህ መታዘዝ አለብህ» አሉት። ሻለቃ ጃገማ በጦር እሳት ተፈትኖ ያገኘውን እድገት ሲነጠቅ አዝኖ «ጄኔራል አቢይ! እኔ ሶስት ሺህ ጦሬን በትኜ በወታደርነት የተቀጠርሁት ተገድጄ ነው። ምስጢራችሁ ይህ ከሆነና ብይናችሁ የማያሰራኝ ከሆነ ግን አሰናብተኝ» አለ። ጄኔራል አቢይ «ከሰራዊት አላባርርህም፤ ጃንሆይ ፊትም አላቀርብህም። ነገር ግን ራስ አበበ እስኪመጡ ተጠባባቂ ሆነህ ተቀመጥ» አሉት። ወጥቶ ሄዶ መኖሪያ ቤቱ ገብቶ ተቀመጠ።

በዚህ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ እያለ ግን ያልታሰበ ሲሳይ «ከሰማይ» ወረደለት። ወደ ማይጨው ከመሄዱ በፊት ለመሸጥ ያስፈቀደው ደን በወኪሉ አማካይነት ስለተሸጠ አስራ አምስት ሺህ ብር አምጥተው ሰጡት። የተቆረጠው ደንም በመደበለት ጠባቂ እንክብካቤ ስላገኘ ተመልሶ እያቆጠቆጠ መሆኑን አረጋገጠ። ሌሎች ትክሉ የተባሉትን ሳይተክሉ ቀርተው ግዴታቸውን ሳይፈጽሙ እሱ ግን ጥቅም ብቻ ሳይሆን ግዴታውንም በመወጣቱ ይበልጥ ደስ አለው። ጃገማ «ሳይደግስ አይጣላ» ብሎ ብስጭቱን ረስቶ ራስ አበበ አረጋይ መጥተው የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጡት ድረስ እንደ እሱ በተለያየ ሰበብ ከስራ ከታገዱት የሰራዊቱ አባሎች ጋር በአራዳ ላይ መሸለል ጀመረ።

ሻለቃ ጃገማ በየቀኑ ከቤቱ ሲወጣ አምስት መቶ ብር ይዞ እየወጣ አራዳ ከሚገኙት የሃኪም ወርቅነህና ዘውዴ ኪዳነ ወልድ ክለብ የምሽት ክበብ፤ ከሲኒማ ኢትዮጵያ ጎን ከነበረው ተራራ ሆቴልና ምሽት ክበብ ... ውስጥ በፈረቃ መዝናናትና መደነስ ጀመረ። ጠርሙስ ውስኪ ከቀረጥ ነፃ አምስት ብር፣ ቀረጥ የተከፈለበት አስራ ሁለት ብር እያወረደ፤ በአራዳ ልጅ ዜማ እየተንሳፈፈ በረረ ...

«ወይ አዲስ አበባ ... እኸ! .. ወይ አራዳ ሆይ ... እኸ ... አገርም እንደሰው... እኸ... ይናፍቃል ወይ!» እያሉ ጃገማ፣ አማን፣ ምህረተአብ ... ዜማ እየተቀበሉ፣ ዜማ እያንቆረቆሩ ... ተዝናኑ።

አራዳ ጀግኖቿን ስታገኝ እንደ አንጡግ ፅጌረዳ ሙልሙል ብላ ፈካች። ፀሐይ፥ ብርሃን ለመጨመር ዝቅ ብላ ተንጠለጠለች። ጨረቃ እንደ ማንን ዛፍ የምትነካ ውብ ፍሬ መሰለች ...

«ወይ ውቤ በርሃ ... እኸ ... ወይ አራዳ ሆይ!» እየተባለ ምድር ቀውጢ ሆነች። የአራዳ ፍቅረኛ እየተንቀረቀበ እየተጣራ ተመራጩ ወደ ውስጥ ሲገባ አራዳነት የጎደለው ደግሞ ወደ ዳር እየተገፋ ተመልካች ሆነ። በአራዳ ልጆች ፍቅር ቆነጃጅት ቀልባቸው እየተሰረቀ ማለሉ። የአራዳ ቅኝት፣ የውቤ በርሃ ዜማ በጀግኖች እየተቀነባበረ ጣፈጠ። ጨዋታው ደራ። ፍቅር በጋለው የአራዳ ልጆች ልብ ላይ እንደ ነጭ እጣን እየተንቸሰቸሰ ጤሰ። የአራዳና የውቤ በርሃ መዓዛ የሚሰነፍጥ ሆነ። የውቤ በረሃ ጠጅ ቤቶችና መሸታ ቤቶች እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት፣ ቡና ቤቶችና ሲኒማ ቤቶች እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት እንዲዘጉ በአዋጅ ቢደነገግም በአራዳዎች ዘዴ፣ በአራዳዎች መላ በር እየተዘጋ፣ ልብ እየተከፈተ ዳንሱ ቀለጠ።

ከሰባት ወር «አቧራው ጤሰ» ጭፈራ በኋላ ራስ አበበ አረጋይ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ጄኔራል አቢይ ጃገማ የብርጌድ አዛዥ ሊሆን አለመቻሉን፣ ሰባት ወራት ተጠባባቂ ሆኖ ደመወዙ እየተከፈለው መቆየቱን አብራርተው ለጦር ሚኒስትሩ አስረዱ። ራስ አበበ የጃገማን የአርበኝነት ተጋድሎ፣ እምባሳጌ እና ራያና አዘቦ የፈፀመውን የጀግንነት ተግባር፣ በፊት በደጃዝማች ገረሱ፣ በኋላ ደግሞ በሜጀር ጄኔራል አበበ ዳምጠው መመረጡንና መወደሱን ያውቃሉ። «ጥብቅ አዛዥነቱ አይገባውም» ተብሎም እሳቸው ፊት ጉዳዩ ደርሶ በውሳኔ የዘጉት ራሳቸው የጦር ሚኒስትሩ ነበሩ።





በሌላ በኩል ደግሞ ልዑል አልጋ ወራሹ በወቅቱ የወሎ ጠቅላይ ግዛት ገዥ ስለነበሩ «ሻለቃ ጃገማ ጀግና መሆኑን ሰምቻለሁና የ6ኛ ብርጌድ አዛዥ አድርገው ይሹሙልኝ» ብለው ለራስ አበበ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ነግረዋቸው ስለነበር ራስ አበበ ለንጉሰ ነገስቱ ጉዳዩን አቅርበው ጄኔራል ከበደ ገብሬ ሻለቃ ጃገማን የ6ኛ ብርጌድ አዛዥ አድርገው እንዲሾሙት አዘዙ። ጄኔራል ከበደ ገብሬ ግን «ይህማ ሊሆን አይችልም፤ ክቡር ሚኒስትር ... ጃገማ የስድስተኛ ብርጌድ አዛዥ መሆን አይችልም፤ እሱ ሻለቃ ነው። ከእሱ በላይ የኮሎኔልነት ማዕረግ ያለው ኮሎኔል ግብሩ የሚባል ስደተኛ መኮንን አለ፤ እሱ ነው የብርጌድ አዛዥ ሊሆን የሚገባው» ብለው ተከራከሩ።

ራስ አበበ ጄኔራሉን ሃሳባቸውን እስኪጨርሱ ጠበቋቸውና «ጨረስህ ጄኔራል?» አሉ። «አዎ ጌታዬ!» አሉ ጄኔራል ከበደ። «ከበደ! አሁን አዛዥነቱ የኔ ነው። እኛ በስራ የምናውቀው ያልኸውን ኮሎኔል ሳይሆን ሻለቃ ጃገማን ነው፤ የ6ኛ ብርጌድ አዛዥነቱ የሚገባው እንደ ወርቅ በእሳት ለተፈተነው ለእሱ ነው» ብለው ወስነው ተነሱ። ሻለቃ ጃገማ የ6ኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ደሴ ሲሄድ ሻለቃ ከበደ በውሳኔው ተበሳጩ።

በዓመቱ ህዝባዊ ጦር፣ የኢትዮጵያ ጦር እና መደበኛ ጦር ሲቀላቀሉ ሻለቃ ከበደ ገብሬ ሻለቃ ጃገማን የብርጌድ አዛዥ ሳይሆን የሻለቃ አዛዥ አድርገው ስላስተላለፉት ሻለቃ ጃገማ በእንግሊዞች እንደገና የሻለቃ አዛዥ ሆኖ ተደለደለ። «ክብሬንና መብቴን ማስጠበቅ ያለብኝ እኔ እንጂ ሌላ አይደለም» የሚለው ጃገማ ፈቃድ ወስዶ አዲስ አበባ ተመለሰ።

«ጄኔራል ከበደ! እኔ የብርጌድ አዛዥ እንደሆንሁ ታውቃለህ። ለእንግሊዞች ስታስተላልፍ ግን በብርጌድ አዛዥነቴ ሳይሆን በሻለቃ አዛዥነቴ ነው። ስለዚህ እንግሊዞች የሻለቃ አዛዥ አደረጉኝ። ለምን ይሆን ብርጌድ አዛዥነቴን ያላስተላለፍኸው?» ብሎ ጠየቀ፥ ሻለቃ ጃገማ።

«እኔ የሚገባኝን ሰርቼ ጉዳዩን አስተላልፌያለሁ። አሁን ጊዜዬን አታባክንብኝ፤ ጉዳይህ ለጄኔራል ኮቶም ተላልፏል። ስለዚህ እዚያ ሂድና ኮቶም ጋር ተነጋግረህ ጨርስ። እኔም ስራዬን ልስራ» አሉ፥ ጄኔራል ከበደ። የያዘውን የማይለቀው ጃገማ «ተስፋ የምቆርጥ መስሎሃል» ብሎ በቀጥታ ሄዶ የጄኔራል ኮቶምን ቢሮ አንኳኳ።

«እምባላጌ ላይ መላ በጠፋበት፣ ጀግና በሚፈለግበት ጊዜ ግዳጄን ከፈፀምኩ በኋላ ደግሞ ወደ ራያና አዘቦ እንድዘምት በጄኔራል አበበ ተመርጬ ጥብቅ የብርጌድ አዛዥ ሆኜ ተሹሜያለሁ። ከመሾምም አልፌ በቦታው ላይ

ሰርቻለሁ:: ቅልቅሉ ሲፈፀምም እኔ የብርጌድ ጥብቅ አዛዥ ነበርሁ ...» አለና ሻለቃ ጃገማ ትንሽ አሰበ:: ከጄኔራል ከበደ ገብሬ ጋር ያደረገውን የቃል ልውውጥ ካነሳ ጄኔራል ኮቶም ከጄኔራል ከበደ ጋር እመካከራለሁ ይለዋል፤ ከጄኔራል ከበደ ጋር ከተነጋገረ ደግሞ ችግሩ ስር ይሰዳል:: ስለዚህ ጃገማ የጄኔራል ከበደን አለመደሰት ሳያነሳ «... እናንተ እንግሊዞች ግን ብርጌድ አዛዥ የሆንሁትን ሻለቃ አዛዥ አድርጋችሁ መደባችሁኝ:: አንተ ራስህ እንደምታስታውሰው ሌላው ቀርቶ ያገኘሁትን ሁለት ሳጥን ቦንብ አንዱን ለአንተ አንዱን ለጄኔራል አበበ ዳምጠው ሰጥቻለሁ» አለው፥ ሻለቃ ጃገማ::

ጄኔራል ኮቶም የሻለቃ ጃገማን ሃሳብ አዳመጠ:: ጃገማም በተናገረው የተሰማውን አስተዋለ:: ሁለቱም አንዱ የአንዱን ስሜት ለማንበብ ሲፎካከሩ ቆዩና «ጥሩ፤ ለኞ ተመልሰህ ና» አለ ጄኔራል ኮቶም::

ባጋጣሚ ሻለቃ ጃገማ ለሦስት ወራት ያህል አብሮት በሻለቃ አዛዥነት የሰራ የእንግሊዝ ከፍተኛ መኮንን «የብርጌድ አዛዥ ሊሆን ይገባል» ብሎ ደብዳቤ ጽፎ ኖሯል:: ያ ደብዳቤ ቅዳሜ ደረሰ:: ጄኔራል ኮቶም ደብዳቤውን አይቶ ጃገማን ሲጠብቅ መጣ:: ደብዳቤው መምጣቱን ሳይገልጽ «ሻለቃ ጃገማ በል የብርጌድ አዛዥነቱን ሰጥቼሃለሁ:: ከእንግሊዞች ጋር እየተስማማህ ስራ» አለው:: በዚህ ውሳኔ ሻለቃ ጃገማ በደስታ ሲቦርቅ ጄኔራል ከበደ ገብሬ እንደገና ተቆጡና አለመግባባታቸው እስከ መንግስቱ ንዋይ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ድረስ ዘለቀ::

* * *

ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ ሻለቃ ጃገማ ደሴ የሚገኘው የስድስተኛው ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ቆየ:: በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር፣ ህዝባዊ ጦርና መደበኛ ጦር በጦር ሚኒስቴር ስር አንድ ሆነው ሲቀላቀሉ ጃገማ የብርጌድ አዛዥነቱን ለማግኘት ውጣ ውረዱን ካለፈ በኋላ የአምስተኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ተሾመ::

የኢትዮጵያ ምድር ጦር በአራት ክፍለ ጦር ከተመደበ በኋላ የሁለተኛ ክፍለ ጦር ምድብ ደሴ ሆነ:: በዚያ ወቅት ሻለቃ ጃገማ የአምስተኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ደሴ ስለነበረ ለብርጌዱና ለክፍለ ጦሩ በወር የሚያስፈልገውን ደመወዝ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት ግምጃ ቤት ጠይቆ በማውጣት ደመወዝ እየከፈለ ግልባጩን ለጦር ሰራዊት ጠቅላይ መምሪያ እንዲያሳውቅ ታዘዘ:: ሻለቃ ጃገማ ትዕዛዙን ተግባራዊ በማድረግ ገንዘቡን ጠይቆ እያወጣ ለሰራተኞች ጉዳይ ኃላፊው በመስጠት እንዲከፈል ያደርጋል:: ከአምስት መቶ ብር በላይ





በሰራተኞች ጉዳይ ኃላፊው እጅ ስለማይቀመጥ ቀሪውን እየተቆጣጠረ ባንክ የማስገባት ግዴታ ነበረበት:: ቀሪው ገንዘብም እየተጠራቀመ አስር ሺህ ብር ደረሰ:: ሻለቃ ጃገማ ለሁለተኛ ክፍለ ጦር አባሎችና እሱ ለሚመራው ብርጌድ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት ገንዘብ ቤት በየወሩ የሚያወጣው ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር ነው::

ሻለቃ ጃገማ ተቀማጩ ገንዘብ አስር ሺህ ብር መድረሱን ሲረዳ ከገንዘብ ቤቱ ማውጣት የሚገባውን ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር ሳያወጣ በየዋህነት ሃያ ስድስት ሺ ብር አውጥቶ በባንክ የተጠራቀመውን አስር ሺህ ብር ከባንክ አውጥቶ በመሙላት በሰራተኛ ጉዳይ ኃላፊው አማካይነት የደመወዝ ክፍያ እንዲፈጸም አደረገ:: ይህን ክፍያ ሲፈጽም ግን እንደተለመደው ለጦር ሰራዊት ጠቅላይ መምሪያ የጦር ሰራዊት ገንዘብና መዝገብ ቤት ግልባጩን ላኪል::

ከዚያም በኋላ እንደተለመደው ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር እየጠየቀ በማውጣት ሲከፍል ቆየ:: ጠቅላይ መምሪያው ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚጠይቀው የሶስት ወር ደመወዝ ስለሆነ አንድ ጊዜ ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር ማውጣት ሲገባው ሃያ ስድስት ሺህ ብር ማውጣቱን የተረዳው የገንዘብ ሚኒስቴር የወሩን ደመወዝ ለዘለቄታው በሃያ ስድስት ሺህ ብር ይዞ የሶስት ወር ደመወዝ ለጠቅላይ መምሪያው ሰጥቶ ኖሯል:: በሶስተኛው ወር ሰላሳ ሺህ ብር ጎደለ:: ለካ ከየወሩ የወር ደመወዝ ክፍያ አስር አስር ሺህ ብር ለሶስት ወር ተነስቷል:: ለጎደለው ገንዘብ ደግሞ ቀጥታ ተጠያቂው ሻለቃ ጃገማ ሆነ፤ ሃሜት መራገብ ጀመረ::

ከዚያ የገንዘብ ሚኒስቴር ኦዲተር መጣ፤ ከጦር ሰራዊት ጠቅላይ መምሪያም ኮሎኔል ተክሌ ሄዱ:: ሻለቃ ጃገማ ያስተላለፋቸው ቴሌግራሞች፣ ግልባጭ የተደረገው የደመወዝ መክፈያ ሰነድ ተመረመረ:: በመጨረሻ ሻለቃ ጃገማ ነፃ ሆኖ ተገኘ::

* * *

ጃገማ ደሴ በነበረበት ጊዜ ከሮቢት ጀምሮ እስከ ኮምቦልቻ ድረስ ግራና ቀኙ ጥቅጥቅ ያለ ደን ነበር:: ስለዚህ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ የሚጓዝ ሁሉ ድኩላ፣ አሳማ፣ ቡሆር፣ ሚዳቋ፣ ጅግራ ... ሲሯሯጥ እያየ ነው:: ጃገማ ሁሌም መንገድ ሲጓዝ ሁለት ጠመንጃና ሽጉጥ አይለየውም:: አንድ ቀን ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ሲሄድ አንዲት ጥንቸል ከቀኝ ወደ ግራ አቋረጠችው::

ጃገማ መኪናውን አቁሞ በመውዜር ጠመንጃው አነጣጥሮ ሲተኩስ ወደ ላይ ጉና ወደቀች።

በሌላ ጊዜ በሌሊት በዚሁ መንገድ ጅፕ መኪናውን ሲነዳ የልጁ ሞግዚት ብቻ ከኋላው ተቀምጣለች። አንድ ድኩላ ከጫካው ተወርውሮ ወጥቶ እፊት እፊቱ መሮጥ ጀመረ። በቀኝ በኩል ጋራ ስለሆነና መንገዱ ዳር ያለው አለት ስለተጠረበ መውጣት አለመቻሉን ጃገማ ሲያስተውል ድኩላውን ወደ ግራው እንዳይታጠፍ እየዘጋ ወደ መንገዱ አስገባው። ጃገማ መውዜሩን አንስቶ የጅፑን በር ከፍቶ፣ በግራ እጁ መሪውን ይዞ፣ ነዳጅ መስጫውን ጫን አድርጎ ፊት ለፊት አልሞ ተኮሰ። ድኩላው ሁለት ጆሮው መካከል ማጅራቱ ላይ ተመቶ ወደቀ። «ጃጌ ጃገማ!» አለ፥ ጃገማ አባ ዳማ። ቆዳውና ስጋው ሳይበላሽ ድኩላውን ይዞ ደሴ ገባ።

አንድ ቀን ደግሞ በዚያው መንገድ ሲጓዝ ጅግራዎች መንገዱን አቋርጠው ወደ ቀኝ ታጥፈው ገቡ። ጃገማ መኪናውን ሲያቆም ጅግራዎች ጫካው ውስጥ ቆመዋል። ጃገማ አንዷ ጅግራ ላይ አልሞ ተኮሰና ሄዶ ሲያይ ሶስት ጅግራዎች አንገት አንገታቸውን ተመተው ወድቀው አገኛቸው።

* * *

በ1938 ዓ.ም. ጀኔራል ከበደ ገብሬ አንድ ደብዳቤ ፃፉ፤ «በአዲሱ ድልድል ምንም ችግር ቢፈጠር ለእኔ ፃፉልኝ፤ በተረፈ ግን ከእንግሊዞች ጋር ተግባብታችሁ ስሩ» ይላል የደብዳቤው መንፈስ። ከድልድሉ በኋላ እንግሊዞች በየክፍለ ጦሩ፣ በየብርጌዱ እየሄዱ ኃላፊነታቸውን ተረከቡ።

በዚያ ወቅት ልዑል አልጋ ወራሽ የጎንደር፣ የወሎና የትግራይ ገዥ ነበሩ። የኢጣሊያ ጦር ደግሞ ጎንደር ተሰባስቦ ቆይቶ ስለነበር በአልጋ ወራሹ አስተባባሪነት አዲስ የውጊያ ዘመቻ ተከፍቶ የተላከው ጦር አራት መቶ ሺህ የሚደርስ ጥይት ማረከና ጥይቱ ደሴ ተወሰደ።

«ያን ጥይት እንግሊዞች ከተረከቡ አንድ ወታደር በአመት ቢያንስ ሶስት መቶ ስልሳ አንድ ጥይት መተኮስ አለበት በሚለው ደንባቸው መሰረት በአጭር ጊዜ ተኩሰው ይጨርሱታል። ኢትዮጵያ ግን እንደዚያ የሚያወላዳ አቅም የሚፈጥር የጥይት ፋብሪካ ስለሌላት ቆጥባ መጠቀም አለባት። ስለዚህ ይህን ችግር 'ችግር ካለባችሁ ፃፉልን' ላሉት ጀኔራል ከበደ ብናስታውቅ ምን ይመስልሃል?» አለ፥ የሻለቃ ጃገማ ኤታማዦር ሹም ሻምበል ፅጌ በሻህ። «ጥሩ





ሃሳብ ነው፤ ይፃፍ» አለ፥ የአምስተኛ ብርጌድ አዛዡ ሻለቃ ጃገማ። ሻምበል ፅጌ በሻህ ማሳሰቢያውን ለማርቀቅና ለመፃፍ ወጣ።

በወቅቱ በነበረው የጦር ሚኒስቴር አሰራር ወታደራዊ ስልጠና ወስደው የጨረሱ አርበኞች የመቶ፣ የሻምበል፣ የሻለቃ፣ የብርጌድ አዛዥ ሆነው በኃላፊነት ሲሾሙ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት የሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ ምሩቅ የሆኑት ደግሞ ኤታማዦር ሹም ይሆናሉ። የአዛዦቹ ድርሻ ጦሩን መምራት፣ አስተዳደራዊ ፍትህ መስጠት፣ የሰራዊታቸውን አባላት የስራ ችሎታ ሪፖርት ማድረግ ነው። ኤታማዦሮች ደግሞ ንብረትን መጠበቅ፣ መሳሪያን ማደል፣ ገንዘብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን መፈፀም ተግባራቸው ነው።

ሻምበል ፅጌ ደብዳቤውን አዘጋጅቶ እንደጨረሰ ሻለቃ ጃገማን እንዲፈርም ጠየቀው። ሻለቃ ጃገማም «ስለ ገንዘብ፣ ንብረትና መሳሪያ ኃላፊነቱ የአንተ ስለሆነ ደንቡ እንደሚፈቅደውና ሁሌም እንደምታደርገው መፈረም ያለብህ አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም» አለ። ሻምበል ፅጌም አስተያየቱ ስላሳመነው ወረቀቱ ላይ ፈርሞ ለጀኔራል ከበደ ገብሬ አሽጎ ላከው።

ጀኔራል ከበደ ደግሞ ከሻምበል ፅጌ የደረሳቸውን ደብዳቤ «ይሄ ደብዳቤ ደርሶኛልና የምታደርገውን አድርግ» ብለው ለጀኔራል ኮቶም ሰጡት። ኮቶም ደብዳቤውን እንዳነበበ እልህ ውስጥ ስለገባ ጊዜ ሳያባክን አውሮፕላኑን እያበረረ ደሴ ሄደና «ፅጌ በሻህን ጥሩልኝ?» አለ። ሻምበል ፅጌ ተጠራ። «እቃህን በሙሉ ያዝ» አለው፥ ጀኔራል ኮቶም። ከዚያ ይዞት በሄደው አውሮፕላን አዲስ አበባ ይዞት ተመለሰና ካለምንም ውጣ ውረድ እንደግል አገልጋዩ ከሰራዊቱ አባረረው።

በዚህ ዓለም ላይ የሚኖር ሰው ሁሉ ሀሴትን የሚያገኘው ፍትህ ሲያገኝ ነውና ሻምበል ፅጌ «ሰው እንደ ዕፅዋት ጥቃትን በዝምታ ማለፍ የለበትም» በሚል እምነት ለንጉሰ ነገስቱ ችሎት ይግባኙን አቀረበ። ሻለቃ ጃገማ ሻምበል ፅጌን የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ፣ ልምድ ያለውና ጥንቁቅ ሆኖ ስላገኘው «ሻምበል ፅጌ በሻህ ታማኝ፣ ታታሪና ስራውን አክባሪ ነው...» ብሎ ቀደም ብሎ ጽፎለት ነበር። በአጋጣሚ ሻለቃ ጃገማ እረፍት ወስዶ አዲስ አበባ ነበር። ከዚያ እንደተለመደው ንጉሰ ነገስቱን እጅ ነስቶ ንጉሰ ነገስቱ ለችሎት ከቆሙበት በስተጀርባ ከልዑላንና ከመኳንንቱ ጋር ቆሟል። ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በስደት በነበሩበት ጊዜ «ለአገራችን ምድር ከተመለስን ለህዝባችን ፍትህ ለመስጠት በቀን ለአንድ ሰዓት ችሎት እንቆማለን» ብለው ተስለው

ስለነበር ከበዓላትና እረፍት ቀናት ውጭ ችሎት መቆማቸውን እያስተጓጉሉም::

ሻለቃ ጃገማ ከንጉሰ ነገስቱ ኋላ ቆሞ ችሎቱን ሲያዳምጥ የሻምበል ፅጌ ጉዳይ ቀረበ:: ንጉሰ ነገስቱ «ጉዳዩ ምንድን ነው?» ብለው ጠየቁ:: «... ደሴ የሚገኘውን አራት መቶ ሺህ ጥይት ... ለእንግሊዞች ብናስረክብ በደንባቸው መሰረት ተኩሰው ስለሚጨርሱት ... እኛ ደግሞ የጥይት ፋብሪካ ስለሌለን ምን እናድርግ?» የሚል ደብዳቤ ወደ ጄኔራል ከበደ ስለመፃፉ፤ ጄኔራል ከበደም ለጄኔራል ኮቶም ጉዳዩን በመምራታቸው ኮቶም ከሰራዊቱ ያባረረው ስለመሆኑ፣ ያን ውሳኔ ይግባኝ ብሎ ሻምበል ፅጌ በሻህ በይግባኝ ጉዳይ እዚህ የቀረበ ስለመሆኑ ተነገራቸው::

አንድ ጉዳይ ወደ ንጉሰ ነገስቱ ዙፋን ችሎት የሚቀርበው አመልካቹ ፍርዱ ሳይስማማው ሲቀር፣ አልተስማማኝም ሲል ደግሞ በቂ ምክንያትና መረጃ ማቅረብ የሚችልና የተፈረደበት ፍርድ ግልባጭ በእጁ ሲገኝ ስለሆነ የሻምበል ፅጌ በሻህ ጉዳይ በይግባኝ ለዙፋን ችሎቱ መቅረቡ ትክክል ነበር::

«ይህን ባለ ለምን ይባረራል? ለሀገር ማሰቡ ነውር ነው?» ጠየቁ፥ ንጉሰ ነገስቱ:: ሻምበል ፅጌ የንጉሰ ነገስቱን ድጋፍ ሲያገኝ «ጃንሆይ! ግፍ ነው የተፈፀመብኝ» አለና ሌላ ወረቀት አወጣ::

«ይህንንም ይመልከቱልኝ፥ ጃንሆይ!» አለ::

«ጥሩ፤ እስኪ ይነበብ» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ:: ሻምበል ፅጌ «ከብርጌዱ አዛዥ የተፃፈልኝ ነው» አለ:: ማስረጃው ተነበበ፤ «ሻምበል ፅጌ በሻህ ታታሪ፣ ታማኝ፣ ስራ ወዳድ ... ነው:: ፊርማ - ሻለቃ ጃገማ ኬሎ፤ ብርጌድ አዛዥ» ይላል፤ ንጉሰ ነገስቱ በፈጣን የማስታወስ ችሎታቸው ተጠቅመው ዞወር ብለው ጃገማን አዩት::

«ሰንበረቱ ተቆርቋሪ ነው ሻምበሉ ያን ደብዳቤ የፃፈው:: በስራው ደግሞ ታታሪ፣ ስራ ወዳድ ... መሆኑን አለቃው መስክሮለታል:: ጄኔራል ኮቶም ምን አልባት በንብረት ምን አገባውና ስልጣኑን አልፎ ደብዳቤ ፃፈ ብሎ ይሆናል የቀጣው:: እኛ ደግሞ መቆርቆሩን ነው የምናየው:: ስለዚህ ከሰራዊት የሚያባርር ጥፋት አላገኘንበትምና ወደ ስራው ይመለስ» በማለት አዘዙ:: ሻምበል ፅጌም ወደ ስራው ተመልሶ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ገብቶ እንዲሰራ ተደረገ::

* * *





አንድ ጊዜ ሻለቃ ጃገማ የመሬት ጥያቄ ጉዳይ ነበረውና ለንጉሰ ነገስቱ እንዲያቀርቡለት ከክብር ዘበኛ ተዛውረው የጦር ሰራዊት ኤታማዦር ሹም ለነበሩት ለጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ሰጠ:: ጄኔራል ሙሉጌታ፥ ያቀረበውን ማመልከቻ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ጨምረው ለንጉሰ ነገስቱ ሲያቀርቡ ሌላው ጉዳይ ይፈፀምና የሻለቃ ጃገማ ብቻ ይመለሳል:: ጄኔራል ሙሉጌታ ሶስት ጊዜ አቅርበው ሶስቴም ጉዳዩ ስላልተፈፀመ «ሻለቃ ጃገማ! ሶስት ጊዜ ጉዳይህን አቅርቤ ማስፈፀም አልቻልሁምና ራስህ ገብተህ አስፈጽም» አሉት:: ሻለቃ ጃገማ ለሌላው ባይፈቀድም ወደ ቤተ-መንግስት ገብቶ ጉዳዩን ለንጉሰ ነገስቱ አቀረበ:: ንጉሰ ነገስቱም ወዲያው ጉዳዩን ፈፀሙለት:: በዚያም ንጉሰ ነገስቱ በሚቀርቡት ሰው ጉዳይ ሌላ ሰው እንዲገባ እንደማይፈልጉ ተረዳ::

በ1947 ዓ.ም ሻለቃ ጃገማ የብርጌድ አዛዥ በነበረበት ጊዜ እሱ ሳይሾም የእሱ የበታቾች የሌፍተናንት ኮሎኔል ማዕረግ እየተሰጣቸው ተሾሙ:: ሻለቃ ጃገማ ሌላ ፈተና ተጋረጠበት:: ብዙ አወጣ፤ አወረደ:: በአገልግሎቱ የሚገባውን ማዕረግ ያላገኘበትን ምስጢር ግን ማወቅ ተሳነው:: «ለምን የሚገባኝን ይከለክሉኛል?» ብሎ ጃገማ እንደ ቀበሮ ራሱን ከፍ አድርጎ ፈጣሪውን ጠየቀ:: መብቱን ለማስከበር እንደገና መጣር አለበት ...

ስለዚህ ፈቃድ ተቀብሎ አዲስ አበባ መጣና በቀጥታ ንጉሰ ነገስቱ ፊት ቀረበ:: ጃገማን ከባህሩ ያወጡት ንጉሰ ነገስቱ ናቸው:: አሁን ግን ጀግናው ጃገማ እውነት በተቀበረችበት ዓለም ገብቶ ሞልቶ የተንቸረፈፈው በራስ መተማመኑ እንደ በረዶ እየሟሟበት ተቸገረ ... ይህን መሰል ችግር ሲፈጠር ወደ አዕምሮ ድቅን ከሚሉ ትውስታዎች ውስጥ አንዱ ታላቁ ደራሲ ሊዮ ቶልስቶይ የፃፈው አስደሳች ተረት መሰል ቁም ነገር ነው::

«በአንድ ደሴት ውስጥ ከሰው ተገልለውና ሃይማኖት አልባ ሆነው የሚኖሩ ሶስት ባህታውያን ነበሩ:: ይጠቀሙበት የነበረው ፀሎት ተራና እዚህ ግባ የማይባል ነበር:: «እኛ ሶስት ነን፤ ጥበብም ሶስት ናት፤ ምህረትህን በእኛ ላይ አስፍን» የሚል ብቻ ነበር፥ ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡት ፀሎት:: በዚህ ተራ ፀሎት ግን ብዙ ፀጋ ያገኙበት ነበር::

«ከደሴቷ ብዙም ሳይርቅ ደግሞ እጅግ የተከበሩ ጳጳስ ይኖራሉ:: እኒህ ጳጳስ ሶስቱ ሰዎች ከሰው ተነጥለው ስለመኖራቸው፣ ተገቢ ስላልሆነውና ምንም ሃይማኖታዊ መሰረት ስለሌለው ተራ ፀሎታቸው ሰሙና ሊያይዋቸውና እግረመንገዳቸውንም ትክክለኛውን ፀሎት ሊያስተምሯቸው ሄዱ ...

«ጳጳሱ ደሴቱን ለቀው ወደመጡበት ለመመለስ ጀልባቸው ላይ ወጡ፤ በጉዞ ላይ እያሉ ወደ እሳቸው ጀልባ ከኋላ እየተጠጋ የነበረ የብርሃን ሰረገላ ተመለከቱ:: የብርሃን ሰረገላው ሲጠጋ ጳጳሱ ዝቅ ብለው ሲመለከቱ በብርሃን ሰረገላው ውስጥ የነበሩት ሶስት ሰዎች ከነበሩበት ወጥተው በውሃው ላይ እየተራመዱ ወደ እሳቸው ተጠጉና፤

«'ብፁዕ አባታችን ያስተማሩንን ፀሎት እረሳነው' አሉ - በትህትና ወደ ጳጳሱ እየተመለከቱ፤ 'ስለዚህ ይቅር ይበሉንና እባክዎ ያስተማሩንን ፀሎት ደግመው ይንገሩን' አሏቸው:: ጳጳሱ ራሳቸውን ግራና ቀኝ እየወዘወዙ 'እናንተ ተወዳጅ ሰዎች!' አሉ - በፍፁም አክብሮት፤ 'ያሳችሁ ይበልጣልና በአሮጌው ፀሎታችሁ ኑሩ' አሏቸው» ይለናል ቶልስቶይ::

ጃገማም ገና በአስራ አምስት አመቱ መሳሪያ ማርኮ፤ የሶስት ሺህ አምስት መቶ አርበኞች መሪ ሆኖ፣ የተራራ ንጉስ ከነበረበት ሰላማዊ ኑሮ ወጥቶ ቢሮክራሲ በበዛበት፣ ፍትህ በተጓደለበት ህይወት እንዳይገባ የመከረው ባለመኖሩ አሮጌውን ሰላማዊ ህይወት አጥቶ በአዲሱ ህይወቱ እንደ ባቄላ በየምድጃው እየተጣደ መቀቀሉ ቀጠለ::

«ጃንሆይ! ከሰራዊቱ ያሰናብቱኝ!» አለ፥ ጓደኞቹ ሲሾሙ የተገለለው ሻለቃ ጃገማ፥ ከንጉሰ ነገስቱ ፊት እንደቀረበ::

«ጃገማ! ለምን?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - ግራ ገብቷቸው:: ልቡ የተሰበረው ጀግና በህይወቱ እንኳን ተናግሮት አስቦት የማያውቅ ሀሳብ ከአንደበቱ ገንፍሎ፤

«ጃንሆይ! እኔ ዘመድ የለኝም ... ጦር ሰራዊቱ ውስጥ የሚያስብልኝ ዘመድ የለኝም» አለ - በማያውቅበት የለቅሶ ቃና::

«ጃገማ! ዘመድ ቢኖርህ ምን እንድትሆን፤ ዘመድ ባይኖርህ ምን እንዳትሆን?» አሉ ንጉሰ ነገስቱ::

«... ከዚህ የበለጠ ምን እሆናለሁ ጃንሆይ? እኔ የብርጌድ አዛዥ ሆኜ በአገልግሎት እየበለጥኋቸው እነሱ ተሾሙ፤ እኔ ግን ...» አላቸው:: ንጉሰ ነገስቱ ለብስጭቱ በቂ ምክንያት እንዳለው ተረዱና ነገሩን ላለማካረር ብለው «... ይህን ጉዳይ ለአበበ ነግረኸዋል?» አሉት::





«ምኔ ናቸውና ለእሳቸው እነግራቸዋለሁ?» አለ፥ ጃገማ - ተስፋው ሙጥጥ ብሎ:: ንጉሰ ነገስቱ ነገር አዋቂና በሳል ስለሆኑ አባባሉን «ያለኸኝ አንተ ነህ ...» እንደማለት ነው ብለው በቀና ተርጉመው «በል ጠብቀኝ!» አሉ:: በደንቡ መሰረት ግን የጃገማ ጉዳይ ማለፍ የነበረበት በጦር ሚኒስትሩ በራስ አበበ በኩል መሆኑ ለራሱ ለጃገማም ግልጽ ነበር::

ሻለቃ ጃገማ ከኢጣሊያውያን ማርኮ የሚጠቀምባቸውን መኪኖች «አስረክብ» ተብሎ በነበረበት ጊዜ እንደ ልቡ ንጉሰ ነገስቱን ማግኘት ባለመቻሉ ... «ፈዛዛ! ማን ከጆርባችን አትቁም አለህ?» ብለው ንጉሰ ነገስቱ ክልውላን ቤተሰባቸው፣ ከከፍተኛ መኳንንት ጋር ለአንድ ሰዓት ችሎት ሲቆሙ ከኋላቸው እንዲቆም ከፈቀዱለት ቆይቷል:: ስለዚህ ያሰናብቱኝ ብሎ ካመለከተ በኋላ በነጋታው የችሎት ሰዓት ሲደርስ ጠብቆ ሄደ:: በሰዓቱ ንጉሰ ነገስቱ ችሎት ወደሚቆሙበት ሲደርሱ ራስ አበበን ጨምሮ መገኘት ያለባቸው ሁሉ ቆመዋል:: ችሎቱ ሲፈፀም ንጉሰ ነገስቱ ራስ አበበን ጠሯቸው::

«ጃገማ ሹመት ባለማግኘቱ አዝኖ ነግሮናል ... ባስቸኳይ የሚገባው ሹመት ይሰጠው» አሉ ኮስተር ብለው::

ራስ አበበም ሆኑ ሌሎች ከፍተኛ መኳንንት የንጉሰ ነገስቱን የመጨረሻ ብስጭታቸውን ገደብ ያውቁታል:: ከዚያ ካለፈ ግን ትልቅ አደጋ ነው:: ለምሳሌ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ አልጋ ወራሽ እንዲሆኑ ከተዋደቁላቸው አንዱ ሊጋባ በየነ ወንድማገኘሁ ነበሩ:: በኋላ ግን ሊጋባ በየነ «ራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽ በመሆናቸው ተራቸውን ይጠብቃሉ እንጂ በመንግስቱ አስተዳደር ውስጥ ገብተው መስራት አይገባቸውም» ብለው ተፈሪ መኮንንን ተቃወሙ:: ተፈሪ ያን አባባል እንደሰሙ ቂማቸው ከገደቡ አለፈ:: ብዙም ሳይቆይ «ሽብር ለማስነሳት ተዘጋጅተሃል» በሚል ሊጋባ በየነ ተወንጅለው ወጥመድ ውስጥ ገቡ:: መከሰሳቸውን ያወቁት በየነ «ምነው እኛው ራሳችን ከመሬት አንስተን አልጋ ላይ ብናወጣው እኛኑን ከሰሰን» ብለው በመውቀሳቸው የተጣለው መረብ ውስጥ ያለጥንቃቄ ወደቁ::

ንጉሰ ነገስቱ ራስ አበበን አነጋግረው ከግቢ ሊወጡ ሲሉ፤ «ጃገማ!» ብለው ተጣሩ:: ጃገማ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጥቶ ቀረብ አለ::

«ትናንት የነገርኸንን ለአበበ ንገረው» አሉ:: ጃገማና ራስ አበበ ተነጋገሩ:: «አይሳነው» የፈቀደውን ማንም ሊሽር አይችልምና ራስ አበበ

ለጄኔራል ኮቶም ማስታወሻ ጽፈው ሰጡት። በዚህም የሌፍተናንት ኮሎኔልነቱን ማዕረግ ጃገማ ማግኘት ቻለ።

* * *

አንድ ጊዜ የዩጎዝላቪያ ጀግኖች ማህበር የኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ዩጎዝላቪያን እንዲጎበኝ ግብዣ አደረገለት። ከኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ደጃዝማች አበበ ሽንቁጤ የልዑካኑ መሪ በመሆን፣ ከጦር ሰራዊት ወልደ ዮሐንስ ተክሉና ጃገማ ኬሎ፣ ከክብር ዘበኛ ነጋ ተገኝ ተመርጠው ወደ ዩጎዝላቪያ ተላኩ ...

የዩጎዝላቪያ የአርበኝነት ተጋድሎ ከኢትዮጵያው ጋር ተመሳሳይ ስልት፣ ውስብስብ ፈተናና ስቃይ ነበረው። ማርሻል ቲቶ ከእነ ኮሎኔል ጃገማ ጋር ተገናኝተው የዩጎዝላቪያን የአርበኝነት የጀግና ኒሻን ከሸለሟቸው በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞች ልዑካን ከንጉሰ ነገስታቸው የተላከውን የብር ሞሰብ ስጦታ አበርክተው ስለአለፈው የአርበኝነት ትዝታና መስዋዕትነት አወጉ። ለክብራቸውም በቤተመንግስት ግብዣ ተደረገላቸው።

ማርሻል ቲቶ «የአርበኞች የመስዋዕትነት መታሰቢያ እንዳይጠፋ ጠንክራችሁ ስሩ» ብለው ቀድመዋቸው አርበኝነትን የጀመሩትን የኢትዮጵያ አርበኞች መከሯቸው።

በዚያ የጉብኝት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአቡነ ጴጥሮስ በስተቀር ሃውልት የቆመለት አርበኛ አልነበረም። በዩጎዝላቪያ ግን ለሶስት ሺህ አምስት መቶ አርበኞች የመታሰቢያ ሃውልት ቆሞላቸዋል። ሃውልት ባልቆመበት ቦታ ደግሞ ዝርዝር የተፃፈበት የተጠረበ ድንጋይና በየሱቆች የሚሸጥ የአርበኞችን ገድል የያዘ መጽሔት አለ።

አንዱ ዩጎዝላቪያዊ «እናንተ አገር ለአርበኞች ሃውልት ይቆምላችኋል?» አለው - ኮሎኔል ጃገማን። «አዎ! ለጀግኖች ሃውልት ይቆማል። ሃውልቱ ግን አበባ ነው፤ ከአመት አንዴ የሚበቅል፤ አደይ አበባ ይባላል» አለው ሳቅ - ብሎ። ሰውየውም የአበባ ሃውልት ሰምቶ ባያውቅም ከጃገማ ጋር አብሮ ሳቀ። ከመሳቅ የበለጠ ምን ጥበብ አለ? ከአበባ የበለጠስ ምን ሃውልት አለ? ለሁሉም ተፈጥሮ የእጇን ትሰጠዋለች...

ጄኔራል ጃገማ በሀገራቸው ላይ ነውር ያልሰሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር አባል ሆነው ማህበሩ እንደ ዩጎዝላቪያ ጀግኖች ማህበር እንዲጠናከር ታላቅ ምኞት አለው። ማህበሩ ከተጠናከረ የአገርን





ታሪክ፣ የጀግኖችን ገድል ለሚቀጥለው ትውልድ እያስተላለፉ በታሪኩና በጀግኖች አባቶቹ የሚኮራ ትውልድ ማፍራት ይቻላል።

የአገራችን ችግር የተፈጥሮ ሀብት አለመኖር ብቻ ሳይሆን የአለውን በአግባቡ ያለመጠቀም ችግርም ነው። ምንም ይሁን ምን ዛሬ ከትናንት ጋር የተቆራኘ ነው። ያን ቁርኝት ማላላትና መፍታት ምንጩን ደፍኖ ወንዙን እንደመጠበቅ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ጃገማ እንደሚያስበው የአርበኞች ማህበር ለአርበኞች ሃውልት እንዲቆም፣ በስማቸው መንገድ፣ ትምህርት ቤት... እንዲሰየም ማድረግ ካልቻለ ተልዕኮውን በአግባቡ እየተወጣ ነው ተብሎ አይታመንም።

* * *

በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ጃገማ የክ/ጦር አዛዥ ሆኖ ከፍተኛ የክብር ዘብ ሰልፍ ሲኖር በፈረስ ጀርባ ላይ ተቀምጠው ሰልፉን የሚያስውቡት ጄኔራል ተድላና ኮሎኔል ጃገማ ነበሩ። ለምሳሌ የግሪኩ ርዕሰ ብሔር ኢትዮጵያን በይፋ በጎበኙበት ወቅት ፍልውሃ ፊት ለፊት ባለው ሜዳ ታላቅ የክብር ሰልፍ ተዘጋጀ። ሰልፈኛውን ከሚመሩት አንዱ ካኪውን በአሚዶ ተኩሶ፣ ቀበቶውን ወልውሎ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ በነጭ ፈረስ በግርማ ሞገስ የሚመጣው እንኮዩ የኬሎና የደላንዱ ልጅ ጃገማ ነበር። የዩጎዝላቪያው ፕሬዚደንት ጄኔራል ቲቶም አገራችንን ሲጎበኙ ልጥልጥ ኑግ በመሰለ ጥቁር ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሰልፉን የመራው ጃገማ ነው።

ሁሌም እንደሚደረገው ጄኔራል ተድላና ጃገማ ሰልፉን እየመሩ ሄደው ንጉሰ ነገስቱ ፊት ለፊት ሲደርሱ ሰላምታ ሰጥተው ያልፉና የሰልፉ መሪ ሰልፈኛውን ይዞ ሲሄድ ም/አዛዡ ኮሎኔል ጃገማ ከሰልፍ መሃል ወጥቶ ከንጉሰ ነገስቱ ፊት ለፊት በመቆም ሰልፈኛው ሄዶ እስኪያልቅ ድረስ ከጠበቀ በኋላ ወጣ በማለት የሰልፈኛው የሰልፍ ትርዒት ማለቁን ለንጉሰ ነገስቱ በሰላምታ አብስሮ ሰልፈኛውን ተከትሎ ይሄዳል። ያኔ ንጉሰ ነገስቱን ጨምሮ ህዝቡ ባጠቃላይ ጭብጨባውን ያቀልጠዋል።

የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ወንድ ልጅ ልዑል መኮንን በሞቱ ጊዜ በተመረጡ ኮሎኔሎች መካከል የሻሙላ ውድድር ተደርጎ ነበር። የሻሙላ ውድድሩ በጥንቃቄ የተደረገና አመራረጡም ጠንካራ ነበር። በውድድሩም ኮሎኔል ጃገማ አሸነፈ። በቀብር ሥነስርዓቱ ንጉሰ ነገስቱ የልጃቸውን አስከሬን ስመው ለመሰናበት እንደተጠጉ ሻሙላውን መዞ ጠባቂ መልአክ መስሎ የቆመው ኮሎኔል ጃገማ ነበር።

# ፲፫

## ዘመናዊ ጦር ግንባታ

ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ ከመወረሯ ሶስት ዓመታት በፊት በቤልጅጋዊው በሻለቃ ፓሌት የሰለጠነና ለበን ጠመንጃ የታጠቀ ስድስት መቶ ሰው ያቀፈ አንድ ሻለቃ ጦር ብቻ ነበራት። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጦር በጀግኖች አርበኞች የአምስት ዓመት ትግል ከተሸነፈና በእንግሊዝ ጦር እርዳታም ከአዲስ አበባ ተባርሮ ንጉሱ ቤተመንግስታቸው ከገቡ በኋላ የእንግሊዝ ወታደራዊ ተራድኦ የኢትዮጵያን ሰራዊት አደራጅ፣ አሰልጣኝና ተቆጣጣሪ ሆነ። የዘር ልዩነቱ እንዲጠናከር፣ አንዱ ብሔር ከሌላው ጋር እንዲጋጭ ሁኔታዎች ተመቻቹ። በስደተኞች፣ በባንዳዎችና በአርበኞች መካከልም አለመግባባቱ እንዲጋጋልና በኤርትራ፣ በኦጋዴንና በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ተንኮል ከህዝቡ ዕይታ እንዲርቅ ተደረገ። የእንግሊዝ ጦር አዛዦች የቼዝ ጨዋታቸውን እያጠነከሩ ወታደሮቻቸውን በመግፋት፣ ፈረሰኞቻቸውን ማዘለል፣ ጳጳሳቸውን በሰያፍ ማስኬድ፣ የካብ ማማቸውን ወደ ንግስታቸው ማስጠጋት ቀጥለው የኢትዮጵያውን ንጉሰ ነገስት «እጅ ወደላይ» ማለት ጀመሩ።

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጨዋታው ስር ሰዶ ሊያጠናቅቃቸው ጥጋቸው መድረሱን ሲያውቁ በኢጣሊያ ወራሪ ሃይል የተጀመረው ጨዋታ በእንግሊዞች መደገሙና ልፋቱ ሁሉ ከዝንጀሮ ቆንጆ መምረጥ እየሆነ መምጣቱ ሲታያቸው ወደ ወዳጃቸው ኮሎኔል ዊንጌት ሄዱ።

«ምን እየተሰራ ነው?»
«በማን?»
«በእናንተ በእንግሊዞች ... የሚሰራውን ፈጣሪ ይወደዋል?»

ኮሎኔል ዊንጌት ፈጣሪን ሲያነሱበት ፊቱ ቲማቲም መሰለ። ለአገሩ ታማኝ ወታደር ነው። በታማኝነትም ግዳጁን እየተወጣ ነው። የግዳጅ ጉዞው ላይ ግን የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል እንኳን የማያውቁት አዲስ ጨዋታ ተጀምሯል። እሱ ያን አይደግፍም፤ ግን ደግሞ ዝም ማለት ነበረበት - ለራሱ ሰላም ሲል።





«ኮሎኔል ዊንጌት! ጠየቅሁህ እኮ! እየሆነ ያለውን ፈጣሪ ይወደዋል?»

«አይወደውም!» የዊንጌት እጆች ተወራጩ፤ ከተቀመጠበት ተነስቶ ተንጎራደደ።

«አንተ በእቅዱ አለህ?» አሉት - ትክ ብለው እያዩት። አየሩ ላይ የተተከሉ ዓይኖቹን ሳይነቅል ብዙ ቆየ። ንጉሰ ነገስቱ ከሄደበት እስኪመለስ ጠበቁት።

«የለሁበትም፥ ግርማዊነትዎ!» አለና ትክ ብሎ በተራው አያቸው። ሁለቱም አንዱ በሌላው ዐይን ውስጥ እውነትን ፍለጋ ተሰማሩ።

«ያምኑኛል?»

«አምንሃለሁ ... ማመኔ ምርጫ የለውም» አሉ ካባቸውን አመቻችተው እየለበሱ።

«እርስዎ የእንግሊዝ ወታደራዊ ተልእኮ (ቢ.ኤም.ኤም) በሚል የታወቀውን ስምምነት ከእንግሊዝ መንግስት ጋር እንደተፈራረሙ በእንግሊዝ ጦር አዛዥ በብርጋዴዬር ላሽ አስተባባሪነት የሚመራ 'ብሮክልኸርስት (Brocklehurst) ተልእኮ (ቢ.ኤም)' በሚል ምህፃረ-ቃል አዲስ እንቅስቃሴ ተጀመረ። እንቅስቃሴው የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች በመከፋፈል ለእርስዎ መንግስት እውቅና ባለመስጠት አገርዎን የጠላት ይዞታ አስተዳደር ብሎ በቅኝ ግዛት ይዞ የመቆየት ተልእኮ ያለው ነው» አላቸው።

«እንደዚያ ነው?!» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - አንገታቸውን በሃዘን ከፍ ዝቅ እያደረጉ። ንጉሰ ነገስቱ በሐሳብ ወደኋላ ተጉዘው ሱዳንና ደብረማርቆስ ላይ መታገታቸው፤ በጄኔራል ካኒንግሃም ከሚመራው የእንግሊዝ ጦር ጋር አብረው አዲስ አበባ እንዲገቡ ሲጠይቁ እንዲቆዩ መደረጋቸው ለበጎ እንዳልነበረና የተንኮል መጠኑ ከጠበቁት በላይ እጅግ ጥልቅ እንደሆነ ገባቸው።

«በል ይህን ምስጢር ስለገለጽህልን ከልብ እናመሰግንሃለን ... ይህ ምስጢር የኔና የአንተ ነው! እምትችለውን ሁሉ እርዳን፤ እኛም እግዚአብሔር በሚሰጠን ሃይል የምንችለውን እንፈጽማለን» አሉት።

* * *

ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት የራሷን ሃይል እያጠናከረች ከእንግሊዞች ወታደራዊ ተፅዕኖ በአፋጣኝ መላቀቅ መሆኑን የተገነዘቡት የኢትዮጵያ መሪ 'ክብር ዘበኛ' በሚል ስም አምስት ሺህ የሰለጠኑ ወታደሮች ያሉት ኃይል ለማደራጀት በፈረንሳዮች እገዛ በስዊድን መኮንኖች እንዲሰለጥን አደረጉ:: ከአርበኞች ተውጣጥቶ የሰለጠነ የህዝባዊ ጦር ሰራዊት በየጠቅላይ ግዛቱ ተደራጀ::

ዘግየት ብሎ ደግሞ ኢትዮጵያና አሜሪካ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ስምምነት ተዋዋሉ:: አሜሪካም መካከለኛው ምስራቅን፣ ኮሚኒስት አገሮችን... መከታተል የሚያስችላትን የወታደራዊ ስለላ እምብርት «ቃኘው ጦር ሰፈር» ብላ አቋቋመች:: በ1937 ዓ.ም የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት ከፍታውን ጨምሮ በመመንደግ የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት አይዘን ሃወር ሌላ ቃል ኪዳን ገቡ:: እያንዳንዳቸው ስምንት ሺህ የሰው ሃይል ያቀፉ ሶስት ክፍለ ጦሮች ለማሰልጠንና ለማስታጠቅ አገራቸው እንደወሰነች አስታወቁ:: ስልጠናው ተጀመረ:: መቶ አምስት ሚሊ ሜትር መድፍ፣ ስልሳ ሚሊ ሜትር አዳፍኔ፣ ቢ.ኤ.አር መትረየስ፣ ኤም ዋን ጠመንጃ፣ ፀረ ታንክና ተሽከርካሪዎች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ::

በአሜሪካ ልባዊ ድጋፍ የኢትዮጵያ ምድር ጦር ቀድሞ ከሰለጠነው ጋር ተዳምሮ በአራት ክፍለ ጦሮች ተደራጀ:: አንደኛው ክፍለ ጦር 'የክብር ዘበኛ ጦር' በሚል ስም መቀመጫውን አዲስ አበባ አደረገ:: ሁለተኛው ክፍለ ጦር መቀመጫው መጀመሪያ ደሴ፣ ቀጥሎ ኤርትራ ሆነ:: ሶስተኛው ክፍለ ጦር በምስራቅ በሯ ሐረር ተመደበ:: አራተኛው ክፍለ ጦር ጠቅላይ ሰፈሩን አዲስ አበባ አድርጎ የተወሰነ ሃይሉን በነገሌ ቦረና አስቀመጠ::

አራቱ ክፍለ ጦሮች በሶስት በሶስት ብርጌድ ተከፈሉ:: ብርጌዶች ደግሞ በሶስት በሶስት እግረኛ ሻለቆች ተደለደሉ:: ሻለቆችም በሶስት ሶስት እግረኛ ሻምበሎች ተመደቡ ... እንዲህ እንዲሀ እያለ እስከ እግረኛ ጓድ ተደራጀ:: ለእያንዳንዱ ክፍለ ጦር፣ ብርጌድ፣ ሻለቃ ... የሰው ሃይል ዝርዝሩ ወጣ፤ አመራሩና የአመራሩም ቁጥር በግልጽ ታወቀ:: ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ የጦር ሃይል አደራጀች::

የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች በአንድ ጦር ሚኒስቴር ስር እንዲተዳደሩ ተደርጎ የጦር ሚኒስትሩ ስሙ-ጥሩው አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ፤ ኤታማዦር ሹሙ ደግሞ ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ሆኑ::





«ማግ» በሚል ምህፃረ-ቃል የሚንቀሳቀሱት የአሜሪካ ጦር መኮንኖች ዋና ፅዛቸውን አዲስ አበባ በማድረግ የኢትዮጵያ ጦር ባለባቸው ክፍለ ጦሮች በአማካሪነት ተመደቡ:: ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴም የወታደሮችን ስልጠና እግር በእግር ከመከታተል፣ በያሉበትም እየሄዱ ከመጎብኘት አልፈው እሳቸውም ወታደራዊ ዩኒፎርም መልበሱን አዘወተሩ:: በፖለቲካውም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካሪ እንዲሆኑ አሜሪካዊው ጆን ስፔንሰር ተቀጠሩ::

በ1942 ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር ሃይል በስዊድኖች ተጀምሮ በአሜሪካውያን እየተደገፈ መደራጀቱን ቀጠለ:: ለመጀመሪያ ጊዜም ኢትዮጵያውያን በአፍሪካ ሰማይ ላይ እንደ ንስር በረሩ:: ከዚያ በኖርዌይ የባህር ሃይል መኮንኖች አሰልጣኝነት የኢትዮጵያ የባህር ሃይል ተቋቋሞ በአሜሪካውያን ወታደራዊ ተራድኦ እየተደገፈ አሁንም ጥቁር አልማዞች እንደ ዶልፊን በቀይ ባህር ላይ ብቅ ጥልቅ እያሉ ተንሳፈፉ::

ከዚያም በኢትዮጵያ ትምህርት መስፋፋት ጀመረ:: አየር መንገድ ተቋቋመ:: የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ስራውን ጀመረ:: ተጨማሪ ሆስፒታሎች ተከፈቱ:: የመሬት ይዞታ አለመሻሻል፣ ያልተማከለ አስተዳደር አለመኖር፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ስልጣን መውደድና ከጊዜው ጋር የሚራመድ የለውጥ ፍላጎት አለመኖር የመሳሰሉት መሰረታዊ የሀገር ችግሮች ከጦር ሃይሉ አዲስ አደረጃጀትና ከልማቱ እንቅስቃሴ ጎን ለጎን መንሰራፋት ቀጠሉ:: ይህ ሁሉ የሆነው ደግሞ እንድም ጣሊያኖች ህዝብ በግፍ ጨፍጭፈው፣ ዝሙትን አስፋፍተው፣ የህዝቡን ምግባርና ሥነልቦና አቃውሰው፣ በህብረተሰቡም መሀል ጥርጣሬና መናናቅ እንዲፈጠር አድርገው በመሄዳቸው ነው:: ኢትዮጵያ ለዚህ ሁሉ ውድመት ከድል በኋላ ከኢጣሊያ መንግስት የጠየቀችው ካሳ መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን ፓውንድ ብቻ ሲሆን ለኢትዮጵያ የተሰጣት ካሳ ግን ከጠየቀችው አንድ ሰባተኛውን ብቻ ነው::

ያ ሁሉ አልፎ ኢትዮጵያ የመንግስታቱ ህብረት የጠየቃትን ግዴታ ለመወጣት ወታደሮቿን ወደ ኮሪያና ኮንጎ አዘመተች:: በእንግሊዝ፣ ኬንያ፣ ሊቢያ፣ ሶማሊያ የተከሰተውን ርሃብ ለመታደግ የገንዘብ እርዳታ የምትሰጥ አገር ሆነች:: የደቡብ አፍሪካና የናሚቢያ ህዝቦች ለሚያደርጉት የነፃነት ትግል ድጋፍ በመስጠትና አማፅያኑንም በወታደራዊ እውቀት በማሰልጠን የአፍሪካውያኑን የነፃነት ጉዞ አገዘች:: በቢያፍራና በናይጀሪያ መንግስት፣ በሰሜንና ደቡብ ሱዳን፣ በአልጀሪያና ሞሮኮ መካከል የነበረው ግጭትና ጦርነት በስምምነት እንዲያልቅ የኢትዮጵያው ንጉስ ነገስት ሸመገሉት::

ኢትዮጵያ የነፃነት ምሳሌ ... ንጉስ ነገስቱ ደግሞ የአፍሪካ አባት ተብለው ዝናቸው በዓለም ናኝቶ ለሰላም የኖቤል ሽልማት እስከ መታጨት ደረሱ።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በአየር ሃይሏ፣ በጦር አካዳሚዋ፣ በዩኒቨርሲቲና በአየር መንገዷ አደገች፤ ለአፍሪካውያን እህትና ወንድሞች ነፃ የትምህርት ዕድል የምትሰጥም አገር ሆነች። በዚያ የጨለማ ዘመን ብርሃን ይፈነጥቃል በሚል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም መስራች አባላቱ ከሆኑት ጥቂት አገራት አንዷ ሆነች። ለአፍሪካውያን ነፃነት፣ ለአፍሪካውያን ወንድማማችነት መጠንከር ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተችው ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ላይ እንዲከፈት መተባበር ብቻ ሳይሆን ህንፃ ገንብታ ሰጠች። «አፍሪካ፣ አፍሪካ፣ አፍሪካ አገራችን ...» ብላ ቅኔ ጽፋ፣ ቅኔዋን በዜማ አቀነባብራ፣ በልጆቿ ሰረቅራቃ ድምጽ አዜመች። "አፍሪካ ... አፍሪካ አገራችን" ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ መዝሙሩ በመላው አፍሪካ እያስገመገመ ተሰራጨ።

* * *

በሶቭየት ህብረት እርዳታ የሚደራጀውን ትልቁን የሱማሌ ጦር ለመቋቋም የጦር መሳሪያ እርዳታ ለመጠየቅ ጄኔራል መርዕድ መንገሻ በንጉሰ ነገስቱ ፈቃድ አሜሪካ አገር ሲሄዱ፤ የአየር ሃይል አዛዡ ጄኔራል አሰፋ አየነ የአየር ሃይሉን ወክለው እንዲያማክሩ የላኩት ከጄኔራል መርዕድ ጋር ትውውቅ የሌላቸውን ሻለቃ ሥምረት መድኃኔን ነው። ሻለቃ ሥምረት የኢትዮጵያ አየር ሃይል የቴክኒክ እና የሎጂስቲክ ኃላፊ ሆነው በአብራሪነትም ያገለግሉ ነበር። ጄኔራል ጃገማ ደግሞ ከገሮ ጎዳና በሚመዘዝ የዘር ሃረግ ከሻለቃ ሥምረት ጋር ዘመድ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ጄኔራል ጃገማን ትምህርት ባስጀመሯቸው የሻለቃ ሥምረት እናት በኩል አጎት ናቸው።

ጄኔራል መርዕድ ጦር ለማጠናከር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ከተማ ይፍሩ ደግሞ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ሄደው አሜሪካ ተገናኙ። ሻለቃ ሥምረትና አቶ ከተማ ኮተቤ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አብረው ተምረዋል፤ በደንብም ይተዋወቃሉ። ጄኔራል መርዕድ አቶ ከተማን «ከማክናማራ ጋር ለሚደረገው ንግግር አስተርጓሚ መድብልኝ» ሲሏቸው ስለ ሻለቃ ሥምረት ቋንቋ ችሎታ አስረዷቸው።

... ከዚያ ጄኔራል መርዕድና ሻለቃ ሥምረት ተግባቡ።





«ጄኔራል መርዕድ! ማክናማራ ኢኮኖሚስት ነው፤ የሚጠይቅዎትም ስለ አገራችን ኢኮኖሚ ነው ብዬ እገምታለሁ፤ ስለዚህ የኢኮኖሚ ጥያቄዎቹን ለመመለስ መዘጋጀት አለብዎት ...» አሏቸው፥ ሻለቃ ሥምረት። ጄኔራል መርዕድ ማክናማራን ለማነጋገር የቻሉት አሜሪካ «የኪዩባ ክራይሲስ» በተባለው ችግር ከሶቪየት ህብረት ጋር በተፋጠጠችበት ወቅት ነው። ወቅቱ የሶቪየቶች የኑክሌየር አረር የተሸከሙ ሰርጓጅ መርከቦች ኪዩባ ጥግ ተጠግተው የኑክሌየር ጦርነት ሊጀምሩ ቋፍ የደረሱበት አስፈሪ ወቅት ነበር። ማክናማራ ጄኔራል መርዕድን ያናገራቸው ግን በተረጋጋ መንፈስ ነው።

«ጄኔራል! የአገራችሁ ትላልቆቹ የገቢ ምንጮች ምንድን ናቸው?» አለ፥ ማክናማራ። ጄኔራል መርዕድ ለቅጽበት የሻለቃ ሥምረትን ዐይን አየት አደረጉት። ሻለቃ ሥምረት እንዳሉት የመጀመሪያው ጥያቄ የኢኮኖሚ ጉዳይን የሚመለከት ሆነ።

«... የአገራችን ዋናዎቹ ሃብቶች የእርሻ፣ የማዕድንና የሌሎችም ውጤቶች እንዲሁም የምንሰጣቸው ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ናቸው፤ ጥንካሬያችንም ህዝባችን ነው» አሉ፥ ጄኔራል መርዕድ። ንግግራቸው ለአንድ ሰአት ያህል ቀጠለ። በመጨረሻ «እንደ እርስዎ ያሉ መሪዎች ያሏት አገር ተስፋ እንዳላት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ» ብሎ ማክናማራ ደስታውን ገለፀና «የሚፈልጉትን ነገር ረዳቴና የፀጥታ አማካሪዬ ሚስተር ቡንዲ ይፈፅምልዎታል» ብሎ ሄደ።

ከቀናት በኋላ ንግግሩ ሲያበቃ ለኢትዮጵያ አየር ኃይል F5 የምትባለው ተዋጊና ተከላካይ የሆነችው ሱፐር ሶኒክ ጄት አውሮፕላን በእርዳታ ተገኘች። ከጊዜ በኋላ ከሱማልያ ጋር በተደረገው ጦርነት ላይ በፍጥነትና በክብደት የሚበልጧትን እና በብዛትም ከአምስት ጊዜ በላይ የሚያጥፏትን የሱማልያ አየር ኃይል የጦር አውሮፕላኖችን ድምጥማጣቸውን አጠፋቻቸው።

# 10

# የሞሳዝጊ ልጆች

በ1940 ዓ.ም. ክጦር ሚኒስቴር የተላኩ ክፍተኛ መኮንኖች ክፍለ ጦሮችንና ብርጌዶችን ሲጎበኙ በሰባተኛ ብርጌድ ክፍተኛ ችግርና መከፋፈል መኖሩን ለመገንዘብ ቻሉ:: ስለዚህ የብርጌድ አዛዥ የነበሩትን አንስተው ኮሎኔል ጃገማን የሰባተኛ ብርጌድ አዛዥ አድርገው አዲግራት ላኩት::

ጃገማ ሰባተኛ ብርጌድ እንደሄደ የስፖርት መጫወቻዎችን አስርቶ ሰራዊቱ በተለያዩ ስፖርቶች እንዲካፈልና ትኩረቱ ስፖርታዊ ውድድር እንዲሆን የመረብ ኳስ፣ የኢላማ ተኩስ ... ዝግጅቶችን አድርጎ ሁለት ወር በማይሞላ ጊዜ በዘርና በጎሳ የተከፋፈሉትን የሰባተኛ ብርጌድ አባላትን እንዲግባቡ አደረጋቸው:: ውድድሩን በማስፋት መቀሌ አጠገብ በሚገኝ ቦታ ከእነ ደጃዝማች ዘውዴና ደጃዝማች የማነ ጋር የኢላማ ተኩስ ውድድር እየገጠመ የሰራዊቱን ልብ የሚሰቅሉ አጋጣሚዎችን ፈጠረ:: ጃገማ ራሱ በዲሞትፈር ጠመንጃ ኢላማ ተኩስ እየተወዳደረ የሚያሸንፈው ስለጠፋና ለውድድሩ የሚቀርበውን ውስኪ እየወሰደ ስላስቸገረ «ጃገማ በዲሞትፈር መተኮስ ስለለመደ ነው የማይስተው» ተብሎ የኢላማ ተኩስ መወዳደሪያው መሳሪያ ተቀየረ:: ጃገማ ግን መሳሪያው ቢቀየርም እያሸነፈ ውስኪውን ሰብስቦ መውሰዱን ቀጠለ:: ብዙም ሳይንደረደር አንድ ሜትር ከዘጠና ይዘል የነበረውና በሽጉጥ ኢላማ ተኩስ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ ውድድር ተካፍሎ አሸናፊ በመሆኑ ከንጉሰ ነገስቱ እጅ ሽልማት ያገኘው ኮሎኔል ጃገማ ፈረስ ግልቢያ፣ ውሃ ዋናና የኢላማ ተኩስ መውደዱ የሚመራውን ሰራዊትም ወደ ስፖርት እንዲሳብ፣ የውድድር ስሜት እንዲፈጠርና «ስፖርትን ለወዳጅነት» የሚለውን አባባልም በተግባር እንዲጠቀምበት አደረገው::

ኮሎኔል ጃገማ ከ1940 ዓ.ም እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ የሰባተኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ቆይቷል:: እሱ አዲግራት በነበረበት ጊዜ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ኤርትራን ከኢጣሊያ ነጥቀው የያዙት እንግሊዞች ኤርትራን ያስተዳድሩ ነበር:: ያ ወቅት ደግሞ «ኤርትራን ከእናት አገሯ ኢትዮጵያ» ጋር ለማቀላቀል ዲፕሎማሲያዊና ውስጣዊ እንቅስቃሴው የተጠናከረበት ወቅት ነበር::





«የሞሳዝጊ ልጆች» የሚባሉት የኤርትራን ወደ እናት አገሯ ኢትዮጵያ መቀላቀል እውን ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አርበኞች ነበሩ:: ሆኖም እንቅስቃሴያቸውንና የእንቀላቀል ጥያቄያቸውን እንግሊዞች አይቀበሉትም:: ስለዚህ የሞሳዝጊ ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ድንበር እየገቡ መውጣታቸውን እንዳወቁ እንግሊዞች ያን ለማቆም እርምጃ መውሰድ ፈለጉ::

በወቅቱ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ዳይሬክተር ደጃዝማች የማነ፤ የአክሱም ገዥ ንቡረዕድ ገብረመስቀል፣ የአዲግራት ገዥ ደጃዝማች ሃይለማርያም፣ የአዲግራት ከንቲባ ግራዝማች ወልደአረጋይ ነበሩ:: ሁሉም የኤርትራን ከኢትዮጵያ መቀላቀል የሚደግፉ፣ ለስኬታማነቱ የሚንቀሳቀሱና ከኮሎኔል ጃገማ ጋር በትብብር የሚሰሩ ነበሩ::

አንድ ቀን ከቀኑ ስድስት ሰዓት ከሩብ ሳይ ኮሎኔል ጃገማ ከስራ ለምሳ ወጥቶ እግረ መንገዱን ወዳጁ የነበረውን የጉምሩክ ኃላፊ ሰላም ብሎ ለማለፍ የቆመች ጆፕ መኪና አጠገብ ቆሞ የነበረውን አንድ እንግሊዛዊ አልፎ ገባ:: ግራዝማች ወልደአረጋይ ጃገማን በዐይናቸው ይቆጣጠሩት ኖሮ እንግሊዙ እንዳያያቸው እየተጠነቀቁ ተከታትለውት ወደ ጉምሩክ ገቡ::

«ኮሎኔል ጃገማ! አገረ ገዥውና እኔ የሰናፌ አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ከሆነው እንግሊዛዊ ተደብቀናል:: አመጣጡ የኤርትራ አርበኞች የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው ከገቡ ይዛችሁ አስረክቡን ለማለት ይመስለናል:: ወንድሞቻችንን መቼም አትግቡ ብለን እንከለክልም:: በሌላ በኩል ደግሞ አገራችን ከእንግሊዝ ጋር የመረዳዳት ስምምነት ፈርማለችና ስምምነቱን ረግጠን እምቢተኛ ልንሆን አንችልም:: ለዚህ አጣብቂኝ ጥሩ መፍትሄ ሆኖ ያገኘነው መደበቅን ነው:: ስለዚህ አንተ ይህን እንግሊዛዊ ወስደህ ጋብዘው፤ ወጭውን በሙሉ እኔ እሸፍናለሁ» አሉት::

... ጃገማ ወደ እንግሊዛዊው አመራና ሰላምታ አቀረበለት:: ከዚያ «ምን ፈልገህ ነው?» አለው::

«አውራጃ ገዥውን ወይም ከንቲባውን ፈልጌ ነበር:: ሁለቱም ለጊዜው የሉም አሉኝ፤ ስለዚህ እዚህ ድረስ መጥቼ ሳላገኛቸው መሄድ ስላልፈለግሁ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ቆይቼ ማግኘቱ አማራጭ እንደሌለው እያሰብሁ ነው» አለው:: «እንደዚያ ከሆነ እስከዚያው ከእኔ ጋር ቆይ:: ኮሎኔል ጃገማ እባላለሁ፤ የሰባተኛ ብርጌድ አዛዥ ነኝ» አለው ጃገማ:: እንግሊዞች የኢትዮጵያን ጦር ስለሚያስለጥኑ፣ ወታደራዊ ግንኙነትም ስለነበር እንግሊዛዊው የአውራጃ ፖሊስ አዛዥ ግብዣውን በደስታ ተቀበለ::

የሞሳዝጊ ልጆች ከሚባሉት አንዱ የኢጣሊያ ሴጀራ መትረየስ አፈታት፣ አገጣጠምና አተኳኮሱን ለመለማመድ ከኤርትራ መጥቶ የተቀመጠው ኮሎኔል ጃገማ ቤት ነው። ጃገማ የሞሳዝጊ ልጅ አንዱ ክፍል እንዲገባና እንዲቀመጥ አድርጎ እንግሊዛዊውን ቤቱ ይዞት ሄደ። ሁለቱ አይጥና ድመት ጎን ለጎን መሆናቸውን እንግሊዛዊው አላወቀም። ምሳ ቀረበ፤ መጠጥ ተከተለ። ጃገማና እንግሊዛዊው እያወሩ መጠጣት ቀጠሉ፤ በሁለቱ አመራር ስር ያሉት ወታደሮች እግር ኳስ እንዲጋጠሙ፣ ሜዳ ቴኒስ አብረው እንዲጫወቱ፣ የፈረስ ግልቢያና የውሃ ዋና ጨዋታም አብረው እንዲያከሂዱ ተስማሙ።

በጨዋታ ጊዜ ለመውሰድም ጃገማ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት አንድ ኢጣሊያዊና አጎቱ ያደረጉትን ፍልሚያም ለእንግሊዛዊው አጫወተው። «ከኢጣሊያ ወረራ ቀደም ብሎ አንድ ኢጣሊያዊ አፄ ምኒልክ ዘንድ ቀርቦ 'አንድ ጎበዝ የሆነ ኢትዮጵያዊ ፈረሰኛ የጦር ውርወራ እንዲገጥመኝ እፈልጋለሁ፤ እሱ ካሸነፈኝ እኔ አልጠይቀውም፤ እኔ አሸንፌ ከገደልሁትም እሱ (እናንተ) አይጠይቀኝም' ብሎ ውጥር አድርጎ ያዛቸው።

«ከኢትዮጵያ ወገንም ለጊዜው የሚደፍር ጠፋ። በዚያ ጊዜ የሆለታ ባላባት የሆነው ወርዶፋ ጩንገሬ (የሲጋባ በቀለ አባት) እኔ እገጥመዋለሁ ብሎ ቀረበ። በዓል ተዘጋጀ፤ ህዝቡ ተሰበሰበ። ንጉሰ ነገስቱም የሁለቱን ውድድር ለማየት ተገኙ። ሁለት ፈረሶች ቀረቡ፤ ለሁለቱም ጋሻና ጦር ተሰጣቸው። 'ማን ተባራሪ ይሁን?' ሲባል የእኔ ዘመድ ፈቃደኛ ሆነ። ጣሊያኑ አባራሪ ሆነና አነጣጥሮ ጦሩን ወረወረ። ወርዶፋ በጋሻው መክቶ ጦሩን አቅጣጫ አስቀይሮ ጣለው። ቀጥሎ 'አዙር' ብሎ ጣሊያኑን አባሮ፣ አባሮ ... ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ጦሩን ወረወረ። የጦሩ ጫፍ እንደ መኪና ጎማ እየተሽከረከረ ሄዶ ኢጣሊያዊው ላይ ተሰካ» አለው።

እንግሊዛዊው ጃገማን ተነስቶ አቀፈውና «የኢጣሊያን መሸነፍ ቀደም ብሎ የተነበየ ድንቅ ውድድር ነው» አለው። እንዲህ ሲጨዋወቱ የዘጠኝ ሰዓቱ ቀጠሮ ተረሳ፤ ሳቅና ሁካታው ቀጠለ። እንግሊዛዊው በጠጣው መጠጥ ሞቅታው ጨመረ። በመጨረሻም ኮሎኔል ጃገማ፤ «ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ይዘን ለእናንተ እንድናስረክባችሁ ለእኛም መመሪያ ተላልፎልናል። ስለዚህ ይህን ለማድረግና ከእንግሊዞች ጋር ተባብረን ለመስራት ዝግጁ ነን። አውራጃ ገዥውንና ከንቲባውንም በሌላ ጊዜ ማግኘት





ከፈለግህ ደግሞ ቀጠሮ አስይዤ እጠብቅሃለሁ» አለው - ፊቱ ቲማቲም የመሰለውን እንግሊዛዊ።

ከዚያ ኮሎኔል ጃገማ፥ እንግሊዛዊዉ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሆኖ አደጋ ካጋጠመው ችግር ስለሚፈጥር ዛላምበሳን አሳልፎት ተመለሰ። እንግሊዛዊው ወደ ሰናፌ እንደተመለሰ ኬላ የሚጠብቁትን ወታደሮች ኢትዮጵያዊው የሰባተኛ ብርጌድ አዛዥ ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ በሚመጣበት ጊዜ ካለ ምንም ጥያቄ ኬላው እንዲከፈትለት አዘዘ።

* * *

ከኤርትራ የመጣው የሞሳዝጊ ልጅ ለአንድ ወር የሴጀራ መትረየሱን አፈታትና አተኳኮስ ተምሮ ተመለሰ። ኮሎኔል ጃገማ በዚያ ብቻ አላቆመም፤ ስልሳ ኤርትራውያን አርበኞችን አስረኛ ሻለቃ ውስጥ ፀጉራቸውን አስላጭቶ፣ ዩኒፎርም በማልበስ በወታደራዊ ሳይንስ አሰለጠናቸው። ከዚያ ሰላሳዎቹ ወደ ኤርትራ ተመልሰው ገቡ፤ ቀሪዎቹ ሰላሳ ኤርትራውያን ደግሞ ወደ መሃል አገር አዲስ አበባ ገቡ። ከእነሱ ውስጥ አንዱ ብሔራዊ ትያትር ፊት ለፊት ያለው «ላዬን ክለብ» ባለቤት ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ ንጉሰ ነገስቱ መሬት ሰጥተዋቸው ወደ ሻሸመኔ ሄዱ።

ኮሎኔል ጃገማ እነዚህን ኤርትራውያን ሲያሰለጥን ኤርትራውያኑ አብርሃ ወልደ ጊዮርጊስ እና ገብረየሱስ የተባሉት የአካለጉዛይ ተወላጆች አንድነቱን ለማምጣት አብረውት ብዙ ይደክሙ ነበር። ጄኔራል ነጋ ሃይለስላሴ የሚባሉ በኤርትራ የኢትዮጵያ ቆንሲል ሆነው ከእንግሊዞች ጋር ሲሰሩ ከከተማ እንዳይወጡ እንግሊዞች ይከለክሉዋቸው ነበር። ስለዚህ አንድ ጊዜ ጄኔራል ነጋ አዲስ አበባ ተመልሰው ከእነ ደጃዝማች የማነ ጋር ተገናኝተው ኤርትራን ከኢትዮጵያ የማቀላቀሉን እቅድ እንዴት ማፋጠን እንደሚገባ ተመካከሩ። ከዚያ ጄኔራል ነጋ አስመራ፣ ደጃዝማች የማነ ደግሞ ሰናፌ ከእሉት አርበኞች ጋር ለመገናኘት አዲግራት ሄዱ። አዲግራት ደርሰው ሊለያዩ ሲሉ «ችግር የለም፤ እኔ ፈቃድ አለኝ። ጄኔራል ነጋንም እንሸኝ። ደጃዝማች የማነም እግረ-መንገዳቸውን ሰናፌ ሄደው ከሚፈልጓቸው ጋር ይገናኛሉ» ብሎ ሃሳብ አቀረበ፥ ኮሎኔል ጃገማ።

ኮሎኔል ነጋና ደጃዝማች የማነ ደስ አላቸው። ሰባት መኪና ይዘው ኤርትራ ድንበር ደረሱ። ድንበሩ ላይ ያሉት የእንግሊዝ ኬላ ጠባቂዎች ኮሎኔል ጃገማ መኖሩን ሲያዩ ካለ ምንም ጥያቄና ፍተሻ ኬላውን ከፈቱት። በዚህም ኮሎኔል ነጋና ደጃዝማች የማነ የሚፈልጉትን ፈጽመው ተለያዩ።

# ፲፫

## የጃገማ የትዳር ሕይወት

ጃገማ ደሴ በነበረበትና ወደ አዲስ አበባ በሚመላለስበትም ወቅት በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለፍቅር ተንበርክኮ፣ በፍቅሩ አንበርክኳል። ሁለቱ ፍቅረኞች እጅ ለእጅ እየተያያዙ ሲናፈሱ የፍቅር ዜማን ከአዕዋፋት ጋር ሲያዜሙ ከከረሙ በኋላ ለመጋባት ወሰኑ። ጃገማ ፍቅረኛውን ለማግባት ሽማግሌ ሊልክ ሲያስብ «እምቢ ካሉ እጠልፍሻለሁ» አላት። «የለም! አባቴ እንዲረግመኝ አልፈልግም። አባቴ እምቢ አይሉምና ሽማግሌ ላክባቸው» አለችው፥ እሷም።

ስለዚህ በወቅቱ ሊቀ ሊቃውንት ቀፀላ የተባሉትንና ደጃዝማች ከፈለውን ሽማግሌዎች አድርጎ ላከ።

«ቀድሞ ቢጠይቀኝ ኖሮ ልጄን በሰጠሁት ነበር፤ አሁን ለሌላ ሰው ቃል ገብቻለሁ፤ ተቀድሟል» አሉ፥ የልጅቷ አባት። ሽማግሌዎች ከዚያ በፊት አባቷ ለሌላ ሰው ሲድሯት ድግስ ከተደገሰ በኋላ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ጋብቻው አለመፈፀሙን ያውቁ ነበርና፤

«እሷስ ፈቅዳለች?» አሉ ሊቀ ሊቃውንት።

«አልጠየቅናትም፤ የእሷ ፈቃድ ካልሆነ እንድራትም ... ልጃችን የምትፈቅደውን ነው የምንቀበለው» አሉ፥ አባት - ክፍተት ፈጥረው።

«እንግዲያው የእሷን ምርጫ እንስማ» አሉ፥ ሊቀ ሊቃውንት። ከዚያ ቀጠሮ ቆርጠው ተለያዩ። ልጅቷ ያን የምርጫ ዕድል ስታገኝ ፈጣሪዋን ተንበርክካ አመሰገነች፤ በሀሳቧም ወጣቱ የጦር መኮንን የእሷ እንደሚሆን ተማመነች። መልሷን ሳትሰጥ ግን አባቷ በስራ ምክንያት ውጭ አገር ሄዱ። ሻለቃ ጃገማም ተመልሶ ደሴ ሄደ።

አባቷ ከጉዟቸው ተመለሱ። የጃገማ ፍቅረኛ እንክይዋን የማጣት ስጋት ቀንና ሌሊት እንቅልፍ ሲነሳት በወላጆቿ በኩል ለሌላ ባል ልትዳር





መሆኑን ሰማች። ወዲያው ወደ ደሴ ደወለች። «ጃግዬ! ቶሎ ድረስ፤ ሊለያዩን ነው፤ አንተን ከማጣ መረገምን እመርጣለሁ። ስለዚህ ለመጥለፍ ተዘጋጅተህ ና፤ የኔ ጌታ ቶሎ ና ... የአባቴን ባህሪ ታውቀዋለህ፤ ካለው ዝንፍ የሚል አይደለም። እኔ ደግሞ አንተን ማጣት የለብኝም» እያለች በማንባት ነገረችው።

ጃገማ ሰማይ ምድሩ ዞረበት። ቀኑ ደንገዝገዝ እያለ ጨለመበት። ተንቆራጠጠ፤ ተጨነቀ፤ የጀግናው ዐይኖች በእንባ ረጠቡ ... ጃገማ ተርበተበተ። ነገር ግን የገባበት ሃላፊነት ሊያስኬደው አልቻለም። ልጅቱም በእንባ እየታጠበች፣ የደሴን መንገድ እያየች በአዲስ ዓለም፣ በሐሮታ ... ታምር የሰራውን ፍቅረኛዋን በሰቀቀን እስከመጨረሻው ጠበቀችው።

ጀግናው ተሸነፈ፤ እንደ በጋ መብረቅ ከየት መጣ ሳይሉት ነጎድጓድ እያሰማ የሚወርደው ጀግና ለፍቅረኛው ሳይሆን ቀረ። ከቀናት በኋላ አዲስ አበባ ሲመለስ ፍቅረኛው አግብታለች። ጨዋታው አልቆ አዲስ አበባ ጨዋታ እንደሌለበት ስታዲዬም አፏን ከፍታ እረጭ ብላለች። ጀግናው ተንበርክኮ ሀቅ ብሎ አለቀሰ! ያች ፍቅረኛው አሁንም አለች፤ ጃገማ በሰማንያ ሰባት ዓመቱም ፍቅረኛውን ያያታል። ከሁለቱ በስተቀር ግን ይህን የተዳፈነ ምስጢር ማንም አያውቅም። አሁን ቅርብ ቤተሰቦች ናቸው!

* * *

ጃገማ አንድ ወንድ ልጅና አራት ሴት ልጆች አሉት። የመጀመሪያ ልጁን በ1939 ዓ.ም የወለደው በእናቷ ከትግራይ ተወላጇ ከወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሃ፤ በአባቷ ደግሞ ከስመ-ጥሩው አርበኛና የዋግ ሹም ተወላጁ ከሌ/ጄኔራል ሃይሉ ከበደ ከተወለደችው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ሃይሉ ነው። ወ/ሮ ዘውዲቱና ጃገማ እሷ በፀበል፣ ጃገማ በስራ አምቦ ሄደው ነው የተዋወቁት። እንደተገናኙ ልባቸው ተከጃጀለ። ጃገማ ቤተሰቦቿን እየጠየቀ አወቀ። ሊያገባት ፈለገና ዋግ ሹምን አስጠየቀ። ዋግ ሹም የጋብቻ ጥያቄውን ከለከሉት። ጃገማ ለራስ መስፍን ስለሺ «እኔና እሷ ተስማምተን ነበር፤ ዋግሹም ግን ከለከሉኝ» ብሎ ነገራቸው። ራስ መስፍንም ዋግሹም ዘንድ ሄደው «አንተ የዋግ ባላባት ስትሆን ጃገማም የሜጫ ባላባት ነው፤ ለምን ጋብቻ ከለከልከው?» ብለው ተቆጡ። ዋግሹምና ራስ መስፍን ተጋጩ። በኋላ ራስ መስፍን እንዳልተሳካ ለጃገማ ነገሩት።

«ጃንሆይን ፈርቼ እንጂ እቤት ገብቼ ልወስዳት እችል ነበር» አላቸው፥ ጃገማ የዋግሹምና የጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊን ወዳጅነት እያሰበ። «ለጃንሆይ እኔ እነግራቸዋለሁ፤ አታስብ» አሉት ራስ መስፍን። ጃገማና ዘውዲቱ በሴቼንቶ ከከተማ እየወጡ መዝናናት ይወዱ ስለነበር ሁለት ሴቼንቶዎች አዘጋጅቶ ዘውዲቱ ዘንድ ደወለ። ተበሳጭቶ ነበር። አልመጣም ብትለው እንኳን ያለችበት ድረስ ለመሄድ ቆርጧል፤ ለምን ቢሉ ዳግመኛ በምንም ሰበብ የሚያፈቅረውን አሳልፎ ሰጥቶ እጁን አጣጥፎ መቀመጥ አልፈለገም።

«ሃሎ ... ዘውዲቱ ... ነይና ከከተማ ወጣ እንበል?» አላት።
«ምነው ድምፅህ ወፈረ?» አለችው ዘውዲቱ።
«ጉንፋን ነው» አላት - እውነቱን ደብቆ።

መጣች።

«ሆለታ ደርሰን እንምጣ» አላት - እንደ ተገናኙ። ዘውዲቱ ምንም ሳላልተጠራጠረች ተስማማች። እሱና እሷ በአንዷ፣ ሰስቱ ሚዜዎች ደግሞ በሌላ ሴቼንቶ ገብተው ተሳፈሩ። ሆለታ ሲደርሱ ሴቼንቶዋ ጉዞዋን ቀጠለች።

«የት ነው የምትወስደኝ?» አለች ዘውዲቱ ኮስተር ብላ።

«አዲስ ዓለም» አላት ሳቅ ብሎ። ሴቼንቶዋ አዲስ ዓለምን መሃል ለመሃል ሰንጥቃ ከነፈች። ዘውዲቱ እየሆነ ያለው ነገር ገባትና አኮረፈች።

ጊንጪ አባ ዶዮ ቤት ገቡ። «የወዳጄን እህት ልጅ ነዋ! ጎሽ ምርጫ እንዲህ ነው!» አሉና በየዘመዱ ልከው ድል ያለ ሰርግ ተደገሰ። ፌስታ ሆኖ ጉግስ እየተጫወቱ ለስምንት ቀን ጊንጪ ቆዩ። በኋላ ራስ መስፍን ስለሺ «ዋግ ሹምን ከፈራህ እዚያው ቆይ፤ በጃንሆይ በኩል ያለውን ግን ስለ አስረዳኋቸው ችግር የለምና መምጣት ትችላለህ» ብለው ላኩበት። ጃገማና ዘውዲቱ ወደ አዲስ አበባ በመመለሱ ተስማሙ። በዚያ መሰረትም አዲስ አበባ ተመልሰው በማዘጋጃ ቤት ተፈራርመው ጋብቻቸውን ህጋዊ አደረጉት። ኮሎኔል ጃገማ ባለቤቱን አቶ መዳኔ ቤት አደራ አስቀምጦ ወደ ደሴ ሄደ። በአመቱ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ተወለደ። ልጁ የሰላም ዘንባባ ይዞ የመጣ ይመስል ምክንያት ሆኖ ዋግ ሹምና ጃገማ እርቀሰላም ፈጠሩ። ኩርፊያው በጋለ መግባባት ተተካ። ከአራት አመታት የሞቀ ትዳር በኋላ ግን የሻለቃ ጃገማን ልብ እንደ በረዶ የሚያቀዘቅዝ ሃዘን መጣ። የወንድ ልጁን እናት





በ1941 ዓ.ም ነፍሰጡር ሳለች በበሽታ ምክንያት በሞት ተነጠቀ። ጃገማ የሱ የህፃንነት ዕጣ ፋንታ በልጁ በመድረሱ ደነገጠ። ልጁ ልክ እንደ እሱ በሞግዚት አደገ። በኋላ ወደ ውጭ አገር ሄደ። አሁን ልጁ በኖረበት በአሜሪካ በስራ ዓለም በማገልገል ላይ ይገኛል።

ወ/ሮ ዘውዲቱ ከሞቱ ከሶስት ዓመታት በኋላ በእናታቸው ሐማሴን (ኤርትራዊ) የሆኑትን ወይዘሮ አስቴር አስፋውን በ1944 ዓ.ም አገባ። አንድ ልጅ ወለዱ። በትዳርም ለሃምሳ አንድ ዓመታት አብረው ኖረው በ1995 ዓ.ም ወይዘሮ አስቴርንም ሞት አስኮብልሎ ከጃገማ ጎን ወሰዳቸው። ጃገማና ወ/ሮ አስቴር ለሃምሳ አንድ አመታት የትዳር ቆይታ ቢኖራቸውም በመካከላቸው ተፈጥሮ በነበረው አለመስማማትና ሕመም ምክንያት ተለያይተው በቆዩበት ጊዜ ሶስት ሴት ልጆችን ወልዷል። ጃገማ የልጅ ልጆችም አፍርቷል፤ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣ ኤርትራዊ፣ ኢጣሊያዊ ደም አላቸው። አሁን ጃገማ እኩያ ሚስቱ ከጎኑ የሉም። ህልሙ ግን ዘላለም ይኖር ይሆናል። ያስባል ... ያቅዳል ... ይታገላል ...

# ፲፪

## መፈንቅለ መንግስት

ሌፍተናንት ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ወታደራዊ የደንብ ልብሱን ለብሶ የገነተልዑል ቤተመንግስትን ደረጃ ወጣና በሰፊውና ረጅሙ የውጭ በር በኩል ወደ ውስጥ ዘለቀ። የውስጡን በር አንኳኩቶ ከፈተው።

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የማርሻል ማዕረግ የነበረውን የደንብ ልብሳቸውን እንደለበሱ ከሰፊው መስኮታቸው አጠገብ ቆመዋል። የግል ጽ/ቤታቸው በር ተከፍቶ የሰላሳ አራት ዓመቱ የካቢኔው የመረጃ ክፍል ሃላፊ ሲገባ ዘወር አሉ። የካቢኔ የመረጃ ክፍል ኃላፊው ወታደራዊ ሰላምታውን በቀለጠፈና በሚያምር እንቅስቃሴ አቀረበ።

«መጣህ ወርቅነህ?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - ወደ መቀመጫቸው እያመሩ። ሲጠብቁት እንደቆዩ ያስታውቃል።

«እምን ጃንሆይ!» ድምፁ እንደ ሰላምታ አሰጣጡ ቆፍጠን ያለና ደስ የሚል ቃና የነበረው ነው። ሌፍተናንት ኮሎኔል ወርቅነህ የቤተ-ክህነት ትምህርት ያለው፣ ወታደራዊ ስልጠናውን በእንደኝነት ያጠናቀቀ፤ በተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ማስከበር ዘመቻ የሻለቃ ጦር አዝማች የነበረ፤ በዚያ ወቅት ደግሞ በፍጥነቱ፣ በብስለቱ፣ በእንደቡቱ ለዛ ታጭቶ የካቢኔ መረጃ ክፍል ሃላፊ የነበረ ቁልፍ ሰው ነው። ቀደም ብሎም የክብር ዘበኛ መረጃ ክፍል ሃላፊ ነበር።

«ምነው ፈለግኸን?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - ሁሌም እንደሚያደርጉት ሌባ ጣቶቻቸውንና አውራ ጣቶቻቸውን አነካክተው።

«ጃንሆይ! ጦር ሰራዊቱ እያለ የክብር ዘበኛ ወደ ኮርያ በመላኩ የጦር ሰራዊትዎ ቅር ተሰኝቶብዎታል። እንደሚያውቁት በጦር ሰራዊቱና በክብር ዘበኛ መካከል መቀናናት አለ፤ ጃንሆይም ወደ ክብር ዘበኛ ያደላሉ፤ ከጦር ሰራዊቱ በላይ በክብር ዘበኛ ነው እምነት ያላቸው ... በማለት የጦሩ አዛዦችም ጭምር ቅሬታቸው ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ ነው፥ ጃንሆይ!» አለ፥ ኮሎኔል ወርቅነህ።





«ይህ ቅሬታ አዲስ መሆኑ ነው?»

«አዲስ እንኳን አይደለም፥ ግርማዊ ጃንሆይ!»
«እህስ?»
«ቅሬታው አሁን በጣም እየተባባሰ ነው ግርማዊ ጃንሆይ!»
«ስለዚህ ምን አሰብህ?»

«ጃንሆይ! ከመረጃ ክፍል ሃላፊነቴ አንፃር ቅሬታቸውን በዋዛ አልመለከተውም። ቅሬታው ሲያድግ፣ መንግስት ግልበጣም ወደማሰብ ሊያመራ ይችላል፥ ጃንሆይ!»

ንጉሰ ነገስቱ በዝምታ ጥቂት ሰኮንዶችን አሳለፉ።

«ሁኔታው በዝምታ የማይታለፍ ይመስላል» አሉ - ዐይናቸውን ብርሃን በሚያስገባው ሰፊና ረጅም መስኮት ላይ ሰንቅረው።

«እም ጃንሆይ!»

«ጥሩ! ኃላፊነትህንሳ ከምን ጀምረህ መወጣት ፈልገሃል?»

«ጃንሆይ! ተገቢ ባይሆንም ለደህንነት ስንል የጦር ሰራዊት መኮንኖችን ፋይል መመርመር አለብን። ከዚያ አመጽ ሊያነሳሱ የሚችሉትን ከፍተኛ መኮንኖችና የበታች መኮንኖች ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ማዛወር ... በአዲስ አበባና አካባቢዋ ያለውን የጦር ሰራዊት ሃይል መቀነስ ...» አለ፥ ኮሎኔል ወርቅነህ። ንጉሰ ነገስቱ ከዚያ ወጣት መኮንን የቀረበውን ሃሳብ ጥልቀት ምስጥ ብለው እንደገና አሰቡት።

«ጃንሆይ! የምድር ጦርን ቅሬታ ለመቀነስም በተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ማስከበር ተግባር የሚሰማራው ሻለቃ ጦር ከምድር ጦር ቢደረግ ጥሩ ይመስለኛል» አላቸው።

«... ወርቅነህ! የመኮንኖች ፋይል እንድትመረምር፣ ከአቶ መኮንን ሃብተወልድ ጋር እየተመካከርክ አስፈላጊ እርምጃዎችንም እንድትወስድ ፈቅደናል» አሉ። ኮሎኔል ወርቅነህ ትዕዛዙን መቀበሉን፣ ተፈፃሚም ለማድረግ መዘጋጀቱን የሚያረጋግጥ ልባዊ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጥቶ ወጣ።

ኮሎኔል ወርቅነህና የክብር ዘበኛ ክፍለጦር አዛዡ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ዋናው በር መግቢያ ላይ ተገናኙ:: «ወርቅነህ ትዕይንቱ ተጀመረ?» አሉ ጄኔራል መንግስቱ::

«አዎ! ንጉሰ ነገስቱ መርቀው ከፈቱት ...» አለ፥ ቅኔ አዋቂው ኮሎኔል:: «እንቅስቃሴ እንጀምራ?» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - ፈገግ ብለው::

«እኔማ የመጀመሪያ ድርሻዬን አቅርቤ ... የምፈልገውን ድጋፍና ፍቅር አግኝቼ ወጣሁ» አለ፥ ኮሎኔል ወርቅነህ - ፈርጠም ብሎ::

«ተራው የእኔ ነዋ?» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ::

* * *

ጄኔራል መንግስቱ እንንጉሡ ጽ/ቤት ገብተው ወታደራዊ ሰላምታ አቀረቡ::

«ከኮሎኔል ወርቅነህ ጋር ተገናኛችሁ?»

«አላገኘሁትም ጃንሆይ!»

«አሁን እኛ ዘንድ ነበረ ... ስለ ደህንነታችን እየደከመ ነው» አሉ - ስብር ባለ መንፈስ::

«አላገኘሁትም፤ ተላልፈናል ማለት ነው::»

«በል አሁን ወደ አንተ ጉዳይ ግባ::»

«ጃንሆይ! በጦር ሰራዊቱ ላይ ጥርጣሬያችን ጨምሯል ... እነሱም እኛን በዐይነ-ቁራኛ እየጠበቁን ነው» አሉና ጄኔራል መንግስቱ ንግግራቸውን ቆም አደረጉ::

«እያዳመጥንህ ነው፤ ቀጥል::»

«ጃንሆይ! በአሸዋ ገበታው ላይ እንደሚያዩት የትኛው ሃይላችን የትኛውን ቦታ እንደሚቆጣጠር፣ የትኞቹ የኢኮኖሚ አውታሮች በቁጥጥራችን ስር እንደሚውሉ፣ አምስቱን የአዲስ አበባ በሮች በተወርዋሪ ሃይላችን እንዴት





ዘግተን እንደምንይዝ፣ መኳንንትንና ሚኒስትሮችን እንዴት እንደምናሰባስብ፣ በአጠቃላይ አመፅን በፍጥነትና በቀላሉ እንዴት በቁጥጥር ስር እንደምናውል ለማጥናት ይቻለን ዘንድ በአይነ ቁራኛ ከሚከታተሉን ጦር ሰራዊቶች ተሰውረን ሌሊት ሌሊት ለመለማመድ የቀረን የእርስዎ ፈቃድ ነው» አሉ፥ መንግስቱ::

«መንግስቱ! በአሸዋ ገበታው ላይ የነደፋችሁትን ስትራቴጅ አይተናል! ልምምዱንም እንድትጀምሩ ፈቅደናል! ስራችሁን ግን ከወርቅነህና ከመኮንን ጋር እየተመካከራችሁ ቀጥሉ:: ስራችሁ እንዲቃናም ለክብር ዘበኛ ሃምሳ ሺህ ብር፣ ለፖሊስ ሰራዊት ሃምሳ ሺህ ብር፣ ለደጃዝማች አሉላ በቀለ ሰላሳ ሺህ ብር ፈቅደናል» አሉ:: ጄኔራል መንግስቱ የክብር ሰላምታ ሰጥተው ወደ በሩ ሲያመሩ፤

«መንግስቱ?»

«አቤት ጃንሆይ!»

«እስኪ ና ... አንተ ሰራዊት ውስጥ የኮሚኒስት ዕውቀት አለን እያሉ ሰራዊቱን እየበከሉ ያሉ እንዳሉ ሰምቻለሁ:: ለምሳሌ ማነው? እንደ ሻለቃ ቃለክርስቶስ አይነቶች:: ቃለክርስቶስ የወዳጃችን ልጅ ስለሆነ፣ ትህትናና ቅልጥፍናውን አይተን አሜሪካ ብንልከው ከኮሚኒስቶች ፍልስፍና ጋር ተነካክቶ መጣ:: የአንተ ወንድምም ካኪና ቀይ ክራባት ማሰር መጀመሩን ሰምተናል:: የአንተን አንተ ምከር፤ ቃለክርስቶስን እኛ ዘንድ አምጣው» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ::

ጄኔራል መንግስቱ መልስ መስጠት ቢያስቡም ንጉሰ ነገስቱ በዝምታ በሩን ጠረቀሙባቸው::

ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ የአርባ ሶስት ዓመት የተጠራቀመ ሃይል ነበራቸው:: በገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው ወታደራዊ ትምህርታቸውን ተከታትለው የጨረሱት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ በፊት ነው:: ከዚያ አምስቱን የወረራ ዘመናት ከጓደኞቻቸው ከእነ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ጋር በስደት ጅቡቲ፣ በርበራና ኬንያ ቆይተው ነው ከድል በኋላ የተመለሱት:: ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ በወታደራዊ ሥነስርዓታቸውና በማስተባበር ችሎታቸው በንጉሰ ነገስቱ ዘንድ ሞገስ በማግኘታቸው ንጉሰ ነገስቱን፣ አልጋቸውንና ዘውዳዊ ስርዓቱን የሚጠብቀው የክብር ዘበኛ (አንደኛ) ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኑ:: ንጉሰ ነገስቱ ከሚያቀርቧቸው፣

መኝታ ክፍላቸው ድረስ መግባት ከተፈቀደላቸው ጥቂት ሰዎችም አንዱ ጄኔራል መንግስቱ ነበሩ።

ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ቅን፣ ርህሩህ፣ ግፍ የማይወዱ፣ «ከዚህ ጎስቋላ ህዝብ የሚመጠጥ ደም ነው የምናባክነው ንብረትና ገንዘብ» በማለት ይቆረቆሩ የነበሩ መኮንን ናቸው። በዚህ ሰብዕናቸው የንጉሰ ነገስቱን ክብርና ሞገስ፣ ከፍተኛ ሃላፊነትና አመኔታ ቢያገኙም የንጉሰ ነገስቱ ፈላጭ ቆራጭነት መብዛት፣ የፍትህ መጓደል፣ ለውሻ መግዣ ሃያ አምስት ሺህ ብር፣ ለፈረስ ሰባ አምስት ሺህ ብር እየወጣ የሚደረገው ብክነትና የተንደላቀቀ ህይወት ችግር ያነካከተውን ህዝብ ድህነት ማባባሱ ጄኔራል መንግስቱ በንጉሰ ነገስቱ ላይ ጥላቻ እንዲፈጥሩ አነሳሳቸው።

«ባርነት፣ ጭሰኝነት፣ ግፍ ... የአረጀ የአፈጀ አገዛዝ ውጤት ነው። የገማና የተበላሸው ደግሞ አናቱ ነው፤ አናቱ ሲለወጥ ሁሉም ይስተካከላል፤ ያን ጊዜ ጭቆና ይቆማል ...» እያለ፥ መውጫ አጥቶ ስቃይ የፈጠረባቸውን ብሶታቸውን በኮሚኒስታዊ ፍልስፍና መነሻ እያዋዛ ከነመፍትሄው የሚያወጋቸው ወንድማቸው ገርማሜ፥ ሲጤስ ቆይቶ እፍ እንደተባለ ደረቅ ቅጠል ብሶታቸውን፣ ቅሬታቸውን ... እያንቦገቦገ አቀጣጠለው። ጄኔራል መንግስቱ ያን መፍትሄ፣ ያን ለውጥ ... እውን ሆኖ ለማየት ተመኙ።

* * *

ኮሎኔል ወርቅነህ የጦር ሃይል መኮንኖችንን ፋይል መርምሮ እንደጨረሰ የጦር ሃይሎች ትምህርት ሃላፊ የነበሩትን ጄኔራል አማን አንዶምን ወደ ሶስተኛ ክፍለ ጦር ሐረር፣ የአንደኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩትን ጄኔራል ያዕቆብ ገብረልዑልን የሁለተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ አድርጎ ደሴ፣ የሆለታ ጦር ት/ቤት አዛዥን የአዲስ አበባ ጥብቅ አዛዥ ... አድርጎ መደባቸው።

አዲስ አበባ የሚገኙትን አስራ አንደኛና ሃያ ስድስተኛ የጦር ሰራዊት ሻለቃዎች በመጨፍለቅ ከእነሱ የተውጣጣ የጦር ሃይል ሻለቃ ለተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ማስከበር ግዳጅ ወደ ኮንጎ እንዲዘምት አደረገ። በሶማሊያ አካባቢ አሳሳቢ አለመረጋጋት አለ፤ ጦሩም ሳስቷል በሚል ምክንያት ደብረ ብርሃን የነበረው ሁለት ሻለቃ ጦር ወደ ነገሌ እንዲላክ ... ለንጉሰ ነገስቱ አቀረበ። ንጉሰ ነገስቱም የቀረበላቸውን ዝውውር ሙሉ በሙሉ አፅድቀው ወደ ላቲን አሜሪካ በረሩ ...

* * *





ኮሎኔል ጃገማ አዲስ ምደባ እየጠበቀ ነው። የጦር ሰራዊቱ ሃይል መበታተኑ ግን ገርሞታል። በተለይም የአስራ አንደኛና የሃያ ስድስተኛ ጦር ሻለቆች መፍረስ አልዋጥልህ አለው። ለሚቀርባቸው አዛዦች «ለምን ሁለቱ ሻለቆች ሳይፈርሱ አንደኛው ሻለቃ ወደ ኮንጎ እንዲዘምት አልተደረገም» ብሎ ቅሬታ አሰማ።

ጄኔራል መርዕድ መንገሻ ደግሞ ንጉሰ ነገስቱ ለጉብኝት ከመሄዳቸው በፊት «የክብር ዘበኛ ሰራዊት ባለው የወታደርና የመሳሪያ የበላይነት የምሰጠውን ትዕዛዝ አሻፈረኝ በማለት ላይ በመሆኑ ሊያምፁ ይችላሉ ብዬ ተጠራጥሬያለሁና ጃንሆይ አንድ መፍትሄ ያብጁለት» በማለት በሐምሌ ወር 1952 ዓ.ም አቅርበዋል። ንጉሰ ነገስቱ ግን «ለእኛ የሚበጀው መች ጠፋን» ብለው ደብዳቤያቸውን ወደ መሳቢያቸው ወርውረውታል።

* * *

በ1953 ዓ.ም በነበሩት የመጀመሪያ ወራት ጃገማ ችሎት ለመስማት ወደ ቤተ-መንግስት ሲሄድ ሚኒስትሮች፣ የጦር አዛዦች ... ንጉሰ ነገስቱን እጅ እየነሱ የአንዷን ሰዓት ችሎት ለመስማት ሲጠባበቁ ያያል። በዚያች ሰዓት የሃይል አዛዦች አንዱ መኪና ውስጥ እየገቡ ማውራት ማዘውተራቸውን ጃገማ ልብ ብሎ ያያል። ነገር ግን ስለምን እንደሚያወሩ አያውቅም፤ ለማወቅም አይፈልግም። ይጫወቱት የነበረው ጉዳይ የገባው ቆይቶ በታህሳስ ወር 1953 ዓ.ም. ነበር።

ጃገማ ንጉሰ ነገስቱ መረጃ የመሰብሰብ ችሎታቸው «ወደር እንደሌለው» ቢገምትም በትክክል ያወቀው ግን በአንድ አጋጣሚ ነው። አንድ ቀን ንጉሰ ነገስቱ ይፈልጉሃል ተብሎ ወደ ቤተ መንግስት ሄደ።

«ጃገማ! በጠላት ጊዜ የግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ልጆች እንዴት ነበሩ?» አሉት፥ ንጉሰ ነገስቱ።

«ጃንሆይ! በጠላት ጊዜ ተራርቀን ነበር የምንኖረው፤ አሁን ነው ያወቅኳቸው» አለ፥ ጃገማ። ንጉሰ ነገስቱ ምስጢር ሊነግራቸው እንዳልፈለገ በሀሊናቸው መዝነው ተረዱ። ከዚያ ቀን በኋላ ምስጢር ጠይቀውት አያውቁም።

በመሰረቱ ግን ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ የአፄ ምኒልክ ጭፍራ ስለነበሩ ራስ መኮንን ሐረርጌ ሲሾሙ ሞግዚት ሆነው መሄዳቸውን ያውቃል።

ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ጅባትና ሜጫ አውራጃን ሲያስተዳድሩ ጀልዱ ወረዳ አምስት ልጆችን እንደወለዱም ያውቃል። በአርበኝነት ዘመንም ግራዝማች ከማይጨው ዘመቻ ተመልሰው «ሴኮንዶ ማይጨው» ብለው ጣሊያኖች በሰየሙት በአዲስ አበባና ሆለታ መካከል ወልመራ ላይ ከእነ ራስ መስፍን ስለሺና ደጃዝማች ከበደ ብዙነህ ጋር መዋጋታቸውን ያውቃል። ከዚያም በተጨማሪ ጃገማና የግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ልጆች በጋብቻ የተሳሰሩ ድንበርተኞች ናቸው። ጃገማ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን ለመርዳት እንዲሄድ የተላከውን የንጉስ ነገስቱን ደብዳቤ ለጃገማ የሰጡትም ልጃቸው ደጃዝማች ፅንቁ ስላሴ ወ/ዮሐንስ ነበሩ። ወደ ጅማ ሲዘምትም ጅባትና ሜጫ አውራጃ ከነበሩትና አብረውት እንዲዘምቱ ከተደረጉት ባላባቶችና መኳንንት ውስጥ አራቱ የግራዝማች ወ/ዮሐንስ ልጆች ናቸው።

ስለዚህ ጃገማ የሚያውቀውን አላውቅም በማለቱ ምስጢር ለማቀበል ያለመፈለጉ መሆኑን ንጉሰ ነገስቱ ተረዱ። ቢሆንም ግን ንጉሰ ነገስቱ ከወጣቶች፣ ከሴት ወይዘሮዎች፣ ከመኳንንት፣ ከጦር አዛዦች ... ሁሉ ምስጢር ያገኛሉ። በተለይ ጠዋት ላይ በግቢያቸው የአበባ ቦታ ወዲያ ወዲህ እያሉ ሲንሸራሸሩ በየተራ የሚጠጉ የተለያዩ ሰዎች ምስጢርና መረጃቸውን ይነግሯቸዋል። ጃገማ ያን አይቶና ተረድቶ ነው ስለማንኛውም ሃሳብ ከሌላ ሰው ጋር ሲወያይ ሶስተኛ ሰው ባለበት የማያናግረው።

ንጉሰ ነገስቱ በከፋፍለህ ግዛ ዘዴ የጦር ሃይሎቻቸውን ካብ ለካብ የሚተያዩ ጠላቶች አድርገዋቸው ቆይተዋል። ለምሳሌ የጦር ሰራዊት አባል የሆነ ሁሉ ከአራት ኪሎ በላይ ከወጣ አለቀለት ማለት ነው። ክቡር ዘበኛም ከምኒልክ ግቢ በታች ከወረደ ይወገራል። ንጉሰ ነገስቱ መጀመሪያ ላይ የሁለቱን ሃይል አመጣጥነው እርስ በርስ እንዲናከሱ በማድረግ ዳኛው እሳቸው እየሆኑ መቆጣጠር ችለው ነበር። ይህን ዘዴ በአየር ሃይልና በአየር ወለድ፣ በግለሰቦችና በጎሳ መሪዎችም መካከል መጠቀማቸውን ጃገማ ተገንዝቧል።

በክብር ዘበኛ ጦርና በጦር ሰራዊቱ ጦር መካከል የነበረው መናናቅና ጥላቻ ሳይፈታ መቆየቱ ለንጉሱ ጠቅሟቸዋል። በዓላማ ግን ሁለቱም አንድ ነበሩ - ለውጥ ፈላጊዎች። እንዲያውም የጦር ሰራዊት ወታደሮች በዩኒፎርም እንኳን ከክብር ዘብ ሰራዊት ያንሳሉ። ለሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ከፍ ያለ ደመወዝ እየተከፈለ በውጊያ አብረው ከጎን ለሚሰለፉት የጦር ሰራዊቱ መኮንኖች ዝቅተኛ ደመወዝ መከፈሉም ያበሳጫቸው ነበር። ከዚያ ባሻገር ደግሞ የጢሰኛውን ለቅሶ፣ የገዥዎችን ፈላጭ ቆራጭነት፣ የፍትህ መጓደል... የጦር ሰራዊቱን ያበግነው ነበር። ጦር ሰራዊቱና የክብር ዘበኛው ሰራዊት





ህብረት መፍጠር ያልቻሉት በዓላማና ፍላጎት ልዩነት ሳይሆን የአለመግባባታቸው ምስጢር ታውቆ መፍትሄ ባለማግኘቱ ነበር።

ቡተረፈ የካርል ማርክስንና የአዳም ስሚዝን የኢኮኖሚ ፍልስፍና ልዩነት በዩኒቨርስቲ የተማሩ፣ ለወታደራዊ ስልጠና ወደ አሜሪካ አገር ሄደው በኮሚኒዝም ፍልስፍና ፀበል የተጠመቁ መኮንኖች በጦር ሰራዊቱም ሆነ በክብር ዘበኛው ሰራዊት ውስጥ ነበሩ።

የመፈንቅለ መንግስቱን ሙከራ ልፍስፍስ ያደረገው፦ አለመግባባ ቶች ያልተፈቱበት፣ ቅስቀሳ ያልተደረገበት፣ ህዝቡን ያላሳወቀና ከጎኑ ያላሰለፈ፣ ድርጅታዊ መዋቅር ያልነበረው፣ መነሻና መድረሻው ያልታወቀ፣ ለመስዋዕትነት የተጠሩት እንኳን አማፂውን ለይተው ያላወቁበት፣ በችኮላ የተደረገ ውሳኔ መሆኑ ነው። ያ ጅምር ግን የተኛ የመሰለው እሳተ ጎመራ ግለቱን እንደሚጨምር፣መተንፈሻ ፈልጎ እንደሚፈነዳና ርደቱና እንቅስቃሴው ሌላ ትልቅ ነውጥ እንደሚፈጥር የጠቆመ ምልክት ነበር።

# ፲፯

# የመፈንቅለ መንግስቱ ድራማ

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል፡፡ የመጋረጃው መደረቢያ ስለተሸበሸበ የበራው መብራት በቤት ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ መግቢያ በሩ ጋ ካለው የዘበኛ ቤት አንድ ወታደር ካፖርት ለብሶ መሳሪያውን ጭኑ ላይ በማድረግ ቁጭ ብሎ ሰማዩ ላይ ብልጭ ድርግም የሚሉትን ከዋክብት ያያል፡፡ የግቢው አበቦችና የጥድ ዛፎች በለሆሳሱ የንፋስ ዝማሬ ወዝወዝ ... ወዝወዝ ... ይላሉ፡፡ አቶ መኮንን ሃብተወልድ፣ ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ፣ ሜጀር ጄኔራል ፅጌ ዲቡና ኮሎኔል ወርቅነህ እራት ይመገባሉ፡፡

«በዚህ አጋጣሚ የምንወያይበት የስራ ጉዳይ አለ» አሉ መኮንን ሃብተወልድ - በዐይኖቻቸው አራቱንም በፈረቃ እየተመለከቱ፡፡

«በአዲስ አበባ ከተማ የአልጋ ግልበጣ ዕቅድ እንዳለ ተባራሪ ጥቆማ አለ! ሰመሆኑ እናንተስ የሰማችሁት ነገር አለ?» አሉ፥ መኮንን ሃብተወልድ - በነጭ ናፐኪን አፋቸውን እያፀዳዱ፡፡

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ «ምን?» ብለው የሚጠጡት ወይን ትን አላቸው፡፡

«ወንድሜን! ... አይዞህ!» አሉ መኮንን፡፡ ወርቅነህና መንግስቱ ተያዩ ...

«ይሄ መሰረት የሌለው 'በሬ ወለደ' አይነት ወሬ ነው ጌታዬ» አለ፥ ኮሎኔል ወርቅነህ፡፡

«ይመስላል!» አሉ፥ ፅጌና መንግስቱ - በአንድ ቃል፡፡

«ይሆናል! ጥቆማን ግን መናቅ ምንጩን ካጣሩ በኋላ ነው፤ ያ ደግሞ አይጠፋችሁም» ብለው ሳቁ፥ የፀሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ ወንድም፡፡ ሶስቱም ፈገግ አሉ ...





በነጋታው ወደኮሎኔል ወርቅነህ ቢሮ ስልክ ተደወለ፡፡ «ኮሎኔል ... መኮንን ነኝ ... አንተ የካቢኔው መረጃ ክፍል ሃላፊ ነህና በዚያ በአልጋ ግልበጣ ዕቅዱ ጭምጭምታ ያገኘኸው አዲስ መረጃ የለም?» ብለውት መሃረባቸውን አውጥተው ተናፈጡ፡፡

«እስከ አሁን ባለኝ መረጃ መሰረት ስለጠየቁኝ ጭምጭምታ የደረስሁበት ወይም የሰማሁት ነገር የለም፡፡ ካለ ግን በፍጥነት አሳውቅዎታለሁ፡፡»

«ጥሩ ኮሎኔል! 'ያልጠረጠረ ተመነጠረ' አይደል የሚባለው ... ዝምታ ለዓመፀኛ ጊዜ ይሰጣል ... መኖር፣ ማደግ፣ መጠናከር ካለብን በጆሮአችን ብቻ ሳይሆን በዐይናችን፣ በምላሳችን፣ በቆዳችን ማዳመጥ አለብን፡፡ ደግሞ በሬ ካራጁ መዋሉን አትርሳ ... መጠራጠር ለደህንነት ሰው የእጅ ባትሪ ነው፡፡» አሉትና ስልኩን ዘጉት፡፡

ኮሎኔል ወርቅነህ ስልኩ ንግግሩን የሚቀጥለው ይመስል ትክ ብሎ ሲያየው ቆየና ጫን ብሎ ተንፍሶ የስልኩን ቁጥሮች አዞረ፡፡

«ሄሎ ... ጄኔራል መንግስቱ! አቶ መኮንን ሃብተወልድ አሁን ደወለውልኝ ነበር ... አዎ የትናንቱን ነው ደግመው የጠየቁኝ ... ይገርምዎታል፤ ዛሬስ ብለው ብለው 'በሬ ካራጁ ይውላልና ተጠንቀቅ' አሉኝ፤ በእውነት! እንደዚህ አሉኝ ... እርስዎ ተዋቸው ይላሉ፣ እሳቸው መች ለቀቁኝ... እሺ! ሰምቼዎታለሁ ... አዎ ይደውሉልኝ! ... ገርማሜ ደውሎ እየመጣሁ ነው ብሎኛል ...» አለና ኮሎኔል ወርቅነህ የስልኩን እጀታ አስቀመጠው፡፡

ኮሎኔል ወርቅነህ የቀን መቁጠሪያ አጀንዳውን አየው ... ታህሳስ 3 ቀን 1953 ዓ.ም ላይ በቀይ እስኪርብቶ አሰመረበት፡፡

* * *

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ በረንዳ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ የጠዋቷ ጀንበር ብርሃን ደማቅና ውብ ነው፡፡ እፅዋት በነፋሻማው አየር ጥዑም የአዕዋፍ ዝማሬን እያዳመጡ ወዲያና ወዲህ ያሸበሽባሉ፡፡
«... አቶ መኮንን ምን አሏችሁ?» አቶ ገርማሜ ወንድሙን ጠየቀ፡፡

«የአልጋ ግልበጣ ዕቅድ ተባራሪ ጥቆማ አለ አሉን፡፡»

«ምን?» ገርማሜ ፊቱ ልውጥውጥ አለ።

«እኛም የለም ... አልናቸው ... ያመኑን ግን አይመስለኝም» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - እንደ መቆዘም ብለው።

«... ወንድምዬ! ያሰብነው ነገር በዚህ ዓይነት የሚሳካ አይመስለኝም» አለ፥ ገርማሜ - ወደኋላው ለጠጥ ብሎ ራሱን እየያዘ።

«ለምን?» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - አንገታቸውን ወደ እሱ አዙረው በትኩረት እየተመለከቱት።

«ለምን? ... ግልፅ እኮ ነው ... እኔን በሃያ አራት ሰዓት አዲስ አበባን ለቅቄ እንድወጣ ንጉሱ በሄዱበት ሆነው አቶ መኮንን ሃብተወልድን አዘዋል» ብሎ ከተንጋለለበት ተመልሶ ቀና አለና «ጃንሆይ ከውጭ አገር ጉብኝታቸው እንደተመለሱም አንተን ከክብር ዘበኛ፣ ጋሼ ጽጌን ደግሞ ከፖሊስ ሰራዊት እንደሚያነሷችሁ ሰምቻለሁ» ብሎ እንደገና ወደኋላው ተለጥጦ ራሱን በቀኝ እጁ አከከ። «አንተንም ጋሽ ፅጌንም ከስልጣናችሁ ካነሱ ደግሞ ያሰብነው ሁሉ ሳይሳካ ውሃ በላው ማለት ነው» አለና እንባው በአይኑ ሲሞላ አይኑን በመጨፈን እንዳይፈስ ተቆጣጥሮ ወደ መጣበት መልሶ ደፋው።

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ከተቀመጡበት ተነስተው ተንጎራደዱና የበረንዳውን ብረት አጥብቀው በሁለቱ እጆቻቸው እየያዙ «አንተ ወደ ምድብ ቦታህ እንደምትሄድ... እኔና ፅጌ ከስልጣናችን እንደምንነሳ ማን ነገረህ?» አሉ - ገርማሜን እያስተዋሉት።

«ጃንሆይ ቴሌግራም ልከዋል ... የቴሌግራሙን መልዕክት ምስጢር የሚተረጉመው ደግሞ ኮሎኔል ወርቅነህ ነው፤ ታውቃለህ ... ሳገኘው ደንግጧል ... ከዚያ ነገረኝ ... ማታ ራት ስትበሉ የሆነውን እንኳን እኔም አልጠየኩት፤ እሱም አላነሳልኝም» ብሎ አየሩን ማግ አድርጎ እንደ ተቆጣች ድመት ተነፋና መልሶ አምቦለቦለው።

«ያሰብነውማ ይሳካል ...» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - የበረንዳውን ብረት በመሃል እጃቸው ነርተው።

«እዬ!» አለ፥ ገርማሜ - የብሽቀት ፈገግታ እያሳየ። መንግስቱ ወንበራቸውን ወደ ወንድማቸው ጠጋ አድርገው ፊት ለፊቱ እየተቀመጡ «ምን ማድረግ እንችላለን ገርማሜ?» አሉት።





«አንድ አማራጭ ብቻ ነው ያለው። አለበለዚያ ተበታትነን ሁሉም ያበቃል» አለ፥ ገርማሜ - ወንድሙን ትክ ብሎ ማየቱ የሰቀጠጠው ይመስል የዐይኖቹን ኳሶች ግራና ቀኝ እያንከራተተ።

«ምንድን ነው አማራጩ?»

«ኩዴታውን ዛሬውኑ ማድረግ ... ኩዴታው ከዛሬ ማለፍ የለበትም» አለ ድምፁን ረገጥ አድርጎ።

«ቀላል ነገር መሰለህ እንዴ ኩዴታ ማድረግ ... ብዙ መስራት፣ ብዙ መድከም ... አጋዥ ተባባሪዎች ማፍራት፣ ዓላማችንን ማስረዳት አለብን። እንዴት አድርገን ዛሬ ኩዴታ እናደርጋለን?» አሉና ጄኔራል መንግስቱ ካጠገቡ ተነስተው የበረንዳውን የብረት ምሰሶ ተደገፉ።

«ተቀደምና! ተቀደምን ... እኔ ከሄድኩ ... አንተና ጋሽ ፅጌ ስልጣናችሁን ከተቀማችሁ በኋላ ... ምንድን ነው የምንፈጥረው? በዚያ ላይ አቶ መኮንን የሸተታቸውን አናውቅም። ጥያቄያቸው በራሱ የማስጠንቀቂያ ደወል ነው። እስኪ ይታይህ፤ 'በሬ ካራጁ' ... ማለት ምን አንድምታ ያለው ይመስልሃል? ኮሎኔል ወርቅነህ እንዲቀየሩ ያደረጋቸው ከፍተኛ መኮንኖችና የሻለቃ ጦሮች ከምድባቸው ተነስተው መንገድ ላይ ናቸው። እንደ እኔ እምነት ወንድማለም ኩዴታውን ማድረግ ያለብን ዛሬ ነው ... የሚቀረው በተመደበው መሰረት ክብር ዘበኛ ጦርን ቦታህን ያዝ ብሎ ትዕዛዝ መስጠት ነው ...» አለ፥ ገርማሜ - ከተቀመጠበት ተነስቶ ሄዶ ከወንድሙ ጎን በመቆም። ጄኔራል መንግስቱ አንገታቸውን ወደ ቀኝ ዘወር አድርገው ትክ ብለው አዩት። ፀጥታ ሰፈነ፤ ሁሉም በየራሳቸው ሃሳብ ነጎዱ ...

«... በል ተዘጋጅ!»

«ለምኑ?»

«ኩዴታውን ዛሬውኑ እንጀምራለን ...» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ።

* * *

እሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ... ማክሰኞ ታህሳስ 4 ቀን 1953 ዓ.ም ጄኔራል ፅጌ ዲቡ ከሚስታቸው ወንድም ከታምራት ጋር ተሳስመው በጆሮው

«ደህና ሁን ወንድሜ» አሉት። ከዚያ የሚጋፋውን መንገደኛና ሸኝ አልፈው ወደ መኪናቸው አመሩ ...

የቢሮው ስልክ «ቅጭልጭል ...» አለ።

«ሃሎ! ... ሃሎ»

«ሃሎ ... ፅጌ»

«ነኝ፥ ጄኔራል መንግስቱ።»

«ምነው ድምፅህ ደከመ? ራት ልጋብዝህ ነው እኔ እንኳን መደወሌ»

«በምን ሰበብ?»

«ገርማሜ ነገ ወደ ጅጅጋ ይሄዳል። ዛሬ እራት እኛ ጋ ነህ።»

«ጋባዥ ከተገኘ ምን ከፍቶኝ። ያውም ከእናንተ ጋር!»

«መጣሁ ጄኔራል!» ስልኩ ተዘጋ ...

* * *

ጂፕ መኪና ወደ ክብር ዘበኛ ጽ/ቤት አመራች። ከውስጥ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይና ጄኔራል ፅጌ ዲቡ ተቀምጠዋል። ራት ቀረበ።

«የምለምንህን ትፈጽምልኛለህ፥ ጄኔራል ፅጌ?»

«ጄኔራል መንግስቱ! ለአንተ ህይወቴንስ ብትጠይቀኝ እከለክልሃለሁ?»

«ነፍስህንማ ለምን፤ ባይሆን ሽጉጥህን ስጠኝ?» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ፤ ገርማሜ በንቃት እየተመለከታቸው ነው።

ጄኔራል ፅጌ ኮልት ሽጉጣቸውን ከወገባቸው መዘው ለመንግስቱ ሰጡ። መንግስቱ አፈፍ አድርገው ተቀበሉና «ያችን እኔና አንተ የምናውቃትንስ? አምጣታ!» አሉ - ፈገግ ብለው። ጄኔራል ፅጌ ሁለተኛውን





ባሬታ ሽጉጥ ኮታቸውን ገለጥ አድርገው እንደ መጀመሪያው ሳይፈጥኑ አቀበሉ - ለውስጥ አዋቂው ጄኔራል መንግስቱ።

«ጄኔራል ፅጌ አሁን ምክንያቴን ልንገርህ። በውድም በግድም ዛሬ መፈንቅለ መንግስት ማድረግ አለብን!»

«ምን ይዘን ጉዞ? በዚህ በጭራሽ አልስማማም። ንጉሰ ነገስቱ የት አሉ? እሳቸውን ሳንይዝ ምን አይነት ኩዴታ እንፈጽማለን?» አሉ፥ ጄኔራል ፅጌ - አንዴ መንግስቱን፣ አንዴ ገርማሜን እያዩ።

«መቀደም የለብንም ፅጌ። ከጉብኝት ሲመለሱ የአፋቸው ማሟሻ እኔና አንተ ከቦታችን መነሳታችንን መንገር ነው። ያም ሆኖ አሁን ጊዜ የለም፤ መፍጠን አለብን። አንተ ከእነዚህ ሁለት መኮንኖች ጋር ሆነህ አስብበት። እኛ ግን ስራችንን ለመጀመር እንሂድ» ብለው ጄኔራል መንግስቱና ገርማሜ ወጥተው አንድ መኪና ውስጥ ገቡ።

ስምንቱ የመስመረኛ መኮንኖች ደግሞ ተሯሩጠው ወደተዘጋጀ ላቸው መኪና ገቡና መኪኖች ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የመኪና በር ከፍተው ጄኔራል መንግስቱ ወረዱና ወደ ሁለተኛዋ መኪና ሄዱ። መኮንኖቹ ሊወርዱ በሩን ሲይዙ «አትውረዱ፤ አሁን ወደ ግርማዊት እቴጌ ቤት እንሄዳለን ... የእናንተ ድርሻ ትዕዛዜን እየተቀበላችሁ ግዴታችሁን መፈፀም ነው። ሁሌም መሆን የሚገባውን እንደምፈፅም ልትተማመኑብኝ ይገባል። የምላችሁ ገባችሁ?» አሉ። የመስመር መኮንኖች አንገታቸውን ላይና ታች በመወዝወዝ እንደገባቸው ገለፁ።

«ጥሩ! ... ከአሁን በኋላ በመጠየቅ የሚባክን ጊዜ የለም፤ ትዕዛዝ እየተቀበላችሁ መፈፀም ነው» አሉና መለስ ብለው ገርማሜ ወደያዛት መኪና ሄዱ ...

እቴጌ ግቢ ሲደርሱ ጨልሟል። ጄኔራል መንግስቱን የሚጠረጥር የለምና በር ተከፍቶላቸው ገቡ። የመስመር መኮንኖች ጨለም ወደአለው ቦታ እየሄዱ በጥንቃቄ ቆሙ። ድንገት አንድ የግርማዊት እቴጌ አሽከር ብቅ አለ። ጠቀሱት ጄኔራል ...

«አባ ሃናን ጥራቸው!» አሉት፤ አባ ሃና ተጠርተው መጡ።

«አባ ሃና?» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - ፋታ ሳይሰጡ በፍጥነት ተጠግተው።

«ጄኔራል ምነው? አትገባም ነበር?»

«... ጦር ሰራዊትና ፖሊስ ለአመፅ ሳይንቀሳቀሱ አልቀሩም፤ የውጭው መንፈስ ልክ አይደለም። ይህን ልገልጽልዎ ነው አመጣጤ» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - ፍፁም ተረጋግተው። አባ ሃና ግን ደንገጥ ብለው ሪዛቸውን በግራ እጃቸው ላግ አደረጉና «እንግዲያውማ ከሃገር ግዛት ሚኒስትሩ ከራስ አንዳርጋቸው ጋርም ተወያዩበት» አሉ።

«እዚህ አሉ የሃገር ግዛት ሚኒስትሩ?»

«አሉ ... አሉ! ወይ ጉድ!» እያሉ አባ ሃና ወደ ውስጥ ገቡ። ጄኔራል መንግስቱ ወደ ውጭ አየት አድርገው አባ ሃናን ተከትለው ገቡ። መንገድ ላይ ከአገር ግዛት ሚኒስትሩ ከራስ አንዳርጋቸው ጋር ተገናኙ።

«አባ ሃና የነገሩኝ እውነት ነው ጄኔራል?»

«አዎን ጌታዬ ... የውጭው መንፈስ ተበላሽቷል!»

«እንዲያ ከሆነማ ልዑል አልጋ ወራሹም እኮ እዚህ አሉ፤ እሳቸውን ጨምረን ብንመክር አይሻልም?»

«ይሻላል! ...» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - በእንዴ የጣሉት መረብ ሶስት ጠብደል አሳ በመያዙ እየተደሰቱ ...

ልዑል አልጋ ወራሽ ስለተፈጠረው ሁኔታ ከክብር ዘበኛ ሰራዊት አዛዥ እንደበት እንዳዳመጡ «ይህ ከሆነማ ራስ አበበንና አቶ መኮንን ሃብተወልድን እናስጠራቻዋ!» አሉ።

«አ! ... ጥሩ ሃሳብ ነው» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ - ሌላ ሁለት ጠብደል አሳ ደግሞ ሾልኮ ወደ መረባቸው ሊገባ ሲከንፍ ...

«ሃሎ! ራስ አበበ - እቴጌ በጠና ታመዋልና ቶሎ ይምጡ ...» አሉ ልዑል አልጋ ወራሹ።

የጦር ሃይሎች ኤታማዦር ሹሙና የምድር ጦር አዛዡ በተጨማሪ እንዲጠሩ ፈለጉ፥ ጄኔራል መንግስቱ። እነዚህ ሁለቱ ከተጨመሩ የኩዴታው ዕቅድ በእንዴ ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ ስኬታማ ሆነ ማለት ነው - ጄኔራል መንግስቱ ባደረጉት የግምት ስሌት፤ በትክክል ሲሰላ ግን ከፍ ይላል።





«... ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ጄኔራል ከበደ ገብሬም ቢመጡ ጥሩ ነበር» አሉ፥ ጄኔራል መንግስቱ።

«ሶስት ቀኑ፥ ጄኔራል መርዕድ ታሞ እቤቱ ከተኛ» አሉ፥ ራስ አንዳርጋቸው - አልጋ ወራሹንና ጄኔራል መንግስቱን እያፈራረቁ እያዩ።

«እንግዲያውስ ጄኔራል ከበደ ገብሬን ቆይቼ እነግረዋለሁ፤ ይተውት» አሉ፥ መንግስቱ - በጄኔራል ከበደ በመተማመን።

«ራስ አበበና አቶ መኮንን እስኪመጡ እንዴ ወጣ ብዬ መጣሁ» ብለው መንግስቱ በፈጣን እርምጃ ወጥተው ለመስመር መኮንኖች ራስ አበበንና አቶ መኮንንን እንደ ደረሱ ወደተዘጋጀው የመስመር መኮንኖች መኪና ውስጥ እንዲያስገቧቸው ነገሯቸው።

«ምነው ዘገዩ? ...» አሉ፥ ራስ አንዳርጋቸው ራስ አበበና አቶ መኮንን ሲቆዩባቸው።

«ይመጣሉ! ... እስከዚያው ወጣ እያልን እንጠብቃቸው» አሉ መንግስቱ። ሶስቱም ተያይዘው ወጡ ...

ራስ አንዳርጋቸውን አንድ የመስመር መኮንን ወደ መኪናው ሲያስገባ አልጋ ወራሹ፥ ገርማሜና መንግስቱ ወደመጡባት መኪና ገቡ። ድንገት አባ ሃና እየሮጡ መጡ። መንግስቱ ለመስመር መኮንኑ «እሳቸውንም ጨምራቸው» አሉ። መኪኖቹ የግርማዊት እቴጌን ቤት ለቀው ወደ ክብር ዘበኛ ጽ/ቤት ተፈተለኩ ...

* * *

ልዕልት መድፈሪያሽወርቅ አበበ ለከፍተኛ መኮንኖች ስልክ እየደወሉ «... ክብር ዘበኞች ልዑል አልጋ ወራሽንና ራስ አንዳርጋቸውን ... ወስደው የት እንዳደረሷቸው አላውቅም። ኧረ እኔ እየተጨነኩ ነው!» አሏቸው።

የራስ አበበ አረጋይ ባለቤት እመቤት ሆይ ቆንጆት ደግሞ የባለቤታቸውን ኤታማዦር ጄኔራል መርዕድን ደውለው «ጄኔራል መርዕድ! - ቆንጆት ነኝ ... ተሻለህ? ከምሽቱ በአራት ሰዓት በመደወሌ ይቅርታ፤ ቢጨንቀኝ ነው» አሉ።

«ምን ሆኑ? የምንስ ጭንቀት ነው ... ኡህ! ኡህ ... ራስ አበበ ደህናም አይደሉ?» አሉ፥ ጄኔራል መርዕድ።

«ወስደዋቸዋል። ግርማዊት እቴጌ ታመዋልና ድረስ አሉት፥ ልዑል አልጋ ወራሹ። እየተደነባበረ ሄደ። ግርማዊት እቴጌ ዘንድ ስደውል ግን እሳቸውም አልታመሙ፤ ራስ አበበንም አላዩም። ልዑል አልጋ ወራሽና ራስ አንዳርጋቸውም የደረሱበት እስካሁን አልታወቀም። ጄኔራል መንግስቱ ነው አሉ ክቤት ይዟቸው የወጣው ...» እንዳሉ አንዳች ረባሽ ኳኳታ ሰሙ፤ «ሃሎ! ሃሎ ... ጄኔራል መርዕድ» እያሉ ተጣሩ እመቤት ሆይ ቆንጅት።

ጄኔራል መርዕድ እሳቸውን ለመያዝ መኪና ወደ እሳቸው ቤት ሲከንፍ በሀሳባቸው ታያቸው። ሮጠው መኝታ ቤታቸው ገቡ፤ ዩኒፎርማቸውን ለበሱ። ሁለት ቦንብ ደረታቸው ላይ አንጠለጠሉ። ሽጉጣቸውን አቀባበሉና ወደ ሳሎን ሮጡ ... አይሰሙም። የሚረግጡትን አያውቁም። የሚታያቸው እሳቸውን ለመያዝ የሚከንፈው ጅፕ መኪናና ላዩ ላይ የተጠመደው መትረየስ ነው። እየተንደረደሩ በሩ ዘንድ ደረሱ፤ አንድ የማይቀር ነገር ሲያስቡ እንደገና ተመለሱና እጃቸው እየተንቀጠቀጠ በቀለበቶቹ እንደምንም ጣቶቻቸውን እየከተቱ አሽከረከሯቸው። ስልኩ ተጣራ፤ የሚያልፉት ሴኮንዶች አመት መሰሏቸው ...

ስልኩ ተነሳ።

«ሃሎ! ጄኔራል ከበደ ነህ? ... ጉድ ፈልቷል፤ ቶሎ ውጣ ... ጠቅላይ ጦር መምሪያ እንገናኝ ...» ብለው ስልኩን ጠረቀሙት።

ሮጠው መኪናቸው ውስጥ ገቡ። ዘበኛው ደንግጦ የበሩ መቀርቀሪያ ያለበት ጠፋው። ተሳደቡ፤ ተራገሙ። ላባቸው ግንባራቸው ላይ ችፍፍ አለ። እጃቸው ውሃ ሆነ። በሩ እንደምንም ተከፈተ። ቁልቁል በረሩ። አንዲት መኪና ስትመጣ መብራቷን ከርቀት አዩት። ከመንገድ ገባ ብለው የመኪናቸውን መብራትና ሞተር አጥፍተው ቆሙ። ሻለቃ ሃይለማርያም ሴንጮ ከጋቢና ቢቀመጥም አላያቸውም። ሙሉ ወታደራዊ ዩኒፎርም የለበሱ ክብር ዘበኞች ጠመንጃቸውን እንደ ችቦ አቁመው በንቃት ተቀምጠዋል። መኪናዋ አልፋ ሄደች ...

«እሁ!» ጫን አርገው ተነፈሱ ጄኔራል መርዕድ። «ተጫውተውብኝ ነበር!» አሉና መኪናቸውን አስጓርተው አስነስተው እያስነጠሩ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ቁልቁል አከነፏት ...

* * *





ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን ሌሊት ላይ አስጠሩት። ግርግሩን በጽሞና ተመልክቶ «ለምን ቸኮላችሁ? ... ለምንስ አልነገሩኝም ጄኔራል?» አለ ጄኔራል መንግስቱን።

መንግስቱ የኮሎኔል ወርቅነህን ቁም ነገርና ቆፍጣናነት ስለሚያውቁት «ለሆነው ሁሉ ጥፋተኛው እኔ ነኝ ወርቅነህ፤ ለአንተ ቀድሜ መንገር ነበረብኝ፤ አንድ ነገር ግን በእርግጠኝነት ልንገርህ» አሉና ጄኔራል መንግስቱ ኮሎኔል ወርቅነህን ተመለከቱት።

«የተመካከርነው አንድ ላይ ነው። በመጨረሻው ሰዓት ለምን እንቅስቃሴው መጀመሩን አላማከራችሁኝም?»

«... ኮሎኔል አማራጭ አልነበረንም - እመነኝ!» አሉት።

«... አምንዎታለሁ!» አለ፥ ኮሎኔል ወርቅነህ - የተቋጠረ ፊቱን ዘና አድርጎ። «በምክንያት እንደማምን ያውቃሉ ጄኔራል ... ቢዘገይም ምክንያታችሁን ተረድቻለሁ። አሁን 'ነብርን አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም' መሆን አለበት ጨዋታው። ስለዚህ ምን እንዳደርግ ይፈልጋሉ ጄኔራል?» አለ ኮሎኔል ወርቅነህ ትዕዛዝ ለመቀበል ከልብ ዝግጁ ሆኖ።

«እንግዲያው ጊዜ አናባክን ... የመረጃ ሰዎችህ ስልኮችን ከማዞሪያ እንዲያጠፉ አሁኑኑ እዘዝ ... ቀሪ መኳንንቱንና የጦር ሃይል አዛዦችን ከገርማሜ ጋር ሆናችሁ ወደዚህ አሰባስቧቸው» አሉ።

... ሻለቃ ቃለክርስቶስም ተጠርቶ መጣ፤ ለእሱና ለሌሎች የክብር ዘበኛ መኮንኖች «ጦር ሰራዊቱ ዘውዱን ለመገልበጥ አምጾዋል ... የሚሰጣችሁን ትዕዛዝ በአስቸኳይ ፈፅሙ» ብለው አዘዙ፥ ጄኔራል መንግስቱ።

ሻለቃ ሃይለማርያም ደግሞ «ጄኔራል መርዕድ ታሞ ተኝቷል ... እዚህ መጥተህ ተኛ ብለህ ይዘኸው ና» ተብሎ ታዘዘ፡

* * *

ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ከበደ ጠቅላይ ጦር መምሪያቸው ውስጥ ሆነው ስለመፈንቅለ መንግስቱ አካሄድ እየደወሉ ለመጠየቅ፣ የሚፈልጉትን

ለመጥራት ቢሞክሩ ስልኩ ዜሮ ሆነ:: ስለዚህ የጄኔራል ከበደ ሾፌር መልእክት ይዞ ወደኮሎኔል ጃገማ ተላከ::

የኮሎኔል ጃገማ ግቢ በር ተንኳኳ::

«ማን ነህ?» አሉ የብርጌድ አዛዡን የሚጠብቁት ዘቦች::

«ኮሎኔል ጃገማን ነው ... ከጄኔራል ከበደ ተልኬ ነው!» አለ የጄኔራል ከበደ ሾፌር:: ጃገማ ተቀሰቀሰ ... ጃገማ ሽጉጡን አቀባብሎ በጓሮ በር ወጣ:: ጂፕ መኪና ቆሟል:: ጃገማ የጄኔራል ከበደ ገብሬን ሾፌር አየው::

«ምነው? ደህና ...» አለ ኮሎኔል ጃገማ::

«ጄኔራል ከበደ ጠቅላይ ጦር መምሪያ በአስቸኳይ ይምጡ ብለዋል» አለ ሾፌሩ::

«እሺ ... ሂድ፥ እከተልሃለሁ» አለ፥ ጃገማ - ሰዓቱን እያየ፤ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ነው:: ጃገማ ስለተጠራበት ጉዳይ መላልሶ አሰበ፤ «ለምን ፈለጉኝ?» መልስ ባይኖረውም ብዙ ጥርጣሬ ወደ አዕምሮው እየመጣበት ወደ ቤቱ ተመልሶ ገባ:: ከባድ ችግር ስለመኖሩ ግን እርግጠኛ ነበር:: ስለዚህ የጦር ሜዳ ልብሱን ለበሰ፤ ሽጉጡን አቀባብሎ ጠበቀና ከመታጠቂያው ሻጥ አደረገው:: አውቶማቲክ ጠመንጃውን በእጁ ይዙ መኪናው ውስጥ ገባና ወደጠቅላይ መምሪያው ከነፈ . . .

መኪናውን ጠምዝዞ ወደ ጦር ሃይሎች መምሪያ ገባ፤ ቁም ያለው የለም:: ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደን ሲያይ ወደ እነሱ ሄዶ ሰላምታ አቀረበ:: የምድር ጦር ዘመቻ ክፍል አዛዡ ኮሎኔል ታደሰ ብሩም አብሯቸው አለ:: ኮሎኔል ታደሰ በኋላ ታዋቂውን የነጻነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላን ወታደራዊ ሳይንስ ያስተማረ፣ በአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ማንዴላ እንዲመለስ ሲጠራ አንድ አውቶማቲክ ሽጉጥ ከሁለት መቶ ጥይቶች ጋር በግል የሸለመ ነው::

«ለምን ተጠራሁ?» አለ አዛዦቹን እያየ:: «ክብር ዘበኛ መፈንቅለ መንግስት አድርጓል ...» አሉት፥ ጄኔራል መርዕድ::

ቀጥለው ደግሞ «ኮሎኔል ጃገማ! በአስቸኳይ ጦርህን አሰባስብና ሃይል አዘጋጅ» አሉት:: ኮሎኔል ጃገማ የሁለተኛ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ከተሾመ





ገና ሰባት ቀኑ ስለነበር «አልችልም ጌታዬ» አላቸው - አንዴ ጄኔራል ከበደ ገብሬን፣ አንዴ ጄኔራል መርዕድን እያየ::

«ለምን አትችልም?» አሉ፥ ጄኔራል መርዕድ:: «... ጦሩ በካምፕ የተሰባሰበ ባለመሆኑ ጉለሌ፣ አቃቂ፣ ኮተቤ ... ነው ያለው:: የጦር ሰፈር ይሰጠኝ ብዬ አመልክቼ ነበር፤ ነገር ግን አልተሰጠኝም» አለ፥ ኮሎኔል ጃገማ- ጄኔራል ከበደን እያየ::

«እውነት ነው፤ አመልክቶ ነበር» አሉ፥ ጄኔራል ከበደ ገብሬ::

«ኮሎኔል ጃገማ! አሁን በአልሆነው ጉዳይ ላይ አንነጋገርም ... ነገር ግን እንደምንም ብለህ ማድረግ የምትችለው ምንድን ነው?» አሉ፥ ጄኔራል መርዕድ::

«ግቢ ውስጥ አንድ መቶ ሃያ የእግረኛ ጦርና አንድ የሞርታር ሻምበል አለ፤ የብርጌድ አባላትን ግን ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ ካልሆነ ከዚያ በፊት ማሰባሰብ አይቻልም:: አምስት መቶ የሚደርሱ አዲስ ሰልጣኞችን ግን ማዘጋጀት እችላለሁ» አለ፥ ኮሎኔል ጃገማ::

«በል ፍጠን፤ እያንዳንዷ ደቂቃ ህልውናና ደህንነትን የምትጠብቅ ናት» አሉት፥ ጄኔራል መርዕድ:: ወታደሮቹ ከመሳሪያ ግምጃ ቤት ጠመንጃና ጥይት ወሰዱ:: ለአዲስ ሰልጣኞች ባዶ ጠመንጃ ተሰጠ:: ከዚያ ለአስር ሰልጣኝ ወታደር አንድ የሰለጠነ ወታደር እየተመደበ ከራስ ብሩ ቤት ጀምሮ እስከ ባቡር ጣቢያ ያለውን መንገድ በንቃት እንዲጠብቁ፣ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ሌላ ሃይል ወደ ውስጥ እንዳያስገቡ ታዘው ወደ ጥበቃቸው ተሰማሩ::

ቀስ በቀስ ፓትርያርኩ፣ ልዑል ደጃዝማች አስራተ ካሳና ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፣ ሊቀ ጳጳሳቱ ... ጄኔራል ኢሳያስ ወደ ጦር መምሪያው ገቡ:: ከዚያ ጄኔራል መርዕድ ሁሉም ተሰባሰበው ባሉበት «የክብር ዘበኞች በንጉሰ ነገስቱ ላይ አምፀው የመንግስት ባለስልጣኖችን ልዑል አልጋ ወራሹን ሳይቀር አስገድደው በቁጥጥር ስር አውለዋል:: ቁልፍ ቦታዎችንም ይዘዋል:: አምስቱን በሮች ዘግተዋል:: አሁን እኛ የምንጠይቀው የእናንተ አቋም ምን እንደሆነ እንድትገልጹልን ነው» አሉና ጄኔራል ከበደ ከተሰብሳቢዎቹ ተጨማሪ ሃሳብ ለማግኘት ጠየቁ ...

ለትንሽ ደቂቃ ፀጥታ ሰፈነ::

«... እኛ ለንጉሰ ነገስቱ ቃለ መሐላ የገባነው ዘውዳዊ አልጋቸውን ለመጠበቅ ነው:: ስለዚህ በቃለ መሐላችን መሰረት ለንጉሰ ነገስቱ አልጋ መዋጋት ነው ያለብን ...» አሉ፥ ኮሎኔል ጃገማና ጥቂት መኮንኖች:: ጄኔራል መርዕድ የሁለቱን መኮንኖች ሃሳብ እንደሰሙ ፊታቸው ፈካ አለ:: ከዚያ «... ጥሩ! የጦር ሰራዊቱ፣ የአየር ሃይሉ ለዘመቻ እንዲዘጋጅ እናዛለን ... ፓትርያርኩ ህዝቡ በክብር ዘበኛ አማፅያን ላይ እንዲነሳሳ ጥሪ ያድርጉልን፤ የክብር ዘበኛ ጦርም አመፅ አነሳሽ ጥቂት መሪዎችን በቁጥጥር ስር እንዲያውል ጥሪ እናደርጋለን:: የንጉስ ነገስቱን አልጋ ለመጣል የሚተባበር ሁሉ በፓትርያርኩ ይወገዝ ...» አሉ::

«ነገሩ ከመክረሩ በፊት የክብር ዘበኞችን ሃሳብና ውሳኔ እንወቅ:: ተቀራርበን ብንወያይም የሚሉትን ለማወቅ ይረዳናል» አሉ፥ ጄኔራል ከበደ ገብሬ::

«... እነሱ ያሰቡትን እየፈፀሙ እኛ ውጥናቸው እንዲሳካ ጊዜ እንዲያገኙ መፍቀድ የለብንም፤ መነጋገሩም ዋጋ የለውም» በማለት በጄኔራል ከበደ የተከለበሰውን የወኔ ማቀዝቀዣ ውሃ አቅጣጫውን አስተው ደፉት፥ ጄኔራል መርዕድ::

ኮሎኔል ሃይሌ ባይከዳኝና ኮሎኔል ታደሰ ብሩ ደብረ ብርሃን፣ ናዝሬት፣ ሆለታ ... የሚገኘው ጦር ወደ አዲስ አበባ እንዲንቀሳቀስ ብዛቱን፣ መንጓዣውን እንዲያጣሩ ሃላፊነት ተቀበሉ:: ኮሎኔል ጃገማ የብርጌድ ሃይሉን አዘጋጅቶ ለውጊያ በተጠንቀቅ እንዲጠብቅ ታዘዘ ...

* * *

ታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ስድስት ቁልፍ ሰዎች ከወደ ክፍለ ጦር ወደ ክብር ዘበኛ ጽ/ቤት ሄደው ገቡ:: ጄኔራል መንግስቱና ኮሎኔል ወርቅነህ ልባቸው በደስታ እየደለቀች አነጋገሯቸው፤ ልዑል አልጋ ወራሹንም እንዲያነጋግሩ ፈቀዱላቸው ...

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይና በቅርባቸው ያሉት ሰዎች አየር ሃይሉ እንዲያዝ፣ አንድ ተወርዋሪ የክብር ዘበኛ ጦር ወደምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ሄዶ እነ ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደ ገብሬን በቁጥጥር ስር እንዲያውል ጠየቁ:: ሁለቱም ተወርዋሪ ሃይሎች ቢዘጋጁም ጄኔራል መንግስቱ አቅማሙ ....





እንዲያውም ሊቀ ጳጳሱ፣ ደጃዝማች ከበደ፣ ጄኔራል ኢሳያስ ... ወደ ክብር ዘበኛ ጽ/ቤት ሲመጡ የጄኔራል መርዕድ ነገር እንደሚያበቃለት በማመን ጄኔራል መንግስቱ ሃይላቸውን ባለመበታተናቸው ደስ አላቸው:: በሌላ ጎን ደግሞ በክብር ዘበኛ በኩል ከጄኔራል መርዕድ ጋር የሚደራደሩ አራት ቁልፍ ሰዎች ተዘጋጁ::

አመፁ ዘገምተኛና ጥራት የጎደለው መሆኑ፣ ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ አለመኖሩ፣ የተቃዋሚ ሃይሎችን ጉልበት በደራሽ ምት ማሽመድመድ አለመቻሉና የአመፁ ፍፃሜ በትክክል አለመታወቁ ... ከአመጹ መሪዎች መካከል የመፈንቅለ መንግስቱን ስኬታማነት የሚጠራጠሩ እንዲፈጠሩ አደረገ::

ጄኔራል መንግስቱ ጄኔራል መርዕድ ወደ ውይይት እንዲመጡ በአልጋ ወራሹ፣ በፓትርያርኩ ቢያባብሉ፤ «እኛ ደም እንዲፈስ አንፈልግም፤ እነሱ ናቸው» እያሉ የሚቻላቸውን ሁሉ ቢጥሩ፤ አስመራ በነበሩት ጄኔራል አቢይ በኩል ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጋር ግንኙነት የጀመሩት ጄኔራል መርዕድ የሚሰጡት መልስ አንድና አንድ ሆነ - እምቢታ:: በዚህ መሃል ከሶስተኛ ክፍለ ጦርና ከሁለተኛ ክፍለ ጦር አንድ አንድ ሻለቃ ታንከኛ፤ ከናዝሬት፣ ከደብረ ብርሃን፣ ከጅማ ... አጠናካሪ ጦር በአስቸኳይ እንዲላክና ለጄኔራል መርዕድ ሪፖርት እንዲያደርግ መታዘዙን የክብር ዘበኛ መረጃ ክፍሎች ጠለፉ:: ሌላ ስጋት ...

ያም ሆኖ ግን አማፅያኑ እስከ ቀኑ አምስት ሰዓት ድረስ አስራ ሰባት ከፍተኛ ባለስልጣናትን፣ ሁለት ደጅ ጠኝዎችን በክብር ዘበኛ ጽ/ቤት ውስጥ በቁጥጥር ስር አዋሉ:: የክብር ዘበኛ መኮንኖች ቁልፍ ቦታዎችን ከመቆጣጠር ባሻገር በተጠንቀቅ ትዕዛዝ እንዲጠባበቁ ተደረገ:: የማጥቃት ስትራቴጂም ተነድፎ አመራር ሰጭዎች ተመደቡ:: የአመፁ የበላይ አስተባባሪም ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ሆኑ ... እነ ጄኔራል መንግስቱም ሆኑ ጄኔራል መርዕድ የየበኩላቸውን ስልት ሲያወጡ ውጥረቱ እንደተካረረ ጀንበር አዘቅዝቃ ተሰወረች::

ንጋት አካባቢ ጄኔራል መንግስቱ፣ ኮሎኔል ወርቅነህ፣ አቶ ገርማሜ ከሻለቃ ቃለክርስቶስ ቢሮ ተሰብስበው «ማንን መሪ እናድርግ?» የሚል አጀንዳ ቀረበ:: እስከዚያ ወቅት ድረስ ግምት እንጂ እየሆነ ያለውን በትክክል የማያውቁት ቃለክርስቶስ «ለምን መሪ እንመርጣለን? ...» አሉ:: ከመለስተኛ ኡተካራ በኋላ ራሳቸው ሻለቃ ቃለክርስቶስ መሪ ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች መርጠው አቀረቡ::

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ልዑል አልጋ ወራሹ ወዳሉበት አመሩ::

«... የኢትዮጵያ ህዝብ እርስዎን መሪ፣ ልዑል ራስ እምሩን ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እንድትሆኑ መርጧችኋል ... ምርጫውን ይቀበላሉ?» አሉ ጄኔራል መንግስቱ::

«... እኔም እስከ ዛሬ ድረስ የምጠብቀው ይኸው ነበር:: የህዝቡን ምርጫ በደስታ ተቀብያለሁ! የኢትዮጵያ ህዝብም በወሰነልኝ ስልጣንና በሚቆርጥልኝ አበል አስተዳድራለሁ ...» አሉ፥ ልዑል አልጋ ወራሹ - ፊታቸው ፈካ ብሎ::

ጄኔራል መንግስቱን ሳቅ አፈናቸው ...

ቀጣዩ የአመፅ ሂደት ከተሳካ አዲስ መንግስት ሲመሰረት ከክብር ዘበኛ፣ ከምድር ጦር፣ ከአየር ሃይል፣ ከፖሊስ ሰራዊት የሚወከሉ ሃያ አባላት ያሉት ጁንታ ለመመስረት ተስማሙ:: ለካቢኔ አባልነትም ከምሁራን መካከል በትምህርታቸው፣ በልምዳቸውና በችሎታቸው 21 ሰዎችን ለመምረጥ ተስማሙ:: የጥበቃ ትዕዛዝም ለአንደኛና ለሁለተኛ ብርጌድ፣ ለሶስተኛ መድፈኛ ሻለቃ ተላለፈ! የቃኘ፣ የትራንስፖርት፣ የመሃንዲስ ሻምበል ተመደበ:: ዋናው የትዕዛዝ መስጫ ማዕከልም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ግቢ እንዲሆን ተወሰነ::

* * *

ረቡዕ እለት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ ጄኔራል ኢሳያስ እነ ጄኔራል መርዕድን «ምን ትጠብቃላችሁ? ክብር ዘበኛ ሊወጋችሁ ተዘጋጅቷል እኮ!» አሉ:: ይህ ማሳሰቢያ በሀሳብ የሚናውዙትን ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደን እባኖ አስነሳቸው:: አመፁን ለመስባበር የጦር ስልቶች ተነደፉ:: ወደ ቤተመንግስት ለውጊያ የሚንቀሳቀሰው የጦር ሰራዊት በሁለተኛ ብርጌድ አዛዥ በኮሎኔል ጃገማ እንዲመራ የምድር ጦር አዛዡ አዘዙ:: ለጥቃት የሚንቀሳቀሰው ሠራዊት ትልቁ ግዳጅ፥ በተሰለፈበት ሁሉ ሽንፈት ገጥሞት ለማያውቀው ጀግና ለኮሎኔል ጃገማ ተሰጠው:: ኮሎኔል ይልማ ሺበሺ ደግሞ የእሱ ምክትል ሆነው ጦሩን እንዲመሩ ተመረጡ:: ከምድር ጦርና ከመከላከያ ሚኒስቴር ውጭ ያለው ጦር ሰራዊት ሁሉ በ2ኛ ብርጌድ አዛዥ በኮሎኔል ጃገማ ስር ናችሁ የሚል መመሪያ ተላለፈ::

በፓትርያርኩ የተፈረመው ጥሪና ውግዘት ለህዝቡ ተበተነ:: ያን ጊዜ 'ጦር ሃይሉ በንጉሰ ነገስቱ ላይ አምጿል' እየተባሉ ግራ ተጋብተው በግዳጅ መስመራቸው ተሰልፈው የነበሩት የክብር ዘበኛ ጦር አባላት «የአመፀው





የጦር ሃይሉ ሳይሆን እኛ ኑረናል» እያሉ «ለምን ሳይነገረን ቀረ?» በሚል ምሬት ግዳጃቸውን መወጣቱን እየተውት ሄዱ:: በቀሩት ላይም መከፋፈሉ ቀጠለ::

ታህሳስ 6 ቀን 1953 ዓ.ም ንጋት ላይ የተወሰኑት ውሳኔዎች ተግባራዊ ሆኑ:: የጁንታው አባላት ስም ዝርዝር ተፃፈ! የካቢኔ አባላት ዝርዝርም ታወቀ! የጥበቃ ትዕዛዙም ተግባራዊ ሆኖ ከትዕዛዝ መስጫ ማዕከሉ የምድር ጦርን መምሪያ በቁጥጥር ስር የሚያውል ተወርዋሪ ሻምበል ተላከ::

እነ ሻለቃ አዲስ ዓለም የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች የመፈንቅለ መንግስቱን ዓላማና ግብ እና እየተደረገ ያለውን ሁሉ እንዲያውቁ፣ ተማሪዎች መፈንቅለ መንግስቱ የራሳቸው እንደሆነ በማመን የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ፣ በምድር ጦር መምሪያ ምሽግ ተቀምጠው ለውጡን የሚቃወሙትንም እንዲያወግዙና ህዝቡን እንዲቀሰቅሱ ጥሪ አደረጉ:: ተማሪዎችም «ሆ!» ብለው መፈክራቸውን ይዘው ለውጡን በመደገፍ ወጡ! ሌላው ቀርቶ ወደ ምድር ጦር መምሪያም ሄዱ:: መጠጋት ግን ተሳናቸው::

የአልጋ ወራሹ ንግግር በቴፕ ተቀርፆ ለህዝቡ በሬዲዮ እየተደጋገመ እንዲሰማ ተደረገ:: ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ጄኔራል መርዕድን ተክተው የጦር ሃይሎች ኤታማዦር ሆነው እንደተሾሙ በሬዲዮ ተላለፈ:: በሰራዊቱ ይወደዱ የነበሩት የጄኔራል ሙሉጌታ መሾም ሰራዊቱን እንደሚያስደስተውም ተገመተ:: በመፈንቅለ መንግስት አድራጊዎች በኩል በአሸናፊነት ለመወጣት የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ቢሞከርም 'ካለ ንጉሰ ነገስቱ ህልውና ኢትዮጵያ መኖር አትችልም' የሚለው የህዝብ ፍርሃትና ተቃውሞ ግን ጥረቱን ሁሉ እያቀጨጨ አኮሰመነው::

ሐሙስ ታህሳስ 6 ቀን 1953 ዓ.ም ከቀኑ ሰባት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ላይ የክብር ዘበኛ ተወርዋሪ አጥቂ እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ ሲሄድ ቆይቶ በአንደኛ ክፍለ ጦር መምሪያ የሞርታር ተኩስ ከፈተ! እነ ኮሎኔል ጃገማ ሲከላከሉ ውለው አደሩ::

* * *

የምድር ጦር አዛዥ ጄኔራል ከበደና ኤታማዦር ሹሙ ጄኔራል መርዕድ በ1952 ዓ.ም የጦር ሰራዊት ሃይል በሚገኝባቸው ቦታዎች እየተዘዋወሩ «አርጅታችኋል» በሚል 830 የጦር ሰራዊት አባላትን በጡረታ

አግልለው ነበር። እነዚህ የጦር ሰራዊት አባሎችም «ጡረታ የወጣነው ባግባቡ አይደለም፤ ፊታችን እየታየ ነው ጡረታ የተባልነው» በሚል አዲስ አበባ መጥተው ክርክር ላይ ነበሩ። ንጉሰ ነገስቱም በጉዳያቸው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ እስከ ሰኔ ወር ደመወዝ እየተቀበሉ እንዲቆዩ አዘዙ። ሰኔ ላይ ደግሞ እስከ ታህሳስ ይቆዩ ተባለ። ታህሳስ ላይ መፈንቅለ መንግስቱ ሲደረግና ልዑል አልጋ ወራሹ ያስነገሩትን አዋጅ ሲሰሙ ወደ ምድር ጦር ዋና መምሪያ ሄዱና ሪፖርት አደረጉ። ኮሎኔል ጃገማ እነዚያ የጦር ሰራዊት አባሎች የጦር ስልት አዋቂና የካበተ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ስለተረዳ ለስምንት መቶው የጦር ሰራዊት አባላትና ለሰላሳ መኮንኖች መሳሪያና ጥይት ከግምጃ ቤት ወጥቶ እንዲሰጣቸው አደረገ።

ይሁን እንጂ ይህ ውሳኔው ከመቅጽበት አለቆቹ ጆሮ ደረሰ፤ «ጡረታ ለወጡትና ለተከፉት የጦር አባላት ጃገማ ጠመንጃ አድሏቸዋልና የበለጠ ችግር እየፈጠረ ነው» ብለው ለጄኔራል ከበደና ለጄኔራል መርዕድ ወነጀሉት። ኮሎኔል ጃገማ ተጠርቶ ጡረታ ለተባሉት ያከፋፈለውን መሳሪያ በአስቸኳይ እንዲቀበል ታዘዘ። ትእዛዙን ተቀብሎ ሄደ።

'ፊታችን እየታየ ነው ጡረታ የተባልነው' ያሉት የጦር ሰራዊት አባሎች ይሸልላሉ፤ ያቅራራሉ፤ «የጠቅል አሽከር፤ እኔ ክንዴን ሳልንተራስ ማነው የሚደፍርህ... » ይላሉ። ጃገማ ቆም ብሎ አስተዋላቸው ... እንደዚያ በወኔ የሰከሩትንና ለውጊያ ዝግጁ የሆኑትን የሰራዊት አባላት ከነበሩበት ለማውጣት መሳሪያ መልሱ ማለት እሳት ለማጥፋት ቤንዚን እንደመጨመር ነው። ጃገማ ጥቂት አሰበ። ከዚያ «ስማችሁ!» ሲል ፀጥ ብለው ቆሙ ... «እንግዲህ አትችሉም የተባላችሁ እናንተ አይደላችሁም? ... ዛሬ ችሎታችሁን የማስመስከሪያ ቀን ናት ...» አላቸው። ያን ሲሰሙ እንደ ሰጋር በቅሎ እየሰገሩ ፉከራውን፣ ሽለላውን አቀለጡት።

ወደ አዛገቹ ተመልሶም «በእነዚህ ሰዎች ለሚመጣ ችግር ሁሉ ሀላፊው እኔ ነኝ ...» አለ። አዛዦችም ሃሳቡን ተቀብለው ፈቀዱ። ኮሎኔል ጃገማ ሙሉ ሻለቃ ጦር አገኘ። ከደብረ ብርሃንና ከሆለታ በመጡት የሰራዊቱ ሃይሎችም ተጠናከረ።

አርብ ታህሳስ 7 ቀን 1953 ዓ.ም ታንከኞች መጡ። ጡረተኞች ከብርጌዱ ጦር ጋር ተቀላቅለው ተጠናከሩና በኮሎኔል ጃገማ ትዕዛዝ ማጥቃት ጀመሩ። የአየር ሃይል አዛዡ የጄኔራል መርዕድን ትዕዛዝ «እምቢ» ወይም «እሺ» ሳይሉ ወላወሉ። አሜሪካዊው ጄኔራል ሊንደል የሃይል ሚዛኑ ወደ አጋደለበት በማበር የንጉሰ ነገስቱን ደጋፊዎች በውጊያ እንዲያግዙ ጠየቃቸው። «ጥያቄዬን ካልፈፀማችሁ ግን ከጂዳ የስኳድሮ ተዋጊ አውሮፕላን





ከአሜሪካ ቤዝ ጠይቄ የአየር ጥቃቱ እንዲፈፀም አደርጋለሁ» አለ። ያን ጊዜ የአየር ሃይል አብራሪዎች ቢ17 ተዋጊ አውሮፕላኖችን እያበረሩ የክብር ዘበኛ ጽ/ቤትን በመትረየስ መደብደብ ጀመሩ ...

የክብር ዘበኛን ጦር ውጊያ እየተቋቋመ ኮሎኔል ጃገማ ወደ ፊት ገሰገሰ። በጉዞው ላይ የሚያጋጥመውን ወደ መምሪያ እዙ ሲያስተላልፍ መስመር ላይ የሚቀርቡት ጄኔራል መርዕድ ብቻ ነበሩ። ኮሎኔል ጃገማ የምድር ጦር አዛዡን ጄኔራል ከበደንም ማነጋገር ቢፈልግም ኤታማዦሩን «እርስዎን አልፈልግም፤ ጄኔራል ከበደን ያቅርቡልኝ» ማለት ባለመቻሉ ወደፊት ይገሰግስ የነበረው የደረሰበትን ለጄኔራል መርዕድ በማሳወቅ ብቻ ነበር።

የመፈንቅለ መንግስቱ አዛዦች በአየር ድብደባውና በውጊያው ጥንካሬ መካከል የማዘዣ ጣቢያቸውን ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግስት ለማዛወር ወሰኑና ሲጓዙ መንገድ ላይ ህዝቡ የንጉሰ ነገስቱን ስም እየጠራ አላሳልፍ አላቸው። ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ በድርጊቱ አዝነው «ለራሱ የሚበጀውን የማይለይ ህዝብ ...» በማለት ምሬታቸውን ገለፁ።

ኮሎኔል ጃገማ የእመፁ መሪዎችና ያገቷቸው ሰዎች ገነተ-ልዑል ግቢ እንዳሉ ከመረጃ ምንጮቹ አረጋገጠ። ከሆለታ የመጣው ጦር በፒያሳ አድርጎ በሰባ ደረጃ በመውጣት ወደ ቤተ መንግስቱ ተጠጋ። ከጦር መምሪያ የተንቀሳቀሰው በአራት ኪሎና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በኩል ወደ ቤተመንግስቱ ተጠጋ። የአየር ድብደባው በቤተ መንግስቱም ቀጠለ። እነ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ይረዳናል ያሉት ፈጥኖ ደራሽ በኮሎኔል ታደሰ ብሩ ትዕዛዝ በክብር ዘበኛ ጦር ላይ አፈሙዙን አዞረ ...

ሁሉም ለእነ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ተስፋ አስቆራጭ ሲሆን የመጨረሻ ስብሰባ አደረጉ፤ «... ህዝቡ በንጉሰ ነገስቱ ረድኤት ብቻ የሚኖር ሆኗል። ሙከራው ባይሳካም ለመጭው ትውልድ መንገድ ከፍተናል ...» እያሉ ጄኔራል መንግስቱ፣ አቶ ገርማሜ፣ ኮሎኔል ወርቅነህ በጀግንነትና በምሬት ንግግር አደረጉ። «የኢትዮጵያ ህዝብ የተለምንለትን ፈር ተከትሎ ዓላማውን ከግብ እንደሚያደርስ እናምናለን!» ብለው እንደ ነቢይ ወደፊት የሚሆነውን ተንብየው በክብር መዝገቡ ላይ ፈረሙበት ...

እስር ለሚደርሱ የጁንታው አባላት በአሜሪካው አምባሳደር በሚስተር ሪቻርድ በኩል ቀርቦ የነበረው ጥገኝነት የማግኘት ጥያቄም በጄኔራል መርዕድና በጄኔራል ከበደ ውድቅ ሆነባቸው። ውጊያውም መፋፋም ቀጠለ። ሳያስቡት ከቤተሰባቸው የተነጠሉት የመፈንቅለ መንግስት

እስተባባሪዎችም ወደ እነሱ እየከነፈ የነበረውን ሞት ለመጋፈጥ የመጨረሻ ውሳኔ አድርገው ወደ ውጊያው ገቡ። ሜጀር ጄኔራል ፅጌ ዲቡ ግራ እንደተጋቡ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ሞተው ተገኙ። ኮሎኔል ወርቅነህ ከቤተመንግስት ወጥቶ ሲያመልጥ ቀጨኔ አካባቢ ሲደርስ ተኩስ ተከፍቶበት ተሰዋ።

* * *

የስመ ጥሩው አርበኛ የጀግናው ሃይለማርያም ማሞ ልጅ ሻምበል ደረጀ ሃይለማርያም ሐረር ሰስተኛ ክፍለ ጦር ሆኖ የክብር ዘበኛን አመፅ ሲሰማ ከድሬዳዋ ናዝሬት በባቡር መጥቶ ናዝሬት ከሚገኘው ታንከኛ ክፍል ገብቶ አንድ «አውቶብላንድ» ታንክና የሚያሽከረክረውን አስር አለቃ ይዞ ወደ አዲስ አበባ ከነፈ። ጎፋስ ስልክ ላይ ጠባቂዎች ነበሩ። እንደደረሰ!

«እናንተ እነማን ናችሁ?» አለ፥ ሻምበል ደረጀ።

«ክብር ዘበኞች ነን» አሉት።

«የማን ደጋፊ ናችሁ?» ብሎ ጠየቀ፥ ሻምበል ደረጀ።

«የንጉሰ ነገስቱ» አሉት።

«እስኪ ፎክሩ?»

«የጠቅል አሽከር ...» ሲሉ ደስ ብሎት ወደ ምድር ጦር መምሪያ ተፈተለከ። የሃይለማርያም ማሞ ልጅ ጄኔራል መርዕድ ዘንድ ሄደ። «ጄኔራል! እኔ የሃይለማርያም ልጅ እነዚህን እጅ ነካሾች ከገቡበት ገብቼ እይዛቸዋለሁ! ለግዳጅ ተዘጋጅታችኋል?» አለ በወኔና ደም ፍላት። «ለጥቃት የሚንቀሳቀሰው ሃይል አዛዥ ኮሎኔል ጃገማ ነው፤ ሂድና እሱ ዘንድ ሪፖርት አድርግ» አሉት፥ ጄኔራል መርዕድ። የጀግናው አርበኛ ልጅ እንደ ግስላ እልህ እያዳፋው ሥነስርዓት እየጠበቀ መንተት አልፈለገም፤ መሄድ ... መፍጠን ... ሁሉንም በቁጥጥር ስር ማድረግ አለበትና ጊዜ ሳይገድል አውቶብላንዱን አዙሮ መጀመሪያ እስጢፋኖስ ቤተክርስትያን ሄዶ ተሳለመ፤ ከዚያ ወደ አመፀኞቹ ተፈተለከ ...

ታችኛው ግቢ ሄደ። አድፍጠው የነበሩት የክብር ዘበኛ አባላት መልስ አልሰጡትም። ከዚያም በቀጥታ ወደ እልፍኝ ወራሹ ግቢ አመራ። መንገድ ላይ ወታደሮች አገኘ። «እናንተ የማናችሁ?» አላቸው። «እኛ የአልጋ ወራሽ





ጠባቂዎች የሆን የጦር ሠራዊት አባላት ነን» አሉት። ተግባቡ። የነበሩትን የአንድ ሻምበል ጦር አባላት «ተከተሉኝ» ብሎ ወደ ገነተ ልዑል ግቢ አመራ። ወደ ግቢው በር ሲደርስ ከውስጥ ተተኮሰበት። ተኩስ ሲከፈትባቸው ተከትለውት የነበሩት የጦር ሠራዊት አባላት በያሉበት ተኙ። እነሱ እንደተኙ ሻምበል ደረጀ ሃይለማርያም የተዘጋውን በር በአውቶብላንድ ታንኩ ገንጥሎ ወደ ውስጥ ገባ። ተኩሱ ቆመ።

አውቶብላንዱ በቀጥታ ጃንሆይ ከመኪና ወርደው ወደሚሄዱበት የቤተመንግስቱ ደጃፍ ደርሶ ቆመ። ከታንኩ ሳይወጣም፤ «ሻምበል ደረጀ ሃይለማርያም ነኝ እጃችሁን ስጡኝ?» አለ። አማፅያኑ ከወታደራዊ ስልት ውጭ በሆነ ጀብደኝነቱ እየተገረሙ «... እጅ ለመስጠት አንተን ነበር የምንጠብቀው!» ብሎ ከመሃላቸው አንዱ እጅ እንደሚሰጥ ጠመንጃውን አጋድሞ ብቅ አለ። የጀግናው አርበኛ የሃይለማርያም ማሞ ልጅ ታንኩን ከፍቶ ዘሎ ወጣ። ከመቆሙ የተኩስ እሩምታ ተተኮሰበት። ሻምበል ደረጀ ምስኪኑ የስመ-ጥር አርበኛ የጦሩ ገበሬ የሃይለማርያም ማሞ ልጅ አንርቶ ወደቀ።

ታንኩ ዞረና አስር አለቃው ሬሳውን እንደምንም ብሎ ጎትቶ አውቶብላንዱ ላይ ጭኖ በማርቆስ በር ወጥቶ ሲሄድ ኮሎኔል ጃገማ ከሚመራው ጦር ጋር ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገናኙ ... «የአስር አለቃውን ቃል ተቀበሉ! የሻምበል ደረጀ ሬሳ ወደ ክፍለ ጦር ይሂድ፤ ታንኩ ለግዳጅ ይሰማራ» ብሎ አዘዘ፥ ኮሎኔል ጃገማ።

በኮሎኔል ሽፈራው የሚመራው የሆለታ ጦር አባላት ከጃገማ ጋር በተመካከሩት መሰረት በደጃች ውቤ ሰፈር በማለፍ በአፍንጮ በር በኩል ወደ ገነተ-ልዑል ገቡ። ኮሎኔል ጃገማ ታንኩቹን አስቀድሞ በአሁኑ 'የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና በር' በሚባለው በር በጅፕ መኪናው ወደ ውስጥ ዘለቀ። እነ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ የጦሩን መቃረብ ሲያዩ ያገቷቸውን ሚኒስትሮች እና መኳንንት ረሽነው በአፍንጮ በር በኩል ወጥተው አመለጡ።

በኮሎኔል ጃገማ የሚመራው ጦር ቤተመንግስቱን ሲቆጣጠር ደጃዝማች በዛብህ (የራስ መስፍን ስለሺ ወንድም) እና ራስ አንዳርጋቸው ልብሳቸው በጥይት ተቀዳዶ አገኛቸው። ጄኔራል መኮንን ደነቀ በስምንት ጥይት ተመትተዋል። በጥይት ተመትተው የነበሩት ራስ አበበ እያጣጣሩ ሆስፒታል እንደደረሱ አረፉ። ጄኔራል መኮንን ግን ዳኑ። ልዑል አልጋ ወራሹና ልዑል ራስ እምሩ ሃይለስላሴም ምንም ሳይሆኑ ከቤተ መንግስቱ ፎቅ ተገኙ። ኮሎኔል ጃገማ አልጋ ወራሹን፣ ራስ እምሩን፣ ራስ

እንዳርጋቸውን፣ ደጃዝማች በዛብህን ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ወሰዳቸው:: ከዚያም ልዕልት ተፈራሽወርቅን በመያዝ ወደ ግርማዊት እቴጌ መኖሪያ ሄዶ ግርማዊት እቴጌን፣ ልዕልት ተናኘወርቅንና ንጉሳውያን ቤተሰቦችን በሙሉ በመሰብሰብ ወደ ራስ እንዳርጋቸው ቤት የቀድሞው የስራ ሚኒስቴር አጠገብ ወሰዳቸው:: ከዚያም ኮሎኔል ጃገማ ንጉሳውያን ቤተሰቦችን ከሶስተኛ ብርጌድ በመጣው ጦር አስጠብቆ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ጠቅላይ ጦር መምሪያ ሲሄድ ጄኔራል መርዕድ በደስታ እጃቸውን ዘርግተው ተቀበሉት፤ ጄኔራል ከበደ ግን ፊታቸውን አዞሩ ...

«ለመሆኑ የክብር ዘበኛን የጦር ግምጃ ቤት አስጠብቀሃል?» አሉት፥ ጄኔራል ከበደ::

«መቼ ጦር ላኩልኝ?» አለ፥ ጃገማ - በቅሬታ::

«አንድ ሻለቃ ጦር እዚህ አለ፤ ነገ ወስደህ አስጠብቅ» አሉት:: ኮሎኔል ጃገማ በእሺታ ራሱን ወዘወዘ::

* * *

የሶስት ቀኑ የመፈንቅለ መንግስት ድራማ በአሳዛኝ ሽንፈት ተፈፀመ:: እነ ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ከቤተ መንግስት ወጥተው ወደ እንጦጦ ሸሹ:: የሃምሳ አለቃ ታከለ በጅብ ተበላ:: ሻምበል ባዬ ጥላሁን እስከ መጨረሻዋ የሞት ፅዋ መቅመሻው ቀን መንግስቱንና ገርማሜን ለምኖ እያበላ ቆይቶ ህዝብ ገደለው:: ጄኔራል መንግስቱ ቆስለው ተያዙ:: ገርማሜ ራሱን ገደለ:: ከዚያ የገርማሜ፣ የጄኔራል ፅጌ ዲቡና የኮሎኔል ወርቅነህ ሬሳ ተሰቀለ:: በመጨረሻም ጄኔራል መንግስቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ... «ይግባኝ አልጠይቅም» ብለው ተክለኃይማኖት አደባባይ ተሰቀሉ:: የጠዋት ጤዛዎች ዘራቸውን ዘርተው ቡቃያቸውን ሳያዩ ረገፉ...

* * *

«ንጉሰ ነገስቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብዐ መንግስት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ፣ ስልጣኑ የማይደፈር ሆኖ በቆየውም ልማድ በአዲሱም ህግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል:: ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የሚነሳ ማንም ሰው በህግ ይቀጣል» በተባለው መሰረት ነቅናቂዎቹ ተቀጥተው «ከራስ በፊት ለሃገርና ለንጉሰ ነገስት» የሚባለው እምነት ቅኝት ሳይለወጥ፤ የንጉሰ ነገስቱ ክብርና ሞገስ ሳይናድ፤ የሞዓ አንበሳ ግንድ ሳይገዘገዝና ሳይቆረጥ ... በግፍ ለመጣል የተደረገው መፈንቅለ መንግስት





እንደ ዘር፥ በላመው አፈር ውስጥ ተሰነቀረ:: ዘሪዎቹ ግን እንደ ወንዴ ንብ ተራክቦ ፈጽመው በራሳቸው ወገን በንቦች መንጋ እየተነደፉ አለፉ ... የሶስቱ ቀን የመፈንቅለ መንግስት ድራማ 'ዝጠኝ ሆነን ዘምተን ምንም አልሆን ... ስምንቱ ሞተው እኔ ተመለስሁ' ዓይነት' ምሬትን ጥሎ አለፈ - የወንድማማቾችን ህይወት ቀጥፎ!

ቅዳሜ ታህሳስ 8 ቀን 1953 ዓ.ም ንጉሰ ነገስቱ ከአስመራ ተነስተው አዲስ አበባ ገቡ:: ከዚያም ቀጥታ ታላቁ ቤተመንግስት ወደሚባለው ኢዮቤልዮ ቤተመንግስት ገብተው ተቀመጡ:: ማክሰኞ ታህሳስ 11 ቀን 1953 ዓ.ም እንጦጦ አካባቢ በነበሩ አነስተኛ የክብር ዘበኛ ሃይሎች መለስተኛ የተኩስ ልውውጥ ተደረገ::

ኮሎኔል ጃገማ ንጉሰ ነገስቱን እጅ የነሳው አዲስ አበባ ከተመለሱ ከአራት ቀን በኋላ ነው:: ሲያዩትም «ጃገማ! የአንተን ስራ ካርቱም ሆነን ሰምተናል ...» ብለውታል:: በኋላ ግን ልዑል ደጃዝማች አስራተ ካሳ «ያን የበቾ ኦሮሞ ሹመው በስንት መከራ ከቤተ-መንግስት አስወጣነው፤ ቀጥለው ደግሞ ይህን የቄስ ልጅ የክብር ዘበኛ አዛዥ አድርገው መኳንንቱን ፈጅቶ ይኸው ይህን ሁሉ ጣጣ ፈጠረ ... ስለዚህ አሁንም በቤተመንግስት ውስጥ ስለሚሾሙት ሰው በሚገባ ማሰብ አለብዎት:: ይህን አሁን የጠቀስኩልዎትን ምክር ደግሞ እኔ ብቻ ሳልሆን አባቴም ሲመክርዎት እንደነበር የሚረሱት አይመስለኝም» አሉ፥ አስራተ ካሳ::

የጨዋ ልጅ ይመረጥ በሚለው አስተያየት መሠረት አዲስ የክብር ዘበኛ አዛዥ ተመረጠ:: ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ከለንደን፣ ሚካኤል እምሩ ከዋሽንግተን፣ አምሃ አበራ ከዩጎዝላቪያ ለካቢኔ አባልነት እየተጠሩ መጡ:: አዲሱ የክብር ዘበኛ አዛዥ ደበበ ሃይለማርያም ሆነው በንጉሰ ነገስቱ መሾማቸው በስድስት ሰዓት በሬዲዮ ዜና ተነገረ::

ጃገማ ተምሮ፣ የአገር ፍቅርን አውቆ ጦሩን የተቀላቀለ አይደለም:: እንደ አያት ቅድመ አያቱ ስሙን ሊያስጠራ፣ ሰዋዊ ክብሩን ሊያስከብር ነው በዱር በገደል ገብቶ አርበኛ የሆነው:: የአገር ፍቅርን ምንነት ሲያውቅ ደግሞ በውታደራዊ ሞያው ትዕዛዝ አክብሮ ግዳጁን ፈፃሚ ሆነ:: ግዴታውን ሲወጣ ደግሞ በዘር ሃረግ መዘዛ ግራ የሚያጋባ እንቅፋት እየገጠመው ተቸገረ ...

ጃገማ በአርበኛነት ጊዜው ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን ከደጃዝማች ዘውዴ ጋር ለማስታረቅና በወሊሶ መንገድ የኢጣሊያን ሰራዊት መውጫ መግቢያ ያሳጡትን ጀግና ለማየት መቶ አርበኞቹን ይዞ ሄዶ ነበር:: ያን ጊዜ ደጃዝማች ገረሱ አንድ ነገር አስተምረውታል - ሁሉም ክፉ አለመሆኑን::

«አንድ ጊዜ» አሉት ገረሱ፤ «አንድ ጊዜ ጣሊያኖችና ባንዳዎች ተከታዮቼን ፈጅተው ከበቡኝ:: እኔም አንድ ጎድጎድ ያለች ጉድባ ውስጥ ተደብቄ እያለሁ ተጠጉኝ:: እንዳልተኩስ ብዙ ናቸው:: ያሉት በቅርብ እርቀት ነው:: የነበረኝ ጥይትም የሚያወላዳ አልነበረም:: አንድ የአማሴን ሹምባሽ ወደ እኔ እያመሩ የነበሩትን፥ በዚህ አይደለም ... በዚያ ሂዱ ... እያለ አቅጣጫቸውን በግድ አስቀየራቸው:: ወደ ኋላ ቀረት ብሎ ዐይን ለዐይን ተያየን:: ከዚያ ወደ እኔ ቀረብ አለና፤

«እርስዎ ለአገርዎ ነፃነት የሚዋደቁ አርበኛ ነዎት ... እኛ ደግሞ የቅኝ ገዥዎች አሽከር ነን:: ለእንጀራ ስንል እንዋጋለን ... እናንተ ባትኖሩ እኛም የነገን ተስፋ ማየት አንችልም:: ባርነት የዘላለም ዕጣ ፈንታችን ሆኖ ይቀር ነበር:: ነገ ያልፍልናል ብሎ ካለማሰብ ደግሞ ሞት ይሻላል:: ደግሞም የእርስዎ አርበኝነት ለእኛም እርነት ነው፤ ስለዚህ እርስዎ አይገደሉም፤ ዝም ብለው እዚሁ ይቀመጡ፤ ማንም ተመልሶ አይመጣም» ብሎኝ ሄደ ብለው ነገሩት::

ወጣቱ የአርበኞች መሪ «ለካ ከጠላት ጋርም ወዳጅ አለ» ብሎ አመለካከቱን አሰፋ:: ሌሎችን ማክበሩ፤ ሌሎችን መውደዱ ጨመረና ተግባቢ ሆነ:: የመግባባት መሰረት ደግሞ ሌሎችን መውደድ፣ ማክበር፣ መፈለግ፣ መረዳት፣ ማመን ነው:: ይህ ሲሟላ ፍቅር አድማስ ሰፊ ይሆናል - ድንበር የሌለው::

* * *

ኮሎኔል ጃገማ፥ ደበበ ሃይለማርያም የክብር ዘበኛ አዛዥ ሆኖ መሾሙን ሲሰማ በስምንት ሰዓት ኮሎኔል ደበበ ቤት ሄዶ በግሉ የተሰማውን ደስታ «እንኳን ደስ አለህ» በማለት ገለጸ:: በዘጠኝ ሰዓት ደግሞ ቅሬታውን ለመግለጽ ወደ ምድር ጦር መምሪያ ሄደ:: ምክትል የምድር ጦር አዛዡን ጄኔራል ተድላ መኮንንን አገኛቸው::

«ከዛሬ ጀምሮ ከጦር ሃይሉ ውጭ ነኝ» አለ፥ ኮሎኔል ጃገማ:: ጊዜው ደግ የሚታሰብበትም ነበርና «ምነው?» አሉት ጄኔራል ተድላ::

«ክብሬ ተነክቷል» አለ፥ ጃገማ - እልህ እየተናነቀው::

«በምን ክብርህ ተነካ?» አሉ፥ ተድላ - በግርምታ እየተመለከቱት::





«ኮሎኔል ደበበን በሞያ እበልጠዋለሁ:: በማዕረግም ቅድሚያ አለኝ:: እኔ ሻለቃ ሆኜ እሱ ሻምበል ነው፤ እኔ ኮሎ ኔል ሆኜ እሱ ሻለቃ የነበረ ነው:: እንዴት በእኔ ላይ ይሾማል? በእርግጥ እኔ ሹሙኝ አልልም፤ ነገር ግን እሱን ስትሾሙ እኔን ወደ ጦር ሰራዊት መመለስ ይገባችሁ ነበር:: እኔ ቤተመንግስት እየጠበቅሁ እንዴት በእኔ ላይ አምጥታችሁ ትሾሙታላችሁ?... በምንስ በልጦኝ ነው? ስለዚህ ክብሬ ተነክቷል» አለ::

ጄኔራል ተድላ ትክ ብለው አዩትና በሀሳባቸው፤ «እውነት ምስጢሩ ስላልገባው ነው ወይንስ ያሾፋል!» አሉ:: ኮሎኔል ጃገማ ወጥቶ ሄደ፤ ሶስት ወራት ሙሉ «የት ነህ?» ያለው አልነበረም::

ለሶስት ወር በቅሬታ ያለስራ ሲቀመጥ የመኮንኖች ክለብ ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመረጠ:: ወዲያው ክለቡን ሲያሳድገውና ተወዳጅ ሲያደርገው እስከ 1963 ዓ.ም ድረስ ለአስር አመታት የመኮንኖችን ክለብ በፕሬዚዳንትነት እንዲመራ ተደረገ:: በክለቡ ከፈፀማቸው ተግባራትም ውስጥ አንዱ አሁን ያለው ህንፃ በንጉሰ ነገስቱ የመሰረት ድንጋይ ተቀምጦ እንዲሰራ ማድረጉ ነው:: ቀድሞ የክለቡ ይዞታ የነበረውን መሬት አስራ ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር አስጨምሮ ሰላሳ ሰባት ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት እንዲኖረውና ለባለ እርስቶቹ ክፍያ ከፍሎ ካርታና ፕላኑ በጦር ሃይሎች ስም እንዲመዘገብ አድርጓል::

* * *

አንድ ቀን ግን ችግር መጣ:: ጦርነትና ግጭት ሲመጣ ጃጌ ጃገማ ፈላጊ አያጣም:: ስምንት መቶ የሚሆኑ የጦር ሰራዊት አባሎች አደሙና ሜዳ ላይ ተሰብስበው «ጄኔራል ከበደ ገብሬ ይሻሩ ... ኮሎኔል ጃገማ ይሾም፤ የምድር ጦር አስተዳደር ክፍሉ ኮሎኔል ወሰኔ ይለወጥልን ... እኛ በዓመት ሁለት ካኪ ልብስ የምንለብሰው ሳንከዳ በዓመት ሶስት ካኪ የሚለብሰው፣ በየሃያው ቀን ስንጋ የሚታረድለት ክብር ዘበኛ ከዳ ... እልጋውን የመለስነው ግን እኛ ነንና ደመወዝ ይጨመርልን» በማለት የኢዮቤልዮ ቤተመንግስትን በር ጥሰው ገቡ::

ችግሩን ለመፍታት ወታደሮቹ የሚወዷቸው ሁለት ጄኔራሎችና ሁለት ኮሎኔሎች ይጠሩ ተባለ:: በዚህም ጄኔራል ወልደስላሴ በረካ፣ ጄኔራል ዋቅጅራ ሰርዳ፣ ኮሎኔል በለጠ አበበና ኮሎኔል ጃገማ ተመረጡ:: ከዚያ ጄኔራል ወልደስላሴና ጄኔራል ዋቅጅራ ሄደው ብሶተኛ ወታደሮችን ሲያነጋግሯቸው ሲፈልጉ ጥያቄ አቅራቢዎች ፊታቸውን እያዞሩ አስቸገሩ:: በኋላ በጄኔራል ዋቅጅራ ፋንታ ኮሎኔል ጃገማ ተተካ::

ወታደሮቹ «ንጉሰ ነገስቱን እናነጋግር፤ ጠይቁልን» ብለው አቤቱታቸውን ነገሯቸው። ንጉሰ ነገስቱም ሊያነጋግሯቸው ፈቃደኛ ሆኑ። ጥያቄያቸውን አቀረቡ።

«አስተዳደር እናንተን አይመለከትም። ስለ በደላችሁ ግን ሌላ ጋ አልሄዳችሁም፤ እኛ ዘንድ ነው የመጣችሁት። መልሳችንን እናስታውቃችኋለን» አሉና ንጉሰ ነገስቱ ገቡ። ወታደሮቹ «መልስ እንጠብቃለን» አሉ። እነ ኮሎኔል ጃገማ ስታዲየም ወስደው «ጥያቄያችሁን አቅርባችኋል፤ ንጉሰ ነገስቱ መልሱን በአንዴ ሊሰጡ አይችሉም፤ ለካቢኔው ማቅረብ፣ ማማከር አለባቸው» አሏቸው። ሃሳባቸውን ተቀብለው ተበታተኑ። በማግስቱ ግን የጠየቁት የደመወዝ ጭማሪ ተፈቀደላቸው።

በዚህ ሰበብም የምድር ጦር አዛዡ «ግርማዊ ጃንሆይ! ኮሎኔል ጃገማኮ ስራው ላይ አይደለም» አሏቸው።

«ለምን?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - በመገረም።

«'መብቴ ተደፈረ' ብሎ።»

«ስለምን መብቱ ተደፈረ?»

«በስልጣንና በሞያ የምበልጠው በላዬ ላይ የክብር ዘበኛ አዛዥ ሆነ... ብሎ ነው ጌታዬ!»

«ልክ ነዋ! - ልክ ነው!» ብለው ቆጣ አሉ። ጄኔራል ከበደ ደነገጡ። «በል በአስቸኳይ የሚመጥነው ቦታ ፈልጋችሁ ሹሙት» አሉ ንጉሱ። ጄኔራል ከበደ ትዕዛዝ መቀበላቸውን ለማረጋገጥ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጡ።

በሰኔ ወር 1953 ዓ.ም ኮሎኔል ጃገማ የአራተኛ ክፍለ ጦር ጥብቅ አዛዥ ሆነ። ከዓመት በኋላ ደግሞ በብርጋዴር ጄኔራል ማዕረግ የአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኖ ተሾመ።

* * *

ውሃ ዋና ወዳዱ ጃገማ በጦር ሃይሎች ውድድር ላይ ከየጠቅላይ ግዛቱ ተመልምለው ከሚቀጠሩ ወታደሮች ውስጥ የውሃ ዋና የሚችሉ ተመርጠው በግዮን ሆቴል እንዲሰለጥኑ በማድረግ ለጦር ሃይሎች ስፖርት





ውድድር አቅርቦ የባህር ሃይልን በዋና በማሸነፍ በክፍለ ጦር አዛዥነት ይመራው የነበረውን የአራተኛ ክፍለ ጦር ለዋንጫ ሽልማት አበቃው። ኮሎኔል ጃገማ የመቻል ስፖርት ክለብ ፕሬዚዳንት ሆኖ ባገለገለባቸው ዓመታት ሌ/ጄኔራል ይልማ ሺበሺና ዶ/ር ከበደ ሃብተማርያም ምክትሎቹ ነበሩ።

ጃገማ ለሁለት ዓመታት የጦር ሃይሎች ስፖርት መሪ በሆነበት ጊዜ ንጉሰ ነገስቱ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሚኒስትሮች በተገኙበት አመታዊ ውድድር ሲደረግ ሰማዩ ጠቁሮ፣ ነጎድጓዱ ሲጮህ ... ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ አስጠርተውት «ጄኔራል! ዝናብ እየመጣ እኮ ነው፤ ቶሎ ቶሎ ብለህ ሸኘን እንጂ» አሉና ንጭንጭ አሉበት። ንጉሰ ነገስቱ የጸሐፊ ትዕዛዝን አስተያየት ሰምተው ነበርና «ጃገማ!» አሉት።

«አቤት ጃንሆይ!» ብሎ ጠጋ አለ።

«'ጫምሺቱ' አምጥተሃል?» አሉት። ፈገግ ብለው፤

«አምጥቻለሁ ጃንሆይ!» አለ፥ ጄኔራል ጃገማ።

«ጫምሺቱ ካለ አታቻኩሉት ... ተውት» አሉ።

ጫምሺቱ ማለት «ዝናብ የሚያስቆም» ማለት ነው። አክሊሉ ሃብተወልድ «ጃንሆይ! ይህ የማይረባና ኋላቀር እምነት እኮ ነው» አሉ። ንጉሰ ነገስቱ ዘና ብለው እየተቀመጡ «ሂድ ጄኔራል ... ቀጥሉ» አሉ። ዶፍ ዝናብ ዙሪያውን እየወረደ ሥነስርዓቱ የሚካሄድበት ቦታ ብቻ ሳይጥል ቆየና ጨዋታው አልቆ ንጉሰ ነገስቱ ወደ መኪናቸው ሄደው በሩ ሲከፈትላቸው ዝናቡ ማንጠባጠብ ጀመረ ...

«አክሊሉ!» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - ጠቅላይ ሚኒስትራቸውን። ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ጠጋ አሉ።

«የአንተን ሳይንስ አየነው!» ብለው ስቀው ወደ መኪናቸው ገቡ።

ንጉሰ ነገስቱና ጄኔራል ጃገማ በጫምሺቱ ያምናሉ። በኦሮሞ ውስጥ እንደ ጫምሺቶች የማያርሱ፣ የማይነግዱ «ማሊማዎች» የሚባሉ ጎሳዎች አሉ። የአካባቢያቸው ሰው ነው የሚያርስላቸው፤ ሶስት ቀን ለራሱ አንድ ቀን ለእነሱ ያርሳል። የማሊማዎቹ ስራ ቀንና ሌሊት «ዋቅን» መለመንና ማመስገን ነው። ታዲያ ከተፈለገ በበጋ ዝናብ ያዘንባሉ ... በክረምት ደግሞ

ሲያስፈልግ ዝናብ ያቆማሉ:: ስለዚህ ዓመታዊ ውድድር ሲደረግ ጫምቪቱ ይጠራና ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ሰማይ ሰማይ ማየት ከጀመረ ካለ ስጋት ጨዋታ ማካሄድ ይቻላል::

አንድ ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ «ነገ ዝናብ አይዘንብም» የሚል ማሳሰቢያ ከ«ሜትሮሎጆስቶች» ሰሙ:: በነጋታው ዝናብ አይኖርም የሚለውን ማሳሰቢያ አምነው ቢሾፍቱ ለመሄድ ወስነው ጉዞ ጀመሩ:: መንገድ ላይ አንዱ አህያውን በዱላ ይነርታታል:: መኪናቸውን አቁመው አስጠሩትና «ምን አርጊ ብለህ ነው የምትደበድባት?» አሉት:: «ጃንሆይ! ጆሮዋን ወደኋላ ቀስራ 'ሂጂ' ብላት 'ዝናብ አለ' ትለኛለች:: እኔ ያልፈራሁትን እሷ ፈራች:: እህ! 'አንች ነሽ እኔ ነኝ የማዝሽ?' ብዬ እኮ ነው መነረቴ ... ዝም ካልኳትማ እኔ ታዛዥ፥ እሷ አዛዥ ሆነችማደል፥ ጃንሆይ? ብዬ ብዬ ደግሞ ለአህያ አዋቂ ፊት ልስጥ፥ ጃንሆይ? እስኪ እግዜር ያሳይም! ዝናብ ቢመጣ ብቻዋን አትመታ፤ የምንደበደብ እኩል፤ ጭቃ የምናቦካ እኩል ...» አላቸው::

«ዝናብ ይመጣል ማለቷንስ አምነኸዋል?»

«እሱማ እውነት ነው፥ ጃንሆይ! ጆሮዋን አቁማ እየነገረችኝ፥ እያይዋት» አለ:: ንጉሰ ነገስቱም ሳቅ አሉና ሾፌራቸውን በአገጫቸው ሂድ አሉት:: መንገድ ላይ ዶፍ ዝናብ መጣል ጀመረ፤ «ይገርማል! ከሱሉልታ የአየር መምሪያ የአገሬ አህዮች ይሻላሉ» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - በስጨት ብለው::

* * *

በ1954 ዓ.ም ደግሞ ጄኔራል ጃገማ እግሩን ተሰብሮ ጦር ሰራዊት ሆስፒታል ገባ:: ንጉሰ ነገስቱ በየሆስፒታሉ ያሉ ህመምተኞችን ሄዶ የመጠየቅ ልምድ ስለነበራቸው በሄዱ ቁጥር ጄኔራል ጃገማን ይጠይቁታል:: ጄኔራል ጃገማ የጦር ሰራዊት ሆስፒታል ተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቸር) ጠበበውና «ይለወጥልኝ፤ ጠበበኝ» ብሎ ጠየቀ:: «እዚህ ሆስፒታል ከዚህ የሰፋ ዊልቸር የለም፤ ግርማዊ ጃንሆይ ሲመጡ እሳቸውን ቢጠይቋቸው ከልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል ያስመጡልዎታል» አሉት:: በሚመጡበት ቀን ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ፀሐይ እየሞቀ ጠበቃቸው:: ንጉሰ ነገስቱ መጡ::





«ጃንሆይ! ዊልቸሩ ስለጠበበኝ ከልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል እንዲመጣልኝ እባክዎ ይዘዙልኝ» አላቸው:: «ጃገማ! ቢታዘዝልህም አይበቃህም ... አንተ እኮ ወፍረሃል» አሉት እየሳቁ::

«ጃንሆይ መወፈሬን አይጥሉት ... የወፈረ ወታደር አይሸሽም» አላቸው ጄኔራል::

«እሱን ተውው ጃገማ! እኛ ብዙ አይተናል፤ ገና ጦርነት ሲጀመር ኋላ እንዳይቀር ቀድሞ የሚሸሸው እሱ ነው» አሉት:: ሁለቱም በጥያቄና መልሱ ፍርስ ብለው ሳቁ ...

ከዚያ ለተሽከርካሪ ወንበሩም፤ ለ"ፊዚዮቴራፒ"ም ወደ ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል ተዛውሮ እንዲተኛ ተፈቀደ:: በሆስፒታሉ አንዲት ፈረንሳዊት "ፊዚዮቴራፒስት" ነበረች:: አምስት ወር እግሩ ላይ የቆየው ብረት እግሩን ሲያንቀሳቅስ እንደሚያመው ነገራት:: አልሰማችውም፤ የእሷን ትዕዛዝ የሚቀበሉት ረዳቶቿም በግድ አነቃንቅ እያሉት ተሰቃየ::

አንድ ቀን ፈረንሳዊቷ መጣችና «እግርህን አንቀሳቅሰው!» አለችው:: «ያመኛል» አላት::

«አያምም፤ አንቀሳቅሰው!» አለችው::

«እሺ ወደ እኔ ጠጋ በይ» አላት:: ጠጋ ስትል በቀኝ እጁ ፀጉሯን ጭምድድ አድርጎ ያዛትና «ያማል?» አላት፤

እያቃሰተች «... አ! በጣም ያማል» አለችው::

«ይኸውልሽ፤ እኔንም እንደዚህ ነው የሚያመኝ» አላት::

ፈረንሳዊቷ "ፊዚዮቴራፒስት" ገባት፤ በጣም ገባት! «ከዛሬ ጀምሮ ያመዋልና ጅምናስቲክ ስራ ብላችሁ እንዳታስቸግሩት» ብላ አዘዘች::

## ፲፰

# የምህረት አዋጅ

ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ የባሌን አመፅ ለመቆጣጠር በፊታውራሪ ወርቁ እንቁስላሴ የሚመራ ዘመቻ ተደረገ። በዘመቻው እንደ ፊታውራሪ ወልደሚካኤል ቡኢ (የገናሌ ባላባት) ያሉት በነጭ ለባሾች ሲገደሉ አመፁ ተባባሰ። እንደገና ደግሞ በኮሎኔል መንገሻ ገብረኪዳን፣ በመቀጠልም በአራተኛ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ በብርጋዴር ጄኔራል ከበደ ያዕቆብ በተደረገው ዘመቻ የባሌን አመፅ ለመቆጣጠር ተሞክሮ ሳይቻል ቀረ። በ1957 ዓ.ም አመፁ እየጠነከረ ስለሄደ በሱማሌ አካባቢ ኦጋዴን፣ በሲዳሞ ቦረና፣ በባሌ ደግሞ ገናሌ፣ ጊኒር፣ ዶሎ፣ ኤልከሬ አውራጃዎች በወታደር አስተዳደር ስር ሆነው በአራተኛ ክፍለ ጦር ትዕዛዝ ስር እንዲተዳደሩ ታወጀ።

ለአራተኛ ጊዜም ጄኔራል ጃገማ አመፁን እንዲያቆም ታዘዘ። የታዘዘውን ለመፈፀም በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ ሁሉም ነገር ተፈቀደለትና በ1962 ዓ.ም ቀዳሚ መምሪያውን ቦረና አደረገ።

ጄኔራል ጃገማ ኦሮሞ ነው። ግዳጁ ሲሰጠው እሸህን በሾህ መሆኑ ገብቶታል። በተለያየ ወቅት ፀጥታውን ለማስከበር የተላኩት ተሿሚዎች ያደረሱትም በደልና ግፍ ሲያንገበግበው ቆይቷል። ስለዚህ ጃገማ ወታደራዊ ግዳጁን በጦርነት ሳይሆን በሰላም መጨረስ እንዳለበት አምኖ ነው ወደ ባሌ የሄደው። አመፁ ከቀጠለ የመሳሪያ ብልጫ የነበረው መንግስት እርምጃ እየወሰደ ብዙ ደም ይፈሳል። ጃገማ ሊመጣ የሚችለውን እልቂት ነው ለማቆም የፈለገው።

ባሌ ሰፊ ጠቅላይ ግዛት እንደሆነና የአስተዳደር ጉድለት እንደአለው ተረድቷል። ባሌ በኦሮሞ ታሪክ የታሪክ መሰረት ነው። ኦሮሞዎች በገዳ ስርዓት ተደራጅተው ወደ ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል የተስፋፉት ከ«መዳ ወላቡ» እንደሆነ በሚገባ ያውቃል። ያን ታሪካዊ ስፍራ ማልማት፣ ህልውናውን ማስከበር እንጂ ማጥፋት እንደማይገባ ያምናል። ስለዚህ ሰላማዊ የጦር ኦፕሬሽን ለመፈፀም ከኢትዮጵያ አየር ሃይል አዛዥ ጋር በፅሞና ተወያይቷል። ወደ ቦረና፣ ሱማሌ፣ ሐረር ... አማፅያኑ እንዳይንቀሳቀሱም በስድስት ሺህ ጦር ሰራዊትና በነጭ ለባሾች ከበባ አስደርጎ ዘግቷል። የአየር ሃይል አውሮፕላኖች የጪስ ማውጫቸውን አውልቀው ለአንድ ሰዓት





በጫካው ላይ እንዲበሩ፣ ሰው በማይገኝባቸው ሜዳዎች ላይ ደግሞ የ«ናፓል» ቦምብ እንዲጥሉ አደረገ። አውሮፕላኖች እንዲበሩና ቦምብ እንዲጣል ያደረገው መንግስት ያለውን ሃይልና በዚያ ሃይሉም ሊያደርሰው የሚችለውን ጉዳት አማፅያኑ እንዲያውቁትና እነሱን ለመደምሰስ የተዘጋጀውን የመንግስት ሃይል በአይናቸው አይተው እንዲረዱት ነው።

ያን የማዳን ወታደራዊ ስልቱን በሚገባ አስቦበት ለጦሩ የአስራ አምስት ቀን ስንቅ በማቅረብ ሰራዊቱ በስንቅ እጦት እንዳይበተንና ህዝቡንም እንዳይዘርፍ ካደረገ በኋላ የአገር ሽማግሌዎችን ሰብስቦ አነጋገረ። «በሰላም የገባ መሳሪያውን ብቻ ያስገባል። ተዋግቶ በግድ የተያዘ ግን ሃብቱ፣ መሬቱና መሳሪያው ይወረሳል። እንዳያችሁት መንግስት ሃይል አለው። ከመንግስት ጋር መዋጋት ትርፋ እልቂት ነው። ስለዚህ ጫካ ያለ ሁሉ በሰላም እጁን ይስጥ። በሰላም የገባ ምህረት ያገኛል» በማለት እንዲሸመግሉ ላካቸው። በቀረበው የሽምግልና ጥሪ መሰረት መጀመሪያ ዋቆ ሉጎ የሚባሉት የዋቆ ጉቶ አጎት፣ የዋቆ ጉቶሚስትና ወንድ ልጅ እጃቸውን ለጄኔራል ጃገማ ኬሎ ሰጡ። ጃገማ እነሱን ይዞ አዲስ አበባ ንጉሰ ነገስቱ ዙፋን በመቅረብ ምህረት እንዲያገኙ አደረገ። በንጉሰ ነገስቱ ፈቃድ ምህረት ሲሰጣቸው ፎቶ እንዲነሱ ተደረገ። ጄኔራል ጃገማ ያን ፎቶ በአውሮፕላን፣ በመኪናና በሰዎች አማካይነት አሰበተነ።

ልክ በወሩ ዋቆ ጉቶ እጃቸውን ለጄኔራል ጃገማ አምነው ሰጡ። ጄኔራል ጃገማ አዲስ አበባ ወስዶ ለንጉሰ ነገስቱ ሊያቀርብ ቤተ-መንግስቱ ኮሪደር ላይ ሲጠባበቅ የምድር ጦር አዛዡ ጄኔራል ከበደ ዋቆን እያዩ ወደ ንጉሰ ነገስቱ ገቡ።

«ግርማዊ ጃንሆይ! በዚህ ሰውዬ (በዋቆ ማለታቸው ነው) ምክንያት የብዙ ሰው ህይወት አልፏል። በግዞት ቢቀመጥ ይሻላል እንጂ ምህረት አግኝቶ ከተመለሰ ሌላ ተጨማሪ ጥፋት እንዲያደርስ መፍቀድ ነው» አሉ።

«ጃገማ የገባው ቃል እንዳለስ?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ።

ጄኔራል ጃገማ ተጠርቶ ብቻውን ገባ። ጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ «ጄኔራል ጃገማ! አሁን የተጠራኸው የምድር ጦር አዛዡ፥ 'ዋቆ በግዞት እንዲቀመጥ ቢደረግስ' ብለው ሃሳብ ስላቀረቡ ነው። ግርማዊ ጃንሆይ ደግሞ 'ጃገማ የገባው ቃል ካለስ?' በማለታቸውም ነውና የተጠራኸው ሃሳብህን ግለጽላቸው» አሉ።

«ግርማዊ ጃንሆይ» አለ ጄኔራል ጃገማ፤ ንጉሰ ነገስቱ ፊታቸውን ወደ እሱ ዘወር አደረጉ:: «ግርማዊ ጃንሆይ! እነሱ እኮ ከእኛ የበለጠ ያስባሉ» አለ፥ ጃገማ::

«እንዴት?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ::

ጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ዐይናቸውን አፍጥጠው እዩት:: ሁሌም ሃሳቡ ከሃሳባቸው የማይገጥመው የምድር ጦር አዛዡ ደግሞ በንቃት ተመለከቱት:: ጄኔራል ጃገማ ረጋ ብሎ ሁሉንም አያቸውና፤

«መጀመሪያ ብዙ መልዕክት ልኬ ... ግርማዊ ጃንሆይ ምህረት ያደርጉላችኋል ብዬ ዋቆ ጉቶ ተጠራጥሮ አጎቱን፣ ሚስቱንና ልጁን ላከ:: የእነሱን ምህረት ሲያረጋግጥ ዋቆ ራሱ መጣ:: አሁን ደግሞ ከድር ዋቆ የሚባለውንና ዋናውን የቦረና ባላባት ጫካ ትቶ ነው የመጣው:: የባሌ ዘመቻ ገና አላለቀም፤ የንጉሰ ነገስቱን ቃል ማጠፍም የማይቆም ችግር ይፈጥራል:: ስለዚህ መንግስት የፈቀደው ምህረት በትክክል መሰጠት አለበት» አለ፥ ጄኔራል ጃገማ - ሃዘን እየተሰማው::

«... ይኸዋ! ... አላልንም?» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - የምድር ጦር አዛዡ ላይ እያፈጠጡ:: ዋቆ ተጠርተው ገቡ:: የቤተመንግስቱ ማማር፣ ስርዓቱ፣ የባለሟሎች ወዝና ውበት እያስፈራም ቢሆን ያማልላል:: ንጉሰ ነገስቱ ዋቆን ለረጅም ጊዜ ሲያዩ ቆዩና «ዋቆ ምን ሆንሁ ብለህ ነው መሸፈትህ? ... እስኪ አስረዳን» አሉ::

«ጃንሆይ! እኔ የአሩሲ ጎሳ ነኝ፤ ተወልጄ ያደግሁት ግን ባሌ ነው:: ወንድሜ ሲዳሞ ውስጥ ይኖራል:: ከመዳ ወላቡ ወደ ሲዳሞ ተሻግሬ ስኖር በቦረና ውስጥ መሪሃ እና ዲጎዲያ የሚባሉ የሱማሌ ጎሳዎች ፈልሰው በመምጣት በሲዳሞ ከሚኖሩ ቦረናዎች ከዶሎባይ፣ ከፊልቱም አልፈው የግጦሽ መሬታችንን አጣበቡብን:: ወደ ላይ እንዳንወጣ ጉጂዎች አሉ፤ ወደ ታች እንዳንወርድ ደግሞ መሪ ሃና ዲጎዲያዎች አሉ:: ኗሪው መሪሃ እና ዲጎዲያዎችን ወደ ታች ካልገፋችሁልን ኬኒያ ወደሚገኘው ጎሳችን እንገባለን ብሎ በዚያ ጊዜ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ለነበሩት ለራስ አንዳርጋቸው አመለከተ:: ራስ አንዳርጋቸው ጉዳዩን ለአገር ግዛት ሚኒስቴር በመንገር አስፈቅደው እነዚህ ከሱማሌ የመጡ ሁለት ጎሳዎች ከቦረና ከተማ ከፊልቱ መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ተገፍተው እንዲቀመጡ ታዘዘ:: ያን ጊዜ እኔንም ተነስተህ ከሶማሌ ጎሳዎች ጋር ሂድ አሉኝ::





«ጃንሆይ አዘንሁ! ... ከልቤ አዘንሁ» ብለው ዋቆ የተናነቃቸውን እንባ እንደምንም መለሱት፤ «'ምነው! እኔ ከባሌ ነው የመጣሁት፤ ኢትዮጵያዊ እንጂ የሶማሌ ጎሳ አይደለሁም፤ ስለምን ተነሳ እባላለሁ?' ብዬ ለአውራጃ ገዥው አመለከትኩ:: አውራጃ ገዥው 'ትነሳለህ' ብለው ፈረዱብኝ:: አገር ግዛት ሚኒስቴር መጥቼ አመለከትሁ ... አገር ግዛት ሚኒስቴር በአለሁበት እንድኖርና እንዳልነካ ቴሌግራም አስተላለፈልኝ፤ ደብዳቤም ፃፈልኝ:: ለአውራጃው ገዥ ወስጄ ሰጠሁ ... የአውራጃው ገዥ ትዕዛዙን ሽረው ደግመው 'አይሆንም፤ ተነስ' አሉኝ:: 'እሺ ተነስ ካላችሁኝ የምከላከልበትና ንብረቴን የምጠብቅበት ጠመንጃ ስጡኝ' ብዬ ጠየቅሁ:: የጠየኩትን መሳሪያ ግን ተከለከልሁ፤ ይባስ ብለው አውራጃ ገዢው ለጉጅና ቦረና ጠመንጃ ሰጥተው 'ካገራችሁ አስነሱት' አሉ::

«ግርማዊ ጃንሆይ! ብዙ ሰው አልቆብኝ፣ ከብቴን ውሃ ወስዶብኝ ... ቀሪ ንብረቴን ሱማሌ ከሚዘርፈኝ ወደ ትውልድ ቦታዬ ወደ ባሌ ልሻገር ብዬ ባሌ ብመለስ 'ዋቆ ጉቶ ሸፍቶ መጥቷልና ያዙት' ብለው ለባሌ ጠቅላይ ግዛት ትዕዛዝ ሰጡ:: በዚያ ሳቢያም ከብትና ንብረቴ ተወረሰ፤ ቤተሰቦቼም ተበተኑ::

«ከዚያ በኋላ መድረሻ ማጣቴን ሳውቀው ከቦረና ወደ ታች ወደተገፉት የሱማሌ ጎሳዎች ሄድሁኝ:: እነሱ ወደ ሱማሌ ወስደው ሰላሳ ጠመንጃዎች ሰጡኝ:: ጠመንጃዎቼን ይዤ በመምጣት ከብቶቼን አስመለስኩ፤ የተበተነውንም ቤተሰቤን አገናኘሁ:: በዚህ ምክንያት ሸፍታ ነው እያሉ ይኸው እስከዛሬ ያንከራትቱኛል ...» አሉ ዋቆ ጉቶ::

«ታዲያ እኛው ኖረናላ ያሸፈትንህ!» አሉ፥ ንጉሰ ነገስቱ - በተመስጦ ሲያዳምጡ ቆይተው:: ከዚያ «በል ምህረቱን አድርገናል ... ለወደፊቱም ችግራችሁን በጃገማ በኩል አሳውቀን» አሉ:: ዋቆ ጉቶ በምህረቱ ተደስተው ወጡ::

በወሩ ደግሞ ጄኔራል ጃገማ እንዳለውም ከድር ዋቆ እጅ ሰጡ:: ጄኔራል ጃገማ ለዋቆና ተከታዮቻቸው አየር ሃይልን አስጎበኛቸው:: በዚህ ዘዴም የባሌ ዘመቻ በጄኔራል ጃገማ አዲስ ስልት ንብረት ሳይወድም፣ ማንም ሳይጎዳ በሰላም ተጠናቆ ገበሬዎቹ ወደየእለት ህይወታቸው ገቡ:: ሶስት ሺህ አምስት መቶ ጠመንጃዎችም ቃል በተገባው መሰረት ተወርሰው ለመንግስት ገቢ ሆኑ:: «አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ነውና የእነ ዋቆ የመብት ትግል ግን ወደ ፖለቲካ ትግል እያደገ ሄደ:: ያ የፖለቲካ አስኳል ግን ከጃገማ ዕይታ ውጭ መሆኑ እውነት ነበር::

ጄኔራል ጃገማ አማፅያኑ ወደ ቦረና፣ ሱማልያ፣ ሐረር ... እንዳይሸሹና እቅዱ እንዳይበላሽ ዙሪያውን የመደበው ጦር የተሰጠው የአስራ አምስት ቀን ቀለብ ነው:: አስራ አምስቱ ቀን ሲያልቅ የቀሩት ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው:: ስንቅ ያመላልሱ የነበሩት አውሮፕላኖች ደግሞ ለሰርቪስ ተመልሰዋል::

እርግጥ ጄኔራል ጃገማ ከባሌ የተወረሰውን ጠመንጃ አይነትና ብዛት ዲፕሎማቶችና ወታደራዊ አታሼዎቻቸው እንዲያዩት ለጋበዙት ንጉሰ ነገስት በእለቱ በአራተኛ ክ/ጦር እንደማይገኝ ገልፆ ተፈቅዶለት ነበር:: የወታደሩ ቀለብ ጉዳይ ሲያሳስበው ግን አዲስ አበባ ተመለሰ:: ለአየር ሃይሉ አዛዥ ለጄኔራል አበራ የገጠመውን ብርቱ ችግር አስረዳቸው:: ጄኔራል አበራም «አሁን ያለህ አማራጭ አንድ ነው:: ግርማዊ ጃንሆይ ከመስኮብ አገር የተሰጧቸው ሁለት ሄሊኮፕተሮች አሏቸው:: ችግሩን ነግረህ እንዲፈቅዱልህ አድርግ:: አንዱ ሄሊኮፕተር ሰላሳ ኩንታል መጫን ይችላል» አሉት::

በአራተኛ ክ/ጦር ግቢ ንጉሰ ነገስቱና ጄኔራል ጃገማ ተያዩ:: «አልመጣም አላልከንም ነበር?» አሉ÷ ንጉሰ ነገስቱ:: ጄኔራል ጃገማ የገጠመውን ችግርና የመጣበትን ምክንያት ካስረዳ በኋላ ሄሊኮፕተራቸውን እንዲፈቅዱለት ንጉሰ ነገስቱን ጠየቀ:: «ከሄሊኮፕተሩ ላይ ያለው ዘውድና መቀመጫዎቹ ይነሱና ያመላልሱልህ፤ ፈቅደናል» አሉት:: ከሁለቱ ሄሊኮፕተሮች ውስጥ አንዱ እንደተባለው ተፈቀደና ጄኔራል አበራ ወደ ባሌ ስንቅ ጭነውበት በረሩ:: ሁለተኛውን ሄሊኮፕተር ግን እነ ራስ መስፍን ስለሺ ባዶ መሬት ለማየት ወደ ሸዋ አካባቢ ይዘውት ሄደው ነበር::

ጄኔራል ጃገማ ያዘጋጀውን የሰራዊቱን ተጨማሪ ስንቅ ጄኔራል አበራ በንጉሰ ነገስቱ ሄሊኮፕተሮች አመላለሱለት:: ንጉሰ ነገስቱም የባሌ አማፅያንን ጦር መሳሪያ አራተኛ ክፍለ ጦር ሄደው ከአዩ በኋላ «ጃገማ እኮ አልፎከረም እንጂ ትልቅ ስራ ነው የሰራው» አሉ÷ ለራስ መስፍን ስለሺ:: «ጃንሆይ! እሱ ምን ሰራ? ትልቅ ስራ የሰሩት እርስዎ ነዎት:: ያኔ የገናሌ ድልድይ ሲሰራ ወደ ዋቆ ጉቶ መልዕክተኛውን አነጋግረው በሰላም እጁን ሰጥቶ እንዲገባ ባይልኩበት ኖሮ ዋቆ እምኖ አይገባም ነበር» አሉ÷ ራስ መስፍን::

«እሱንስ መላ ያመጣው ጃገማ አይደል!» አሉ÷ ንጉሰ ነገስቱ::



# ፲፱

## በውጥኑ የቀረ ሌላ የመፈንቅለ መንግስት ሀሳብ

ልዑል አልጋ ወራሹ «ስልጣን ከያዙ 'ሞናርኪ ኮንስቲቲዩሽን' እመሰርታለሁ ... ህዝቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ይመርጣል ... » ስለሚሉ የለውጥ ፈላጊዎች ቁጥር እየተበራከተ ሄደ:: ይህን ለውጥ ይፈልጉት ከነበሩት መካከል ደግሞ እነ ደጃዝማች ታከለ፣ ዋግሹም ወሰን ሃይሉ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ነበሩ:: ጃገማም ለውጥ ከሚፈልጉት ጋር ተባባሪ ሆነ ...

ንጉሰ ነገስቱ በአገር ውስጥም ይሁን በአፍሪካ ብዙ አክባሪና አድናቂ ነበራቸው:: «ኢትዮጵያን ማየት የራሴን የአፍሪካዊነቴን ስረ-መሰረት እንደመጎብኘት፣ ንጉሰ ነገስቱንም ማግኘት ከታሪክ ጋር እንደመጨባበጥ እቆጥረዋለሁ» በማለት የደቡብ አፍሪካው የነጻነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ ተቀኝቶላቸዋል:: በጄኔራል መንግስቱ ንዋይ ተደርጎ በነበረው የመፈንቅለ መንግስት ወቅትም የሱዳኑ ፕሬዚዳንት ኒሜሪ «ግርማዊነትዎ! የተደረገብዎትን መፈንቅለ-መንግስት ለማክሸፍ አስራ አምስት ሺህ የጦር ሰራዊት ሃይል በትዕዛዝዎ ስር ለመሆን ዝግጁ ነው» በሚል ቃል የገባው ምንም ጊዜ ሳይወስድ ነበር::

እርግጥ ነው አሁን በካሪቢያውያን፣ በአፍሪካዊ አሜሪካውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ገደል አለ:: ያን ገደል የቆፈረውና ጥልቀቱ እንዲጨምር የሚያደርጉት የሁለቱም አማካሪና አዋቂ የሆኑት ጥቂት የነጭ ምሁራን ናቸው:: ለዚህ መነሻው ደግሞ የንጉሰ ነገስቱ ተቀባይነትና ኢትዮጵያም ቅድስት ሃገር መባሏ ናቸው::

ንጉሰ ነገስቱ የካሪቢያን አገራት ሲጎበኙ እንደ አፄ ምኒልክና እንደ ልጅ ኢያሱ እሳቸውም የካሪቢያን አገራት ህዝቦች ወደ ሁለተኛዋ አገራቸው እንዲመጡ ጋበዙ፤ መጡ:: እንደ ሚስተር ፎርድ (የፕሮፌሰር አቢይ አባት) የመሳሰሉት በሞያቸው አገራቸውን ረዱ፤ በጠላት ወረራ ጊዜም አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ከእነ ራስ እምሩ ጋር በመሆን በአርበኝነት ተዋደቁ ...

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ለአገራቸው ብዙ እንደሰሩ ጃገማም ያውቃል፤ ስለዚህ ያከብራቸዋል:: ይሁን እንጂ በጣም የሚቀርቧቸው ሰዎች ሳይቀሩ

ለውጥ እንደሚያስፈልግ የሚያምነው፤ የገበሬዎች፣ የተማሪዎች ... አመፅ በአማራጭ የፖለቲካ አቅጣጫ ተተክቶ መፍትሄ እንዲመጣ የሚፈልገው ሰው ቁጥር በርካታ ነበር። ለዚህም ንጉሰ ነገስቱን «በክብር ስልጣንዎን ለቀው ለቀጣዮቹ ይስጡ» ሲሏቸው መጀመሪያ እየተቆጡ የበቀል እርምጃ ቢወስዱም፤ በኋላ ግን «እሺ» ማለት ጀምረው ነበር። በየዘውድ በዓሉ ወቅት በቃ ለውጥ ሊያደርጉ ነው ተብለው ሲጠበቁ ንግግራቸውን በጉጉት የሚያዳምጠውን ሁሉ «... እስጀምሮ ሳስጨረሰን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው!» ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ቆሽቱ ያራል። ቆሽታቸው ከሚያረው ለውጥ ፈላጊዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ጄኔራል ጃገማ ነበር።

እንዲያውም አንድ ጊዜ ጄኔራል ጃገማ የአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በነበረበት ወቅት ሁለት የቴኒስ ኮርትና አንድ የኳስ ሜዳ አዘጋጅቶ ንጉሰ ነገስቱ እንዲመርቁለት ጠራቸው። በዚያ ወቅት ከተሳካ እሳቸውን ይዞ ለውጥ ለማድረግ ከዋግሹም ወሰን፣ ከቀኛዝማች ወልደ አማኑኤልና ከሌሎች ጋር ተስማምቶ ነበር። ይህን ከመፈፀሙ በፊት ግን ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሃብተወልድ አስጠሩት።

አክሊሉ ከጃገማ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥረው ስለነበር እቤታቸው በሚያዘጋጁት የእራት ግብዣ ጄኔራል ጃገማንም ይጋብዙታል። ባለቤታቸውንም «ወንድሜ ነው፤ እወቂው» ብለው አስተዋውቀውታል። አንዴ እንዲያውም ዶ/ር ዳሲዮስ ከሚባል ግሪካዊ ወዳጃቸው ጋር ተጋብዞ ጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ከግሪካዊው ባለቤት ጋር ሲደንሱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈቃድ ጃገማ ከባለቤታቸው ጋር በዳንስ ተውረግርጓል።

ብዙ ጊዜ የባሌ፣ የአርሲ፣ የወለጋ፣ የኢሉባቡር፣ የጎጃም ... ፀጥታ ከፖሊስ ሃይል ቁጥጥር በላይ ከሆነ ለእርዳታ የሚሄደው አራተኛ ክፍለ ጦር ነው። አንድ ጊዜ ታዲያ ንጉሰ ነገስቱ የውጭ አገር ጉብኝት ላይ እያሉ፣ «የጎጃም ገበሬዎች አመፁ ...» ተብሎ በመኳንንትና ሚኒስትሮች መካከል መተራመስ ተፈጠረ። የአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ጃገማ ጎጃም ከነበረው ሻለቃ ጦር መረጃ ይደርሰዋል። ለጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ «የገበሬዎች አመፅ በዝምታ መታለፍ የለበትም» የሚለው በመብዛቱ በአየር ሃይል ለማስደብደብ ይወስናሉ። ጄኔራል ጃገማ ውሳኔውን ሲሰማ ተገርሞ በጥሪያቸው መሰረት ቀጥታ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ሲሄድ ኮሪደሩ ላይ አገኛቸው፤ «... የወሰኑትን ውሳኔ ሰማሁ፤ እኔ ከሻለቃ ጦሬ ባገኘሁት መረጃ መሰረት አመፁ በመንግስት ላይ አይደለም። የገበሬዎቹ ጥያቄ ደጃዝማች ፀሐይ እንቁስላሴና ሁለቱ የአውራጃ ገዢዎች እንዲነሱ የመጠየቅ ነው። እርግጠኛ ነኝ እነዚህ ሰዎች ቢነሱ ወይንም ለስራ ጉዳይ ተብሎ እንኳን ወደ አዲስ አበባ ቢጠሩ



በውጥን የቀረ ሴራ የመፈንቅለ መንግስት ሀሳብ

አመፁ ይቆማል። በማይገባ ውሳኔ አግባብ ያልሆነ እርምጃ መወሰድ ምን ይጠቅማል፥ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር?» አሏቸው።

«ጄኔራል በምን እርግጠኛ ሆንህ?» አሉት፥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፅሞና። «ጌታዬ! ችግሩ እኮ በቀጥታ ይመለከተኛል። እርግጠኛ ባልሆን የሚያስጠይቀኝንም ምክር አልሰጥም» አላቸው።

«እሺ! ችግሩ እንዲህ እንዳልኸው ከሆነማ ማን ደም ሲፈስ ማየት ይፈልጋል፥ ጄኔራል?» ብለውት ወደ ቢሯቸው ሄዱ ...

ደጃዝማች ፀሐይና ሰዎቻቸው ሲነሱ የጎጃም ገበሬዎች አመፅ ቆመ። ንጉስ ነገስቱ ከጉብኝታቸው ሲመለሱ «ግርማዊ ጃንሆይ! እኔ ጄኔራል ጃገማን በቆራጥ የጦር ሰውነቱ ነበር የማውቀው፤ አሁን ግን በፖለቲካ አመራርም ቆራጥ መሆኑን አወቅሁ፤ ጎጃም ላይ የአውሮፕላን ድብደባ እንዳይፈፀም የመከረኝ እሱ ነው። እባክዎ! ጠርተው ያመስግኑልኝ» አሉ።

«እሺ! ጥሩ፤ አስጠራው» አሉ፥ ንጉስ ነገስቱ።

ጄኔራል ጃገማ ተጠራ ...

«ጄኔራል! የመከርከኝንና የተወሰነውን ጠቃሚ ውሳኔ ለጃንሆይ ነግሬ ሊያመሰግኑህ ይፈልጋሉና ቢሯቸው ሂድ» አሉት፥ ጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ። እንደተለመደው ቀበቶውን ወልውሎ ሄደ። ንጉስ ነገስቱ ፓትርያርኩን አነጋግረው እስኪጨርሱ ጠብቆ ገባ ...

«ጃገማ አንተን በስራህ የማናውቅህ ሆነና አክሊሉ ሊያስተዋውቀን ፈለገ!» ብለው አሰናበቱት። ጸሐፌ ትዕዛዝ የሆነውን ሲሰሙ «አየኸው! መሪ ማለት እንደ አገራችን ወንዝ ከላይ ወደ ታች የሚፈስና በፈለገው አቅጣጫ የሚጓዝ፣ ለምን ብለህ የማትጠይቀው፣ የገባልህንም ቃል ካልመሰለው ዞር ብሎ የማያይ ነው። ውሳኔው ደግሞ ሁሌም ትክክል ነው። አየህ ጄኔራል! ጃንሆይ አሁን አንድ ነገር ይሁን ይሉና ቃል ይገባሉ፤ ከልዕልት ተናኘወርቅ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ፍፁም ተቃራኒውን ይወስናሉ። ሃሳባቸውን ለመጨበጥ፣ ቃላቸውን ይጠብቃሉ ብሎ ለማመን ከባድ ነው!...» እንዳሉ ስልካቸው ጮኸ።

«አቤት ግርማዊ ጃንሆይ! - እሺ ... እሺ ... እሺ!» ብለው ስልኩን ዘጉት።

«ጄኔራል ጃገማ! አንተ የማትግባባው ሰው የምድር ጦር አዛዥ ሆኗልና ከእሱ ስር ሆነህ መስራት የምትፈልግ አይመስለኝም:: ከዚህ በፊትም 'በእሱ ስር ሆኜ አልታዘዝም' ብለህ የነበረውን ችግር አውቃለሁ:: ሁለተኛ ደግሞ የባሌ ጠቅላይ ግዛት ህዝብም በፀጥታ ማስከበሩ የሰራኸውን ግምት ውስጥ በማስገባት 'እንደራሲያችን ይሁን' ብለው ጠይቀዋልና የባሌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆነህ እንድትሰራ እኔም ሆንሁ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ስለተስማማን ንጉሰ ነገስቱ ሹመውሃል» አሉት፥ ጸሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ::

ጄኔራል ጃገማ ከሚወደው ሰራዊት ቤት መውጣት ባይፈልግም ምርጫ ስላልነበረው «ሹመቱን እሺ ልቀበል፣ ነገር ግን ወታደራዊ 'ካርየሬ' ሊጠበቅልኝ ይገባል» አለ::

«...ይከበርልሃል፣ ሁለት አጃቢ ወታደርም ተመድቦልሃል» አሉት፥ አክሊሉ::

ይህ ሁሉ ሲሆን ጄኔራል ጃገማ ስፖርት ወዳድ በመሆኑ ቴኒስና ካርታ ይጫወታል እንጂ ከማንም ጋር ስለሰውጡ በየሜዳው አያወራም:: በቀን በቀን ሳያገኛቸው ከማይውለው ከጄኔራል አሰፋ ደምሴ ጋር እንደተለመደው አንድ ጊዜ ተገናኝተው ካርታ ሲጫወቱ ቆዩና «ጄኔራል ጃገማ! ... ጃንሆይ ይፈልጉሃል?» አሉት::

«ለምንድን ይፈልጉኛል?» አላቸው - ቆፍጠን ብሎ::

«እንዲያው የተጠረጠርክበት ነገር ያለ ይመስለኛል:: ከመንግስት ለውጥ ፈላጊዎች ጋርም ግንኙነት ሳይኖረው አይቀርም በሚለው ጉዳይ ሊጠይቁህ ፈልገው ይሆናል» አሉት::

«እኔን ... እርስዎም ይሄው ያውቁኛል» አለ - ዐይን ዐይናቸውን ትክ ብሎ እያየ:: ጄኔራል አሰፋ ራሳቸውን ከፍና ዝቅ አድርገው እየወዘወዙ በእሱ ላይ በጎ አመለካከት እንዳላቸው ገለፁለት::

«ታዲያ ምን ባደርግ ይሻላል?» አላቸው::

«እንግዲህ ከጠየቁህ ... 'እርግጥ አለበት እየተባለ ይወራል:: ግርማዊ ጃንሆይ ግን እርግጠኛ ነኝ፥ አያምኑም' በላቸው» አሉት:: ከዚያ እንዳሉትም እጅ ሊነሳ ቤተመንግስት ሲሄድ ንጉሰ ነገስቱ እንደሚፈልጉት ተነገረው::





«ጃገማ! የሚወራብህን እየሰማህ ነው?» አሉት፥ ንጉሰ ነገስቱ - እጅ ነስቶ ሲጨርስ:: «... ይወራል! ግርማዊ ጃንሆይ! ... ጃንሆይ ግን አያምኑም» አለ - ዘና ብሎ:: ንጉሰ ነገስቱ ሳቅ ብለው «አንተ ቁንጮህን ይዘን ያሳደግንህ ልጃችን ነህ:: ይሁን እንጂ አንተም ብትጨመር እግዜር የሰጠንን መንግስታችንን የሚነቀንቅ የለም:: እግዚአብሔር በቃ ካለ ደግሞ ማንም ቢረዳን መንግስታችን ሲቀጥል አይችልም:: ስለዚህ የእኛ እጣ ፋንታ ወዲህ ሳይሆን ወዲያ... ከስር ሳይሆን ከላይ ነው...» አሉና ሸኙት::

ጄኔራል አሰፋ «ይገርማችኋል፣ ከጄኔራል ጃገማ ጋር የማንገናኝበት ቀን የለም፣ ካለ ጨዋታ ሌላ አያስብም:: የሚወራበት ሁሉ ውሸት ነው ...» እያሉ ተከራከሩለት::

ጄኔራል ጃገማ የለውጥ ሃሳቡ ደጋፊ ስለመሆኑ ለንጉሰ ነገስቱ መረጃ ሳይደርሳቸው አልቀረም:: ነገር ግን በሌሎች ላይ የደረሰው የከፋ ነገር በሱ ላይ ያልደረሰበት በሦስት ምክንያቶች ነው ብሎ ያምናል:: 1ኛ) ፈጣሪ እየጠበቀው ነው:: 2ኛ) የንጉሰ ነገስቱ የእልፍኝ አስከልካይ ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ የልብ ጓደኛውና «አቢዮ!» (ጋሼ) እያለ የሚጠራው ወዳጁ ስለሆነ ክፉ ነገር ሲሰማ ያስተባብልለታል፣ ከአቅሙ በላይ ከሆነም ቀስ ብሎ «እንዲህ ተብለሃልና መልስ አዘጋጅ» ይለዋል ቀድሞ:: 3ኛ) ስለ ለውጥ ፍላጎቱ ከማንም ሰው ጋር ሲያወራ ምስክር በሌለበት ነው::

* * *

ከ1933 ዓ.ም እስከ 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ የጦር አደረጃጀት አስተሳሰብ በምዕራባውያኑ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነበር:: በዚያ አስተሳሰብ መሰረት የጦር ኃይል የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የለውም:: ግዳጁ ወሰንንና ሰላምን ማስከበር ብቻ ነው:: የአገሪቱ ንጉሰ ነገስት የማርሻል ማዕረግ፣ ልጃቸው ልዑል አልጋ ወራሽ ደግሞ የሙሉ ጄኔራል ስልጣን ነበራቸው::

ጃገማ አለምን በብርሃን እንደ አጥለቀለቀው ሳይንቲስት እንደ ቶማስ አልቫ ኤድሰን ዘመናዊ ትምህርት ቤትን የረገጠው ለሶስት ወራት ብቻ ነው:: ሶስት ወራት! ከዚያ ለስድስት ወራት በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ወታደራዊ ስልጠና ወሰደ፣ አጫጭር የመኮንኖች ስልጠና አገኘ፣ አበቃ! ከዚያ ውጭ ህይወት በምትሰጠው ትምህርት እየታገዘ በተሰማራበት የጦር ቤት እስከ መጨረሻው የወታደራዊ ስልጣን እርከን ለመድረስ በቃ:: ከንጉሰ ነገስቱም በጀግንነቱ ከበሬታን አገኘ፣ በአመራሩም የሰራዊት አባላቱ የሚያመሰግኑት ሆነ:: በአርበኝነት ጀግንነቱና በወታደራዊ ስልጣኑ ከማርሻል ቲቶ ጋር ለመገናኘት በቃ:: ይህ ዘመናዊ የትምህርት ዕድል የተነፈገው የጦር ሰው ታዲያ ዕለት በዕለት ለመማር ዝግጁ ነበር:: ለዚያም ነው የሲኒየር

ኦፊሰርነት፣ የውትድርናና የአስተዳደር ትምህርት የወሰደውና ከምያውም ውጭ በንብ እርባታ ሞያ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ዲፕሎማ ያገኘው።

ጄኔራል ጃገማ ደብረብርሃን የሶስተኛ ብርጌድ አዛዥ በነበረበት ጊዜ የመጀመሪያው የአሜሪካው የጦር መሳሪያ እርዳታ «ኤም ዋን» ጠመንጃ ለእሱ ብርጌድ ተሰጠ። ያን አዲስ መሳሪያ ለሰራዊቱ ለማሳየትና ለማሰልጠን በንጉሰ ነገስቱ ፈቃድ ውቅሮ፣ አዲግራት እንዳደረገው ሁሉ ሃምሳ ጋሻ መሬት የስልጠና ክልል ቀጠና ተፈቀደለት። በዚያ ስልጠና ወቅት ደግሞ ጃገማ በህይወቱ ትልቅ ትምህርት አግኝቷል። ያም እንግሊዞችና አሜሪካውያን በወታደር ዕጣ ፋንታ ላይ ያላቸውን መሰረታዊ ልዩነት መረዳቱ ነው።

እንግሊዞች «አንድ ወታደር በጦርነት ወቅት ምንም ይሁን ምን ካለትዕዛዝ ምሽጉን ለቆ ቢሄድ በህግ ይጠየቅና እስከ ሞት ቅጣት ይቀጣል» ብለው ነው፥ ጄኔራል ጃገማን ያስተማሩት። ደብረ ብርሃን የነበረው አሜሪካዊ ግን «አንድ ወታደር ምሽግ ውስጥ አድሮ፣ ሁለት ሶስት ቀን ትኩስ ምግብ ሳያገኝ፣ ሽሚዝና ውስጥ ሱሪውን ሳይለውጥ ቀርቶ መሳሪያውን ጥሎ፣ ምሽጉን ትቶ ቢወጣ ... ያን ወታደር ሰባት ኪሎ ሜትር ወደኋላ ተመልሶ እንዲታጠብ፣ ሙዚቃ እንዲያዳምጥ፣ ዳንስ እንዲደንስና እንዲዝናና ለሰባት ቀናት ፈቃድ ያገኛል ... አንድን ወታደር በጦርነት ወቅት ለማዳን ሶስት መቶ ወይም ከዚያ በላይ የመድፍ ጥይት እንተኩሳለን» እያለ ሲያስተምር፥ ጃገማ ሳያስበው «እንዴት እንደዚህ ይሆናል?» ብሎ ጠየቀው።

«አየህ ኮሎኔል!» ብሎ ትክ ብሎ በፈገግታ እየውና «አንድ ጥሩ የአሜሪካ ወታደር አሰልጥኖ፣ ልምድ ያለው ለማድረግ ቢያንስ ሃያ አምስት ዓመት ይወስዳል። የመድፍ ጥይት ግን በአንድ ሰዓት ብዙ ሺህ ልንሰራ እንችላለን። በጦርነት ወቅት ትኩረት ማግኘት ያለበት ወታደሩ ነው፤ ገባህ አይደል?» አለ።

ጃገማ በነጮች መካከል ያለው የአስተሳሰብ ልዩነት ገረመው፤ አሜሪካውያን ለወታደር ህይወት የሚሰጡት ክበሬታም አስደሰተው ...

* * *

ትክክለኛ አስተሳሰብ ከትክክለኛ እውቀት የሚመነጭ ነው። ትክክለኛ ተግባርም የትክክለኛ አስተሳሰብ ውጤት ነው። የንጉሰ ነገስቱ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጣዊ ችግሯ የበዛበት፣ ተቃውሞው ያየለበት፣ ቀዝቃዛው ጦርነት ፍም ማውጣት የጀመረበት ... ጊዜ ነበር።





ያን ሀገር አቀፋዊና ዓለማቀፋዊ ማዕበል የንጉሰ ነገስቱ ጉልበትና የአስተሳሰብ ደረጃ ለጊዜው የሚቋቋሙትና የሚጠቀሙበት ነበር። የእነ ጄኔራል መንግስቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራም ወቅቱን ጠብቆ የተከሰተ ነበር ማለት ይቻላል። ችግሩ ግን ህዝቡን በማሳወቅ፣ በማዘጋጀት፣ በመቀስቀስና የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ላይ ባለመመስረቱ መፈንቅለ መንግስቱ መክሸፉ ነው። ከመፈንቅለ መንግስቱ በኋላ ግን መንግስት በነበረው አስተሳሰብ መምራት ሲጀምር የተለባበሱት ችግሮች እየፈጠጡ፤ ተቃውሞው እየከረረ ... ሲሄድ ለውጥ የሚያመጡ ሰዎች ይፈለጉ ጀመር።

አቶ ከተማ ይፍሩና ቀኛዝማች ወልደ አማኑኤል ያን ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ ብለው በማመን ጄኔራል መርዕድን መፈንቅለ መንግስት እንዲያደርጉ ገፋፏቸው። «ማንን ይዤ ነው መፈንቅለ መንግስቱን የማደርገው?» ሲሉም «ጃገማንና አበበ ገመዳን ይዘው ነዋ። ጃገማ የአራተኛ ክ/ጦር አዛዥ፣ አበበ ገመዳ የሶስተኛ ክ/ጦር አዛዥ ይሁኑ እንጂ እንደ ክብር ዘበኛ አዛዥ ደበበ ኃ/ማርያም የሚገባቸውን የሜጀር ጄኔራልነት ማዕረግና ሊከፈላቸው የሚገባውን ደመዎዝ ስላላገኙ ቅሬታ አላቸው» አሏቸው።

«ጃገማን አምነዋለሁ፤ ነገር ግን እስኪ ልዘጋጅ ...» አሉ። ከዚያ ጊዜ በኋላ «ጃገማ! ታዲያስ! መቼ ነው የማነጋግርህ?» ይሉታል፥ ጃገማን ባገኙት ቁጥር። «ይኸው አለሁ!» ይላቸዋል፥ ጃገማ፤ «ወይድ ...» ብለው ስቀው ይሄዳሉ። ሶስት ዓመት ሙሉ ሲፎክሩ ቆዩ ...

በ1958 ዓ.ም ጃገማ «ሜጀር ጄኔራል» ተብሎ ተሾመ። በዚያው ዓመት ጳጉሜ ላይ ጄኔራል ጃገማ የአሜሪካ ልዑክ መሪ ሆኖ ለጉብኝት እንዲሄድ ታዘዘ። ጃገማ ከመጓዙ አንድ ቀን በፊት ጄኔራል መርዕድ ንጉሰ ነገስቱ ፊት ቀርበው «ሱማሌ ልትወረን ነውና የሚያስፈልገውን ዝግጅት እንዳደርግ ይፍቀዱልኝ» ብለው ጠየቁ። «አይይ!» አሉና ንጉሰ ነገስቱ የጄኔራል መርዕድን ሃሳብ አጣጣሉባቸው። ጄኔራል መርዕድ «ጃንሆይ! መስራት ካልቻልሁ ... ሀሳቤን ካልተቀበሉ ... እንግዲያው ስልጣኔን ለሌላ ይስጡት ... አልፈልገውም» አሉ - በስጨት ብለው። «አንተ! ለዚህም ደርሰሃላ!» ብለው ንጉሰ ነገስቱ ዐይናቸው እንደ እሳት እየተንቀለቀለ ጄኔራልን ሊመቷቸው ሲነሱ ልዑል ራስ እምሩ መሃል ገቡ ...

ጄኔራል ጃገማ በዚያ ወቅት በፀጥታ ጉዳይ ጄኔራል መርዕድ ቢሮ በስብሰባ ላይ ነበር። ጄኔራል መርዕድ ስልክ ደውለው «ጄኔራል ጃገማ ይቆየኝ፤ ሌሎች ይሂዱ» አሉ።

ጃገማ ጠበቃቸው:: ጫን ጫን እየተነፈሱ መጡ፤ ዐይናቸው እንደ ስጋ ቤት አምፖል ፈጦ ይንቦገቦጋል ...

«እግዚእትነ ማርያምን እኒህ ሰውዬ አገራችንን ሊያጠፏት ነው÷ ጄኔራል ጃገማ ... ስለዚህ ሰው ሳይቀድመን እንቅደም» አሉ - ሰውነታቸውን በንዴት እያርገፈገፉ::

«ዛሬውኑ ለምን አናደርገውም! እስካሁንም ያቀዩት እርስዎ ነዎት፤ እኔ ምን ጊዜም ዝግጁ ነኝ ...» አለ÷ የበጋው መብረቅ ጃገማ አባ ዳማ:: ጄኔራል መርዕድ ቁርጥ ያለ ውሳኔውን ሲሰሙ ሰውነታቸው ላይ በረዶ እንደተጨመረባቸው ሁሉ ችስስ ብለው ቀዘቀዙ:: «የለም! ጃገማ አሁን የአንተን ዕድል አላበላሽም ... ቢበዛ አንድ ወር ነው የምትቆየው፤ ጉብኝትህን ጨርሰህ ተመለስ! እስከዚያ ሙያ በልብ ነው» አሉ÷ ጄኔራል መርዕድ - እውነቱ ሲያፈጥ እየሸሹ:: ጃገማ፤ «ለዚህ ነው ይህ ሁሉ መልዕክት ... ይህ ሁሉ ድንፋታ ... ፋከራ ብቻ!» ብሎ እያሰበ ራሱን ነቀነቀ::

እርብ ቀን ሜጀር ጄኔራል ጃገማ ልዑካኑን እየመራ ወደ አሜሪካ በረረ:: ቅዳሜ አሜሪካ ደረሰ:: እሁድ እለት ጠዋት የኢትዮጵያ ልዑካን የቤዝቦል ጨዋታ እንዲያዩ ተጋብዘው ሲመለከቱ «ሜጀር ጄኔራል ጃገማ ኬሎ... የኢትዮጵያ ልኡካን መሪ በሩ ድረስ ይፈለጋሉ» ተብሎ በድምፅ ማጉያ ሲጠራ ሰምቶ ሄደ ...

«የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም ጄኔራል መርዕድ መንገሻ በነበረባቸው የስኳር በሽታ ሳቢያ በትናንትናው እለት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ መንግስቴ ይህን ለእርስዎ እንዳስታውቅዎት አዞኛል» አለው÷ አሜሪካዊው መኮንን::

ሜጀር ጄኔራል ጃገማ የሚናገረው ጠፋው ...

ከጄኔራል መርዕድ ጋር ሐሙስ እለት ተገናኝቷል:: እርብ እለት ጉዞ ጀመረ:: እሱ አሜሪካ ሲገባ እሳቸው አረፉ ... ራሱን እየወዘወዘ አዘነ:: በመቀደማቸው ቆሽቱ አረረ:: ጄኔራል መርዕድ «ሳንቀደም እንቅደም» ብለው ዋሽተውት ብቻቸውን ቀድመው ከዕይታ ተሰወሩ ...

ጃገማ «ግርማዊ ጃንሆይ! ጄኔራል መርዕድ ለጦር ሰራዊትም የብረት መዝጊያ ነበሩ፤ እና ቀኝ እጅዎን ስላጡ እግዚአብሔር ያጥናዎ!» የሚል ቴሌግራም አስተላለፈ:: «...እግዚአብሔር ያመጣው ነውና ምንም አይደለም!» የሚል ቀዝቀዝ ያለ የቴሌግራም መልስ መጣለት::.





ሜጀር ጄኔራል ጃገማ ከግራ የአትላንቲክ፣ ከቀኝ የፓስፊክ ውቅያኖስ ነፋስ እያግለበለበው ከመሃል በሃሳብ ሰጥሞ እንደ ጅብራ ተገትሮ ቀረ ... ከደቂቃዎች በኋላ ነቃ:: እጁን ከኪሱ ከቶ አንድ ማስታወሻ አውጥቶ ገለጠው...

የማናየው÷ ነገር ግን በውጤቱ ህልውናውን የምናውቀው ሃይል አለ:: እንደ ኤሌክትሪክ ... ኤክስሬይ ያለ ግን የማይታየን የፈጣሪ ሃይል አለ:: ጃገማ ይህ ሃይል መኖሩን ያምናል ... ከልቡ ያምናል!

ማስታወሻው ውስጥ የነበረውን ጥቅስ አየው፤ «ከሃይለኛው ከእግዚአብሔር በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለእናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእሱ ላይ ጣሉት» የሚለውን ደግሞ ደጋግሞ አነበበው::

* * *

በንጉሰ ነገስቱ ረጅም የስልጣን ዘመናት በፍርድ ቤት የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሁለት ሰዎች ናቸው - ደጃዝማች በላይ ዘለቀና ብርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ ንዋይ:: ጀግናው በላይ ሲሰቀል የሞት ፍርዱን በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ ያስፈፀሙት ጄኔራል መንግስቱ ናቸው:: በዚያች ዘግናኝ ቀን ኢትዮጵያ «የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ!» እየተባለች በሃዘን ተኮራምታ ተቀመጠች::

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ ጄኔራል መንግስቱ «ይግባኝ አልጠይቅም» ብለው በስቅላት ተገደሉ:: ጄኔራል መንግስቱን አሳደው ያስያዙት የምድር ጦሩ ኤታማዦር ሹም ጄኔራል መርዕድ ደግሞ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ማሰባቸው ተደረሰበትና እሳቸውም ሁለቱን ጀግኖች በቅርብ ርቀት ተከትለው ሶስተኛነታቸውን አስጠብቀው እንደሚባለው ከሆነ በሽይ ላይ የተጨመረ መርዛቸውን እንደ ሶቅራጦስ ተጎንጭተው የነሃስ ድንጋያቸውን ተንተራሱ ...

# ፳

## ሜጫና ቱለማ

በአስራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ መጨረሻ አካባቢ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የልማት ማህበራት እንዲቋቋሙ ለብዙ ጊዜ ሲቀርብላቸው የነበረውን ጥያቄ በመቀበል ፈቃደኝነታቸውን አሳዩ። ያን ተከትሎ ምሁሩ አቶ ሃይለማርያም ገመዳ የ«ቱለማ» ማህበርን አቋቋሙ። ኮሎኔል አለሙ ቂጤሳ ደግሞ የ«ሜጫ» ማህበርን አምቦ ላይ አቋቋሙ። እነዚህ ሁለት የማህበራት መስራቾች በአዲስ አበባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እየተገናኙ ማህበራቸውን ማጠናከር ቀጠሉ ...

ኦሮሞዎች ከዘመናት በፊት መዳ ወላቡ ላይ እጅግ ድንቅ የሆነውን የገዳ ስርዓታቸውን በመከተል ስርዓቱ የተጠናከረ፣ ማህበረሰቡን የሚያረካ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስልት ፈጥረዋል። የህዝቡ ሥነልቦና እየደረጀ ሲሄድ፤ ክንዳቸው ፈረጠመ። በገዳ ስርዓት አምስት ዋና ዋና የኦሮሞ ጎሳዎች አሉ። አምስቱ ጎሳዎች ካለምንም አድልዎ እየተፈራረቁ እያንዳንዳቸው ለስምንት ዓመታት ይገዛሉ፤ በየአርባ አመቱ ልጅ የአባቱ ስልጣን ተመልሶ ይደርሰዋል። በገዳ ስርዓት ሁለት የገዳ መደቦች አሉ። አንደኛው የአባቶች ገዳ መደብ ሲሆን ሜልባ፣ ሙዳና፣ ኪሎሌ፣ ቡፎሌና ምችሌ የተባሉትን ያካትታል። ሁለተኛው ደግሞ የልጆች ገዳ መደብ ነው። ይህም ሐርሙፋ፣ ሮባሌ፣ ቢርማጂ፣ ሙለታና ዱሎ የተባሉትን ያቅፋል። ሁለቱም የገዳ መደቦች የዕድሜ ገደብን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ስህተት አይፈጠርም።

በዚህ በምስራቅ አፍሪካ የነበረው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስርዓት ጥንካሬ እያደገ ሲሄድ መልክአምድራዊ ፖለቲካዊ የሆኑ ነገሮች ከግምት እየገቡ ቆዩ። በመጨረሻ በገዳ ስርዓቱ ወደ ስልጣን የሚወጡት መሪዎች አዳዲስ ድሎችን ለኦሮሞ ህዝብ በማጎናፀፍ ሥርዓቱ እንዲስፋፋ ለማድረግ ቃል ገብተው ተንቀሳቀሱ። ይዘውት የተነሱት ስርዓት ካለምንም መደነቃቀፍ አዳዲስ ቦታዎችን ለመያዝ ያደረጉትን ትግል እያሳካው ሄደ። በአገሪቱ በወቅቱ የምስራቅ ኢትዮጵያ ሙስሊሞች በኦቶማን ኢምፓየር፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግስት ደግሞ በፖርቹጋሎች እየተረዱ በጦርነት ማገዶ ውስጥ በመሆናቸው መስፋፋቱ ብዙም የሚገድበው አደጋ ሳይጋረጥበት ቀጠለ።





የጎሳ መሪዎችም ሸዋ ላይ ተሰባሰቡና «በዝተናል እና መላውን ሀገር ለመያዝ ተከፋፍለን እንገዝ» ብለው ተስማሙ። ከዚያ ማን በየት አቅጣጫ ያስፋፋ የሚለው ላይ ጎሳዎቹን የሚወክሉ ወንድማማቾች ውይይት አደረጉና «ኮርማዎቻችን በሄዱበት እንሂድ» ብለው ወሰኑ። የሜጫ ኮርማ ወደ ምዕራብ ሄደ። የእሱ ጎሳ የሆኑት ወደ ጅባትና ሜጫ፣ ኢሉባቡር፣ ጅማ ... ሄዱና ሁሉም ሜጮች ተባሉ።

አንዱ የቱለማ ኮርማ ሸዋ ቀረ። ስለዚህ ሸዋ የቀሩት የቱለማ ወገኖች ቱለማዎች ተባሉ። የሌሎች ወንድማማቾች ኮርማዎች ደግሞ ወደ ወሎ እና ትግራይ ሄዱ። መስፋፋቱም ስኬታማ ሆኖ አሁን እጅግ በርካታ የህዝብ ቁጥር ያለውን የኦሮሞ ብሔር ፈጠረ።

አቶ ሃይለማርያም የቱለማን፣ ኮሎኔል ዓለሙ ደግሞ የሜጫን ልማት ማህበር በየግል አቋቁመው ሲንቀሳቀሱ ቆዩ። በኋላ ግን አቶ ሃይለማርያም «ሰዲራ በርቱምንና ቦረንን ወለደ ... የኦሮሞ ህዝብ በሁለቱ አባቶች በበርቱምና ቦረን ተመደበ። ሜጫና ቱለማ የቦረን ልጆች የሆኑ ወንድማማቾች ናቸው፤ ስለዚህ እኛ ወንድማማቾች ነን፤ በሁለት ተባድነን መንቀሳቀሳችን ተገቢ አይደለም» አሉ። ኮሎኔል አለሙም በሃሳቡ ተስማሙ። ሁለቱም ለአባሎቻቸው ሁኔታውን አስረድተው «የሜጫና ቱለማ» መረዳጃ ማህበር ህዳር 17 ቀን 1957 ዓ.ም ተቋቋመ። የሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር «ወንድምህን እንደራስህ ውደድ ...» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መሰረት አድርጎ የልማት እንቅስቃሴዎችን ለማድረግና ልማትንና ብልፅግናን ለማምጣት የተቋቋመ ነው።

ጀኔራል ጃገማ የሜጫና ቱለማ ማህበር ሲቋቋም የአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆኖ ሰራዊቱ ውስጥ ነበር። ማህበሩ የተቋቋመበት ዓመት የሃምሳ ሶስቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ የፈጠረው ብዙ ምስቅልቅል ገና ያልተስተካከለበት፣ የባሌ ገበሬዎች አመፅም እየተጠናከረ የመጣበት ዓመት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የንጉሰ ነገስቱ ተቃዋሚዎች ንጉስ ነገስቱ ላይ አደጋ ለመጣል የሚመክሩበት፣ "ኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ" እንዲመሰረት የሚናፈቅበት ወቅት ነበር - 1957 ዓ.ም።

በዚያ ፈታኝ አገራዊ እንቅስቃሴ ታህሳስ 10 ቀን 1957 ዓ.ም ከሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር በኮሎኔል ዓለሙ ፊርማ የተዘጋጀ ደብዳቤ ለጀኔራል ጃገማ ተሰጠው። ደብዳቤው ጃጋማ የማህበሩ አስተባባሪ ኮሚቴ አባልና አማካሪ እንደሆነ የሚያስታውቅ ነው።

ጄኔራል ጃገማ በአገሪቱ ላይ የፖለቲካ ለውጥ እንዲመጣ ከሚንቀሳቀሱት ጋር አብሮ በሚሰራበት በዚያ ወቅት በልምድና በስራ አስተሳሰቡ ዳብሮ አገራዊ ርዕይ በማየት ላይ እያለ ከሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር የአባልነት ጥያቄ ሲቀርብለት «ለልማት የተቋቋመ መሆኑን ባውቅም በኋላ ወደ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሊቀየር ይችላል ... ያ ደግሞ ከስራ ባህሪዬ ጋር ይጋጫል። በኢትዮጵያ የጦር አደረጃጀት ደንብ የጦር ሃይል አባል የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንዳይኖረው ያዛል» የሚል፤ ሲሰሙት ቀጥተኛ፣ ሲያጤኑት ግን ጥልቅ ትርጉም ያለው ምላሽ ለማህበሩ አቀረበ።

ይህን እንዲል ያበቃው ደግሞ በወቅቱ የነበረው የልማት ማህበሩ አደረጃጀት በግልፅነት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ማንኛውም መረጃ በግለሰቦች አማካይነት እንዴት ንጉሰ ነገስቱ ዘንድ እንደሚቀርብ ማየቱና በእንደዚያ ያለ ሀቡዕ ባልሆነ ማህበር መሳተፍ በእሳት መጫወት እንደሆነ ማወቁ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጦር ሃይሎች ሆስፒታል በነበረ የውጭ ሀገር ሃኪም የሞያ እንዝህላልነት ምክንያት እግሩ ላይ የነበረው ህመም እየጨመረ ሄደ። በህክምና ቦርድ ውጭ ሄዶ እንዲታከም ተፈቀደለትና ኦስትሪያ ቬና ለስምንት ወራት በጀርባው ተኝቶ፣ እግሩ ወደ ላይ ተሰቅሎ ስቃዩን በጥንካሬ በሚወጣበት ጊዜ አንድ የጋዜጣ ቁራጭ ውስጥ የነበረው ደብዳቤ ደረሰው። የጋዜጣው ላይ ጽሑፍ «ጄኔራል መርዕድ የጎጃም ክፍለ ሃገር የልማት ፕሬዚዳንት ሆኑ» ይላል። እዚያው ደብዳቤ ውስጥ ደግሞ «ጄኔራል ጃገማ አንተ ፖለቲካ ውስጥ አልገባም ትላለህ ... የአንተ እለቃ ግን የልማት ማህበር ፕሬዚዳንት ሆኑ» ይላል፥ የኮሎኔል ዓለሙ ማስታወሻ።

ጄኔራል ጃገማ ኮሎኔል ዓለሙ የላኩለት የጋዜጣ ቁራጭና ማስታወሻ ምን ማለት እንደሆነ ገብቶታል። የእሱ ሃሳብ ግን ለኮሎኔል ዓለሙ ግልጽ አልነበረም። ጃገማ ካደረገው ትግልና ከደረሰበት ማዕረግ እንዲሁም ብስለት አንፃር ተጠላልፎ የተዘረጋው የንጉሰ ነገስቱ መረብ ጠልፎ ሳይዘው «ሞያ በልብ ነው» በማለት የሚመኘው "ኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ" እንዲመሰረት ነው የፈለገው። እነ ኮሎኔል ደግሞ ምሽግ እንኳን የሌለው የፊት ለፊት ትግል መስርተው «ና!» እያሉት ነው። ስለዚህ ጃገማ ጄኔራል መርዕድ ገብተዋል ብሎ ወደ ማህበሩ ሮጦ መግባት አልፈለገም። እግሩ በአምስት ሴንቲ ሜትር አጥሮ፣ ስምንት ወራት በፅናት በጀርባው ተኝቶ ከዳነ ከአንድ ዓመት በኋላ ከቪየና ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። ለሶስት ዓመታት ከስራው ቢርቅም የአራተኛ ክፍለ ጦር አዛዥነቱ ግን እንደተጠበቀ ቆየው።





«ግርማዊ ጃንሆይ!» አለ፥ ጄኔራል ጃገማ - የንጉሰ ነገስቱን የቀስት አቅጣጫ ለማስቀየር። «... እኔ ከግርማዊነትዎ የበለጠ ማሰብም፣ ማወቅም አልችልም» አለ - ከእነ ደጃዝማች ታከለ፣ ከእነ ልዑል እልጋ ወራሽ የፖለቲካ ተስፋ ጋር ያለውን ቁርኝት እያሰበ። «አሁን ጃንሆይ ለልማት ብለው ያቋቋሙት ማህበር ቆይቶ ወደ ፖለቲካ ማህበርነት ሊለወጥ ይችላል ብዬ አልገባም ብዬ ነበር ... አሁን ግን ልማት ማህበሩ በጎሳ ከሆነ እኔም ኦሮሞ ነኝና ይፍቀዱልኝ፤ ልግባ» አለ። ንጉሰ ነገስቱ፤

«... ገዳይ በልጅነቱ
ዶቃ ሳይወጣ ከአንገቱ
ጃጌ ጃገማቸው

እንደ ገጠመ የሚፈጃቸው ...» ብሎ የፎከረውን፣ ሶስት ሺህ አምስት መቶ አርበኞችን የመራውን ወጣት የአርበኞች መሪ ከእነ ቅቤው፣ ጎፈሬውን ሲያዘናፍለው ... አስታወሱና ፊት ለፊታቸው ከቆመው ጄኔራል ጋር እያስተያዩት።

«ጃገማ ጭንቀትህ ገብቶናል ... ቢሆንም ፈቅደንልሃልና ግባ» አሉት። ንጉሰ ነገስቱ ነገር የሚገባቸው መሆኑንና የማስታወስ ችሎታቸውንም ያውቃልና እጅ ነስቶ ወጣ። ከዚያም የሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር አባል ሆነ። ማህበሩም መንገድ በሌለበት መንገድ፣ ት/ቤት በሌለበት ት/ቤት፣ መስጊድ በሌለበት መስጊድ ለመስራት መተዳደሪያ ደንቡን አርቅቆ መንቀሳቀሱን ቀጠለ ...

በባሌ፣ በሐረር፣ በወሎ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣ በጂማ ... የነበሩ ኦሮሞዎች ሁሉም የሜጫና ቱለማ ማህበር አባል ሲሆኑ ጃገማ እንደገመተው መንግስት ስጋት አደረበትና መረጃ አነፍናፊዎች ወረሩት። በኋላም እንዲፈርስ ተፈለገ።

«ግርማዊ ጃንሆይ! የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበርን ሊያፈርሰው ይፈልጋል፤ አሁን እንደተረዳሁት በአካባቢያችን ያሉት ጎረቤት አገራት ህዝቦች የእስልምና ተከታይ ስለሆኑና አብዛኛው የኢትዮጵያ ኦሮሞ ሙስሊሞች ወደዚህ ማህበር ስለገቡ ማህበሩ መቆየቱ መልካም ጎን አለውና ሳይፈርስ ቢቀጥል ጥሩ ነው» የሚል ማመልከቻ ጄኔራል ጃገማ በ1958 ዓ.ም ለንጉሰ ነገስቱ አቀረበ።

«ጃገማ! ጥሩ ሃሳብ ነው፤ አሁን ወደ አሜሪካው ጉብኝትህ ሂድና በሰላም ተመለስ እንጂ የሚፈርስ ነገር የለም» ብለው ቃል ገቡለት። ጄኔራል ጃገማ ንጉሱ የገቡትን ቃል አላመነም። ለአለማመኑ ምክንያቱ ደግሞ ጸሐፊ

ትዕዛዝ አክሊሉ የነገሩት ነው:: ... እሱን ለማስመስገን ንጉሰ ነገስቱ ዘንድ እንዲቀርብ ከአደረጉት በኋላ ንጉሱ አፌሴላዊ ምስጋና ሳያቀርቡለት ሲቀሩ ጸሐፊ ትዕዛዝ ስለንጉሱ ባህሪና ቃላቸውን የማይወብቁ ስለመሆናቸው የነገሩትን አስታወሰ:: በኋላ የፈራው ደረሰ፤ የሜጫና ቱለማ አመራሮች ታሰሩ፤ መረዳጃ ማህበሩም ፈረሰ::

* * *

ከብዙ ዓመታት በኋላ ኢህአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተደረገላቸው ጥሪ ወደ ሽግግር መንግስቱ ሲመጡ ጄኔራል ዋቆ ጉቶም የ«ቶኩችማ» ሊቀመንበር ሆነው ወንበር ተሰጣቸው:: በዚያ ወቅት ሆቴል ዲ አፍሪክ የነበሩት ጄኔራል ዋቆ ከጄኔራል ጃገማ ጋር ተገናኙ::

«ጄኔራል! ለምንድን ነው የኦሮሞ ድርጅትን የማይደግፉ ...» አሉ፥ ጄኔራል ዋቆ::

«እኔ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ነኝ፤ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ደግሞ ከአምስት መቶ አመት በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖረ ነው:: ስለዚህ እዚህች አገር ከኦሮሞ የበለጠ ኢትዮጵያዊ የለም ብዬ አምናለሁ:: በመሆኑም ኦሮሞ የኢትዮጵያ ግንድ ነው:: ግንድ እንዴት ይገነጠላል?! ግንድ አይገነጠልም:: ግንድ ከተገነጠለ ዛፉ ወደቀ ማለት ነው፤ የሚገነጠል ቅርንጫፍ ነው:: ኦሮሞ የኢትዮጵያ አለኝታ ነው፤ ብዛት አለው፤ ጭንቅላት አለው፤ ጀግንነት አለው፤ ህብረት አለው ... ተምረን፣ ታግለን፣ የተለያዩ ቋንቋዎችን አውቀን በተራችን ኢትዮጵያን መምራት አለብን እንጂ ተጠያቂው ልገንጠል ብሎ ጠያቂ ሲሆን ልተባበረው አልችልም ...» አሉ፥ ጄኔራል ጃገማ - በወኔ!

«ጄኔራል! እኔም እኮ ይኸን ነው የማምነው ...» አሉ፥ ጄኔራል ዋቆ:: ከዚያ ቀን በኋላ ዋቆና ጃገማ ሲገናኙ የሚያነሷቸው ሃሳቦች እየነጠሩ የሚመለሱት ቅርንጫፉ ላይ ሳይሆን ግንዱ ላይ ነው ...



# ፳፩

## የለውጥ ማዕበል

ጄኔራል ጃገማ የባሌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆኖ የዲንሾ ፓርክ ተከልሎ እንዲሰጥና ልማቶች እንዲስፋፉ ጥረት ያድርግ እንጂ የለውጥ ፈላጊው ቁጥር እየተበራከተ፣ የተማሪዎች ተቃውሞም ምሬቱ እየጨመረ ስለሄደ የንጉሰ ነገስቱ አገዛዝ ወገቡን እንደተመታ እባብ ተሽመደመደ:: በዚያ ወቅት ምንም እንኳን ጄኔራል ጃገማ የባሌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ቢሆንም የውትድርና የስራ ስምሪቴ ይጠበቅልኝ ብሎ ባመለከተው መሰረት የሰራዊቱ መኮንኖች የሚደርሱበትን የመጨረሻ ማዕረግ በ1963 ዓ.ም አግኝቶ ሌፍተናንት ጄኔራል ሆኖ ተሾመ:: በ1965 ዓ.ም ደግሞ የብሔራዊ ጦር አዛዥ ሆኖ አዲስ አበባ ተመለሰ::

በ1966 ዓ.ም የነገሌ ጦር ሠራዊት አባላት«የምንጠጣው ውሃና የምንበላው እህል ከአፈር ጋር እየተቀላቀለ ተቸግረናል» በማለት በተደጋጋሚ ሲያመለክቱ ከቆዩ በኋላ የሻለቃውን ጦር አዛዥ፣ ቀጥሎም የብርጌድ አዛዡንና አለቆቻቸውን በሙሉ አሰሩ:: የክ/ጦሩ አዛዥ ከአዲስ አበባ ጉዳዩን ለማጣራት ሲሄዱ እሳቸውንም መለዮዋቸውን አስወልቀው አሰሯቸው:: ውጥረቱን ለማርገብና በቁጥጥር ስር ለማዋል በወቅቱ የምድር ጦር አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ተላኩ:: እስራቱ እሳቸውንም ሳይምር ቀረ::

ከምድር ጦር አዛዡ እስራት በኋላ ንጉሰ ነገስቱ ካቢኔያቸውን ሰብስበው የቦረና ጦር አለቆች፣ የክ/ጦር አዛዡ፣ የምድር ጦር አዛዡ ደግሞ ጉዳዩን ለማጣራት ተልከው እዚያው ታስረው መቅረታቸውንና የቀረው ወደ እሳቸው መምጣት ብቻ መሆኑን በማሳወቅ ጦሩ እንዲመታ፣ ሃይል የሚያንስ ከሆነም የውጭ እገዛ እንዲጠየቅ አሳሰቡ:: ካቢኔው በንጉሰ ነገስቱ ሀሳብና በችግሩ ላይ ከተነጋገረ በኋላ ጦሩ ከመመታቱ በፊት አንድ የመጨረሻ እድል እንዲሰጥና በንጉሰ ነገስቱ መልዕክተኛ እንዲላክ ተወሰነ::

በውሳኔው መሠረትም የአየር ሃይል አዛዡ ብርጋዴር ጄኔራል አበራ ወ/ማርያም በንጉሰ ነገስቱ ታዘው ሄዱ:: ጄኔራል አበራ የንጉሰ ነገስቱን መልዕክት ለሠራዊቱ በንባብ አሰምተው ሲጨርሱ «አለቆቻችንን ያሰርነው ጥያቄያችን ሁሉ ከንቱ ስለሆነብን ነው:: አሁንም ከዚህ በፊት የጠየቅነው

ጥያቄ በምድር ጦር አዛዡና በመከላከያ ሚኒስትሩ እጅ ስለሚገኝ ጉዳዩን ተከታትላችሁ አስፈጽሙልን» ብለው የታሰሩትን ሁሉ ፈቷቸው።

የምድር ጦር አዛዡ ጄኔራል ድረሴ እንደተፈቱ አውሮፕላን አስነስተው ጠረፍ ያሉ ወታደሮችን አነጋግረው አዲስ አበባ በመመለስ ማታውኑ ጉዳዩን ለንጉሰ ነገስቱ አስረዱ። በነጋታው ንጉሰ ነገስቱ የካቢኔ ስብሰባ በመጥራት ጄኔራል አበራ ከብርጌዱ ያመጡት መልእክት እንዳይነበብ ተደርጎ ንጉሰ ነገስቱ ከጄኔራል ድረሴ ባገኙት መረጃ ብቻ በመወሰን የወታደሩ አቤቱታ ሳይቀርብና መፍትሄም ሳይሰጠው ስብሰባውን ዘግተው ተነሱ።

ታክሲ ነጂዎች «የነዳጅ ዋጋ ማካካሻ» በሚል የተደረገውን የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ተቃውመው አድማ መቱ። መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ጦሩ፣ ነጋዴዎች ... ሁሉም የየራሳቸውን ችግር እያስቀደሙ በከፍተኛ ተቃውሞ እና በሚያስፈራ እልህ የጋራ ጠላታቸው የነበረውን የስርዓቱን ቁንጮና የዘውድ አገዛዙን ለመጋፈጥ ሲጓዙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት ለንጉሰ ነገስቱ የሥራ መልቀቂያ አቀረቡ።

የካቲት 19 ቀን 1966 ዓ.ም ጄኔራል አቢይ አበበ አዲስ ካቢኔ እንዲመሰርቱ ንጉሰ ነገስቱ አዘዙ። የጄኔራል አቢይ ካቢኔ ገና ሳይመሰረት ተቃውሞ ገጠመውና ልጅ እንዳልካቸው መኮንን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ልጓም በሌለው ሌጣ ፈረስ ላይ ወጡ። እርሳቸው ፋታ እየተመኙ፣ በተማሪና በምሁራን ደግሞ 'ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም'... እየተባሉ መሳለቂያ ሆነው የተመኙት ፋታ ሳይገኝ የወጡበት ፈረስ በርግጎ ወስዳቸውና አፉን በርግዶ ከተቀመጠው አፈሙዝ ገብተው ተወተፉ ...

ሁሉም ነገር ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆነ። ያን የትግል ውጤት የሚያስተባብር ድርጅት ባለመኖሩ «የጦር ሃይሎች፣ የፖሊስ ሰራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ» ተቋቋመና አባላቱ እነ ሻምበል አጥናፉ አባተ ወደሚገኙበት አራተኛ ክ/ጦር ገቡ። ሻለቃ መንግስቱ ሃይለማርያምም ከሶስተኛ ክ/ጦር የተመረጡትንና በስልጣን ቀዳሚነት ከምስራቅ ኢትዮጵያ የመጡትን ተመራጮች በመምራት አዲስ አበባ ገቡ።

የአራተኛ ክፍለ ጦርም ከፍተኛና መለስተኛ መኮንኖች ተሰብስበው እንዳሉ ለአስተባባሪው ኮሚቴ መሪ የነበሩት መንግስቱ ኃ/ማርያም ተነሱ። በጥቁር ገበታ ላይ የዘውድ ስዕል ስለው «ዘውዱን ሳንለውጥ አስተዳደሩን ብቻ መለወጥ ስለፈለግን ድጋፍ ስጡን» ብለው ጠየቁ። በዚህ ወቅት ከትንሽ ዝምታ በኋላ ሌፍተናንት ጄኔራል ጃገማ እንጋፋ ስለሆነ የመጀመሪያው





የመናገር እድል ተሰጠው። «ኢትዮጵያ ለሶስት ሺህ አመታት የቆየችው በዘውድ አገዛዝ ስር እንደሆነ የሰማሁ ስለሆነ ዘውዱ የማይነካ ከሆነ ለውጡን እቀበላለሁ» አሉ። ከእሱ በኋላ የድጋፍ ሀሳብ ቀጠለ። አስተባባሪ ኮሚቴው አራተኛ ክፍለ ጦርን እንደ ንብ ቀፎ ተጠቅሞ የህዝቡን ልብ ትርታ እየቀሰመ፣ ራሱን ለማጠናከር የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የፍትህ ኮሚቴዎችን አቋቋመ።

ከዚያ በስልጣንና በአስተዳደር በደል ፈፅመዋል፣አላግባብ በልፅገዋል... የተባሉ ባለስልጣኖችን አስተባባሪ ኮሚቴው እየለቀመ ወደ እስር ቤት ይወረውራቸው ጀመረ። መፈክሩም «ካለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!» ሆነ። እህያውን ፈርቶ ዳውላውን ቢሆንም ህዝቡ ባለስልጣኖች ከፉ እንጂ ንጉሰ ነገስቱ ጥሩ ናቸው ማለቱን ስላላቆመ ባለስልጣኖች እየተለቀሙ ሲታሰሩ ህዝቡ ድጋፉን ቀጠለ።

የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የእናቱ አባት ናቸው የሚባሉት የወቅቱ የግቢ ሚኒስትሩ ደጃዝማች ከበደ ተሰማና ሌሎችም ንጉሰ ነገስቱን «ሰራዊቱ ለእርስዎ ያለው ታማኝነት አይለወጥም» አሏቸው። ህዝቡም የበታች ሹማምንቱ ላይ እንጂ እሳቸው ላይ ጣቱን እንዳልቀሰረ ተገነዘቡ። ስለዚህ ንጉሰ ነገስቱ መንግስታቸውን ሲያገለግሉ የኖሩት ሹማምንት እየተለቀሙ ሲታሰሩ እንኳን ሲቃወሙ ከተደበቁበት እየወጡ እጃቸውን እንዲሰጡ ያግባቧቸው እንደነበር ለቤተመንግስት የሚቀርቡ ሰዎች ያስታውሳሉ።

አስተባባሪ ኮሚቴው የዛፉን ቅርንጫፍ መልምሎ ከጨረሰ በኋላ ግን ንጉሰ ነገስቱን «የደበቁትን፣ በውጭ አገር ያልዎትን ብር ያምጡ ...» እያለ ይፈትናቸው ጀመር። የሃይል ሚዛን ሙሉ በሙሉ ተዛብቶ፣ አስተባባሪ ኮሚቴው እየተጠናከረ እያለ ንጉሰ ነገስቱ ሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ.ም በቤተ-መንግስታቸው የመጨረሻ ልደታቸውን አከበሩ። የቀድሞ ጥበባቸውና ዘዴያቸው ሁሉ እሳት እንዳቃጠለው ገመድ ቅርፅ ብቻ መቅረቱ ተረጋገጠ።

* * *

ሌፍተናንት ጄኔራል ጃገማ ለውጥን አጥብቆ ሲሻ ኖሯልና ንጉሰ ነገስቱ ሳይዋረዱ የህዝቡን ኑሮ የሚለውጡ፣ አገሪቱን ሊያበለፅጉ የሚችሉ አዲስ መሪዎች እንዲፈጠሩና አገሪቱ በአዲስ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መርህ እንድትመራ ነበር ምኞቱ።

በግዛት መስፋፋት የኢትዮጵያን አንድነት ለመበታተን በዚያድ ባሬ መንግስት የተደረገውን ወረራ በአመራራቸው የደመሰሱት ሜጀር ጄኔራል አማን አምዶም የሌፍተናንት ጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው ለይምስል

በዙፋን ላይ በነበሩት ንጉሰ ነገስት ሲሾሙ ጃገማ መልካም ቀን እንደሚመጣ ተማመነ። በዚህ መሃል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር አዛዥ የነበረው ሌፍተናንት ጀኔራል ጃገማ ሁሌም ንጉሰ ነገስቱን እጅ መንሳት አላቆመምና እንደተለመደው ቤተመንግስት ሄደ።

«ጃገማ» አሉት፥ ንጉሰ ነገስቱ - ድክምክም ባለ ድምፅ።

«አቤት ጃንሆይ!» አለ፥ ጃገማ።

«ሽፍት!» አሉት። ጃገማ ጆሮውን አላመነም።

«'ሽፍት' አሉኝ፥ ጃንሆይ?»

«አ...ዎ! ሽ-ፍ-ት» አሉት - የቃሉን ድምጾች እየረገጡ።

ሌፍተናንት ጀኔራል ጃገማ «እግዜር የሰጠንን መንግስታችንን አንተም ብትጨመር የሚነቀንቅ የለም፣ እግዚአብሔር በቃ ካለ ደግሞ ማንም ቢረዳን መንግስታችን ሊቀጥል አይችልም» ያሉትን አስታወሰና «ቀደም ብለው ቢያዙኝ ጥሩ ነበር። አሁን ግን ኬላው ሁሉ ተዘግቷል፤ መውጫ መግቢያ የለም» አላቸው። ንጉሰ ነገስቱ ጫን አድርገው ተነፈሱ።

«እነዚህ ደርጎች የሚሰሩትን አልወደድነውም። እንግዲያው ስምንት መቶ ጠመንጃ አውጣና ለምክር ቤታችን አባል ለዘውዴ ጥላሁን ስጠው» አሉ።

«ግርማዊ ጃንሆይ፥ እ...ሺ! ነገር ግን በጽሑፍ ልታዘዝ» አለ፥ ጀኔራል ጃገማ።

የተጀመረው አዲስ ተስፋ እንዲጠፋ አይፈልግም። የመሳሪያ ጥያቄው ደግሞ የራሳቸው ሳይሆን ግቢ ውስጥ አብረዋቸው ያሉት የደጃዝማች ከበደ ሃሳብ መሆኑ ገብቶታል። በዚህ ወጥመድ ተይዞ ደግሞ በአስተባባሪ ኮሚቴው የሰላ ጥርስ እንዲቀረጠፍ አልፈለገም። ስለዚህ ጀኔራል ጃገማ ቀጥታ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደነበሩት ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ቢሮ ሄዶ «ልጅ እንዳልካቸው! ጃንሆይ ስምንት መቶ ጠመንጃ ጠይቀውኛል። እኔ ደግሞ ትዕዛዝዎ በጽሑፍ ይድረሰኝ ብያለሁ፤ ስለዚህ ወረቀቱ ቢመጣ እንዳትፈርም፤ ከፈረምክ ግን አንተም ሆንህ እኔ ጉዳዩ ከመፈፀሙ በፊት እስር ቤት ነን»





አላቸው። ልጅ እንዳልካቸውም ደጃዝማች ዘውዴ ወደ ቤተመንግስት እንዳይገቡ አግደው ወረቀቱ ላይም ሳይፈርሙ ቀሩ።

በሌላ ቀን ጀኔራል ጃገማና ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ቤተመንግስት ተያዩ። ደጃዝማች ከበደ ወደ ጀኔራል ጃገማ ቀረብ ብለው «አንተ እኮ አካያ ሆንህብን!» አሉት። ቋንቋው ስላልገባው 'ምን ማለት ነው አካያ?' ብሎ እያሰበ ዝም አለ፤ በኋላ ግን ሲወጣ አካያ ምን ማለት እንደሆነ ጠየቀ። «አካያ ወንዝ ሲሞላ፣ ጎርፍ ሲመጣ ለሽ ብሎ የሚተኛና ደራሽ ውሃው ሲያልፍ ቀና የሚል የዛፍ አይነት ነው!» አሉት። ጃገማ ሳቅ ብሎ «አካያ ማለት በኦሮምኛ 'አለልቱ' የምንለውን ነዋ!» አለ።

* * *

በሐምሌና በነሐሴ ወር 1966 ዓ.ም ኢትዮጵያ በልጅ ሚካኤል እምሩ ጠቅላይ ሚኒስትርነት መረጋጋት የጠፋባትና ማዕበል የሚንጣት ጀልባ መሰለች። የኮሚኒዝም ፅንሰ ሀሳብ ከምስራቅ አውሮፓ፣ ከሶቪየት ህብረት፣ ከቻይናና ከኪዩባ እየተነሳ የኢትዮጵያ ምሁራንን የአእምሮ በር መደብደብና አንጎላቸውን በርግዶ መቆጣጠር ጀመረ። በርዕዮተ-ዓለሙ የሰከሩትም ወደ ከርሰ ምድር ሰጥሞ ራሱ ብቻ የቀረውን የቀድሞ መንግስት በፕሮፓጋንዳ መራኄ እናት አናቱን እየወቀሩ እንደሚስማር ቁልቁል ያሰጥሙት ጀመር ...

አስተባባሪ ኮሚቴው በአየር ላይ እንዳለ ስሙን «ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት» ብሎ በመሰየም ሁለት ሚሳይሎችን በሁለት አቅጣጫ አስወነጨፈ። አንደኛው ህዝቡን ፀጥ የሚያደርግ በውጭ ጋዜጠኛ የተዘጋጀ ፊልም በማቅረብ፣ ፀጥታውን አጠናክረው የሚጠብቁ ሃይሎችን በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በተጠንቀቅ በማቆምና የሚወድቀውን መንግስት የሚተኩትን መሪዎች በማዘጋጀት የተደረገ ነው። ሁለተኛውና ወደ ኢዮቤልዮ ቤተመንግስት የተወነጨፈው ሚሳየል ደግሞ በሻለቃ ደበላ ዲንሳ የሚመራና ሲወደሱ የኖሩትን፤ የሰሎሞናዊው ስርወ መንግስት ዘር ለዘለዓለም እንደሚገዛ፣ እሳቸውም ስዩመ-እግዚአብሔር ስለሆኑ ህዝቡ ካለ ንጉሰ ነገስቱ፥ ንግስት እንደሌለው የንብ መንጋ እንደሚበተን በመግለጽ ሲያሳምኑ የኖሩትን ንጉሰ ነገስት ዕጣ ፋንታ ለመፈረካከስ የተንቀሳቀሰ ነበር።

«ከ50 ዓመት በላይ ሲመሩ ... አገሪቱን አሁን ካለችበት ችግር ላይ እንድትወድቅ አድርገዋታል ... ከእንግዲህ ወዲህ ይህን ከፍተኛ ሃላፊነት መሸከም አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪም ዕድሜዎ ገፍቷል» አሏቸው፥ መልዕክተኞቹ። ንጉሰ ነገስቱ በክብር ዘበኛ አዛዥ በጀኔራል አበበ ተቀነባብሮ

የነበረውን የማክሸፍ እርምጃ «ተዉ! አይሆንም» ብለው ያቆሙት ትዝ አላቸው:: ቶሎ ደግሞ መሆን ያለበት እንደማይቀር፣ እግዚአብሔር በቃ እንዳለ የተረዱ ይመስላል::

«... የተናገራችሁትን ሰምተናል፤ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ስንሆን ስም ብቻ አይደለም፤ ቢሆንም በየጊዜው የሚለዋወጠው ነገር ደግሞ ለሃገር የሚጠቅም ነገር እስካለበት ... ያነበባችሁትን ሰምተናል፤ የኢትዮጵያን ታሪክ ጠብቃችሁ ማልማት ከቻላችሁ የእኛ ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃል ... ካልቻላችሁ የእናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ይቆምና የእኛ ይቀጥላል! የኢትዮጵያ ህዝብ እድል የእኛን መወገድ የሚጠይቅ ከሆነ ግን ስራችንን አቁመን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል ዝግጁ ነን» አሉ - ጭል ጭል ይል የነበረውን ተስፋቸውን «እፍ» ብለው ድርግም አድርገው በማጥፋት::

ይህን የንጉሰ ነገስቱን ንግግር ብዙዎች በ1782 ዓ.ም ፈረንሳይ ባካሄደችው አብዮት የፈረንሳይ ህዝብ የወከላቸው እንደራሴዎች በንጉሳቸው ሉዊ አስራ ስድስተኛ ላይ የፈረዱት የሞት ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት፤ «ህዝቤ ሆይ! ጥፋት ሳይኖርብኝ መገደሌ ነው፤ በእኔ ደም ግን የፈረንሳይ ህዝብ የተሻለ ህይወት እንዲጎናፀፍ እመኛለሁ» ብለው ከተናዘዙት ጋር አመሳስለውታል::

* * *

... ከርቀት፣ በጣም ከርቀት የሙዚቃ ዜማ በአየር ላይ እየተስረቀረቀ ይሰማል::

«ዐይናን ያላየኋት ... የሩቅ ዘመዴ አለች ... ለመኖር አልሻም ... እጅሽም ይቆረጥ፣ ዐይንሽም ይታወር ... ለማየት ጉጉቴ ጤንነትሽን ነበር... » ሙዚቃው ይንቆረቆራል ...

አንዲት ቮክስ ቫገን፥ በጅፕ መኪናቸው ላይ መትረየስ በደገኑ ወታደሮች ታጅባ እየተነዳች ከኢዮቤልዮ ቤተ መንግስት ጎበጥ ብላ ወጣች:: በዚያች መኪና ውስጥ የንጉሶች ንጉስ፣ 225ኛው የይሁዳ አንበሳ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራች፣ በዓለም ከታወቁ መሪዎች አንዱ፣ አንበሳ አጉራሹ፣ በመንግስታቱ ማህበር «... ፍርዳችሁን ታሪክ ሲያስታውሰው ይኖራል ... በችልታ የምትመለከቱት በሃገሬ ላይ የሚተላለፈው ወረራ ነገ ደግሞ በተራው እናንተ ዘንድ ይመጣል» በሚል ትንቢታዊ ንግግር፥ ያሾፉትን አገራት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አፋቸውን ያስያዛቸው ታላቅ መሪ፣ ኋይት ሃውስን በኦፊሴል የጎበኘ ጥቁር መሪ፣ የራስታዎች መሲህ፣





ህዝቡ መሬት የሚስምለት፤ የአፍሪካ አባት እየተባለ የተሞካሸ ገናናው የኢትዮጵያ መሪ ... መቀመጡን ማንም ሊገምት አይችልም::

ንጉሰ ነገስት ከዙፋኑ፣ አንበሳ ከዱሩ፣ አሳ ከባህሩ ... ከወጣ አለቀለት፥ ሆነ እውነቱ:: የህይወት እውነት ግን የቱ ነው? ተኝቶ የሚታለመው ወይንስ ቆሞ የሚቃዠው? መልስ የሌለው ጥያቄ ሁሌም ይመጣል፤ ሁሌም ይሄዳል ... መልስ ከሌላቸው ጥቂት ክስተቶች አንዱ፥ የነበረው እንዳልነበረ መሆኑ ነው! እንደ ሲኒማ ማሳያ ሸራ ትርዒቱ ካለፈ፤ ውበቱ፣ ፍቅሩ፣ ኩራቱ፣ ዝናው ... ከአበቃ በኋላ ቢነኩት፣ ቢዳብሱት አልነበረምና አይኖርም ... ወይም ነበርና የለም ...

* * *

ሁሌም የመፈክር ውጤቱ ተቃራኒ ነው በሚያሰኝ አኳኋን «ካለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም» ያለው ደርግ እንቅስቃሴው የበርካታ ሰዎችን ደም በማፍሰስ ተጀመረ:: ጄኔራል ጃገማ እጁን አውጥቶ የደገፋቸው ደርጎች የሄዱበት አቅጣጫ ፈፅሞ ያልጠበቀው አቅጣጫ ሆነ:: የግል ወዳጁ የሆነው ጄኔራል አማን አንድ ጊዜ «ጄኔራል ጃገማ! እነዚህ ደርጎች አስቸገሩኝ ... ስለዚህ እበታትናቸዋለሁ» አለው - በስጨት ብሎ::

«አማን ተጠንቀቅ!» አለው፥ ጃገማ:: በጄኔራል አማንና በደርጎች መሃል ልዩነቱ ተካረረ:: ሽምግልና ተጀመረ::

ምሽት ላይ ጄኔራል ጃገማ ከባለቤቱ ጋር ዘመድ ቤት ራት በልቶ ሲመለስ በየመንገዱ የጦር ሃይሎች እንቅስቃሴ በዛ:: ውጥረት የሰፈነበት ምሽት ሆነ:: ወደ ቤቱ ሲያቀና ጦር ሃይሎች አካባቢ የታንኮች እንቅስቃሴ አስተዋለ:: በመጨረሻም ጀግናው ጄኔራል አማን እሱ ለቅጣት ሲያስባቸው ትንንሾቹ ፍየሎች ግን «ሻዕቢያን ደግፏል» በሚል ነፍሱን ነጠቁት:: የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የሳንድኸረስት ጦር አካዳሚ ምሩቁ፣ አገሩን ከጠላት ወረራ የጠበቀው ጀግና፣ በአመራሩ የተመሰገነው ጄኔራል፥ ኮትኩቶ ባሳደጋቸው የሰራዊት አባላት እንደ ጠላት በታንክ ተከቦ ተሰዋ!

ጃገማ ተስፋ ቆረጠ::

የአርበኞች መሪው፤ የሻለቃ፣ የብርጌድ፣ የክፍለ ጦር ... አዛዡ፤ የመከላከያ ሚኒስቴር የትምህርት ምክትል ረዳቱና በሌሎች ከፍተኛ ሃላፊነቶች አገሩን ያገለገለው ጃገማ መስራት በሚችልበት ዕድሜ በ55 ዓመቱ ነው ጡረታ የወጣው:: የደርግ መንግስት የሲዳሞ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ

ወይም የህዝብ ደህንነት ሃላፊ እናድርግህ ብሎት ነበር። ኮሚኒዝምን የሚጠላው ጃገማ ከኮሚኒስቶች ጋር መስራት ስላልፈለገ «በውዴታ ከሆነ አልፈልግም፤ በግዴታ ከሆነ ግን ...» ሲል ተውት።

ጃገማ በስራ ዓለም በነበረበት ጊዜ ምንም እንኳን ዘመናዊ ት/ቤት ገብቶ የመማር እድል ባይገጥመውም የካዴት፣ የአስተዳደር፣ የሲኒየር ኦፊሴርነት፣ የስታፍ ኮሌጅ ኮርስ ተምሯል። በደርግ ጊዜ ጡረታ ከወጣ በኋላ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ገብቶ የንብ አረባብ ዘዴ ተምሮ ዲፕሎማ አግኝቷል። ከመቶ በላይ ለሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችም የተማረውን በተግባር በማዋል ዘመናዊ ቀፎ ሰርቶላቸዋል። በጊንጪ ዘመናዊ የከብት እርባታ እቋቁሟል። መስራትም ሃጢያት በነበረበት በዚያ ዘመን «ህዝብ ታሳድማለህ» በሚል ያለአገር ውስጥ ደህንነት ሀላፊው ትዕዛዝ ከከተማ እንዳይወጣና መውጣት ካለበት ለሀላፊው የት፣ መቼ፣ ለምን ... እንደሚሄድ እንዲገልጽ ተደርጎ የቁም እስረኛ ሆነ።

ከዚያ የጀርባው አጥንት ተጋጠመና የህክምና ቦርድ ውጭ አገር ሄዶ እንዲታከም ጻፈለት። በጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን አማካይነት ለሊቀመንበር መንግስቱ ጉዳዩ ቀረበ። ሊቀመንበሩም ከሶሻሊስት አገሮች ወደ አንዱ እንዲሄድ ወሰኑ። ጄኔራል ጃገማ ግን አንድ ከፍተኛ መኮንን ሶሻሊስት አገር ሄዶ «ኮምኒዝምን እልደግፍም» በማለቱ በቂ ህክምና ሳይሰጠው ሲሰቃይ መቆየቱን ስለነገረው፣ ለሶሻሊስቶችም የነበረው ጥላቻ ከፍተኛ ስለነበረ በሶሻሊስት አገራት የነበረውን የህክምና ዕድል ሰርዞ በራሱ ወጭ አሜሪካ ሄዶ ለመታከም ጠየቀ።

ከነበረውም ገንዘብ አምስት መቶ ብር ብቻ መንዝሮ በወቅቱ ምንዛሪ ሁለት መቶ ሃምሳ ዶላር ብቻ ይዞ «ከሃይለኛው ከእግዚአብሔር በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለእናንተ ያስባልና» የሚለውን ጥቅስ ደረቱ ኪስ ከቶ ለመታከም ወደ አሜሪካ ሄደ። እዚያም ከባለቤቱ እህት ልጅ ቤት ተቀመጠ። የባለቤቱ እህት፥ የአቶ ሰይፉ ማህተመስላሴ ባለቤት ወ/ሮ ሶፍያ እስፋው ናቸው። አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት ከልጃቸው ጋር ይተዋወቅ ኖሮ ስልክ ደወለ፤ ጃገማ አነሳ።

«... ሃሎ ... የለችም»

«ማን ልበል እርስዎን?» አለ ወጣቱ።

«ጄኔራል ጃገማ።»





«ጃገማ ኬሎ ... አባባ! ቤተሰቦቼ ያውቁዎታል፤ ብዙ ጊዜ ሲያነሱዎትም እሰማ ነበር» አለ፥ ወጣቱ። ተዋወቁ ... ጃገማ ለህክምና መምጣቱን ተናገረ። በሳምንቱ እንደገና ተደወለ ... ጃገማ አነሳ።

«ጄኔራል! ለህክምና ነው የመጣሁት አላሉኝም ነበር?» ጠየቀ፥ ወጣቱ።

«አዎ፤ ብዬሃለሁ! ... ነገር ግን አንድ ሁለት ሃኪም ዘንድ ሄድኩ፤ አሁን ሶስተኛ ሃኪም እየፈለግሁ ነው» አለ፥ ሌፍተናንት ጄኔራል ጃገማ።

«እስኪ ከአዲስ አበባ ያመጡትን የህክምና ወረቀት ፎቶ ኮፒ አድርገው ይላኩልኝ» አለ፥ ወጣቱ።

ይህ ወጣት የሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ገንዘብ ያዥ የሆነች አንዲት አፍሪካዊ አሜሪካዊት ወዳጅ ነው። «የአባቴ ጓደኛ ናቸው ... ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ ነው ... እንዴት መርዳት ይቻላል?» ብሎ ጥቁር አሜሪካዊ ጓደኛውን ጠይቋት ነበር።

«ዕድሜው ከ65 ዓመት በላይ ከሆነና ድንገተኛ ተብሎ ከገባ በነፃ የሚያሳክም ድርጅት አለ» አለችው። ጥቁር አሜሪካዊቷ ከሚረዱት ድርጅቶች ጋር አገናኘችውና ጃገማ በድንገተኛ በር ገብቶ ተመረመረ። «በአስቸኳይ ይተኛ» ተባለ። በእናቷ ኤርትራዊ በአባቷ ሶሪያዊ የሆነች ነርስ ተጠግታ፤

«ከየት ነው የመጣኸው?» አለችው።

«ከኢትዮጵያ» አላት፥ ጄኔራል ጃገማ።

«አሁን ልትተኛ ነው?»

«ዝነኛ የነርቭ ሃኪም ማነው?» አላት።

«ለአንጎል ኦፕራሲዮን አንድ ጎበዝ ሃኪም አለ፤ ፀባዩ ግን ቁጡ ነው። ሌላው ሙሴ ይባላል፤ ብዙ በሽተኞች ጥሩ ሰው ነው ይሉታል» አለችው።

«በይ እንግዲያው እሱ እንዲያየኝ አድርጊኝ?» አላት።

«... ውይ! እንዲያውም ያው» አለችው - ራቅ ብሎ ኮሪደሩ ላይ የቆመውን እየጠቆመች:: ሄዳ አነጋገረችለት:: ጃገማም አነጋገረው::

«ሰኞ ናና ተመርመር፤ ማክሰኞ ኦፕራሲዮን ትሆናለህ» አለው:: ሰኞ ሄዶ ፎርም ሞላ፤ ከዚያ ተኛ:: በሶስት ዓመት ጊዜ ወስጥ ራሱ ሶስት ጊዜ፣ ባለቤቱ ደግሞ ሁለት ጊዜ በነፃ ኦፕራሲዮን ሆኑ:: ጥቅሷም ፊት ለፊቱ ተለጥፋ ጠዋትና ማታ ያያት ነበር!

አሜሪካ እንደሄደ በዚህ አኳኋን ጀግንነቱን የሰማ ኢትዮጵያዊ በአጋጣሚ በስልክ አግኝቶ በእሱ አማካይነት ታክሞና ድኖ ወደ ሃገሩ ተመለሰ:: እሱም የጠበቀት ሳይሆን ያልጠበቁት መሆኑን በተግባር አይቶ አረጋገጠ::

ደርግም አገሪቱን «ጥርስ ውስጥ የገባች» አድርጎ፣ ኢኮኖሚዋንም ከጎረቤት አገሮች የኢኮኖሚ ደረጃ በአመታት ወደኋላ አስቀርቶ አስራ ሰባት ዓመታት ከኖረ በኋላ በሰፈረው ቁና ተሰፍሮ የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ዘመኑ አበቃ ... ጃገማም ይህን ሁሉ በዓይኑ አየ::

* * *

በ1983 ዓ.ም ኢህአዴግ አገሪቱን ሲቆጣጠር ጃገማ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት» የሚል ድርጅት አቋቁሞ እስከ 1990 ዓ.ም. ተንቀሳቅሷል:: በዚህም ሳይገደብ የኢትዮጵያ አንጋፋ የምድር ጦር ሰራዊት ጡረተኞች ማህበር ሊቀመንበር ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል:: ቀደም ሲልም የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ መታሰቢያ ድርጅት ሲቋቋምም ቢትወደድ ዘውዴ ፕሬዚደንት ሲሆኑ ጃገማ ምክትል ነበር፤ በኋላ ደግሞ ፕሬዚደንት:: ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ታላላቅ ሰዎች የመሰረቱት «ኢትዮጵያዊነት» የተባለው ማህበርም መስራችና መሪ ነው::

* * *

በመስከረም ወር 2000 ዓ.ም በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ኤምባሲ ወታደራዊ ጉዳይ አስፈጻሚ ኮሎኔል ሳንዲ÷ ጀኔራል ጃገማ አርበኝነት የፈፀመባቸውን ቦታዎች፣ አብረውት የነበሩትን ተከታዮቹን አስተያየት ለማዳመጥ ሄዶ በአየውና በሰማው ተገርሞ ሲደነቅ ከዋለ በኋላ የምሳ ግብዣ ተደረገ:: ከምሳ ግብዣው በኋላ ኮሎኔል ሳንዲ ለጀኔራል ጃገማ ሙሉ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጥቶ «አንተ ግፍና ጭቆና ከአፍሪካ ምድር እንዲወገድ





ታላቅ ተጋድሎ ያደረግክ ኢትዮጵያዊው ቲቶ ነህ» አለው:: የሰማንያ ሰባት ዓመቱ ጀኔራል ጃገማ÷ ኮሎኔል ሳንዲ «ኢትዮጵያዊው ቲቶ» ሲለው ማመስገኑ ቢያስደስተውም ምሳሌ ፍለጋ ርቆ መሄዱን ግን አልወደደለትም:: ስለዚህ ጀኔራል ጃገማ በኮሎኔል ሳንዲ ሙገሳና መወድስ ዝም አለ - መደሰት፣ መሳቅ የጠፋው ይመስል!

* * *

አስራ ሰባት ጊዜ ቀዶ ህክምና ሲደረግለት በጥንካሬ የማለዳዋን ጀንበር ለማየት ይጓጓ የነበረው ጀግና፣ ዘለዓለም እንደሚኖር ሁሌም የሚያስበው ጃጌ ጃገማ ... ዛሬም በሕይወት አለ:: መርፌ ሲወድቅ የሚሰማው ጆሮው ማዳመጥ ቢቀንስም፣ በርካታ ኒሻን የደረደረበት ደረቱ በጃኬት ቢጀቦንም፣ ፈጣንና ቀልጣፋ እጆቹን እንደልብ ለማዘዝ ቢቸገርም፣ ሜትር ከዘጠና ይዘልባቸው የነበሩ እግሮቹ ካለድጋፍ መንቀሳቀስ ቢሳናቸውም ... በዚህ የእርጅና ዘመኑ÷ ሩቅ አሳሚው አእምሮውና በራስ መተማመን የፈጠረለት ወኔው ግን አሁንም እንደ ልጅነት ጊዜው ጠንካራና ትኩስ ናቸው:: ያን ሁሉ ገድል ሰርቶ እዚህ የደረሰው ያ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ጀግና ... ይኸውና ዛሬ ታሪኩ ተጽፎ የመጨረሻውን መጀመሪያ በዐይኑ በብረቱ ለማየት በቃ:: ... ወደፊትም በጀግንነቱ ሲታወስ ይኖራል!

———— // ————

# የጸሐፊው ማስታወሻ

በጀግንነታቸው፣ በሞያቸውና በአመራር ብቃታቸው አንቱ የተባሉት የእኒህ ኢትዮጵያዊ አርበኛ የህይወት ታሪክ በቀረበበት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባለታሪኩ በአንተነት እየተጠቀሱ እንዲገለጹ ተደርጓል:: ይህ የሆነባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1) የኦሮሞ ጀግና (ቀጠሌ) አንተ ተብሎ ነው የሚጠራው::
2) በሀገራችንም ሆነ በውጭው ዓለም ጀግናን አንተ ብሎ መጥራት የተለመደ ነው::
3) የአንድን ሰው የልጅነት፣ የጎልማሳነትና የሽምግልና ዘመን ህይወት ለመግለጽ ጉራማይሌ ያልሆነ አንድ ወጥ አጠራር መጠቀሙ በአጻጻፍ ቴክኒክነት ይመረጣል::



# ዋቢ መጻሕፍት


ሁሴን አህመድ (ጄኔራል):: 1997 ዓ.ም.:: *መስዋዕትነትና ፅናት*:: አዲስ አበባ፣ ስታር ማተሚያ ቤት::

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ:: 1999 ዓ.ም:: **የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ**:: አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ቃለክርስቶስ አባይ (ኮሎኔል):: 1977 ዓ.ም:: **የ1953ቱ የመንግስት ግልበጣ ሙከራና ከ1908-1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሒደት**:: አዲስ አበባ::

ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም (ፊታውራሪ):: 1999 ዓ.ም:: **ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)**:: አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ተክለፃድቅ መኩሪያ:: 1961 ዓ.ም:: **የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ**:: አዲስ አበባ::

ኃይለ ሥላሴ (ቀዳማዊ):: 1965 ዓ.ም.:: **ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ**:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ኅሩይ ወልደሥላሴ (ብላቴን ጌታ):: 1920 ዓ.ም:: **የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል**:: አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት::

ወርቅነህ አባ ሶሪ (ተ/አባ ገዳ):: 2000 ዓ.ም:: **ገዳ ሥርዓት - የኦሮሞ ሕዝብ የዲሞክራሲ፣ የአንድነትና የነፃነት ሥርዓት ከየት ወዴት?** አዲስ አበባ::

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ:: 1998 ዓ.ም.:: **የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ (አንደኛ መጽሐፍ)**:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ጳውሎስ ኞኞ:: 1984 ዓ.ም:: **አጤ ምኒልክ**:: አዲስ አበባ፣ ሴማይ ፕሪንተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.::

____________:: **የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት**::

Abebe Hailemelekot. 2000. **The Victory of Adwa**. Addis Ababa: Commercial Printing Press.

Bahru Zewde (Prof.). 2002. **Pioneers of Change in Ethiopia**. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.